<u>መንፈሳዊ ትምት</u>

Miko ZE Ethiopia

1/ ወደ ምስራቅ ተመልከቱ

በዲ/ን ቤርዘሊ

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖታችን ቤተክርስቲያን የምትታነፀው ምስራቁን አቅጣጫ ጠብቃ ነው እዲሁም ከቤተክርስቲያኑ ጋር አብሮ የሚሰራው ቤተልሄም በስተምስራቅ በኩል ይደረጋል

በፀሎት ሰዓትም ወደምስራቅ ዞረን ነው የምንፀልየው

በስረአተ ቀብር ላይም የሞተ ሰው ሲቀበር ራሱ ወደ ምዕራብ እግሩ ወደ ምስራቅ ሆኖ ይቀበራል

ሌላው ዲይቆኑ በስረአተ ቅዳሴው ላይ ወደምስራቅ ተመልከቱ ይላል ለምን ይሆን ?

1፦የአዳም አባታችን ጥንተ ርስት ገነት በምስራቅ ናት ዘፍ 2፥8

ይች እርስታችን በአዳም በደል ምክኒያት በኪሩቤል ሰይፍ ተዘግታ ስትኖር ሞትን ድል አድርጎ በበደልን ክሶ ጌታችን መዳህኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ከፈተልን

ሉቃ 23፥43

ወደምስራቅ በዞርን ቁጥር ወደገነት ለመግባት የተሰጠን ተስፍ ትዝ ይለናል የተከፈተችውም ቤታችን ገነት በእምነት ወለል ብላ ትታየናለች በክርስቶስ ያገኘነውን ፀጋ እናስባለን ምድራውያን አለመሆናችንም ይታወሰነል

2፦ጌታ የተወለደው በምስራቅ ነው

ሰብዓሰገል ኮከቡን ያዩት በምስራቅ ሲሆን ያኮከብ የምህረተ እግዚአብሄር ምሳሌ ነው

እነርሱን ወደ እግዚአብሄር እዳደረሳቸው ሁሉ እኛንም ወደ ለመለመው መስክ ይመራናል ማቴ 2፥2

መዝ 22፥14 ወደ ምስራቅ በዞርን ቁጥር የጌታ መወለድ እና ያደረገልን ውለታ ይታወሰናል የምህረቱ ኮከብ እየመራን መሆኑ ትዝ ይለናል ።

3፦ ምስራቅ የእመቤታችን ምሳሌ ነው

ከምስራቅ ጨለማውን የሚገፈው ፀሀይ እደሚወጣ ሁሉ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያምም የአለምን የሀጥያት ጨለማ የሚገፍ ፀሀዬ ፅድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ወጥቶል (ተገኝቱል)

ለእናንተ ስሜን ለምትፈሩ የፅድቅ ፀሀይ ትወጣላችሁለች ሚል 4፥1

ህዝ 44፥1፦4 ነብዩ ህዝቅየልም እመቤታችንን ያያት በምስራቅ ነው

ስለዚህ ወደ ምስራቅ በዞርን ቁጥር እመቤታችን ትዝዝዝ ትለናለች የፅድቅ ፀሀይ ክርስቶስ ስለተወለደልን በጨለማ አለመሆናችን ትዝ እያለን ከሀጥያት እንርቃለን

4፦የአለም ድህነት የተገኘው በምስራቅ ነው

ጌታ የተሰቀለው እና አለምን ያዳነው በምስራቅ ነው እየሩስ አሌም ምስራቃዊት ከተማናት እና በመሆኑን ወደ ምስራቅ በዞርን ቁጥር የተሰቀለውን ክርስቶስን እና የተከፈለልንን ዋጋ እናስባለን

5፦ክርስትናና ቤተክርስቲያን የተመሰረቱት በምስራቅ ነው።

የመጅመሪያው ቤተክርስቲያን የተመሰረተው በእየሩስ አሌም ሲሆን ወንጌል የተሰበከውም ከዚሁ በመነሳት ነው ።ስለዚህ ወደምስራቅ ስንዞር

የቤተክርስቲያን ጉዞ የወንጌል መስፍፍት ና የህዝበ አለም መዳን ትዝ ይለናል

6፦ ምስራቅ የእግዚአብሄር ክብር መገለጫ ነው ።

ኢሳ 28:13 እግዚአብሄርን በምስራቅ የእስራኤልንም አምላክ የእግዚአብሄርን ስም በባህር ደሴቶች አክብሩ

ህዝ 43፦2 የእስራኤል አምላክ ክብር ከምስራቅ መንገድ መጣ

7፦የጌታ ዳግም ምፅአትም ከምስራቅ ነው

ዘካ 14፥14 በዚያን ቀን እግሮቹ በእየሩስ አሌም ትይዩ በምስራቅ በኩል ይቆማሉ

ሐዋ 1፦11 ይህ ከእናንተ ወደሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደሰማይ ሲርግ እዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል ።

8፦ቅዱሳን አበው ሲፀልዩ ወደ ምድራቅ ይዞሩ ነበር ዳን 6፥9 ወደ እየሩስ አሌም ያለውን መስኮት ከፍቶ ይፀልይ ነበረ ነብዩ ዳንኤል እግዚአብሄር ምሉዕ በኩልሄ (የሌለበት ቦታ የሌለ) መሆኑን ያውቃል። ነገርግን ወደ እየሩስ አሌም መዞሩ ነፍሱ የምታስባት እዲኖራት ነው

9፦ታቦቱ በምስራቅ በኩል ባለው ቤተ መቅደስ አስቀምጠን ስጋወ ደሙ የሚፈተተው ጌታ በምስራቅ ሀገር ጎለጎታ ለኛ ስጋውን መቁረሱ ደሙን ማፍሰሱበማሰብ ነው ።

10፦በስረአተ ቅዳሴ ላይ ዲያቆኑ ወደ ምስራቅ ተመልከቱ በምስራቅ የተደረገልንን ውለታ የተከፈለልንን ዋጋ ምስራቀ ምስራቃት ከሆነችው እመቤታችን የተገኘውን ፀሀዬ ፅድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን አስቡ ማለቱ ነው ።

11፦ በቀብር ስነስረአት የአስከሬኑን ፊት ወደ ምስራቅ የሚዞርበት

ምክኒያት

በዳግም ምፅአት በሚነሳበት ጊዜ ፊቱን ወደጌታ እዲያዞር እና እዲመለከት በማስብ ነው ።

እንግዲህ ወደምስራቅ መዞር የክርስቶስን የማዳን ስራ የቅዱሳንን ህይወት የሰማዕታትን ገድል የክርስቲያንን ተስፈ የሚያሳስበን ነው እና ወደ ምስራቅ እንዞራለን

ይህንን ስረአት ያስተማሩን አበው በረከታቸው ይደርብን

አሜን

የዘመድኩን የዓላማው ደጋፊዎች

2/ "የሰማይ አምላክ የከናውንልናል እኛም ባርያዎቹ ተነስተን እንሰራለን"

ተሀድሶን/የእናት ጡት ነካሾችን/በመዋጋት ግንባር ቀደም የሆነው ወንድማችንን መምህር ዘመድኩንን የማግኘት እድሉን አግኝተን ነበር ።

በጉዳያችንም ላይ ስለተዘጉበት የ facebook Account እና ወደ ፊትም መስራት ስላሰበው

Website and Blog development በሐሳቡ ላይ ተጨዋውተናል።

በመሆኑም የ IT ባለሙያ የሆኑ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች ስራውን በከፍተኛ ሁኔታ እየተወጡት እንደሆነም ነግሮናል።ሰሞኑንም Website እና blog ተደራሽ ይሆናል ማለት ነው።

እኛም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ከወንድማችን ከመምህር ዘመድኩን ዓለማዎች ጎን ከመቼውም ግዜ በበለጠ የምንቆምበት ግዜ አሁን ነው። # የቤተ ክርስትያናችን ጉዳይ ስለ ሚያገባን#

መረጃ ለምትፈልጉ የእጅ ስልኩም 0911608054 ነው።እውነትም ክፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል።

"የገሐነም ደጆች አይችሏትም"

like . Gojam Eshetu

እኛ የተዋህዶ ልጆች ሀገራችን በሠማይ ነው ማንም ምንምቢያወራ ከድንግል ማርያም እቅፍ የሚያወጣን የለም

Miko ZE Ethiopia

3/ የ ቆሙ መቃብሮች

በመ/ር ስምዓኮነ መላክ

መቃብር ሰዎች ሲሞቱ ወይም ነፍሳቸው ከሥጋቸው ሲለይ በክብር የሚያርፍበት ቦታ መቃብር ይባላል። መቃብር የሚለው ቃል የጎደጎደ ምድር ተብሎ ይተረጎማል። መዝ.14፥4፣ ኢሳ.22፥16 ሲያልንም መቃብር ሲል ይገኛል። መትሕተ ታሕቲት ናትና።

በማን ጊዜ እንደተጀመረ ባይታወቅም የሚቀበሩት በርስትነት በያዙት ቦታ ነበር ዘፍ.13። ያ ልማድ ሆኖልን ዛሬም በአዲስ ኪዳን የምንኖር ክርስቲያኖች እንደ አባቶቻችን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ እንቀበራለን።

ስለምን ቢሉ ሥጋውን ደሙን የበላንበትና የጠጣንበት ብቸኛዋ ርስታችን በምድር ቤተ ክርስቲያናችን ናትና ነው።

የቀደመው ርስት በዋጋ ይገዛ ነበር የዛሬዋ የምእመናን ርስት ቤተ ክርስቲያን ዋጋዋ የክርስቶስ ደም ነውና ደሙ በነጠበበት ቦታ ብቻ ስትሠራ ትኖራለች የምእመናን መቃብር በጌታ ደም የተገዛ እንጂ በሰቅል በተመዘነ ወርቅ የተገዛ አይደለም። ይህም የጌታ ደም ከሁሉ በላይ የከበረ እንደሆነ የምእመናንም መቃብር የከበረ መሆኑን ያመለክታል።

ለዛሬው ግን መቃብርን ያነሣነው ከአቤል ሞት ጀምሮ እስከ ጌታ ዳግም ምፅአት የማያቋርጥ ታሪክ ያለውን ጀግና ባለ ታሪክ መቃብርን ታሪኩን ለትውልድ ልናስተዋውቅለት ሳይሆን መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለቆሙ መቃብሮች የተናገረውን ቃል ማስታወስ ስለሚገባ ነው።

መድኀኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ስብከት በጀመረ በመጨረሻው ዓመት በመቅደስ ተገኝቶ ለሕዝቡና ለደቀመዛሙርቱ ተናገረ፦ “ታላቅ ሽክም ማሰር ስለሚችሉት መሸከም ግን ስለማይወዱት ስለ ጻፎችና ፈሪሳውያን ነበር የተናገረው።

ለብዙዎች ብዙውን ኀጢአታቸውን በፍቅር የሸፈነው ጌታ ስለ ወንጀለኞች ሲጠየቅ ዝም የሚለው አምላክ ዮሐ.8፥11፣ ሉቃ.7፥47 በቤተ መቅደሱ አደባባይ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል የእነዚህን ታላላቅ የኦሪት አገልጋዮች በደል መዘርዘር ጀመረ። ተመክሮ ያልተመለሰን ሰው በአደባባይ ሊወቅሱት ይገባልና ጌታ በቅዱስ ወንጌል እንደተናገረው “ቢሰማህ ብቻውን አድርገህ ብቻህን ሆነህ ምከረው ባይሰማህ ካንተ ጋር ሁለት ሆናችሁ ምከረው..... እነርሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት”

ማቴ.18፥15-17 ብሎ በእግዚአብሔር ጉባኤ ላይም የማይገባ ነገርን አድርገዋልና መገሰጽ ስለሚገባቸው በታላቅ ቃል ገሰጻቸው 1 ቆሮ.5፥5 በመጽሐፍ ቃልህ እውነት ነው ተብሎ የተነገረለት መምህር ነውና ዮሐ.17፥17 እነርሱን ከውስጥ እስከ ውጭ ሊገልጹ በሚችሉ የተግሣፅ ቃላት ገሰፃቸው።

በዘመኑ የነበሩ መምህራን አባቶቻቸው በሠሩት ኀጢአት የተጸጸቱ ለመመሰል አባቶቻቸው የገደሏቸው የነቢያትን መቃብር በኖራ እየለሰኑ ይሠሩና ያሠሩ ነበርና ያንኑ የሠሩትን ልስን መቃብር እየተመለከተ “የተለሰነ መቃብር የምትመስሉ” ሲል ተናገራቸው ይህ መቃብር ቢከፍቱት ለአፍንጫ የሚከረፋ ለዐይንም የሚከፋ ነገር አይታጣበትም። ሥጋው ተልከስክሶ አጥንቱ ተከስክሶ፣ እዥ ፈሶ ሲታይ ከውጭ የተለሰነ ውበቱን ያጠፋዋል። አብረውት እንዳይኖሩ ያስገድዳል በዚህ ረጅም ዕድሜው እንደላዩ ሁሉ ውስጡ አምሮ አያውቅም።

ዘመኑን ሁሉ ሕይወት በሌላቸው ነገሮች የተሞላ ሆኖ ይኖራል እንጂ። ከዕለታት ባንዱ ስንኳን ንጹህ ነገር ክርስቶስን ቢያገኝ በሥጋ የሞተው በመንፈስ ግን ሕያው የሆነው ጌታ በትንሣኤ አሸንፎት ይዞ ማስቀረትም አይቻለው ብሎ ባዶውን ቀርቶ ይሄው እስከዛሬ ያለ ክርስቶስ ይኖራል። በእውነት ክርስቶስ በመቃብር መስሎ የተናገረበት ነገሩ ምን ይመስላችኋል? ለጊዜው የሚያመለክተው በዚያ ዘመን እስከ ክርስቶስ ወደ መቃብር መውረድ ድረስ በሰው ልጆች ላይ ሙስና መቃብር በሥጋቸው ወደ ሲዖል መውረድ በነፍሳቸው የግድ የነበረባቸው መሆኑን ያመላክታል።

በዘመኑ ባለ ጊዜ ሆኖ ሞት ውጦ መቃብር ተረግጦ የማስቀረት ኀይል

ነበረውና። ያንን የሚገልጽ ሲሆን ፍጻሜው ግን ከውጭ ለሰው መልካም መስለው ስለሚታዩት ከውስጥ ግን ለእግዚአብሔር የሚመች በጎ ተግባር የሌላቸው ሰዎች እንዲገሰጹበት የተጻፈ ነው።

ከውጭ ሲያዩአቸው ይጸልያሉ ይጾማሉ በጾምና በጸሎት ብዛት በገድልና በትሩፋት ጠውልገው ይታያሉ ስመ እግዚአብሔርን ጠርተው ይምላሉ ሐሰቱን እውነት ያስመስላሉ በልባቸው የሌላውን የእግዚአብሔር ቃል አንሥተው ሲናገሩ በቂሳርያ ከተመሰገነው ጴጥሮስ ይበልጣሉ ዝምነታን በማያውቀው አንደበታቸውም ደግመውና ደጋግመው ስሙን ሲጠሩ ከጳውሎስ በላይ ሰባኪ ይመስላሉ ከውስጣቸው ግን እንዲህ አይደሉም። አመጽንና ሽንገላን ተሞልተዋል። በክፉ ምኞታቸውና አስቀያሚ በሆነው መሻታቸው የገዛ ነፍሳቸውን ገለው የገዛ ሥጋቸውን መቃብር አድርገው ቀብረዋል።

በወይንና በአረቂ አልሰከሩም እንጂ በጎጢአት ሰክረው ወድቀዋል። ከመብልና ከመጠጥ እንጂ ክፉ ተግባራቸውን ከመተው የማይከለክሉ ይልቁንም በሞተ ሥራ የተሞሉ የቆሙ መቃብሮች ሆነዋል ስለዚህም መቃብር ውስጥ ያሉ ሙታንን ስንኳን የማይጠላ ጌታ ለተለሰኑ መቃብሮችም በቤተ መቅደሱ አደባባይ ቆሞ አሳምረው የለሰኑአቸው ልስን መቃብሮችን አሻግሮ እየተመለከተ ሁሉም ወደ መዳን የሚደርሱበትን ሕያው መልእክቱን አስተላለፉ።

ወንድሜ ሆይ! አንተስ እንዳምን ነህ? ከውስጥህስ ምን ይገኛል? እግዚአበሔር አንተን ክርስቲያን አድርጎ ሐዋርያት ከሰበሰቧት አንዲት ማኅበር አባል ሲያደርግህ ምን ዓይነት ዓላማ እንደነበረው ታውቃለህ?

ጨለማውን ዓለም ካንተ በሚወጣው የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን ሊሞላው፣ ሕይወት አልጫ ለሆነችባቸው ማጣጫ ሊያደርግህ ማቴ.5፥12-13 በአሕዛብ መካከል ስሙን አሸክሞ ሊልክህ ሐዋ.9፥5 ዓላማ ስላለው ነው። የታመመትንና በአጋንንት ተይዘው የሚሰቃዩትንም የሚፈውሳቸው ለምጻሞችን የሚያነጻቸው የረከሱትን የሚቀድሳቸው አንተን መሣሪያ አድርጎ እንደሆነ ታውቃለህ? አንተ ግን ለዚህ ዓላማ የተጠራህ መሆንህን የረሳህ ትመስላለህ። በአለባበስህና በከንፈርህ ብቻ እግዚአብሔርን ታመልካለህ ቀን ቆጥረህ ደማቅ በሆኑ የዓመትና የወር በዓላት ብቻ ለእግዚአብሔር ትዘምራለህ በሌላው ቀን ግን ትጠፋለህ ቃሉን ታውቃለህ እንደ ቃሉ መኖር ግን ተስኖሃል ከውጭ እንጂ ከውስጥ የሚታይ ነገር የሌለህ መጥፎ ሰው ሆነሃል። በክፉ መሻትህ እየወጋህ ሕያዊት ነፍስህን ገለህ የቆመ መቃብር ሆነሃታል።

የማይታይ የተሰወረ የማይገለጥ የተከደነ አለ ይመስልሀልን? ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመት ቆይታ በኋላ ተከድኖ ይኖር የነበረ መቃብር መገለጡን በጌታ ደም ድብቅ ምሥጢሩን ከረጅም ዓመታት በኋላ ማጣቱን እንዳትረሳ ማቴ.27፥57 አንተ ሆይ! ሳይነግሩት የሰውን ማንነቱን የሚያውቅ ጌታ አንተንስ ቢገልጥህ? ዮሐ.2፥25 ከላይ የተለሰነ ኖራህን ቢያነሳብህስ? የቆመው መቃብርነትህ በጌታ ቃል የሞተውን ሳይሆን ሕያው የሆነ አልዓዛርን የሚያስገኝ ይመስልሃል? ብታምን የልቡናህን ትንሣኤ ዛሬ ታየ ዛሬም የተለሰነው መቃብር በር ላይ ቆሞ ይጣራል በውስጥህ ያሉት ሙታን አካሎችህ ዛሬ ድምጹን የሚሰሙበት ጊዜ ደርሷል እርሱም አሁን ነው ዮሐ.5፥25።

የሚያሳዝነው ነገር ተዘግቶ ተለስኖ መቀመጡ ነው እንጂ የተከፈተ መቃብርማ ለብዙዎች የሚያስገርም ምስጢር ተገኝቶበታል እኮ! ሉቃ.24፥12 መላእክቱ የከበቡት የጌታ ደቀ መዛሙርት የጎበኙት ያ ቅዱስ መቃብር ባዶም ቢሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ትንሣኤውን የሰበከ እርሱ ነበር።

ወንድሜ ሆይ! የቆመ መቃብር ብትሆንም ለእግዚአብሔር ቃል የተከፈተ ልብ ካለህ እውነት እልሃለሁ ስላንተ ወዳንተ ወደመቃብሩ መላእክቱን ያዝልሀል ለደቀ መዛሙርቱ ሳይቀር የሚደንቅ ጥበብን ይገልጥብሃል ለጌታችን ቃል የተከፈተ ልብህ ዝቅ ብለው ቢያዩትስ የጌታ ልብስ ብቻ እንጂ ሌላ ምን ይገኝበታል። ከእውቀት፣ ከጥበብህ ከቅድስና የተለየሁ ባዶ ሰው ነኝ ብለህ ብታምን እንኳን እግዚአብሔር ባዶነትህን ለምስክርነት ይሻዋልና ከላይህ ላይ ያለ ልስንህን አስወግደው።

አለበለዚያ የክፉዎች አጋንንት ማደሪያ መሆንህን አትርሳው። ማቴ.8፥28 ከዚያ በፊት ግን አሁን ዕድል አለህ። እንደውጪ ሁሉ ውስጠኛውንም የመቃብር ክፍል ማጽዳት ትችላለህ። አንተ እኮ! ዕድለኛ ነህ። የአባትህ ድምጹ እስከመቃብር ድረስ ዘልቆ ይሰማል ቅዱስ የሆነው ደሙ በመቃብር ያሉትን ሳይቀር መቃብራቸውን ከፍቶ ይቀድሳል እንዳትረሳ! ይሄ ዕድል ላንተም ተሰጥቶሃል። ደግሞም አንድ ነገር አለ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባው ቃል ኪዳን አለ መቃብሩን ከፍቶ ለሞቱ አጥንቶች ሕይወትን ሰጥቶ የሚያኖርበት ጊዜ አለ ይሄ ቃል ኪዳን ላንተም የተገባ ቃል ኪዳን ነውና አትፍራ ምን አልባትም ይሄ ቃል ኪዳን ላንተም የተገባ ተስፋ አትቁረጥ።

በዙሪያህ ሆነው ከመቃብሩ ደጃፍ ድንጋዩን ማን ያንከባልልናል የሚሉም

ይኖራሉ ድንጋዩ ታላቅ ቢሆንም ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሔር መላኩን ልኮ አንተ ባልጠበቅከው ሰዓት ሊያነሣው እንደሚችል አትጠራጠር። መቃብር ብዙ ጎያላንን ይዞ ማስቀረቱ የተገለጠ ነው። እነ ዳዊት እነሶምሶን፣ ዮፍታሔ፣ ጌዴዎን ሌሎችም ጎያላን መቃብር ያድራሉ ደራሲዎቹ የደረሱላቸው ተራኪዎቹ የተረኩላቸው ዜመኞቹም ያዜሙላቸው ጀግኖች ሁሉም ከመቃብር አላመለጡም ምድራዊ ፍጥረት ሥጋዊ ደማዊ ሰውነት ሁሉም የመቃብር ምርኮኞች ሆነዋል።

አንተ ሆይ! ባንተም ውስጥ ስንት ጎያላን የእግዚአብሔር ቃላት ተቀብረው ቀርተዋል መሰለህ? እነ አባ ጳውሊ ከዓለም ወጥተው የኮበለሉባቸው እነ አባ እንጦንስ ሥርዓተ መላእክትን የተላመዱባቸው ይሄ ግዙፍ ዓለም የተከናወነባቸው እነዚያ ሰባሪ ቃላቶች አንተ ዘንድ ሲደርሱ ግን ሳይሠሩ ቀብረህ አስቀርተሃቸዋል።

እውነት እልሃለሁ አዲስ ሆነህ የምትሠራው በቅዱስ ቃሉ ነውና ቃሉን ጠብቅ ብታምንም ባትምንም በክፉት ብትሆን ሳትወድ በግድ “መቃብር ሆይ ይዞ ማስቀረትህ ወዴት አለ?” ሆሴ.13፥14፣ 1 ቆሮ 15፥55 ተብለህ መጣልህ አይቀርምና ይህ የፈጣሪህ ድምጽ ወዳንተ ባደረበት ቅጽበት ወዲህ በፈቃድህ ንስሓ ግባ ይሄ ጊዜ ለሌላ ለምንም የተመደበ አይደለም የንስሓ ብቻ ነው።

“እነሆ መቃብራችሁን እከፍታለሁ ከመቃብራችሁም አወጣችኋለሁ ወደ እስራኤል ምድርም አገባችኋለሁ መቃብራችሁን በከፈትሁ ጊዜ ከመቃብራችሁም ባወጣኋችሁ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ ታውቃላችሁ” ሕዝ.37፥12-13።

Like · Gebremeskel Degwale

አሜን አምላከ ቅዱሳን ወደ ልቦናችን ይመልሰን።

Like · Semere Semere

ለጌታችን ቃል የተከፈተ ልብህ ዝቅ ብለው ቢያዩትስ የጌታ ልብስ ብቻ እንጂ ሌላ ምን ይገኝበታል።

Miko ZE Ethiopia

4/ በእምነት ስለመጋደል (ስለ መታገል)፦

1. ኦሪት ዘፍጥረት 30፥8

ራሔልም፦ ብርቱ ትግልን ከእኅቴ ጋር ታገልሁ፥ አሸነፍሁም አለች፤ ስሙንም ንፍታሌም ብላ ጠራችው።

2. ኦሪት ዘኍልቁ 13፥30

ካሌብም ሕዝቡን በሙሴ ፊት ዝም አሰኘና፦ ማሸነፍ እንችላለንንና እንውጣ፥ እንውረሰው አለ።

3. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 1፥30

በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት፥ ያው መጋደል ደርሶባችኋልና።

4. ወደ ቆላስይስ ሰዎች 2፥1

ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት ፊቴንም በሥጋ ስላላዩት ሁሉ እንዴት ያለ

ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና፤

5. ወደ ሮሜ ሰዎች

4፥20-21

ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፥ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፥ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም።

6. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

3፥8-9

ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፥ በእርሱ አገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጕድፍ እቈጥራለሁ፤

7. ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6፥18

በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤

5/ "<u>እግዚአብሔር በአንድም መንገድ በሌላም ይናገራል።" ኢዮ.33፥14</u>

ቀዳሚ ገጽ

የዐቢይ ጾም ሳምንታት

ማኅበረ ቅዱሳን

ለሕጻናት

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

ክርስቲያናዊ ሕይወትና ሥነ ምግባር

ስብከት

ዜና

ትምህርተ ሃይማኖት

ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን

የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት

የቤተክርስቲያን ታሪክ

ኪነ- ጥበብ

ግእዝ ይማሩ

ያግኙን

ባሕረ ሐሳብ የዘመን መቁጠሪያ

ይህ ሶፍትዌር ከዚህ በፊት በ 2000

ዓ.ም. /እ.ኤ.አ. በ 2008 /

በተለቀቀው ሶፍትዌር ላይ አንዳንድ ማስተካከያዎች በማድረግ ማተም

/ፕሪንት ማድረግ/ እንዲቻል ተዘጋጅቶ

የቀረበ ነው። ወደ ኮምፒዩተርዎ

በመጫን ይጠቅሙ።

ሶፍትዌሩን እዚህ በመጫን ይጠቅሙ።

ሌሎች መካነ ድሮች

ድምፀ ተዋህዶ የማኅበረ ቅዱሳን ሬዲዮ

የማኅበረ ቅዱሳን የቴሌቪዥን መርሀ ግብር

ማኅበረ ቅዱሳን ህብር ሚዲያ መካነ ድር

ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ አዲስ አበባ

ማኅበረ ቅዱሳን አሜሪካ ማዕከል

ማኅበረ ቅዱሳን ድምጸ-ተዋህዶ(አሜሪካ)

ማኅበረ ቅዱሳን አውሮፓ ማዕከል

ማኅበረ ቅዱሳን አውሮፓ ማዕከል ፖልቶክ

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ መጽሐፍት 1

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ መጽሐፍ

የቀድሞው ድረ-ገጽ

ይህንን በመጫን የቀድሞውን ድረገጽ ይመልከቱ ፈልግ

“የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻው መቃጠሉን ስሰማ አልቅሻለሁ” /ወ/ሮ መስታወት ዓለሙ/

መስከረም 8 ቀን 2008 ዓ.ም

በእንዳለ ደምስስ

በማኅበረ ቅዱሳን የልማት ተቋማት አስተዳደር የንዋያተ ቅድሳት መማረቻ ክፍል በቅርቡ በደረሰበት የእሳት ቃጠሎ በርካታ የልብስ ስፌት ማሽኖችና አልባሳት በመውደማቸው ምእመናን እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ወ/ሮመስታወት Â ዓለሙ ይባላሉ። መስከረም 7 ቀን 2008 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከባለቤታቸው ጋር በመሆን አንድ የልብስ ስፌት ማሽን ይዘው ወደ ማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ይደርሳሉ። ማሽኑንም ለልማት ተቋማት

አስተዳደር ዳይሬክተር ለአቶ ኃይሉ ፍስሐ ያስረክባሉ።

ከርክክቡ በኋላ ወ/ሮ መስታወት Â ዓለሙ ለምን ማሽኑን ለመስጠት እንደፈለጉ ጠየቅናቸው። የሚከተለውንም ምላሽ ሰጡን።

ማኅበረ ቅዱሳን ቤተ ክርስቲያንን በመደገፍ እየሰጠ ባለው አገልግሎት በጣም ደስተኛ ነኝ። በአገልግሎቱም መንፈሳዊ ሃሴት ይሰማኛል። የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻው ከነማሽኖቹ መቃጠሉን በሬድዮ ስሰማ በጣም አዘንኩለሁ፤ አልቅሻለሁም። ማዘን፤ ማልቀስ ብቻ ውጤት ስለማይኖረው ልጄ ትጠቀምበት የነበረውን የልብስ ስፌት ማሽን ለመስጠት ወሰንኩ። በዚሁ መሠረት ማኅበሩ እንዲጠቀምበት አበርክቻለሁ ብለዋል። ሌሎችም ማኅበሩ የሚሰጠውን አገልግሎት ለማጠናከር የድርሻቸውን እንዲወጡ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

የልማት ተቋማት ዳሬክተር አቶ ኃይሉ ፍስሐ ሥጦታውን ከተረከቡ በኋላ ወ/ሮ መስታወት

እና Â ባለቤታቸው Â የልብስ ስፌት ማሽኑን ለማኅበሩ አገልግሎት በማበርከታቸው መደሰታቸውን በመግለጽ ላበረከቱት ሥጦታም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

< ወደኋላ ወደፊት >

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለዘለአለም ትኑር

<u>6/ ክርስቶሳዊ የሆነች የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ስለ ሃይማኖት ያላት</u>

አስተምሕሮ፡-

ሃይማኖትን በአፍ አምኖ በልብ መካድ እንደ አርዮስ መሆን ነው፤ በልብ አምኖ በአፍ ቢክዱም እንደ ጴጥሮስ መሆን ነው፤ ቅዱስ ጴጥሮስ ንስሐ ባይገባ ኖሮ የልቡ እምነት ባልጠቀመውም ነበር። እንግዲህ የልብን በአፍ የአፍን በልብ አንድ አድርጎ፤ አስተባብሮ ማመን ይገባል። አመንኩ በዘነበብኩ፤ በተናገርኩት አመንኩ ብሎ ክቡር ዳዊት ተናግሯል (መዝ.115፡1)። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው አፍኒ ዘየአምን ቦቱ ይጸድቅ ወልብኒ ዘየአምን ቦቱ የሐዩ፤ አፉን ልቡን አንድ አድርጎ በእውነት ያመነ ሰው ይድናል እንዳለ (2 ኛ.ቆ.4፡13)።

በልብ ማመን እንደምን ነው ቢሉ በሃይማኖት ፀንተን የክርስቶስን ፍቅር የሚያስጥለን ማንም የለም ብሎ አምኖ ፀንቶ መኖር ነው። መኑ የኃድገነ ፍቅሮ ለክርስቶስ ሕማምኑ፤ ምንዳቤኑ፤ ረሀብኑ፤ ዕርቃንኑ፤ መጥባሕትኑ፤ ጻዕርኑ፤ የክርስቶስን ፍቅር ማን ያስተወናል፤ ሕማም ነውን? መከራ ነውን? እሳት ነውን? ረሀብ ነውን? መታረዝ ነውን? በሰይፍ መቆረጥ ነውን? ጭንቅ ነውን? ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረ (ሮሜ. 8፡33-36)

የቀና ሃይማኖት ካለን ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን የሚችል የለም። እመኒ አፍርሑኒ በስደት ውስተ መካናት ርሑቃት ወእመኒ ወደዩኒ ውስተ እሳት። ወደ ሩቅ ቦታ እናሳድድሃለን፤ ወደ እሳትም እንጥልሃለን ቢሉኝ ለአናብስት አሳልፈው ቢሰጡኝ፤ ወደ ጥልቅ ባሕርም ቢያሰጥሙኝ፤ እጄን እግሬንም በሰይፍ ቢቆርጡኝ፤ ልዩ ልዩ በሆነ ሥቃይ ቢያሰቃዩኝ፤ እኔ ሃይማኖቴን አልክድም ልቡናዬ በቃለ እግዚአብሔር፤ በኢየሱስ ክርስቶስ የጸና ነው እንዳለ ሳዊሮስ። ስለዚህ የክርስቶስን ፍቅር ሊያስተወን የሚችል የለም።

ክርስቲያን የሆነ ሰው ሁሉ ሃይማኖቱን ተምሮ ካወቀ በኋላ በጎውን ሥራ ካልሠራ እንደ አጋንንት መሆኑ ነው። ወአንተሰ ተአምን ከመ አሐዱ ውእቱ እግዚአብሔር ወሠናየ ትገብር አጋንንትኒ የአምኑ፡፤ ኪያሁ ወይሰግዱ እንዳለ ያዕቆብ (ያዕ.2፡19)።

ዮሐንስ አፈ ወርቅም እመቦ ብእሲ ዘቦቱ ሃይማኖት ወምግባሩሰ እኩይ ውእቱ ናሁ ክህደ ሃይማኖቶ ወአጽአለ ሕገ ተምህሮ፤ ሃይማኖት ያለው ሰው ቢኖር ምግባሩ ክፉ ከሆነ እነሆ ሃይማኖቱን ካደ የትምህርትንም ሕግ አሰደበ ብሏል፤ ምግባርም ሠርቶ ሃይማኖትን ካልተማረ ካላወቀ በምግባር ብቻ ሊጸድቅ ክርስቲያን ሊባል አይቻለውም። ሃይማኖት ርትዕት ትእዛዘ ስነ ምግባራት፤ ወዘእንበሌሃሰ ኢይትከሃሎ ለክርስቲያናዊ ይሰመይ ክርስቲያነ፤ የቀናች ሃይማኖት የምግባርን መልክ ትይዛለች፤ በምግባር መልክ ትገለጻለች፤ እንዲህ ካልሆነ ግን ክርስቲያም ተብሎ ሊጠራ አይገባውም እንዳለ ዮሐንስ አፈ ወርቅ።

በጎ ምግባር የሌለው ሃይማኖት፤ ነፍስ የተለየው ሥጋን ይመስላል፤ ነፍስ የተለየው ሥጋ መውረድ መውረድ መውጣት፤ መብላት መጠጣት፤ ተግባረ ሥጋ ተግባረ ነፍስን መሥራት እንደማይችል ሁሉ በጎ ሥራም የሌለው ሃይማኖት ተራራ ማፍለስ፤ ድውይ መፈወስ ተአምራትን ሁሉ ማድረግ አይቻለውም። ከመ ሥጋ ዘአልቦ መንፈስ ውእቱ ከማሁ ሃይማኖትኒ እንተ አልባቲ ምግባረ ሠናይ ምውት ይእቲ ለሊሃ፤ ነፍስ የሌለው ሥጋ የሞተ እንደሆነ ሁሉ በጎ ምግባር የሌላት ሃይማኖትም በራስዋ የሞተች ናት (ያዕ.2፡17)።

በአፍ ማመን እንደምን ነው ቢሉ እነሆ ክርስቲያን የሆነ ሰው ሁሉ ስለ

ሃይማኖቱ ማናቸውንም ነገር ሳይፈራና ሳያፍር ገልጦ መናገር ይገባል።

ወልደ እግዚአብሔር በአባቱ ፊት ልጄ ወዳጄ ብሎ እንዲያምነው እንዲወደው፤ ክቡር ዳዊት ወእነግር ስምዓከ በቅድመ ነገሥት ወኢይትኃፈር ብሎአል (መዝ.118፡45-46)። ከአላውያን ነገሥታት ፊት ምስክርነትህን እናገራለሁ አላፍርም አልፈራም ብሎ እንደተናገረ ዮሐንስ መጥምቅ የሄሮድስን የሄሮድያዳን ፊት፤ ኤልያስ የአክአብን የኤልዛቤልን ፊት፤ ሠለስቱ ደቂቅ የናቡከደነጾርን ፊት እንዳላፈሩ። ጌታም በወንጌል ወለዘሰ አምነኒ በቅድመ ሰብእ አነኒ አአምኖ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት፤ በሰው ፊት ያመነኝን እኔም በአባቴ ፊት ልጄ ወዳጄ እለዋለሁ እንዳለ (ማቴ.10፡32)።

ለክርስቲያን ልጅ ሁሉ ከተግባረ ሥጋ ከተግባረ ነፍስ አስቀድሞ የቀና ሃይማኖትን መማር ይገባዋል፤ ለበጎ ሥራ ሁሉ መሠረቱ የቀና ሃይማኖት ነውና

David Sileshi

7/ :::: ሕግጋተ እግዚአብሔር ::::

::::::::::::::::::::::::::::::::

1. ሕገ ልቦና (የሕሊና ሕግ):-

2. አሠርቱ ቃላት: /አሠርቱ ትዕዛዛት/ /አሠርቱ ሕግጋት/ /ሕገ መጽሐፍ (ሕገ ኦሪት)/:-

3. ስድስቱ ሕግጋት /ስድስቱ ትዕዛዘተ / /ስድስቱ ቃላተ/

ወንጌል:-

4. አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን:-

5. በለተ ምጽአት ከጌታችን የምንጠየቃቸውና የምንመልሳቸው 6

ጥያቄዎች:-

ከላይ በተራ ቁጥር የተዘረዘሩ ሕግጋት ማብራሪያ ተሰቶባቸዋል

አንብበው ይጠቀሙ:+

+እግዚአብሔር አማላክ ፈጣሪ እንደመሆኑ ፈቃዱ የማይለወጥ

ቀዋሚ ስለሆነ ጊዜያዊና ቅጽበታዊ ፍጥረት አልፈጠረም:

ፈጥሮም ያለዓላማ: ያለሕግ ያለሥርዓት አልተወም።

በዓለሙ ሙሉ የሆነ እግዚአብሔር ሕግጋቱም ሁሉን

የሚመለከትና ለዓለሙ ሁሉ ቀዋሚ የሆኑ ሕግጋት ናቸው።

እነዚህም:- ሕገ ልቦና (የሕሊና ሕግ) : አሠርቱ ቃላት: ስድስቱ

ቃላተ ወንጌል ናቸው።

+++++++

:::1::: ሕገ ልቦና (የሕሊና ሕግ):-

በሰው ልቦና አንድ ጊዜ ከተጻፈ ሳያረጅ ከትውልድ ወደ ትውልድ

ሲተላለፍ የሚኖር ሕግ ነው። ሕገ ልቦና በሰው ሁሉ ልብ

የሚገኝ እያንዳንዱን ሰው ማንም ሳያስተምረው: ክፉውንና ደጉን

ለይቶ ሳይነግሩት እንዲያውቅ የሚያደርገው ነው። እውነተኛ ሰው

ምንም ባይማር በዚህ በሕገ ልቦና ወይም በሕገ ተፈጥሮ

መሰረት እውነትን ከሐሰት: ጽድቅን ከኃጢአት: ደጉን ከክፉ ለይቶ

ያውቃል። ከዚህም የተነሣ እውነቱን ይናገራል: ይሰራል ከክፉም ይርቃል።

+። ስለ ሕገ ተፈጥሮ (ሕገ ልቦና) ቅዱሳት መጽሐፍት በተለያየ መንገድ ይመሰክራሉ። ስለዚህም ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ አለ:-

፤ እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና።

፤ ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል፤

፤ በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና።

፤ ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ÷ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤

፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው÷ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ። (ወደ ሮሜ ሰዎች ምዕ. 2÷11-15)

+ይኽ ሕገ ልቦና የተባለው ያን ጊዜ በተፈጥሮ እንደተሰጠ ያለ የጸናም ሕግ ይሁን እንጂ የሰው ልጅ በሕገ ልቦና ብቻ ሊጠበቅ ባለመቻሉ በግድ የጹሑፍ ሕግ አስፈለገ። ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ በእጁ ጽፎ ሌላ ሕግን በሙሴ አማካይነት ለጊዜው ለእሥራኤል ወገን ፍጻሜው ግን ለሰው ልጅ ሁሉ ሰጥቷል። ቀጥሎም የጌታ ደቀ መዛሙርት ሐዲሱን የኪዳን ሕግ

(ስድስቱን ቃላት ወንጌል) በጹሑፍ አበርክተዋል።

++++++++++

:::2::: አሠርቱ ቃላት: አሠርቱ ትዕዛዛት: አሠርቱ ሕግጋት: ሕገ መጽሐፍ(ሕገ ኦሪት):-

የሚባሉት እግዚአብሔር አምላክ ግንኙነቱን ከእስራኤል ህዝብ ጋር በማድረግ መገናኛ ይሆኑ ዘንድ የሠራቸውና የደነገጋቸው ሲሆኑ: በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ አሠርቱ ቃላት እየተባሉ የሚጠሩ ናቸው። እነዚህም እግዚአብሔር በሁለት ሠሌዳ ጽፎ ለእስራኤል ያስተላለፈው ሕግ ነው።

ሁለቱ የሕግ ጽላት የአስርቱ ቃላት ማደሪያ ሠሌዳ ሁነው የተሰጡ ናቸው። እንደ ሊቃውንቱ አስተያየት በአንደኛው ጽላት ሦስት ቃላት እግዚአብሔር ወይም እግዚአብሔር አምላክን የሚመለከቱ ለእርሱ ልናደርግና ልንፈፅመው የሚገባንን የሚገልጡ ናቸው። በሁለተኛው ጽላት ደግሞ ሰባት አንቀጾች ተጽፈውበታል: ይኸውም ሰውን የሚመለከቱ ማለት ሰው አንዱ ለሌላው ሊያደርገውና ሊፈጽመው የሚገባውን የሚያሳዩ አሠርቱ ቃላት በመጀመሪያ ለሰው መመሪያ እንዲሆኑ በጽሁፍ የተላለፉ ህግጋት ናቸው። ምክንያቱም የሰው ልጅ በመጀመሪያ በሕገ ልቦና እንዲሁም በሕገ ህሊና በሕግ ሊጸና ለእግዚአብሔርም ሊታዘዝ ተፈጥሮ ነበር: ይህ ግን ባለመቻሉ በጣኣትና በማታ እያነበበ: እያየም ሰው የሆነ ሁሉ እንዲጠብቀውና እንዲፈጽመው እግዚአብሔር አምላክ ስለፈቃደ ሕጉን በጽሁፍ

ሰጠው እነዚህ በጽሁፍ የተላለፉ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት
ለክርስቲያኑ ህዝብ አሁንም አስፈላጊዎች ናቸው።
+ ከአሠርቱ ቃላት ዘጠኙ ተጠብቀው እንደኛው እንኳን ከፈረሠ
አሠርቱ ሕግጋት ሁሉ እንደፈረሱ ይገመታል እንጂ የዘጠኙ
መጠበቅ ምንም ዋጋ የለውም። ለምሳሌ አሥር በር ያለው ቤት
ቢኖር ዘጠኙ በሮች ቢዘጉና አንዱ ክፍቱን ቢያድር: ሌባ ክፍት
በሆነው በአንደኛው በር ገብቶ ንብረቱን ሁሉ ከወሰደው የዘጠኙ
በሮች መዘጋት ምንም ጥቅም አላስገኘም ማለት ነው
የአንደኛው መከፈት ለንብረቱ መጥፋት ምክንያት ሆኗልና።
አሠርቱ ቃላትም በትክክል ካልተጠበቁ ዋጋ የማያሰጡ
መሆናቸውን ሐዋርያው ያዕቆብ እንዲህ ሲል ያስረዳል:-
" ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም
ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤ አታመንዝር ያለው ደግሞ።
አትግደል ብሎአልና፤"
(የያዕቆብ መልእክት 2:10)
:::::::::::::
10 ቱ ትዕዛዛት እነማን ናቸው
:::::::::::::
>አንቀጽ 1:-
" ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።"
(ኦሪት ዘጸአት 20:3)
::::::

>አንቀጽ 2:-

" የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤

እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።

"

(ኦሪት ዘጸአት 20:7)

:::::

>አንቀጽ 3:-

" የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።"

(ኦሪት ዘጸአት 20:8)

:::::

>አንቀጽ 4:-

" አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ

በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።"

(ኦሪት ዘጸአት 20:12)

:::::

>አንቀጽ 5:-

፤ አትግደል።

(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:13)

:::::

>አንቀጽ 6:-

፤ አታመንዝር።

(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:14)

:::::

>አንቀጽ 7:-

፤ አትስረቅ።

(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:15)

:::::

>አንቀጽ 8:-

፤ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።

(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:16)

:::::

>አንቀጽ 9

፤ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም

ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ

ማናቸውንም አትመኝ።

(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:17)

:::::

>አንቀጽ 10

" ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፤ "

(ኦሪት ዘሌዋውያን 19:18)

++++++

:::3::: ስድስቱ ሕግጋት (ትዕዛዘተ) ወንጌል:-

እንደ ብሉይ ኪዳን እምነት ስርዓት ህግን እንደፈፀመ

የሚቆጠረው ፍፁምም አይሁዳዊ ነው የሚባለው አሠርቱ ቃላተ

ኦሪትን የጠበቀው ነበር። በሐዲስ ኪዳንም አሠርቱ ቃላት ኦሪት
ምንም ሳይነኩ እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪ ሌሎችም
አዲሶች ሕጎች አስፈለጉ። አሠርቱ ቃላተ ኦሪት መጠበቃቸውንና
እንዳሉም መጽናታቸውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
፤ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤
ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።
፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ
አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ
እስኪፈጸም ድረስ። (የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:17-18) ሲል
ግልጽ አድርጎ ተናግሯል።
+ከዚህ በተጨማሪ ግን እነዚህኑ አሠርቱ ቃላትን በስድስቱ
አንቀጽ አጠቃሎና አሳጥሮ ቃላተ ወንጌል ወይም ትዕዛዛተ
ወንጌል ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ግን እላችኋለሁ
እያለ አጥብቆ: አጽንቶና ወስኖ ተናግሮ ይገኛል።
አሁንም የሐዲስ ኪዳንን ህግጋት ስናቀርብ እነዚህ የብሉይ
ኪዳን ህግጋት ለሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ ሆነው አጥረውና
ተጠቃልለው በስድስት ቃላት ይቅረቡ እንጂ አሁንም መሠረቶቹ
አሠርቱ ቃላት ናቸው።
ሆኖም አጥረው: ተጠቃለው ከበድም ብለው ለሐዲስ ኪዳን
መታወቂያ መለያም ሕግ ሆነው የቀረቡ ሲሆን እነዚህን ሕግጋት
ለይቶ: ጠንቅቆ ማወቅና መጠቀም በጣም አስፈላጊ በመሆኑ
እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል:-

:::::

>አንቀጽ 1:-

አትግደል ላለው

" ለቀደሙት። አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል።"

+++++++

" እኔ ግን እላችኋለሁ÷ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።"

(የማቴዎስወንጌል 5:21÷22)

:::::

>አንቀጽ 2:-

አታመንዝር ላለው

" አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል።"

+++++++

" እኔ ግን እላችኋለሁ÷ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።"

(የማቴዎስ ወንጌል 5:27÷28)

:::::

>አንቀጽ 3:-

መፍታት እንደማይገባ

፤ ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ።

++++++

፤ እኔ ግን እላችኋለሁ÷ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል÷ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:31÷32)

:::::

>አንቀጽ 4:-

ፈጽመህ አትማል ላለው

፤ ደግሞ ለቀደሙት። በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደተባለ ሰምታችኋል።

++++++++

፤ እኔ ግን እላችኋለሁ። ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤

፤ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤

በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤

፤ በራስህም አትማል÷ አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና።

፤ ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህም የወጣ ከክፉው ነው።

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:33-37)

:::::

>አንቀጽ 5:-

"ክፋውን በክፉ አትቃወሙ"

፤ ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል።

+++++++

፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፋውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ

ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፤

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:38-39)

:::::

>አንቀጽ 6:-

"ጠላትህን ስለመውደድ"

፤ ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ

ሰምታችኋል።

+++++++

፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ

ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥

ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም

ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥

በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።

፤ የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ

ያደርጉ የለምን?

፤ ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ

ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?

፤ እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን
ሁኑ።
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:43-48)
+++++++
:::4::: አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን:-
ስድስቱ ቃላተ ወንጌል የአስርቱ ቃላት ኦሪት መጠበቂያና
ማጠረያ እንደሆኑ አንድም አሠርቱ ቃላት በስድስት ቃላተ
ወንጌል እንደጸኑ ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ደግሞ አሥሩ አንቀጸ
ብፁዓን ይታጠራሉ: ይጸናሉ: ፍጹምነታቸው እንዲታወቅ ይሆናል።
እነዚህ አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን የሕግ ፈጻሚነት ምልክትና
የፍፁምነት መታወቂያ ትሩፋት ናቸው እንጂ ሕግጋት አይደሉም።
እነዚህ የፍጹምነት: የብፅዕናና የቅድስና መታወቂያ አንቀጾች
ጌታ የተናገራቸው ሱሆኑ የፍፁምነት ማዕረግ የሚሰጡ ናቸው።
እነዚህ አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን ወይም ሕገ ትሩፋት የሚባሉት
የሚከተሉት ናቸው:-
1. " በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ
ሰማያት የእነርሱ ናትና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:3)
2. " የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መፅናናትን ያገኛሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:4)
3. " የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:5)

4. " ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥
ይጠግባሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:6)
5. " የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:7)
6. " ልበ ንጹሐኞ ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:8)
7. " የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች
ይባላሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:9)
8. " ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት
የእነርሱ ናትና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:10)
9. ፤ ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን
ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ።
፤ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም
አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ
አሳድደዋቸዋልና።
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:11-12)
10. " ይህን ብታውቁ፥ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ።"
(የዮሐንስ ወንጌል 13:17)
+ሙሴ ዘጠኙን ሕግጋት በኦሪት ዘፀአት 20:17 ተናግሮ

አሥረኛውን በኦሪት ዘሌዋውያን 19:18 እንዳመጣው ጌታም
የተናገረውን አስሩን አንቀጸ ብፁዓን 9 ኙን በማቴዎስ ወንጌል
ተናግሮ አስረኛውን በዮሐንስ ወንጌል ያመጣዋል። ይህም
የመጨረሻው የብፅዕና አንቀጽ ትህትና ነው።

+++++++

:::5::: በለተ ምጽአት ከጌታችን የምንጠየቃቸውና
የምንመልሳቸው 6 ጥያቄዎች:-

ትንሣኤ ዘጉባኤ:- ትንሳኤ ዘጉባኤ ማለት በዕለተ ምጽአት ጌታ
ለፍርድ ሲመጣ በእርሱ ትእዛዝ (በአዋጅ ድምፅ) ተለያይተው
በተለያየ ስፍራ ይኖሩ የነበሩ ነፍስና ሥጋ ከሞት በኋላ በነፍስና
ስጋ ህይወት መገኘትና ተዋህዶ መነሳት ማለት ነው። ይህ ሰውን
ብቻ የሚመለከት ነው።

+++++++

" በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤
እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ
ዘላለም ጕስቍልና። "
(ትንቢተ ዳንኤል 12:2)

" በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤
መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ
ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።"
(የዮሐንስ ወንጌል 5:28-29)

" እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን

እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።"

(የዮሐንስ ራእይ 22:12)

" እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን።"

(የዮሐንስ ራእይ 1:7)

፤ ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤

፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።

፤ ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።

(1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ምዕ. 4:16-18)

:: :: :: :: :: :: :: ::

*1 የመጀመሪያው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አውሬ የበላው ነፋስ የበተነው ያለቀውና የደቀቀው ሁሉ ራሱ በፈረሰበት ቦታ ላይ ይሰበሰባል። (ያዕቆብ ዘስሩግ ቁ.91)

*2 ሁለተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አጥንትና ሥጋ ተዋህደው ሳይንቀሳቀስ ትኩስ ሬሳ ይሆናሉ አጥንቶችና ጂማቶች ከስጋና ከደም ጋር ይያያዛሉ። እስኪነሱ ያለመንቀሳቀስ ፍጹም በድን ይሆናል።

*3 ሶስተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ በቅዋሚ አካል በምትናገር አንደበት ከራስ ጠጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ከቁጥር ሳይጓድሉ ከሰውነታቸው ሳይከፈል ወንድ በአቅመ አዳም የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ: ሴት በአቅመ ሔዋን የአስራ አምስት ዓመት ቆንጆ ሆነው በአርባ ቀን በእናቱ ማኅፀን ደም ሆኖ የወረደ ጽንስ ሳይቀር እያንዳንዱ የሥራውን ዋጋ ሊቀበል ይነሳሉ።

++++++

፤ የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤

፤ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥

፤ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።

፤ ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል። እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።

፤ ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥

፤ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና።

፤ ጻድቃንም መልሰው ይሉታል። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ?

፤ እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ?

፤ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን?

፤ ንጉሡም መልሶ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።

፤ በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል። እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።

፤ ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፥

፤ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና።

፤ እነርሱ ደግሞ ይመልሱና። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል።

፤ ያን ጊዜ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል።

፤ እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 25:31-46)

::::: ተፈጸመ :::::

ጌታችን መድኃኒታችና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰራቸው

ሕግጋት እንድንፈጽም ይርዳን: አለማመናችንን ይርዳው አሜን።

ወ ስ ብ ሐ ት ለ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር

ወ ለ ወ ላ ዲ ቱ ድ ን ግ ል

ወ ለ መ ስ ቀ ሉ ክ ቡ ር

አ...ሜ...ን

(ምንጭ:ነገረ ምጽአት ከሚል መጽሐፍ አባ ወልደ ዮሐንስ ወ/

ኢየሱስ እንዳዘጋጁት በከፊል የተወሰደና በተጨማሪም ከ 81

አህዱ መጽሐፍት የተወሰደ)

በእንተ ቤተ ክርስትያን ዘሻሸመኔ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

8/ "<u>መከሩስ ብዙ ነው ሰራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው" ማቴ. ፱÷፴፰</u>

ቃሉን የተናገረው ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን

ፀሃፊው ደግሞ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ነው። ቅ/ማቴዎስ ቁጥሩ

ከ 12 ቱ ሐዋርያት ሲሆን ወደዚህ አገልግሎት ከመጠራቱ በፊት በሙያው

ቀራጭ ነበር ። ማቴ.9÷9፤ ሉቃ.5÷27

በጠቀስነው ክፍለ ምንባብ ላይ እንደምናነበው:- ጌታችንና መድሃኒታችን

ኢየሱስ ክርስቶስ በምኩራባቸው እያስተማረ የመንግስቱን ወንጌል እየሰበከ ድውያነ ሥጋን በተዓምራት ድውያነ ነፍስን በትምህርት እየፈወሰ በመንደሩ ሁሉ ያልፍ ነበር። በዚህን ግዜም ህዝቡ ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች ተበትነው ሲያያቸው አሳዘኑት(ወርእዮ ብዙኃነ ሰብዓ አምሐርዎ ወተሠሃሎሙ እስመ ስሩሐን እሙንቱ ወግዱፋን ከመ ዐባግዕ ዘአልቦ ኖላዊ) እንዲል። ደቀመዛሙርቱንም እንዲህ አላቸው:-" መከሩ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው እንግዲህ የመከሩ ጌታ ሠራተኞችን እንዲል ክ ለምኑት" ማቴ.9÷36-38

ዛሬም በዘመናችን እየሀነ ያለው ይኸው ነው መንጋውን የሚጠብቁ እረኞች ጠፍተው መንጋው ተበትኗል። በግድም እንደምንም የተሰበሰበውንም ለመበተን የማይሳሱ እረኞች ዘመናችን አሳይቶናል። በከተማችንም እየሆነ ያለው ከዚህ የተለየ አደለም ህዝቡ በራሱ ጥረት ይሰበሰባል ጥቂት ምንደኞች ሊበትኑት ይጥራሉ ለዚህም ይሰበስባሉ ህዝቡን ያረጋጋሉ የሚባሉት በዚህ ሰዓት ከአውደ ምህረት ተሰደዋል አልያም ወደ ወህኒ ተልከዋል። እውነተኛው የበጎች እረኛ ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ዛሬም ህዝቡን ከመበተን ይጠብቃል።ነገም እውነተኛ እረኝችን እንዲያስነሳ እናምናለን።

ይህን መልዕክት የምታነቡ ሁሉ ስለ ቤተ ክርስትያን ሰላም አብዝታችሁ ጸልዩ። በከተማችን ያላችሁና ይህ ችግር ያገኛችሁ ክርስትያኖችም በትዕግስት ደጅ ጥኑ በጸሎትም በርቱ ሁሉን መርምሩ መልካሙንም ያዙ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑ እንደ ክርስትያን በጥበብ ተመላለሱ ለክፋትም ምላሽ አትስጡ እርስ በርሳችሁም ስለ ቤተ ክርስትያን አንድነት ተወያዩ መረጃው

ለሌላቸውም ችግሩን ከመሰረቱ አስረዱ።

የቤተ ክርስትያን አምላክ የሰላም ዘመን ያምጣልን።

የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የመላዕክት ጥበቃ የቅዱሳኑ ሁሉ ጸሎት ከኛ አይለየን። አሜን! ይቆየን።

የማርያም ባሪያ ኤፍራታ ኦርቶዶክስ with Sara Yemariyam Lij

ይትባረክ እግዚአብሄር አምላክ አበዊነ የጸረ ሐራጥቃ ይፋዊ የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ጉባኤ 2 እንድምታን በተከታታይ እናቀርባለን።

ማሳሰብያ ይህን ተከታታይ ፖስት share በማድረግ እንዲሁም ፖስት በማድረግ እንድታጋሩ ይሁን

ክፍል አንድ

By Daniel king

9/ ጉባኤው ‹‹ ከካራን ውጡ ከነአን ግቡ ››በተሰኘው ኦርቶዶክሳዊ መዝሙር ተከፍቶዋል የመዝሙሩ እንድምታ እግዚአብሄር ከማይከብርበት የክርስቶስ አምላክት በአማላጅነት ሚዛን በሚዋርድበት አዳራሽ ማህበራት ሃራጥቃ አቀንቃኞች ባዘጋጁት ጉባኤ ባገኙት አጋጣሚ ቤተክርስቲያንን ማይወክል መንገድን ከሚያስተምሩ ተከታይነት የፕሮቴስታንት ፍርፋሪ ለቃቃሚነት ውጡ ወደተቀደሰችው ርትዕት ሃይማኖት ግቡ የሚል ዘመኑን የዋጀ መልእክት ነው።

በመምህር ምህረተ አብ አማካኝነት እግዚአብሄር የተናገረውን የቤተክርስቲያን ድምጽ እንዳስስ።

መምህሩ በሰላምታ ጀመሩ ‹‹በእግዚአብሄር እጅ በመነዳት ሰማያዊን ተስፋን ባዘለች በቅድስት ቤተክርስቲያን የተሰበሰባቹ እግዚአብሄር የሚወዳቹ አባቶቼ እናቶቼ ወንዶቼ እህቶቼ እንደምን ዋላቹ‹‹ እግዚአብሄር ይመስገን ››((7)ግዜ ተብሎዋል)። እግዚአብሄር አባታችን እግዚአብሔር አምላካችን በመለኮታዊው ጥባቆት ጠብቆ ለዚ ሰአት ስላደረሰን ክብርና ምስጋና ውዳሴ እና አምልኮ ለስሙ ይሁን።

የሚወዱንን መውደድ አቅቶን በምንቸገርበት በዚህ አለም የምንጠላውን አፍቅሮ እስከሞት የደረሰ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።በብእር ጫፍ ሳይሆን በደሙ ቀለምነት ስማችንን የጻፈ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰው ያለውን ሰጥቶ ሲጨበጨብለት ራሱን የሰጠ ቤዛ ሆኖ ያዳነን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ክብር ሁሉ አልፋና ኦሜጋ ለሆነው ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን። አምላክን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ለወለደች ከወለደቹም በውሃላ ማህተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ እንደወትሮ የኖረች የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ምስጋና ይድረሳት። ቅዱሳንም ሁሉ እንደተሰጣቸው ጸጋ ምስጋና ይድረሳቸው። >>

የትምህርቱ መጀመርያ የተደረገው ወደውሃላ በመመለስ በዘመነ ሰማእታት ክርስትናን ከአለም ለማጥፋት አላዊያን ነገስታት ያደረጉትን ሰይጣናዊ ስብሰባ ነው አንድም ጉባኤ ኬልቄዶንን ‹‹ጉባኤ ከላባት የውሸች ጉባኤ››ን ነው የሰይጣን ጉባኤ የተባለው ኦርቶዶክሳዊያንን ለማጥፋ የንስጥሮስና የአርዮስን ትምህርት በገዢዎች የተረዱ መናፍቃን የተባበሩበት በጉባኤው

የተገኙትን የኦርቶዶክስ እምነት አባቶች እግራቸውን በመጋዝ ቆርጠው አይናቸውን አፍስሰው በደረቁ ላጭተው ጥርሳቸውን አውልቀው ሰማእትነት የተፈቀደላቸውን ገድለው የመለሱበት የውሾች የተረገመን ጉባኤ ነው።

ይህ ጉባኤ በክርስቶስ ጠላት በሰይጣን (በሉሲፈር) የተመራ ነበር ክርስቶስን በተዋህዶ ሰው መሆን ያልተቀበሉ በዚ ዘመን <<ካቶሊክ>>ብለን የምንጠራቸው የሁለት ባህሪ ትምህርትን ያጸኑበት የክህደት ሁሉ ክህደት የሆነ ትምህርት ነው።

አንድም በዘመነ ሰማእታት ክርስትናን ለማጥፋት በሰይፍ መሞከራቸውን ሚያስረዳ ነው ብዙ አላዊያን ነገስታ 10ሩ የሮማ ነገስታት ተነስተው የክርስቲያኖችን ደም እንደ ጎርፍ አፍስሰዋል እነ ትራዢያን እነዳርክዮስ ዲዮቅልጢያኖስ በተለያየ ዘመን ይህንኑ ደምማፍሰስ አድርገዋልና ግን ክርስቲያንን በደም ማስቆም አይቻሉም በደም ነውና የተመሰረተው ይህንንም ማጠቃለያ ጉባኤው በግጥም ገልፆታል

ክርስትናን በሰይፍ ለማጥፋ መነሳት ማራገብ ያህል ነው ነፋስን ወደ እሳት ኔሮን ተጨምሮ ንጉሰ ነገስተቷ

ሮማም አልቻለች በጦር ሰራዊቷ ክርስትና ሃይማኖት በሰይፍ አላለቀም ከጳውሎስ አናት ጋር ተቆርጦአልወደቀም

ሲሉ መምህሩ በጥበብ በግጥም በተሰጣቸው ጸጋ ገልጸዋል

<<ከጳውሎስ አናት ጋር ተቆርጦ አልወደቀም>>ሲሉ አንድም ብርሃነ አለም ጳውሎስ አህዛብን ወደ ክርስቶስ ያመጣ ነውና አንድም ክርስትናን ከብሉይ ከቱፊት ከአዋልድ ከህግ ጋር አጣጥሞ ሰብኮዋልና

አንድም ስለ ቤተክርስቲያን ከሚደርስበት መከራ አብልጦ ያስብ ነበርና

አንድም ጳውሎስን የመሰለ ጠቢብ ለግሪክ ፈላስፋዎች ከንቱ ትምህርታቸውን አውድሞ ክርስትናን ሰብኮዋልና

አንድም የትርገዋሜ አባት ነውና አንድም በጳውሎስ አማካኝነት ሰማእትነትን የተቀበሉ ሃዋርያትን ሁሉ መግለጥ ነውና አንድም ሃዋርያት በሰማእትነት ያቆሙዋት ሃይማኖት መሆንዋን ሲያጠይቅ ነውና አንድም ሃዋርያትን በመግደል ሺ ሃዋርያት መፈጠራቸውንን ሲያጠይቅ ነው። ይቆየን።

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ይእዜኑ ወዘልፈኒ ወለአለም አለም አሜን።

የዘመድኩን የዓላማው ደጋፊዎች

<u>10/ "የሰማይ አምላክ የከናውንልናል እኛም ባርያዎቹ ተነስተን እንሰራለን"</u>

ተሀድሶን/የእናት ጡት ነካሾችን/በመዋጋት ግንባር ቀደም የሆነው ወንድማችንን መምህር ዘመድኩንን የማግኘት እድሉን አግኝተን ነበር ።

በጉዳያችንም ላይ ስለተዘጉበት የ facebook Account እና ወደ ፊትም መስራት ስላሰበው

Website and Blog development በሐሳቡ ላይ ተጨዋውተናል።

በመሆኑም የ IT ባለሙያ የሆኑ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች ስራውን በከፍተኛ ሁኔታ እየተወጡት እንደሆነም ነግሮናል።ሰሞኑንም Website እና blog ተደራሽ ይሆናል ማለት ነው።

እኛም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ከወንድማችን ከመምህር ዘመድኩን ዓላማዎች ጎን ከመቼውም ግዜ በበለጠ የምንቆምበት ግዜ አሁን ነው። # የቤተ ክርስትያናችን ጉዳይ ስለ ሚያገባን#

መረጃ ለምትፈልጉ የእጅ ስልኩም 0911608054 ነው።እውነትም ክፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል።

"የገሐነም ደጆች አይችሏትም"

Yesterday at 5:11pm · Public · in Mobile Uploads

View Full Size · Send as Message · Report

ማህተቤን አልበጥስም and 423 others like this.

View previous comments...

Joshua Mosses Elias

አቃጣሪ ስራ ፈት ሁላ ድሮስ ህፃን ተረት ተረት እንጂ እውነት መች ትፋልጋላችው!አሳዳጁ ፈርኦን ቢያሳድደን እስከ ቀይ ባህር ድረስ ነው!

Like · Reply · Report · 2 hours ago

Ortodoxe Negn

ዘመዴ እግዚአብሔር ይርዳህ አይዞህ ፥ ወደ ቀራኒዮ ጉዞ ድንግል ማርያምን ይዞ ።

Like · Reply · Report · 1 hour ago

Ortodoxe Negn

Joshua ይቅርታ ወንድም ተዋህዶ ታድሰናለች እንጂ አትታደስም ተዋህዶ አንዲት ናት አባቶች የሞቱላት አሁን በመጡ ዘመናዊ መናፍቃን አንከተልም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለዘላለም ትኑር አሜን

Like · 2 · Reply · Report · 1 hour ago

Balay Endu

አጋንንት እና ፕሮቴስታንት መቼም አንድ ናቸው ስለ እመ.ቅ.ድ.ማረያእም እና ስለ መዳንያለም ሲነገር ይቃጠላሉ የተዋህዶ ልጆች እግዚአብሄር ይጠብቃቹህ በስራቹህ እግ/ሄር ከእናንተ ጋር ይሁን !!!

11/ "ያገለግለኝ ዘንድ ህዝቤን ልቀቅ"

ኦ.ዘጸ ፰፥፪ እግዝአብሄርም እንዲህ ይላል ያገለግለኝ ዘንድ ህዝቤን ልቀቅ:ለመልቀቅ እንቢ ብትል ግን እንሆ እኔ አገርህን በጌጉንቸሮች እመታለሁ።

ኦ.ዘጸ ፲፬፥፲፭ እግዚአብሄርም ሙሴን አለው ለምን ትጮህብኛለህ እንዲጓዙ ለእሥራኤል ልጆች ንገር ።አንተም በትርህን አንሣ እጅህንም በባህሩ ዘርጋ ክፈለውም የእሥራኤል ልጆች በባህሩ ውስጥ በየብሥ

ያልፋሉ።እንሆም እኔ የግብፃውያን ልብ አፀናለሁ በኃላቸውም ይገባለሁ፥.....ሺ፯ 74 74 ሙሴም እጁን በባህር ላይ ዘረጋ ባህሩም ማለዳ ወደ መፍሠሡ ተመለሠ ግብፃውያን ከእነርሱ ሸሹ እግዚአብሄርም ግብፃውያንን በባህሩ መካከል ጣላቸው።ወኃውም ተመልሶ በኃለቸው ወደ ባህር የገቡትን ሰረገሎችን ፈረሰኞችን የፈርሆንን ሠራዊቱ ሁሉ ከደነ.....።

እግዚአብሄር ይናገራል እኛም ባህሩን በዝማሬ እንሻገራለን

እግዚእብሄር አምላክ እንደ ሙሴ ለህዝቡና ለቤተክርሥቲን የሚታዘዝ አባት ይሥጥልን አሜን።

12/ “ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ

በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፥ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ፥ የብዙዎችን ኃጢአት

ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ፥ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል” /ዕብ.9፥ 27-28/።

ምን ማለት ነው???

ቅዱስ ጳውሎስ በመልዕክቱ ሊነግረን የፈለገው ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት

እንዲሉ ለሰው ኑሮ ኑሮ

ሞት እንዲቆየው ኋላም መቃብር እንዲከተለው ሁላችንም ከፊት

የሚጠብቀን አንድ ጊዜ

“መሞት” አለ። ሆኖም ግን ይህ “ሞት” ክርስቲያኖች ለምንሆን ለእኛ

ከድካማችን ዕረፍት

እንጂ እውነተኛ ሞት አይደለም፤ ሞት የሚሠለጥንብን አይደለም።

ሞትስ ሰው የኃጢአቱን

ትብትብ ተሸክሞ ሳለ ሥርየተ ኃጢአትን ሳያገኝ መንግሥተ ሰማያትን

ሲያጣ ነውና። ስለዚህ

ከድካም ካረፍን በኋላ የዘለዓለም ሕይወት አለን። ክርስቶስም

የብዙዎችን ሰዎች ኃጢአት

ያስተሠርይ ዘንድ ኑሮ ኑሮ አምስት ሺ አምስት ዘመን ሲፈጸም አንድ

ጊዜ ራሱን ሠዋ። አዎ!

በአዳም ምክንያት የመጣው ሞት ሁሉን ለማጥፋት መጣ። ክብር

ምስጋና ለስም አጠራሩ

ይሁንና ጌታችንም ኃጢአት ሳይኖርበት ስለ እኛ ኃጥእ አሰኘ። እርሱ

ንጹሕ ሲሆን “ከኃጥአን

ጋር ተቈጠረ” /ኢሳ.53፡12/፤ የእኛን ኃጢአት የራሱ እንደ ሆነ

ቈጥሮ ወደ መስቀል

ወጣ /2 ቆሮ.5፡21/። ማመንን ደኅንነትን ለወደዱም አዳናቸው።

“አባት ሆይ

የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው” ብሎ /ሉቃ.23፡34/

ሥርየተ ኃጢአትን

ሰጣቸው፤ ይቅር አላቸው። ከእንግዲህ ወዲህ ግን የሰውን ኃጢአት

ለመሸከም ሳይሆን

ያዳናቸውን ወደ አዘጋጀላቸው ርስት ወደ ሀገራቸው ለመውሰድ

ይመጣል። የዘይት

ማሰሮአቸውን ሞልተው ተስፋ ለሚያደርጉት፣ ለሚጠባበቁት ለሁለተኛ

ጊዜ ያለ ኃጢአት

ይታይላቸዋል፤ ይመጣላቸዋል። ዓለምን ለማሳለፍ፣ ጻድቃንን

ለማወደስ፣ ኃጥአንን

ለመውቀስ፣ ሞትንና ዲያብሎስን ወደ ጥልቁ በመጣል ለመደምሰስ፣

መንግሥቱንም

ለምእመናን ለማውረስ ይመጣል። ወንድሜ!... እኅቴ!... የኢየሱስን

መምጣት

ትጠባበቃለህን/ ትጠባበቂያለሽን? እንግዲያው ከወንጌላዊው ጋር፡-

“ይህን የሚመሰክር

አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል፤ አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና”

እንበል /ራዕ.22፡20/።

13/ ክፉዎች ደስታቸውን የመሠረቱት በሚጠሉት ሰው ውድቀት ላይ

ነው። ደስታቸው መንፈሳዊ ሳይሆን ሰይጣናዊ ነው። ሠርጋቸውን

የሚያደርጉት ሞታችን ላይ ነው። ወድቀን ካላየ ደስታ የላቸውም። የእኛን

መርዶ ለመስማት ጆሮዎቻቸው የነቁ ናቸው። ታዲያ ውርደታችንን ለሚናፍቁ

ትልቁ መፍትሔ ከሚያዋርድ ግብር ተጠብቆ መኖር ነው። እንድንታመም ክፉ ለሚናገሩን አለመታመም መፍትሔው ነው። ካልታመምን መልሰው ይታመማሉ። በእውነት መረጃ አለኝ የሚሉ ነገር ግን መርጃ አለኝ ብለው መናገር የማይችሉ ስንት አሳዛኞች አሉ። ነቢዩ ከእነዚህ እንዲጠብቀው ጸለየ።

ነቢዩ በመቀጠል፦ ‹‹የሚሹህ ሁሉ በአንተ ሐሤት ያድርጉ ደስም ይበላቸው፤ ማዳንህን የሚወደዱ ሁልጊዜ፦ እግዚአብሔር ታላቅ ነው ይበሉ›› ይላል (መዝ. 69÷4)። ነቢዩ እውነተኛ ወዳጆቹ የእግዚአብሔር ወዳጆች እንደሆኑ ያምናል። የእኛ ወዳጆች የእግዚአብሔር ወዳጆች ላይሆኑ ይችላሉ፤ የእግዚአብሔር ወዳጆች ግን የእኛ ወዳጆች ናቸው። የእኛ ወዳጆች ቀን ዐይተው፣ መሐላቸውን አፍርሰው ሊለወጡ ይችላሉ። የእግዚአብሔር ወዳጆች ግን ፍቅራቸው በዘመናት ያው ነው። የፍቅራቸው መሠረቱ እውነት እንጂ ሁኔታ አይደለም። ነቢዩ ስለ መልካሞች ሲጸልይ፣ በእግዚአብሔር ፊትም መልካሙን ሲመኝላቸው እናያለን። እኛ ስለ መልካሞች መጸለይ የሚያስፈልግ አይመስለንም፤ ነገር ግን በመልካም ሥራቸው እንዲጸኑ ጸጋን መለመን ተገቢ ነው። ከእነርሱ ያነስን ደካሞች መሆናችንን ብናምን እንኳ መጸለይ መልካም ነው፤ ምክንያቱም ጸሎትን የሚመልሰው አንዱና ብርቱው እግዚአብሔር ነውና። በመልካሞች ፊት ስለ መልካምነታቸው ውዳሴ ከማቅረብ፣ በእግዚአብሔር ፊት ስለ እነርሱ መጸለይ እውነተኛነት ነው።

እውነተኛ ደስታ ያለው እግዚአብሔርን በመሻት ውስጥ ነው። የዓለም መሻት እንቅልፍ የሚነሣ እንጂ የሚያሳርፍ አይደለም። እግዚአብሔር ግን ሲሹት እንኳ ያረካል። የእግዚአብሔርን ትድግና ብቻ የሚጠባበቁም

ታላቅነቱን እንደሚያዩ ነቢዩ ተናግሯል። እኛስ የምንሻው ምንድነው? መዳንን የምንናፍቀውስ ከርእዮተ ዓለሞች ወይስ ከአዋቂዎች ነው? እግዚአብሔር ታላቅ ነው ብለን በሥራው ለመዘመር ተስፋችን እርሱ ሊሆን ይገባዋል። እግዚአብሔር ለማዳን ያያል!! ሰዎች ለትዝብት፣ እግዚአብሔር ግን ለመሸፈን ያያል። ሰዎች ያዩትን ለማሳየት፣ እግዚአብሔር ግን በጉድለታችን ላይ ሙላቱን ለመግለጥ ያያል! ለትልልቅ ሰዎች ችግራችንን ለማስረዳት፣ የጠቢባንን እርዳታ ለማግኘት ብዙ ዘመን ተገልጠናል። በነጩ የጽድቅ ሸማ ለሚሰውረው ጌታ ግን ዛሬ እንገለጥ። ከነቢዩ ጋር እንዲህ እያልን እንጸልይ፦

‹‹እኔ ችግረኛና ምስኪን ነኝ፤ አቤቱ÷ እርዳኝ፤
ረዳቴ ታዳጊዬም አንተ ነህ፤ አቤቱ÷ አትዘግይ››
(መዝ. 69÷5)።

14/ “በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፣ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።” (ማቴዎስ 5:3)

--- ሀብትና ዕውቀት፣ ሥልጣንና ጉልበት እያላቸው የማይታበዩና የማይኩሩ፣ ሁሉ የእግዚአብሔር ነው ብለው ለእግዚአብሔር አሳልፈው የሚሰጡ ሰዎች ብፁዓን ይባላሉ። በመንፈስ ድሆች የሆኑ የተባለውም ለዚህ ነው። ጌዴዎን ጎያል ሲሆን እግዚአብሔርም እስራኤልን እንዲያድን በመረጠው ጊዜ በመንፈስ ድሃ ሆኖ ተገኝቷል። “ጌታ ሆይ እስራኤልን በምን አድናለሁ? ወገኔ ከምናሜ ነገድ ከሁሉ ይልቅ የተጠቃ ነው። እኔ በአባቴ

ቤት የሁሉ ታናሽ ነኝ።” ሲል ነው ለተገለጠለት የእግዚአብሔር መልአክ የመለሰው። መሳ.6፡12-15። በእግዚአብሔር ኃይል በሦስት መቶ ሰው ብቻ ምድያማውያንን ድል ካደረገ በኋላ የእስራኤል ልጆች ተሰብስበው አንተ ልጅህም የልጅህም ደግሞ ግዙን ባሉት ጊዜ በመንፈስ ድሃ ሆኖ የተገኘው የጌድዮን መልስ “እኔ አልገዛችሁም፣ ልጄም አይገዛችሁም እግዚአብሔር ይገዛችኋል።” የሚል ነበር። እንዲህም በማድረጉ እስከ እድሜው ፍጻሜ ድረስ ለአርባ ዘመናት ሰላምና በረከት ዘመንን አሳለፈ። መሳ.8፡22-28። አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኘ የእግዚአብሔር ወዳጅ ሲሆን በመንፈስ ድሃ የሆነ ሰው በመሆኑ እኔ አፈርና አመድ ነኝ ብሏል። ዘፍ.18፡3፣ ዘፍ.18፡25፣ ያዕ.2፡23። ልበ አምላክ ዳዊት ሰባት ሀብታት ፍጹም ጸጋ የተሰጠው የእግዚአብሔር የልብ ሰው ሲሆን በሰውም ሆነ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ድሃ ያደረገ ሰው ነበር። ንጉሡ ሳኦል ልጁን ሊድርለት ባለ ጊዜ “ለንጉሥ አማች እሆን ዘንድ እኔ ማነኝ? ሰውነቴስ ምንድነው?” ሲል ለንጉሡ መልሶለታል።1ኛ.ሳሙ.18፡18። በእግዚአብሔር ፊት ሲዘምርም “እኔ ግን ትል ነኝ ሰውም አይደለሁም፤ ማላገጫ በሕዝብም ዘንድ የተናቅሁ ነኝ” ብሏል። መዝ.21፡6።

“የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው። መጽናናትን ያገኛሉና።” (ማቴዎስ 5፡4)

--- ኃጢአታቸውን እያሰቡ እንደ አዳም፣ እንደ ዳዊትና እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ የባልንጀራቸውን ኃጢአት እያሰቡ ለንጉሥ ሳኦል እንዳለቀ ሰው እንደ ሳሙኤል /1ኛ ሳሙ.16፡1/ ሰማዕታትን እያሰቡ ለቅዱስ እስጢፋኖስ እንዳለቀሱት ደጋግ ሰዎች፣ መከራ መስቀልን እያሰበ ሰባ ዘመን

እንዳለቀሰው እንደ ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ የሚያዝኑ ሰዎች ብፁዓን ይባላሉ።

“ስለጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና።” (ማቴዎስ 5፡6)

--- ስለጽድቅ ብለው ረኃቡንና ጥሙን ታግሰው፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በመብል በመጠጥ አትወረስም፣ አንድም ቢፈጽማት የእግዚአብሔርን መንግሥት የምታሰጥ አትወረስም፣ አንድም ቢፈጽሟት የእግዚአብሔርን መንግሥት የምታሰጥ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ የሆነ እምነትን ተስፋንና ፍቅርን እንጂ መብል መጠጥን አትሰብክም አንድም ልብላ ልጠጣ በምትል ሰውነት ወንጌል አትዋሐድም /ሮሜ.14፡19/ መብል ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም ባንበላ ምንም አይጐድልብንም ብንበላም ምንም አናተርፍም /1ኛ.ቆሮ.8፡8/። መብል ለሆድ ነው፣ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል። ብለው የሚጾሙ ሰዎች ብፁዓን ይባላሉ። “ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ” ሲልም እውነት በሕይወታቸው ነግሣባቸው የሚኖሩትን ያመለክታል። ጾመ ሙሴ ዘዳ.9፡9፣ ጾመ አስቴር 4፡16፣ 9፡31 ጾመ ዳንኤል፣ ዳን.10፡2 ጾመ ዳዊት፣ 2ኛ ሳሙ.12፡22 መዝ.108፡24፣ ጾመ ሐዋርያት የሐዋ.13፡2 ወዘተ ተመልከት።

ምንጭ፡- ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ 4ኛ ዓመት ቁጥር 2 ጎንደር 1989 ዓ.ም.

15/ ጠላትህን ውደድ

አንድ ትንሽ ልጅ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኘበትን መድኃኒት መስቀል ክርስቲያን የመሆን መለያ ምልክቱ ነውና በአንገቱ አስሮ ሲሄድ በሉተር ፍልስፍና የከሰረ አንድ መናፍቅ “አባትህ የሞተበትን መስቀል በአንገትህ ለምን ታስራለህ? ይህ እኮ አባት የተገደለበትን ሽጉጥ እንደ መያዝ ይቆጠራል። ስለዚህ ጠላትህን በአንገትህ ልታስር አይገባም። ወይስ ደግሞ ኢየሱስን አትወድደውም?” ይለዋል። ልጁም የተማረ ነውና “ለእኔስ ጠላቴ አይደለም፤ ጠላቴ ቢሆን እንኳ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠላትህን ውደድ ስላለኝ ወድጄ በአንገቴ አስሬዋለሁና አልፈታውም አልበጥሰውምም” አለው። መናፍቁም የመቱት ያህል አፍሮ ወደ ኋላው ተመለሰ።

† † † መ/ዳዊት 59/60:4 ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ፥ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው። † † †

16/ † አሥርቱ ትዕዛዛት † (The Ten Commandments)

ከእግዚአብሔር አምላክ በቀጥታ በሙሴ አማካኝነት ለእስራኤላውያን የተሰጠ ሕግ ነው። የተሰጡትም እስራኤላውያን ከግብጽ ከወጡ በ 3 ኛው ወር ፋሲካን ካከበሩ በ 3 ኛው ቀን በደብረ ሲና ሰፍረው ሳለ ነበር። ዘፀ. 19፡1-4 በዘዳ. 34፡28 ዘዳ. 4፡13 ላይ አሥሩ ትዕዛዛት አሥር

መሆናቸውን እንረዳለን።

በዝርዝር ተጽፈው የሚገኙት ግን በዘዳ. 20፡ 3 እና 17 እና ዘዳ. 5፡5-21 ላይ ነው። አሥርቱ ቃላትና ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ለእስራኤል ዘስጋና ለእስራኤል ዘነፍስ የተዘጋጁ ስለሆነ ሁላችንንም ይመለከታል። እነርሱም፡-

1. ‹‹ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ፤ አትስገድላቸው፤ አታምልካቸው ›› ዘፀ. 20፡2-6

2. ‹‹ የእግዚአብሔር የአምላክን ስም በከንቱ አትጥራ። ›› ዘፀ. 20፡7

42 3. ‹‹ የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ /አክብረውም/ ›› ዘፀ. 20፡ 8

4. ‹‹ አባትህንና እናትህን አክብር ›› ዘዳ. 20፡12

5. ‹‹ አትግደል ›› ዘፀ. 20፡13

6. ‹‹ አታመንዝር ›› ዘፀ. 20፡14

7. ‹‹ አትስረቅ ›› ዘፀ. 20፡15

8. ‹‹ በሐሰት አትመስክር ›› ዘፀ. 20፡16

9. ‹‹ አትመኝ ›› ዘፀ. 20፡17

10. ‹‹ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ ›› ዘሌ. 19፡18

- አሥርቱ ሕግጋት የብሉይ ኪዳን መሠረቶች ናቸው። የእግዚአብሔርን ሕግ ብትጠብቁ ብትፈጽሙትም ሕዝቤ ትሆናላችሁ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ ብሎ ቃልኪዳን ገባ። ሕዝቡም በአንድ አፍ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ‹‹እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለን›› ብለው ቃል ኪዳን ገቡ። ዘፀ. 19፡8፤ 24፡1-8 ቅዱስ ጳውሎስም እንደነገረን

ይህ ፊተኛው ኪዳን ያለ ደም አልተመረቀምና ዕብ. 18፡ 22 ሙሴ ኪዳኑን ለማጽናት የደም መርጨትን ሥርዓት እንዳደረገ በሐዲስ ኪዳንም ቢሆን ሥነ ሥርዐቱ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያላቸው ሕግጋት ናቸው። ማቴ 5፡17፣ 19፡15-22 ፣ዮሐ 1፡12 እግዚአብሔር ሕዝቦቹና ልጆቹ ሊያረገን ይህን ታላቅ ተስፋ በመስጠት ቃል ከገባልን እኛ ደግሞ ትዕዛዙን ለመጠበቅ ምን ያህል ቃል ገብተንለታል? ጌታችን ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ ዮሐ 14፡15 እንዲሁም ከሆነ እንደ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለን ብለን ከሁሉ በፊት ለእግዚአብሔር ቃል መግባት አለብን። ክርስትናውን ስንጀምር የመጀመርያ ሥራችን መሆን ያለበት ይህ ነው።

የዐሥርቱ ትዕዛዛት ዓላማ

ዐሥርቱ ትዕዛዛት የተሰጡት በሚከተሉት ዓላማዎች ነው። ይኸውም፡-

1. ከግብጽ ምድር ስላወጣቸው ውለታውን እንዲያስቡ

2. ወደ ፊት በአረማዊያን መካከል ሲመላለሱ ከኃጢአት እንዲቆጠቡ

3. መንፈሳዊ አካሄዳቸው ምን ምን አቅጣጫ መከተል እንዳለበት ለማሳየት ነው።

የዐሥርቱ ትዕዛዛት አከፋፈል

የክርስቲያን ሕግ የፍቅር ሕግ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞበታል ካለ በኋላ ከዐሥርቱ ትዕዛዛት የተወሰኑትን በመጥቀስ ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ መሆኑን በግልጽ ይነግራል። ሮሜ 13፡8-10 ታዲያ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረ ፍቅር በሁለት ይከፈላል። ማቴ 22፡34-41

1 ፍቅረ እግዚአብሔር 2 ፍቅረ ቢጽ

1. ፍቅረ እግዚአብሔር: ከአንደኛ ትዕዛዝ እስከ ሦስተኛው ያሉት ሲሆኑ እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ናቸው።

2. ፍቅረ ቢጽ: ከአራተኛ ትዕዛዝ እስከ አሥረኛ ትዕዛዝ ያሉት ሲሆኑ በለእንጀራን የሚመለከቱ ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ በአዎንታዊና በአሉታ ከመነገራቸው አንጻር በሁለት ይከፈላሉ ይኸውም፦

1. ሕግ በአሉታ የተነገሩ /አታድርግ/

2. ትዕዛዝ በአዎንታ የተነገሩ /አድርግ/

ከዚህም ሌላ ከአፈጻጸማቸው አንጻር ሲታዩ በሦስት ይከፈላሉ።

1. በሐልዮ የሚፈጸሙ 1፣3፣4 እና 9 በሐሳብ

2. በነቢብ የሚፈጸሙ 2፣ 8 በመናገር

3. በገቢር የሚፈጸሙ 5፣6፣7 እና 10 በሥራ ናቸው።

ምንጭ ፦ ሕግጋተ እግዚአብሔር መጽሐፈ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ 3ኛ የተወሰደ እንዲሁም የ/መ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት

17/ >ኢየሩሳሌም በብሉይም: በሐዲስም ቅድስት ሃገረ እግዚአብሔር ናት:: ' # ኢየሩ ' ማለት 'ሃገር' ማለት ሲሆን ' # ሳሌም' ደግሞ 'ሰላም' ማለት ነው:: ስለዚህ በቁሙ 'ሃገረ ሰላም': ' # ሃገረ_ክርስቶስ ' ማለት ነው::

+ኢየሩሳሌም የሚለው ቃል በቁሙ ቅድስት ሃገርን ሲመለከት በምሥጢሩ

ግን የቤተ ክርስቲያን: የመንግስተ ሰማያት እና የአማናዊት ሃገረ ሰላም

ድንግል_ማርያም መጠሪያ ነው:: ኢየሩሳሌምን በከተማ ደረጃ የመሠረታት ታላቁ ካህን

መልከ_ጼዴቅ ሲሆን 'ንጉሠ ሳሌም' ተብሎም ኑሮባታል::

+ይህች ቅድስት ሃገር በብሉይ ዘመን እግዚአብሔር በረድኤት ቢገለጥባት: ጻድቃነ ብሊት ቢኖሩባት ተቀድሳለች:: በሐዲስ ኪዳን ግን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማያት ወርዶ 33 ዓመት ከ3 ወር ያህል የድኅነ ትሥራውን ቢፈጽምባት: ለድንግል ማርያምና ለብዙ ቅዱሳን ቤት ብትሆን የበለጠ ተቀድሳለች::

+ዛሬም ድረስ ከተለያዩ ክፍላተ ዓለማት በብዙ ድካምና ወጪ ሊያዩዎት ይጉዋዛሉ:: የቀደመው ዘመን አባቶቻችንም ይህችን ቅድስት ከተማ ለመሳለም እስከ ደም ጠብታ ከፍለዋል::

+ወደ ዋናው ጉዳያችን እንለፍና የኢየሩሳሌምን መታነጽ እንይ:: ኢየሩሳሌም በአሕዛብ እጅ ብዙ ጊዜ ፈርሳ ታንጻለች:: እኛ ግን ዛሬ የምናከብረው የከተማዋን መታነጽ ሳይሆን በከተማዋ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መንገድ በአንድ ጊዜ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት መታነጻቸውን ነው:: ይሕስ እንደምን ነው ቢሉ:-

+ከክርስቶስ ዕርገት 300 ዓመታት በሁዋላ ለቤተ ክርስቲያን የተነሳችው # ቅድስት_ዕሌኒ በጦ ሃሳብ በሕሊናዋ ተመላልሳልና ተነሳች:: # ጉባኤ_ኒቅያ ከተጠናቀቀ በሁዋላ ልጇ ቆስጠንጢኖስ በነገሠ በ20 ዓመቱ በ227 ዓ/ም አካባቢ ቅዱስ ዕጸ መስቀሉን ትፈልግ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ አደረገች::

+መስቀሉን ፈልጋ ያገኘችበት ታሪክ ለነገ ይቆየንና መስቀሉን ካገኘችው በሁዋላ በሙሉ ከተማዋ ላይ አብያተ ክርስቲያናትን ለማነጽ ከልጇ ጋር ተስማማች::

+ለሕንጻው የሚሆን ብዙ ወርቅ: ብርና እንቁ ጭና ማምጣቷን የተመለከቱት # አባ_መቃርስ (የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ ናቸው) "ልምከርሽ! ቤተ ክርስቲያኑን በጠንካራ አለት ላይ ሥሪ:: ወርቅና ብሩን ግን ለነዳያን በትኚ" ስላሏት በአካባቢው ላሉ ነዳያን ታላቅ ፌሽታ ሆነ:: እጅግ ብዙ ሠራዊት: ብዙ ሺህ ሠራተኞች ታጥቀው 80 አብያተ ክርስቲያናትን ያንጹ ጀመሩ::

+ሥራው ረቂቅና ብዙ ሥለ ነበረ እጅግ አድካሚ ነበር:: ቅድስት ዕሌኒ ሃገሪቷን በቤተ መቅደሶች መሸፈን ስለ ፈለገች እንዲታነጽ ያዘዘችው የቤተ ክርስቲያን ቁጥር 80 ደረሰ:: እነዚህም ጌታ ከጽንሰቱ እስከ ዕርገቱ የረገጣቸውና # እመ_ብርሃን የረገጠቻቸው ቦታዎች ናቸው::

+# ቤተ_ልሔም : # ዮርዳኖስ : # ደብረ_ሊባኖስ :

ደብረ_ታቦር : # ደብረ_ዘይት : # ጐልጐታ :

ጌቴ_ሴማኒ : # ቤተ_ሳይዳ : # ጽርሃ_ጽዮን ደግሞ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: በአካባቢው ያሉ ነዳያን ሳይርባቸው: ሠራተኞችም ደሞዝ ሳይቸግራቸው: 80 ው አብያተ ክርስቲያናት በፈጣሪ ረዳትነት: በ 10 ዓመታት ታነጹ::

+ቀጥሎም ንጉሡ ቅዱስ ቆስጠንጢኖስ በዓለም ያሉ ታላላቅ ቅዱሳን ሊቃነ ጳጳሳትን ጠርቶ: ሁሉም እስከ መስከረም 15 ቀን ወደ ኢየሩሳሌም በተሰበሰቡበት የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ቅዳሴ ቤት በአንድ ላይ ሲከበር

ከዝማሬው ብዛት: ከአምላክ ጸጋ የተነሳ በከተማዋ ታይቶ የማይታወቅ ሐሴት ተደረገ::

*ኢየሩሳሌም ፍጹም አጊጣ እስከ መከራ ቀን (አሕዛብ እስከ ተነሱበት) ቆይታለች::

+"+ # ቅዱስ_ጦቢት (ጻድቅ ነቢይ) "+

=>ከክርስቶስ ልደት በፊት እሥራኤላውያን ክፋትን ሲያበዙ ጠላት መጥቶ ይማርካቸው: ንስሃ ሲገቡ ደግሞ በድንቅ ተአምር ይወጡ ነበር:: ሕዝቡ ሲማረክ ነቢያት እረኞች ናቸውና ያለ ጥፋታቸው አብረው ይማረኩ ነበር:: በዚያም ሕዝቡን ያስተምራሉ: ያጽናናሉ::

+በተመሳሳይ እሥራኤላውያን ተማርከው ወደ # ነነዌ በወረዱበት ወራት ጦቢት የሚሉት ደግ ሰው በመካከላቸው ነበር:: ይህ ደግ ሰው ከምርኮ በፊት መልካም አምልኮት የነበረው: አሥራቱን በኩራቱን የሚያወጣ: ለነዳያን የሚራራ ነበር::

+ከተማረኩ በሁዋላም ሕዝቡ ከአሕዛብ ጋራ ሲቀላቀሉ እርሱ ንጽሕናውን ጠብቆ እግዚአብሔርን ያመልክ ነበር:: ቅዱስ ጦቢት በተለይ የሞተ ሰው ሲያገኝ ሳይቀብር እህል አይቀምስም ነበር:: በዚህም ምክንያት የዘወትር ጠመኛ ነበር::

+ይሕ ቅዱስ እድሜው 58 በሆነ ጊዜ ዓይኑ ጠፋ:: ብዙ በመሰቃየቱም ሞቱን ለመነ:: በሌላ አቅጣጫ ደግሞ # ሣራ 'አስማንድዮስ' የሚባል ጋኔን 7 ባሎቿን እየገደለ አሳቅቁዋት ነበርና እርሷም ሞቷን ተመኘች::

+እግዚአብሔር ግን መልአኩን ልኮ: # ቅዱስ_ሩፋኤል አዛርያን መስሎ የጦብያና የሣራን ጋብቻ ባርኩዋል:: ጋኔኑንም በጥልቁ አስጥሞታል:: በዓሣ

ሐሞትም የጣቢት ዓይኑ በርቶለት በእድሜው ላይ 100 ዓመታት ተጨምረውለታል:: ቅዱስ ጣቢት ብዙ ሕብረ ትንቢቶችን ተናግሮ በ158 ዓመቱ በዚህች ቀን ዐርፏል::

+"+ # አባ_አጋቶን_ባሕታዊ +"+

=>ይህንን ቅዱስ የማያውቅ የቤተ ክርስቲያን ሰው ይኖራል ብየ አልገምትም:: እርሱ ታላቅ ጻድቅ: ገዳማዊና የእግዚአብሔር ሰው ሲሆን አንደበቱን ከክፉት ይከለክል ዘንድ ለ30 ዓመታት ድንጋይ ጕርሶ ኖሯል::

+ይህንን ቅዱስ # ሊቃውንት ሲገልጹት "ክምረ ክምር ጽድቁ እስከ አስተርአየ" ይሉታል:: ትእግስቱ: ደግነቱ: አርምሞው: ትሩፋቱ ከመነገር በላይ ነው:: በነበረበት በ4 ኛው መቶ ክ/ዘመንም እንደ ኮከብ ያበራ ታላቅ አባት ነው::

=>አምላክ ቅዱሳን የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያንን ሰላምና ደስታ ያሳየን:: ከበዓላቱ ከሚገኘውም ጸጋ በረከት አይለየን::

=>መስከረም 16 ቀን የሚከበሩ ዓመታዊ የቅዱሳን በዓላት=

1.ሕንጸታ ለኢየሩሳሌም

2.ቅድስት እሌኒ ንግሥት

3.ቅዱስ ጣቢት ነቢይ

4.ቅዱሳን ጠብያና ሣራ

5.አባ አጋቶን ባሕታዊ

=>ወርኀዊ በዓላት

1.ኪዳነ ምሕረት (የሰባቱ ኪዳናት ማሕተም)

2.ቅድስት ኤልሳቤጥ (የመጥምቁ ዮሐንስ እናት)

3.ቅዱስ ገብረ ማርያም ጻድቅ ንጉሠ ኢትዮድያ (የቅ/ላሊበላ ወንድም)

4.ቅዱስ አኖሬዎስ ንጉሥ ጻድቅ

5.አባ አቡናፍር ገዳማዊ

6.አባ ዳንኤል ጻድቅ

7.ቅዱስ አባ ዮሐንስ ጻድቅ (ወንጌሉ ዘወርቅ)

=>+"+ ወደ # እግዚአብሔር ቤት እንሒድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ::

#ኢየሩሳሌም ሆይ እግሮቻችን በአደባባይሽ ቆሙ::

ኢየሩሳሌምስ እርስ በርሷ እንደ ተገለጠች ከተማ ተሠርታለች . . .

ስለ ወንድሞቼ ስለ ባልንጀሮቼም በውስጥሽ ሰላም ይሁን አልሁ::

ስለ አምላካችን ስለ እግዚአብሔር ቤት ላንቺ መልካምነትሽን ፈለግሁ::

+"+ (መዝ. 121:1-9)

<ወስብሐት ለእግዚአብሔር>

18/ ሶሊያና ቤዝ ሶላማጢስ

ጋብቻ ለመመስረት ያሰበ አንድ ወጣት ከቤተሰብና ከጓደኞቹ ጋር

ተማክሮ ከጨረሰ በኋላ የመንፈስ አባቱ ዘንድ በመሔድ ይህንን

ውሳኔውን አስረዳቸው። ጥበበኛውም አባት ለማግባት ያለውን

ጉጉት በልጁ ፊት ላይ እያስተዋሉ አሳቡ መልካም እንደሆነ

ገልጸው ማስታወሻና ብዕራቸውን በማውጣት “ስለ ልጅቷ ትንሽ ነገር ንገረኝ” በማለት ጥያቄ አቀረቡለት። እርሱም እንዲህ አለ “ትውልዷ ከነገስታት ዘር እድገቷም በምኞት መሐል ነው” አለ። እኚህም አባት በሙሉ ልብ ሆነው በያዙት ማስታወሻ ላይ ዜሮ ጻፉ። ወጣቱም ስለ ልጅቷ ማብራራቱን ቀጠለ፦

“በጣም ውብ ናት” አለ። እርሳቸውም ሌላ ዜሮ ጻፉ።

“በጣም ዝነኛ ናት” አለ። ደግመው ሌላ ዜሮ ጻፉ።

“በጣም ሀብታም ናት” አለ። ጥበበኛውም ሌላ ዜሮ ጻፉ።

“በጣም ምሁር ናት” አለ። አሁንም ሌላ ዜሮ ጻፉ።

“በጣም ዘመናዊ ናት” አለ። ተጨማሪ ሌላ ዜሮ ጻፉ።

በመጨረሻ ግን የረሳውን አንድ ነገር ነገራቸው “ልባም እንዲሁም ሕይወቷ ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና የተሰጠ ነው” አላቸው። ጥበበኛውም አባት ፊታቸው ላይ ፈገግታ እየተነበበባቸው አስቀድሞ ከጻፉአቸው ስድስት ዜሮዎች ፊት አንድ ቁጥርን ጽፈው “በል ሂድና አግባት” አሉት። ወጣቱም በደስታ ከፊታቸው ሄደ።

ማስተዋል የጎደለው ፍቅር ጥልቀት የሌለው መሳሳብ ውጤት ነው። ብዙ ጊዜም በሌላው ሰው አካላዊ ገጽታና ውጫዊ አቋም ላይ የተመሰረተ ነው። ምንም እንኳን መማረክ ወደ ፍቅር የሚመራ አንደኛው መንገድ ቢሆንም እውነተኛ ፍቅር ግን በአካላዊ ውበት፣ በአፋዊ መስፈርት ከመሸነፍ ያለፈ ነው። አካላዊ ውበት የጊዜያዊ ጉጉት መገለጫ ሲሆን ፍቅር ግን

በሌላው ውስጥ ያለውን መልካሙን ነገር በመሻት ትዕግስትን
መሰረት የሚያደረግ ነው። ይህም የትኛውንም ልብ የመንካት፣
በላቀና በጠለቀ መንገድ የመግዛት ጉልበት ነው።
ማንኛውም ሰው በዘመኑ የሚያሳልፋቸው ትልልቅም ይሁን
ትንንሽ ውሳኔዎች አሉ። ሕይወትም በዚህ የዕለት ተዕለት ቋሚ
የመምረጥና የመወሰን ተግባር ላይ የተመሰረተች ናት። ጋብቻ
የእኛን ትልልቅ ውሳኔ ከሚፈልጉ ነገሮች አንዱ ነው።
የምናመልከውን እንመርጣለን፣ የምንኖርበትን አካባቢ
እንመርጣለን፣ የልባችንን የምናካፍለው ባልንጀራ እንመርጣለን፣
በትዳር አጋር የሚሆነንን እንመርጣለን፣ በአጠቃላይ መሆን
የምንፈልገውን እንመርጣለን። በእርግጥ ምርጫችንን
ከምንኖረው በላይ ተጽእኖ ወደ ኑሮአችን የሚያመጣውን
መኖራችን ግልጽ ነው። ነገር ግን በዚህም ውስጥ ከእውነት ጋር
ያለን ትስስር ሊደበዝዝ አይገባም። ምርጫችን ውስጥ ሞትም
ሕይወትም፣ ደስታም ሀዘንም፣ ክብርም ውርደትም አለ።
መርጠን ዘመናችንን የእንባ ልናደርገው መብቱ የእኛ ነው።

Binyam Aregawi

19/ ◆ አንድ ደሃ ‹ ጌታ ሆይ የማደርገው ጫማ የለኝም› ብሎ ፈጣሪውን
አማረረ፤ እልፍ ቢል እግር የሌለው ውሃ ውስጥ እንደሚዋኝ በደረቱ

እየዳሀየ የሚሄድ ሰው አየ። ሰው ሆይ ትርፍ ነገር የለኝም ብለህ ፈጣሪህን አታስመርርር፤ ከሌለህ ነገር ይልቅ ያለህ ይበዛልና። ትርፍ ነገር ቢኖርህ መልካም ሄደህ ደግነትን ጽድቅን አድርግበት ሁለት ያለው ምንም ለሌለው ይስጥ ይላልና። ደግሞም ስላለህ ነገር <<ተመስገን>> ማለትን እወቅበት፤ የሌለህን ነገር ብቻ እያሰበክ ሁሌ የምታማርር አትሁን፤ ስግብግብነት ይሆንብሃልና። ስግብግብ ሰው መጥፊያውን ይለምናል። በቤተክርስትያናችን የሚነገር አንድ ታሪክ ላስታውሳችሁ፦ አንድ ሰው ነበረ ይህ ሰው እግዚአብሔርን ወርቅ ስጠኝ ብሎ ይለምነዋል እግዚአብሔርም ምን ያህል ይለዋል አንድ እፍኝ ይለምንና ይሰጠዋል፤ ዳግመኛም አነሰኝ ትንሽ ጨምርልኝ ይላል፤ ምን ያህል ልስጥህ ይለዋል 1 ማደበሪያ ሙሉ ስጠኝ ይለዋል እንደቃሉ ይሰጠዋል። አሁንም ሲያስበው ይሄ ትንሽ ጊዜ ነው የሚያቆየኝ ይልና ሁለት ሶስት እያለ 10 ማዳበሪያ ያስደርጋል ተሰቶት ይሄዳል። አሁንም ሲያስበው አነሰውና ጌታ ሆይ ይሄ ከጊዜ በኋላ ሊያልቅ ይችላል ስለዚህ እባክህን በቃ የነካሁት ሁሉ ወርቅ ይሁንልኝ ይለዋል፤ እግዚብሔርም እንዳልክ ይሁንልህ ይለውና ወደቤቱ መሄድ ይጀምራል። ገና የቤቱን በር ሲያንኳኳ ወርቅ ይሆናል ከዛ እቤት ይገባና ሚስቱን እግዚአብሔር የነካሁት ሁሉ ወርቅ እንዲሆን ለምኘው ፈቅዶልኛልና እንዳትነኪኝ ተጠንቀቂ ይላታል። ኋላ ምግብ ሲበላ እሷ ቀስ አድርጋ ንክኪ ሳይኖር እንድታጐርሰው ያደርግና መግብ በጉርሻ መብላቱን ይቀጥላል። ስታጐርሰው ሳታውቅ እጆቿ ይነካኩና ሚስቱ ወርቅ ሆነች ደንግጦ እየጮኸ ራሱን በእጆቹ ቢዝ እርሱም ወርቅ ሆነ ጨኸት ሰምተው የመጡትም ጎረቤቶች የዚሁ ነገር ሰለባ ሆኑ፤ ወርቅ በወርቅ። ይህቺ በልጅነቴ የሰማኋት

ታሪክ ሁሌም ትገርመኛለች፤ አንዳንዴ የምንለምነው ነገር እራሳችንን የሚጎዳ የሚያጠፋ ሆኖ እናገኘዋለን፤ ሰውየው በለመነው ነገር እንኳን ሚስቱን እራሱንም አጥፍቷል፤ አላርዝመውና፣ ምን እንደሚያስፈልገን መቼ እንደሚያስፈልገን ስለእኛ ከእኛ በላይ ፈጣሪያችን ያውቅልናል እስቲ ያንተ ፈቃድ ይሁን እንበለው። መከራም ቢሆን ደስታም ቢሆን ማግኘትም ቢሆን ማጣትም ቢሆን ጌታ ሆይ አንተ የወድድከው ይሁን።

ቀዶየሚያለብስ ቆርሶ የሚያጐርስ ያድርገን።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለአለሙ አሜን። ሐምሌ 6 2005

Miko ZE Ethiopia

Bini Zelideta

20/ ‹‹‹ ዘመነ አስተርእዮ ››› (የመገለጥ ዘመን)፣(ዘመነ ሥጋዌ)

በቤ/ክናችን ስያሜ መሠረት አሁን ያለንበት ወቅት ‹‹‹ ዘመነ አስተርእዮ ››› (የመገለጥ ዘመን) ፣ (ዘመነ ሥጋዌ) ይባላል። ይህም የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክስቶስን ሥጋ የመልበስ ምስጢር ለማጠየቅ ነው ። ጌታ ለአዳም በገባው ቃል መሠረት አምስት ሺህ ዘመን ተገባድዶ ፣ አልቆ የምሥራች የተሰበከበት ዘመን ነው። በዚህም ምክንያት ቤ/ክ እስከ ጥር 11 ቀን ድረስ የጌታን በሥጋ መገለጥ እና የመዳናችንን ነገር ህብረ ብዙ በሆኑ ምስጢራት እና ዜማ ታስበዋለች ። ዘመነ አስተርእዮ ለሰው

ልጆች የሰበከው የምስራች በቃላት የማይገለጽ ታላቅ ምስጢር ነው ። ምክንያቱም አምላክ ወልደ አምላክ ፣ ፈጣሪ ዓለማት ፣ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ፣ አካላዊ ቃል ፣ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን ከሠይጣን ልቦና ሰውሮ በድንግል ማኅጸን ከትሟልና ። ድንግልም << ሰማይን ከነ ግሱ ፤ ምድርን ከነልብሱ >> ተሸከመችው ። የመለኮቱ ባሕርይ የማይመረመር ልዑል አምላክ 99ኙን ነገደ መላእክት ትቶ አንዱን አዳምን ሊፈልግ ወረደ። ቤተ አይሁድ እና የሠይጣን ሠራዊት የጌታንልት ይጠብቁ የነበው በቤተመንግሥት እና ቤተክህነት ሲሆን እርሱ ግን በከብቶች ግርግም ተገኘ ። ለዚህ ነው አበው << እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ዓምን የያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል(ይልቃል) >> ብለው የተናገሩት ። እኔም ጸሎታችሁ ያስበኝ እንጂ ይህን ዘመነ አስተርእዮ አስመልክቶ አምላክ በፈቀደ መጠን ጥቂት ፣ ጥቂት ለመጻፍና ለአናንተ ለማካፈል ወድጀለሁ። በቀጣይ ጽሑፍ እስከማገኛችሁ ድረስ በጉጉት እጠብቃለሁ ለዛሬው ግን ይብቃኝ። ሰላመ እግዚአብሔር ፣ የድንግል ማርያም ፍጹም ምልጃ እና የቅዱሳን ጸሎት አይለየን ።አሜን ።(ይቆየን)

21/ በመንፈሳዊ ሕይወቴ መሠረታዊ ለውጥን ለማምጣት ምን ላድርግ?

® መቅረዝ ዘተዋሕዶ፣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ

ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

የዚኽ ትምህርት መሠረታዊ ዓላማ

ክርስቲያኖች በሕይወታቸው መሠረታዊ

ለውጥ እንዲያመጡ ማበረታታት ነው።

በሕይወታችን ተለውጠው እንድናያቸው

የምንፈልጋቸው ነገሮች እጅግ ብዙ ናቸው።

ዓይነታቸውም እንደየመለካችን የተለያዩ

ናቸው። አንዳንዶቻችን ደመወዛችን

እንዲለወጥ እንፈልጋለን፤ አንዳንዶቻችን

ባሕርያችን እንዲሻሻል እንሻለን።

አንዳንዶቻችን ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለን ሽካራ

ግንኙነት ተለውጦ ማየት እንፈልጋለን።

አንዳንዶቻችን ትዳራችን የሰመረ እንዲኾን

እንፈልጋለን። አንዳንዶቻችን ክፉ እየተናገርን

ሰዎችን በቁጣ ስለምንሳደብ ተቸግረን

ይኾናል። በአጠቃላይ በሕይወታችን

ተለውጠው ማየት የምንፈልጋቸው ነገሮች

እጅግ ብዙ ናቸው። እነዚኽ ተለውጠው

እንድናያቸው የምንፈልጋቸው ነገሮች

እንዲለወጡም ብዙ ጥረን ይኾናል። ባለሙያ

አማክረን ይኾናል። ብዙ መጻሕፍትን ገዝተን

አንብበን ይኾናል። እጅግ ብዙ ጊዜ

እግዚአብሔርን ተማጽነነው ይኾናል።

ስላልተለወጥንም ተስፋ ቈርጠን ይኾናል።

ለውጥ ማምጣት በሕይወታችን እጅግ የከበደ
ነገር መስሎ ተሰምቶንም ይኾናል።
“ለምን አልተለወጥኩም? ስለምንስ አምላክ
ጸሎቴን አልሰማም?” ብለን መጠየቅ
አስፈላጊ ብቻ ሳይኾን ግድ ነው። እንዲኽ ብለን
የጠየቅን እንደኾነ ችግራችን የቱ ጋር እንደኾነ
ለማወቅ በዚያም መፍትሔውን ለመፈለግ
ከባድ አይኾንምና። እስኪ ለዛሬ የይስሐቅ ልጅ
የያዕቆብን ሕይወት በማንሣት የእኛ ችግር የቱ
ጋር እንዳለ እንፈትሸው!
1. አብዛኛውን ጊዜ የሰው እይታና
የእግዚአብሔር እይታየተለያየ ስለኾነ
እግዚአብሔር በሚጠቅመን መዓዝን
ይዞምራል፤ እኛ ግን አይኾንም ብለን
በተቃራኒው እንዞምራለን። እኛ የምናየው
አፍአዊው ሲኾን እግዚአብሔር ግን
ውሳጣዊውን ውበት ይመለከታል። ይኸውም
ከእግዚአብሔር ቃል መረዳት እንችላለን፦
“ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይም፤ ...
ሰው ፊትን ያያል፤ እግዚአብሔር ግን ልብን
ያያል” እንዲል /፩ኛ ሳሙ.፲፮፡፯/። ስለዚኽ
የእኛ ጥያቄ የቱ ጋር ነበር? ውስጣችን

እንዲለወጥ ነው ወይስ አፍአዊ ማንነታችን?

ይኽን ስናስተካል የምንፈልገው ለውጥ

በሕይወታችን በቀላሉ ይመጣል። ቅደም

ተከተሉን ስናስተካክል የምንፈልገው ለውጥም

አብሮ ይመጣል። ክብር ይግባውና ጌታችንና

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አንድ ጊዜ

መምህራኑ ሕግንና ፈሪሳውያንን

ሲወቅሳቸው፦ “እናንተ ግብዞች ጻፎችና

ፈሪሳውያን በውስጡ ቅሚያና ስስት ተሞልቶ

ሳለ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ

ስለምታጠሩ ወዮላችኁ” ብሏቸው ነበር /

ማቴ.፳፫፥፳፭/። ይኽን ሲላቸው ግን አፍአዊው

የቆሸሸ ይኹን ማለቱ አልነበረም፤ ንጽሕና

(ለውጥ) መዘመር ያለበት ከውስጥ እንደኾነ

ሲነግራቸው ነው እንጂ።

2. ኹላችንም እንደምናነበው ያዕቆብ ወልደ

ይስሐቅ አስቀድሞ አታላይ ሰው ነበር። ውሸት

የሕይወቱ አንድ አካል ነበር። በኦሪት ዘፍጥረት

ምዕራፍ ፴፪ ላይ እንደምናነበው ግን ሕይወቱ

ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተለወጠ።

የተለወጠው ግን ሕይወቱ ብቻ አልነበረም፤

ስሙም ጭምር እንጂ። እስራኤል ተባለ።

መጽሐፍ እንደሚነግረን ያዕቆብ ጭው ባለ
በረኻ ላይ ብቻውን ቀረ። አንድ “ሰው”
መጥቶም እስኪነጋ ድረስ ታገለው። ሰውየው
“እንዳላሸነፈው” ባየ ጊዜም የጭኑን ሽሉዳ
ነካው፤ የያዕቆብም የጭኑ ሹልዳ ሲታገለው
ደነዘዘ /ዘፍ.፴፪፡፳፬-፳፭/። ይኼ ትግል
የእውነት ትግል እንጂ ዛሬ በመስኮተ ትዕይንት
(በቴሌቪዥን) እንደምናየው የውሸት ትግል
አልነበረም። ትግሉ የደቂቃዎች ሳይኾን
እስኪነጋ ድረስ የነበረ ነው። ለምን እንዲኽ
ኾነ? አውግስጢኖስ የተባለ የጥንታዊቷ ቤተ
ክርስቲያን ሊቅ ሲመልሰው፦ ይኼ ትግል
ያዕቆብ የሚባረክበት መንገድ ስለነበረ ነው።
እግዚአብሔር እንዲኽ ባለ ትግል እንድንቆይ
የሚያደርገን የምንባረክበት መንገድ እርሱ
ሲኾን ነው። የምንለወጥበትና የምንሻሻልበት
መንገድ እርሱ ሲኾን ትግሉ የአንድ ሌሊት ብቻ
ሳይኾን ዓመታትንም የሚፈጅ ሊኾን ይችላል።
እንዲኽ በጣር በድካም ያገኘነው ነገር በቀላሉ
አናጠፋውምና፤ እናገኘዋለን እንጂ።
የምናገኘው ነገር በትግልና በጣር ሲኾን
ጣዕሙ ለዛው እስከምንድረስ ጣፋጭ እንደኾነ

እናጣጥሚለን” ይላል። በርግጥም ይኽን
ከአዳም ሕይወት ልንማረው፣ ልናውቀው፣
ልንረዳው እንችላለን። የሚደንቀው ደግሞ
“ልቀቀኝ” ያለው ሰውዬ ያዕቆብን ባርኮት
መኼዱ ነው። ለካስ ያዕቆብ ሲታገል ያደረው
ከእግዚአብሔር ጋር ኑሯል። ያዕቆብ ይኽን
የሚያውቀው በኋላ ላይ ነው። ምንም እንኳን
ሲታገለው ቢያድርም የጭኑን ሽሉዳ ነካ
ሲያደርገው ሲደነዝዝበት፥ ሲታገል የነበረው
ከተራ ሰው ጋር እንዳልኾነ ገባውና
“ካልባረክከኝ አልለቅኽም” አለው።
ተወዳጆች ሆይ! እኛ ብንኾን ምንድነው
የምንለው? “ልቀቀኝ” ሲለን “ጥርግ በል”
አንልምን? ያዕቆብ ግን አንዲኽ አላለም።
“ካልባረክከኝ አልለቅኽም” አለው እንጂ።
3. ያዕቆብ የተባረከበት ምክንያት እስከ
መጨረሻ ድረስ በመታገሉ ነው። ስለዚኽ
ከእኛ እስከመጨረሻ ድረስ መታገል
ያስፈልጋል ማለት ነው። የኹላችንም ችግር
ለጥ ብለን ተኝተን ሳለ መባረክን፣ ጭናችን
ሳይነካ መለወጥን፣ በትንሹ እየሰለቸን
መባረክን መሻታችን ነው። ማግኘት

የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት፣ እንዲለወጥ
የምንፈልገውን ነገር እንዲለወጥልን ምን
ያክል እንጸልያለን? የእኛ ትግል እኮ የግድ
የያዕቆብ ዓይነት ትግል እንዲኾን
አይጠበቅም። ታድያ ስንት ቀን ታገልን? ስንት
ቀን ጸለይን? አንዲት ቀን ነውን? ኹለት ቀን
ነውን? አንድ ወር ነውን? ተወዳጆች ሆይ!
አስቀድመን እንደተነጋገርን የእግዚአብሔር
አሠራርና የእኛ አሠራር በእጅጉ የተለያየ ነው።
ለውጥ የምንፈልግ ከኾነ በቀላሉ የምናኮርፍ
መኾን የለብንም፤ መሻሻል የምንሻ ከኾነ
በቀላሉ የምንወድቅ ልንኾን አይገባም፤ ዘላቂ
የኾነ መዓዛ ክርስትና ያለን ሰዎች እንድንኾን
ስንሻ ፅኑዎች መኾን አለብን። ሰዎች ምድራዊ
ዓላማቸውን ለማሳካት እስከምድን ድረስ
እንደሚታገሉ ከነፍስ ጌር ኔልሰን ማንዴላ
መማር እንችላለን። ማንዴላ ያመኑበትን
ምድራዊ ዓላማ ለማሳካት ብዙ የግል
ጉዳያቸውን ሠዉተዋል። የሚያምኑበት ዓላማ
ግቡ እንዲመታ ኧኧ ዓመት በወኅኒ ቤት
ማሳለፍ ነበረባቸው። እኛ ክርስቲያኖች'ማ፣
ዓላማችን ዘልኣለማዊ ሕይወት የኾነ እኛ'ማ

ምን ያኽል ልንፀና ያስፈልገን ይኾን? አባታችን
እግዚአብሔር እንዲኽ እንድንታገል
የሚፈልገው አስቀድመን እንደተነጋገርነው
የምናገኘው ነገር በትግልና በጣር ሲኾን
ጣዕሙ ለዛው እስከምንድረስ ጣፋጭ እንደኾነ
እንዲገባን ከዚያም እንደ ቀዳማዊው አዳም
በቀላሉ እንዳንሰናከል ነው። ብጹዕ የኾነ
ሐዋርያ ጳውሎስም፦ “ባንዝልም በጊዜው
እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት
አንታክትም” ያለው ስለዚኹ ነው /ገላ.፮፡፱/።
ያዕቆብ ሳይዝል ታገለ፤ በጊዜው (ሊነጋ
ሲልም) አጨደ (ተባረከ)።
4. ያዕቆብ ከመባረኩ በፊት፦ “ስምኽ ማን
ነው” ተብሎ ተጠይቆ ነበር። እግዚአብሔር
ስሙ ጠፍቶት ኣይደለም። ያዕቆብ መናገር
የሚገባው ነገር ስለነበረ እንጂ። ያዕቆብ
ማለት አስቀድመን እንደተናገርን አሰናካይ፣
አታላይ ማለት ነው። ገና ከእናቱ ማኅፀን
አንሥቶ የወንድሙን ሰኮና በመያዝ ማሰናከል
ዠመረ፤ አባቱን የበግ አጐዛ ለብሶ አታለለ።
ስለዚኽ ይኽ ሥራው እግዚኣብሔር ሲጠይቀው
መመለስ ነበረበት። “የእኔ ስም አሰናካይ ነው፤

ትኽክለኛ ስሜ አታላይ ነው” ብሎ መናገርና
ማመን ነበረበት። ዛሬ እግዚኣብሔር ስምኽ/
ሽ ማን ነው ብሎ ቢጠይቀን ማን ብለን
እንመልሳለን? ሰርቀን እንደኾነ፣ ዋሸተን
እንደኾነ፣ ነገር አጣምመን እንደኾነ
እግዚኣብሔር ስማችን ቢጠይቀን ማን ብለን
እንመልስ ነበር? እግዚኣብሔር ሲጠይቀን
“የእኔ ስም ገ/እግዚኣብሔር ሳይኾን ሌባ
ነው! ስሜ ገ/ማርያም ሳይኾን ውሸታም
ነው” ብለን እንድንመልስና እንድናምን
ይፈልጋል። “ስሜ ትዕቢት፣ ቅናት፣ ሙስና፣
ምንዝር፣ መዳራት፣ ስስት ነው” ሳንልና
ሳናምን ለውጥ፣ በረከት ፈፅሞ ወደ ቤታችን
ደጅ አይጠጋም። ያዕቆብ “ስሜ እያወቅከው
ስለምን ትጠይቀኛለኽ?” ኣላለም። ዛሬ
በንስሐ አባቶቻችን ፊት ንስሐ የምንገባውም
ስለዚኹ ነው። ማመካኘት ከእኛ መራቅ
አለበት። ማመካኘት ለቀዳማይቱ እናታችንም
አልጠቀማትም። ማመካኘትን ትተን ስናምን
መለወጥ እንዝምራለን። ዝቅ ስንል ጸጋ
እግዚኣብሔር ወደ እኛ ይመጣል። መጽሐፍ
ሲናገር፦ “እግዚኣብሔር ትዕቢተኞችን

ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል”

ይላል /ያዕ.፬፡፮/። የመለወጣችን መስጢር

የእግዚአብሔር ጸጋ ነው! የመለወጣችን ኃይል

የእግዚአብሔር ጸጋ ነው።

ያዕቆብ ትክክለኛ ስሙ ሲናገር “እስራኤል”

ተባለ። መዝሙርያ አሰናካይ አታላይ ነበር፤

አኹን ግን የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ኾነ፤

እስራኤል ማለት ሕዝበ እግዚአብሔር ማለት

ነውና። ከአፍአ ስናየው የተለወጠ ነገር

የለም። አፍአዊ መልኩን ስናየው ድሮ

የምናውቀው ያዕቆብ ነው። ውስጡ ግን

ፍጹም ተለውጧል። ስለዚኽ ለውጥን

ስንፈልግ ከውስጥ መዝሙር አለብን።

ያዕቆብ ከተባረከ በኋላ፦ “እግዚአብሔርን

ፊት ለፊት አየኹ፤ ሰውነቴም ድና ቀረች” ሲል

የዚያን ቦታ ስም ጵንኤል ብሎ ጠራው /

ዘፍ.፴፪፡፴/። ከዚያ በኋላ ፀሐይ ወጣችበት።

ነገር ግን በጭኑ ምክንያት ያነክስ ነበር።

ይኸውም ያለ ምክንያት አይደለም። ጭን

ከሰውነት ክፍላችን እጅግ ጠንካራ የኾነ ጡንቻ

ያለበት የሰውነት ክፍል ነው። ስለዚኽ ያዕቆብ

በጉልበቱ እንዳይመካ እግዚአብሔር ምልክት

አደረገለት። የተባረከባትን ቀን እንዳይረሳና
ኹል ጊዜ እንዲያስታውሳት ትእምርት
አደረገለት። በረከቱና ለውጡም እስከ
መጨረሻ ኾነለት። በእኛ ዓቅም የሚመጣ
ለውጥ ግን እንዲኽ ዘላቂ አይኾንም።
በአጠቃላይ ካንቀላፋንበት የስንፍና ፍራሽ
በደወል (እኛ ችግር ነው ብለን በምናስበው
ነገርም ቢኾን) እግዚአብሔር ሲቀሰቅሰን
ተደናብረን ልንሸሽ አይገባም፤ የምንባረክበት
መንገድ እርሱ ሊኾን ስለሚችል። ችግራችንን
እስከ መጨረሻው ድረስ እንታገለው፤
የምንለወጥበት መንገድ እርሱ ሊኾን
ስለሚችል። እግዚአብሔር ስማችንን
ሲጠይቀን ሲጠይቀን ማመካኘትን ትተን
ትክክለኛ ማንነታችንን፣ እውነተኛ ስማችንን
እንንገረው። ያኔ በረከት ወደ እኛ ይመጣል።
ለወጥ ወደ እኛ ይመጣል።
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፦
“የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ
የሚያሰኝ ፍጹምም የኾነው ነገርምን እንደኾነ
ፈትናችኁ ታውቁ ዘንድ በልባችኁ መታደስ
ተለወጡ እንጂ ይኽን ዓለም አትምሰሉ”

ይለናል /ሮሜ.፲፪፡፪/።

በእውነት እንድንለወጥ ለርስት መንግሥቱም

የበቃን የተዘጋጀን እንኾን ዘንድ

የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም

አማላጅነት የቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት

አይለየን። አሜን!!!

Orthodox and Bible

22/ ተዋህደ ስንል ምን ማለት ነው?

ያ ቅድመ አለም ከአብ ዘንድ የነበረው ወልድ/ቃል/ ከድንግል ከስጋዋ ስጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ተወለደ። የሐ 1፤14 ያ ቃል ስጋ ሆነ። እንዲል። ቃል ስጋ ሆነ ሲባል ተለዉጦ ስጋ የሆነ አይደለም በቃና ዘገሊላ ወሐው ወደ ወይን ተጅ እንደተለወጠው ቃል ወደ ስጋነት አልተለወጠም። ወይም በልብስ ላይ ልብስ እንደሚለበሰው በቃል ላይ ስጋ አልተደረበበትም። መለኮትም ስጋን አላጣፋውም ስጋም መለኮትን አልዋጠውም።አንድ ብረት በእሳት ውስጥ ቢጨመር ብረቱ ቅርጹን ሳይለቅ የእሳትነትን ባህርይ

እንደሚይዝ ስጋ የመለኮትን ባህርይ ገንዘብ አደረገ። እሳቱ በብረቱ በሚደረ ቅርጽ እንደሚወጣለት መለኮት ከስጋ ጋር በመዋሀዱ ታየ ተዳሰሰ ተኛ ተነሳ ተባለ።ይህ የወልድ ሰው መሆን ምስጢር ታላቅ ነው። እንደምስ የረቀቀ ነው።ሐዋርያው ለዚህ ነው ይህ ሚስጢር ታላቅ ነው። እግዚአብሔርን መምሰል ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው ያለው።1 ኛጢሞ 3፤17

ዓለም የዳነው በተዋህዶ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ተዋህዶን ለማብራራት የሚከተለውን የክርስቶስ ትምህርት እንውሰድ፡እውነት እውነት እላችሏለሁ ስጋየን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ህይወት አለው። ዮሐ 6፤55 ይህ ቃል እንዲሚያስረዳን ስጋውና ደሙ የዘለዓለም ህይወትን ለማግኘት ወሳኝ መሆኑን ነው። ታዲያ ስጋውና ደሙ ከማርያም የተገኘ የሰው ስጋ ነው። የሰው ስጋ ደግሞ ብቻውን ሊያድን አይችልም ኢንዲያውም ሊያም ይችላል። መለኮት ደግሞ ስጋ የለውም። ስለዚህ ይህ ስጋና ደም በተዋህዶ የከበረ ነው እንላለን። ስጋን መለኮት ስለተዋህደው አዳኝ አደረገው። መለኮት ስጋን ስለተዋህደው የሚዳሰስ የሚጨበጥ አደረገው። በመሆኑም በተዋህዶ የከበረ ስጋውና ደሙ መዳኛ ሆነ።

ተዋህዶ ያለመለያየት ያለመነጣጠል ያለመጠፋፋት ያለመቀላቀል ሰውና እግዚአብሔር አንድ የሆነባት ሰው የዳነባት ምንነት እምነት። በዚች የማያምኑ ሁሉ አይድኑም አዳኛቸውን አያውቁምና። ተዋህዶ አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ። ተዋህዶ ሰው በእግዚአብሔርነት ዙፋን ተቀመጠ ተዋህዶ ጥልቅ ምስጢር።

በተዋህዶ የተገለጠው የአብ ልጅ የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ይሁን። አሜን!!!

Abba Thomas

23/ ለምን አልተቀሰፍኩም?

ምስጋና እና አዳኝ የሚባሉ ከርዮንና ቤተልሔም በሚባል አካባቢ ተወለዱ አብረው ባያድጉም ከብዙ አመታት በኋላ የከርዮኑ ምስጋና የቤተልሔሙን አዳኝ አገኘው ታናዝ ይሆንም ዘንድ መረጠው ሌሎች በርካቶች ቢኖሩትም ከገሊላ እንጂ ከይሁዳ የሆነው የከርዮኑ ምስጋና ብቻ ነበር ባለው ንቃተ ህሊና ሻል ባለ ቦታ ተመድቦ ስራውን በጉድለት ያከናውን ነበር ትልቁ የምስጋና ጉድለት ንፍገት ወይም ስስት ነው።

ስስት ያለውን ላለመስጠት መቆንጠጥ ብቻ ሳይሆን የእርሱ ሆነውንምወደራሱ ለማምጣት አግባብ ያልሆነውን መንገድ መጠቀምንም ያካትታል ዓለም ከባለ ሃብቶች በስተጀርባ ወንጀል አይጠፋም ትላለች

ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢነዳ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ካላዳነ ምን ይረባዋል? በዚህ አጥር ውስጥም ላሉት ከዚህ በመነጨ ሓጢአት ለከርዮኑ ምስጋና የተጠቀሰውን ይጋራሉ { ባይወለድ ይሻለው ነበር} ማቴ 26 ፡24

አዳኙ ድህነትና ሕይወት የሚገኘው በእርሱ ብቻ መሆኑን ለአገልጋዮቹ ባስታወቀበት እለት የከርዮኑ ሰው ሃሳቡን በልቡ አትብቆ ተቃወመ። ግን ለምን አልተቀሰፍ ? ዮሐ 6፡ 65 ቢሆንም ከሚቃወምና ከሚክድ ጋር አብሮ መኖርን ለተከታዮቹ ለማስተማር የከሃዲውን አብሮ መኖርን ቻለ ። መቻቻል ለከሃዲዎች የመመለሻ እድል መስጠት እንጂ በሓሳቡ

ለመስማማት የሚፈረም ሰነድ አይደለም።

እራሱንና ሆዱን የሚወድ እውነተኛውን ፍቅር ከማወቅ አይደርስም እውነተኛ ፍቅርን ለመከተል አስቀድሞ እራስን መካድ ያስፈልጋል ማድረግ ስትችል መተው መሆን ስትችል አለመሆን ስለ ሰው ልጆች ፍቅር ሲል እራሱን ደሐ ያደረገውን አምላክ በዓይነ ህልና እየተመለከቱ መምሰል እንጂ እራስን በአለባበስና

በንጽህና ጉድለት ማጎሳቆል ወይደግሞ ባደባባይ ትንኝን መጸየፍ በጓዳ ግመልን መዋጥ አይደለም።

ለእለተ ዓርብ ስድስት ቀን ጎደል በቢታንያ የእራት ግብዣ ወቅት ማርያም የተባለች ሴት በቤተልሔም የተወለደውን አዳኝ ሽቱ ቀባችው ቅኖችና አስተዋዮች በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ስርየት ጸጋን ይሻሉ

ማስተዋል የጎደላቸው በሐላፊ ገንዘም የማያልፈውብ መንግስተ ሰማያት ያጣሉ ወይ ለመንፈሳዊው አገልግሎት ዋጋ ይመድባሉ ከዐመታት በኋላ ጴትሮስ ሲሞን መሰሪውን ከገንዘብህ ጋራ አብረህ ጥፋ ይለዋል የከርዮኑ ምስጋና አገልግሎት ላይ ለዋለው ሽቶ ተመን ያወጣል ስለጉዳዩ ዮሐንስ በቦታው የነበረው ዮሐንስ እንዲህ ሲል ያስረዳል {ሌባ ስለነበር} ዮሐ 12፡4

በደሐው ስም የሚለምኑ ለምን ለደሐው አይሰጥም የሚሉ ደጎች ብቻ ሳይሆኑ ሌቦችን ይህንን አባባል እንደ አባባል እንደሚጠቀሙበት በዮሐንስ ሚያን ካስቀመጥናቸው እንለያቸዋልን። ግን ለምን አልተቀሰፍኩም?

ምስጋና ሽቶው ተሸጦ ከሽያጩ ባለመስረቁ ሌላ የስርቆት መንገድ ወይም የመክበሪያ ስልት እንዲፈልግ ልቡን ይህንን ጉዳይ ለሚያስፈጽም የከፈተ

ይመስላል ከ8 መቶ ዐመት በፊት ዘካርያስ የተባለ ለመስዋእት የሚያስፈልግ ነገር ከሚገዛበት ሙዳይ ምጽዋት ገንዘብ ወጪ እንደሚሆን ተናግሮ ነበር መጠኑም ለባሪያ የሚሰጥ ያህል ነበር ዘካ 11፡12

የቤተልሔሙ አዳኝ ለአገልጋዮቹ በቃልና በተግባር ያስተምር ነበር ከልብ ሁሉን ለመተው ያልፈቀደን ሰው በቃልና በተግባር ብቻ ሳይሆን በግልኮስም ትምህርቱ ቢሰጡትም ጪጫ ልቡን አያርስም

የዓገልጋዮቹን እግር በማጠብ ትህትናን እራስን ዝቅ ማድረግ ታዛዥነትን ባስተማረበት ወቅትም አዳኝነቱን ያልተቀበለውን የከርዮኑ ምስጋናን አለየው። ለምን አልተቀሰፍኩም? አምላካዊ ምህረት ከዳተኛን በቶሎ ለይቶ አያስታውቅም

ለዐርብ ጥቂት ሰአታት ጉዳይ በቢታንያ እራት የተጋበዘው አዳኝ አገልጋዮቹን የመጨረሻውን እራት አደረገላቸው በመአድም ሳሉ እግርን ያጠቡ እጆች እንጀራን ኮርሰው ለከዳተኛ ከመስጠት አልተቆጠቡም ስንቶቻችን እንጀራ የቆረሱልንን ያባቶቻችንን እጆች ስመናል ወይም ነክሰናል ይሁን እንጂ ከዳተኞች ከመጥፎ ተግባራቸው ይመለሱ ዘንድ ጠቆም ማድረጉ አይከፋም እናም ከእናንተ የሚክድ ይኖራል ሲል አስታወቃቸው በእርሱ ፊት ማንም ጥፋተኛ ስላለመሆኑ በልበ ሙሉነት ሊናገር የሚችል ብጹእ የለም በዐለም ግን ይህ እራስን ዝቅ ማድረግ ለደካሞች እስፕሪ ሆኖ ሊደርሱ ወደማይገባቸው ወንበር ላይ አፈናጥሮ እየጎለታቸው ነው። እኔ እሆንን ? በማለት ከዳተኛ ላለመሆናቸው ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ወደራሳቸው እየጠቆሙ ጠየቁ የሆነ ሆኖ የሚከዳ ግን አለ ። ለምን አልተቀሰፍኩም ? አዳኙ ግን ወደ ንስሐ የሚመራ ሃሳብ አቀረበ ቁራሽ በመስጠት ክህደት

በእምነት ጥላቻ በፍቅር እንዲለወጥ ፍቅሩን ገለጠለት ይሁን እንጂ የከርዮኑ ምስጋና ልቡን ለእውነተኛና አምላካዊ ፍቅር ሳይሆን ለአስመሳይነትና ሆደ ጩቤ አፈቅቤነትን በጌቴሴማኔ የሚስምበትን አፉን ለተሟገተላቸው ድሆች ሳይሆን ሙዳይ ምጽዋቱን ለሚጣባበቁ ሐብታሞች አሳልፌ ልስጣችሁ ሲል ከፈተ።የታል የተቀሰፍኩት ?

መሸቶ ነበር ይሁዳም ወጣ ጭለማም ተቀበለው ምን አልባት በብርሃን ከማጥፋት በጭለማ ማጥፋት በዐለም የተሻል የአይን መደበቂያ ይሆናል ከህሊና መሸሸግ ግን አይቻልም ጥፋታችንን ሰው ሲነግረን እንጂ እራሳችን ስናስበው አያሳፍረንም ይህ የህሊና ክህደት ነው እግዚአብሔር በህሊናችን ውስጥ አለ ለህሊና ወቀሳ እጁን የማይሰጥ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የተገዛውን ሕይወቱን ክርስቶስን በመክዳት የተቀደሰ አካሉን በሐጢአት ዋጋ ለሞት የሸጠ ነው። በሞት መቀሰፍ ማለት ከእግዚአብሔር መለየት ነው ። ሐጢአትን በመቃወም በቅድስና መመላለስ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ነው።

Ethiopian Orthodox Tewahdo Books የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ መጻሕፍት አንባብያን ቡድን

24/ መካከለኛ ማለት ምን ማለት ነው?ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ እንዳስተማረው

ኃይለ ኢየሱስ መርሻ እንደተረጎመው: የቅዱስ ጳውሎስ መልክት ወደ

ጢሞቴዎስ 2 ተኛ እትም,2006

አስቀድሞ እንደተናገረ "እውነትን ወደማወቅ ይደርሱ ዘንድ" ይላል:: ይህም ዓለም በእውነት ውስጥ አለመሆኗን ያመለክታል:: አሁን ደግሞ "አንድ እግዚያብሔር አለ" ይላል:: ይህም አንዳንዶች ብዙ ነው እንደሚሉት አደለም:: መካከለኛ እንዲሆን እግዚያብሔር አንድያ ልጁን ላከው ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ መውደዱን ለማረጋገጥ:: ግን ልጁ እግዚያብሔር አደለምን? በ እውነት በእጅጉ እግዚያብሔር ነው:: ታዲያ ለምን "አንድ እግዚያብሔር አለ"? ይህ ከጣኦታት አንጻር የተባለ ነው እንጂ ከልጁ አንጻር አደለም:: እሱ/ሐዋርያው/ እየተናገረ ያለው ስለ እውነት እና ስለ ስህተት ነውና:: አሁን በመካከል ያለ ሰው ለማስታረቅ የሁለቱንም ወገን የሚጋራው ሊኖር ግድ ነው:: ይህ በሁለቱም ወገን ቀረቤታ ያለው ሰው መሆን የአስታራቂ/በመካከል ያለ ሰው/ ጠባይ ነውና:: ከአንዱ ጋር ቀረቤታ ኖሮት ከሌላኛው ጋር ከሌለው ግን መካከለኛ/አስታራቂ/ ሊሆን አይችልምና::

ስለዚህ እሱ/ልጁ/ ከአብ ባሕርይ ጋር አንድነት ከሌለው የአብ ባሕርይ ባሕርዩ ካልሆነ አስታራቂ ሊሆን አይችልም የተለየ ይሆናል እንጂ:: ወደ ሰዎች መጥቷልና የሰውን ባሕርይ ባሕርይው ካደረገ የእግዚያብሔር ባሕርይ ባሕርይው ነው ማለት ነው:: ምክኒያቱም ከእግዚያብሔር መጥቷልና::ምክኒያቱም በሁለቱ ባሕርያት መካከል ያስታርቅ ነበርና የግድ የሁለቱን ባህርያትም መቅረብ አለበት:: በሁለት ቦታዎች መካከል ያለ ቦታ እያንዳንዱን ቦታ እንደሚያገናኝ ሁለቱ ባሕርያት መዋሐድ እንዳለባቸው ግድ ነው:: ይህም ቦታው ሁለቱንም እንደሚያገናኝ በተዋሕዶ የከበረው

አንዱ ባሕርይም ሁለቱንም ባሕርያት ያሳያል:: በመሆኑም እሱ ሰው ሆነ እንደምንል ሁሉ እሱ እግዚያብሔርም ነበር:: ሰው/ፍጡሩና የአዳም ልጅ/መካከለኛ ሊሆን አይቻልም:: ምክኒያቱም ሰው ወደ እግዚያብሔር የግድ መለመን አለበትና:: ሊያስታርቃቸው የሚገባቸው ሰዎች ሊቀበሉት አልቻሉምና እግዚያብሔርም አስታራቂ ሊሆን አልቻለም ነበር::

2 ጢሞ 2፣5 አንድ እግዚአብሔር አለና። በእግዚአብሔርና በሠው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ። እርሱም ሠው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። 6 ራሱን ለሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበር:: —

Binyam Aregawi

25/ አቤቱ የምፀፀትበት ጊዜ እንዳይመጣ በቶሎ እንዳመሰግንህ ፍቀድልኝ። ይህ ጸሎቴ ነውና ላደርገውም እመኛለሁና አትከልክለኝ።በመዘግየቴም ምክንያት ፀፀት እንዳትገለኝ በቶሎ ፈቃድህን አደርግ ዘንድ እርዳኝ።

October 5, 2013 at 6:14pm

«• •» አንድ መነኩሴ ወደ አባ ባውሚን መጣና ያለህባት ጐጆ ለምን ክፍት ሆነች ቢለው ልሣናችን ክፉ እንዳይናገር እንድንዘጋ እንጂ ቤታችንን እንድንዘጋ አልታዘዝንም ብሎ መለሰለት።

«• •» ቅዱስ አርሳንዮስ ብዙ ጊዜ ብዙ እናገራለሁ በመናገሬም አዝናልሁ በዝምታዬ ግን ያዘንኩበት ጊዜ የለም አለ፤ አባ አጋቶንም ባንደበቱ እንዳይናገር 30 አመት ጠጠር ጐርሶ ይኖር ነበር። ትእግስተኛው

አባታችን እዮብም ‹‹ በሰማይ የምትኖር አባቴ ሆይ ! አስተምረኝ እኔም ዝም እላለው: የተሳሳትኩትንም ንገረኝ›› ይል ነበር። (እዮብ 6፤24) እየራበው እንኳ « በልቼ ያጠገብከኝ እግዚአብሔር ተመስገን ! » ይል ነበር ። ዝም እላለው ማለቱ እግዚአብሔር እንዲናገር ስለወደደ ነው እኛም እግዚአብሔር እንዲናገር ዝም እንበል፤ በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይስጠን ።

«• •» አንድ አባት ሌላውን አባት በተባሕትዎ ወደሚኖርበት በዐት ሄደና ወርሐ ፆም ዛሬ ገባ አለው አረጋዊው አባት ሲመልስም በእውነት እልሀለሁ ብሕትውና ከጀመርኩ 53 ዓመቴ ነው በዚሁ ዘመን ፆም መቼ እንደሚወጣ አስታውሼ አላውቅም ሲልመለሰለት።

{}{ ነገርን ነገር ያነሳዋልና ብዙ ጊዜ አንድ የሚነሳ ክርክር አለ ይኸውም ‹ዓሳ ጾም አለው ወይስ የለውም› እያሉ ብዙ ሚከራከሩ አሉ እኔ ግን የአንድ አባትን መልስ ላካፍላቹ፤ እሳቸው ለዚህ ጥያቄ ሲመልሱ ‹እንኳን ዓሳ ወፍራም እንጀራም ጾም አለው› ነበር ያሉት። እውነት ነው ከቅቤ እየጾምን በጮን ደግሞ ‹‹‹ሽኖለጋ››› ቅቤ እንበላለን፤ ከላም ወተት እየጾምን የዱቄትና የአኩሪ አተር ወተት እንጠጣለን፤.... ያማረ የተደራጀ ከሥጋና ከወተት በላይ ሰውነትን የሚገነባ የጾም ብፊ እየበላን ልበአምላክ ቅዱስ ዳዊት ‹‹ ጕልበቶቼ በጾም ደከሙ ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ። መዝ 108(109)፤24›› ያለውን እየተጋፋን ‹ጾምን› እንላለን፤ ጾም ከጠዋት እስከማታ ተጋፍቶ መብላት ከሆነማ ታዲያ ምኑን ጾምነው ??? ወንድሞች ሆይ ለሁሉም ግን አስቀድመን የጾምን ትርጉም እንወቅ። }{}

«• •» ለአንድ መነኩሴ ሰይጣን የብርሃን መልአክ መስሎ ተገለጸለትና «እኔ ገብርኤል ነኝ ወደ አንተ ተልኬ መጣሁ» አለው። በዚህ ጊዜ

መነኩሴው «እስኪ ወደ ሌላ ተልከህ እንደሆነ ልብ አድርግ፤ እኔ እንኳንስ አንተን የገዛ ኃጢዓቴን እንኳ ለማየት የበቃሁ አይደለሁም» አለው። ይህን ሲሰማ ከትህትናው ፊት መቆየት የተሳነው ጠላት እንደ ትቢያ በኖ ጠፋ።

«• •» አባ ዳንኤል ለመነኩሴ ከአንድ ሰዓት በላይ እንዲተኛ አይፈቀድም ይላል። ራሱ አባዳንኤል ከ 24 ሰዓት ውስጥ አንድ ሰዓት የማትሞላ የእንቅልፍ ጊዜ ነበረችው 'እንቅልፍን' አንተ መጥፎ ባርያ ይኸውልህ በሥጋዬ ላይ እረፍበት በማለት ለጥቂት ጊዜ ይቀመጥ ነበር በቀረው ጊዜው ግን ቁሞ በመፀለይ ብቻ ያሳልፈው ነበር። ማንም ይሁን በምንኩስና ዓለም ውስጥ ካለ ለእንቅልፍ ጊዜና ቦታ መስጠት የለበትም ይላል አባ ዳንኤል።

«• •» ቅዱስ ጳኩሚስ አንዲት ሴት ብዙ አጋንንት ሰፍረውባት ስትሰቃይ አየና «አቤቱ ጌታዬ ሆይ ይህን ሁሉ እንዴት ትችለዋለኽ» ብሎ በእርሷ ላይ ያለውን የአጋንንት መንጋ ወደ እርሱ እንዲገለበጥ ፈጣሪውን ለመነ፤ በዚህ ጊዜ በአንድ ቀፎ ውስጥ ያሉ ንቦች ወደ ሌላ ቀፎ እንደሚገለበጡ እነዚያ አጋንንት በሙሉ ከዚያች ሴትዮ ወጥተው በአባ ጳጉሚስ ላይ ሰፈሩ፤ እርሱም ማቅ ለብሶ አመድ ነስንሶ በሥግደት በጾምና በጸሎት አሰቃያቸው፤ የዚህን ቅዱስ አባት ትሩፋትና ተጋድሎ ስላልቻሉ አጋንንቱ «እንሂድ እንጂ እንግዲህማ ምን እናደርጋለን» ሲሉ ሰማቸው፤ ቅዱስ ጳኩሚስም «ለምን አትቆዩም ሰው እንዲህ ካለ ኃጥእ ወዳጁ ቤት እኮ ጥቂት ጊዜ ያርፋል» ቢላቸው «እኛስ ከገነት ካስወጣነው ከአዳም በቀር እንዲህ ያለ ሰው አላየንም ትሩፋቱ አቃጠለን ሊያስቀምጠን አልቻለም» ብለው መስክረውለት ሄዱ።

በጐ ያደረጉበእምነት በምግባር የጸኑ ጌታን ያስደሰቱ የነዚህን የቅዱሳን ነገር

ባሰብኩ ጊዜ ዘወትር የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ሰናይ መልእክት አስታውሳለሁ ‹‹...ነገር ግን ያለዐሳብ ልትኖሩ እወዳለኹ። ‘ያላገባውጌታን’ እንዴት ደስ እንዲያሠኘው ‘የጌታን ነገር’ ያስባል፤‘ያገባው ግን ሚስቱን’ እንዴት ደስ እንዲያሠኛት የዓለምን ነገርያስባል÷ልቡም ተከፍሏል። ‘ያልተጋባች ሴትና ድንግል’ በሥጋም በነፍስም እንዲቀደሱ ‘የጌታን ነገር ያስባሉ’፤ ‘የተጋባች’ ግን ‘ባሏን’ እንዴት ደስ እንድታሠኘው‘የዓለምን ነገር’ ታስባለች። ~1ኛ ቆሮንቶስ 7፤32-34 (ቢቻል ሙሉውን ያንብቡት)››

_-:¦:-_____◊_____-:¦:-_

ጌታ ሆይ እንደነዚህ ካሉ ብጹአን ከሚሆኑ አባቶች በረከት ረድኤት ስጠን፤ በእነረሱም ጸሎት ዘወትር ጠብቀን። በእውነት አንተን ለማመስገን መፈጠር መታደል ነውና ጌታ ሆይ ለምሰጋና አድርገኝ ! ይህ ጸሎቴ ነውና ላደርገውም እመኛለሁና አትከልክለኝ።

አቤቱ የምፀፀትበት ጊዜ እንዳይመጣ በቶሎ እንዳመሰግንህ ፍቀድልኝ። በመዘግየቴም ምክንያት ፀፀት እንዳትገለኝ በቶሎ ፈቃድህን አደርግ ዘንድ እርዳኝ።

ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ÷ አቤቱ÷ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች። ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች፤ መቼ እደርሳለሁ ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ ? ዘወትር። አምላክህ ወዴት ነው ? ሲሉኝ እንባዬ በቀንና በሌሊት ምግብ ሆነኝ። . . . ነፍሴ ሆይ÷ ለምን ታዝኛለሽ? ለምንስ ታውኪኛለሽ? የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ በእግዚአብሔር ታመኚ። ~ መዝ 41(42) :1-11 ~

እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው፤ ልዑል ሆይ ለስምኽም ዝማሬ ማቅረብ በማለዳ ምሕረትን በሌሊትም እውነትኽን ማውራት ዐሥር አውታር ባለው በበገና ከምስጋና ጋራም በመሰንቆ።

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን ለአምላክ ለመድኀኒታችን እልል እንበል። በምስጋና ወደ ፊቱ እንድረስ በዝማሬም ለርሱ እልል እንበል እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ነውና በአማልክትም ኹሉ ላይ ታላቅ ንጉሥ ነውና።

~መዝሙር 91 እና 94፤1~

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

{}{~ ከ ግንቦት 6 2005 ዓ.ም ማስታወሻ የተጻፈ ~}{}

☆══════════ ▯ ══════════☆

እንደዚህች ባለች በእሁድ ሰንበት (ዳግማይ ትንሳኤ) በዝግ ቤት ውስጥ ሳሉ በመካከላቸው ቆሞ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው።

ሰላም ለእናንተ ይሁን እነሆ ሰላማችሁን መለስኩላችሁ፤ ታረኩአችሁ ከእግዚአብሔር አባቴ ጋርም አስታረኩአችሁ፤ ሞትን ሞትኩላቹ የሞትንም መውጊያ ከእናንተ ዘንድ አጠፋሁላችሁ፤ ገና ኃጢአተኞች ሳላቹ አሳልፌ አልሰጠኁችሁምና።

ሐዋርያት ከጌታ መሰቀል ቡኃላ አይሁድን ፈርተው በዝግ ቤት ውስጥ በርሀብና በጥማት ሰላም አጥተው ተጨንቀው ሳሉ ክርስቶስ በሞተ በ 3 ኛው ቀን ባለች በእሁድ ሰንበት በዝግ ቤት ውስጥ ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ ሰላም ለእናንተ ይሁን ብሎ አላቸው። ሐዋርያት ግን ደነገጡ ምትሀት

መሰላቸው። ክርስቶስ ለምትሃት ሥጋና አጥንት የለውም የተቸነከሩ እጆቼ የተወጋውም ጎኔ ይኸው እዩና እመኑ አላቸው። ምትሀት አይበላም አይጠጣም እርሱ ግን ከእነርሱ ጋር በላ ጠጣ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ዲዲሞስ የተባለ ቶማስ አልነበረም። ሐዋርያትም ጌታ እንደተነሳ ሲነግሩትⷪ ካላየሁ የተወጋ ጐኑን ካልዳሰስኩ አላምንም አለ።

ቶማስ በቀኖት የተቸነከሩትን እጆቹና እግሮቹን ካላየሁ በጦር የተወጋውን ጐኑን ካልዳሰስኩ አላምንም ለምን አለ ? ቢሉ ትንሳኤ ሙታንን ከሚያምኑ (ሰው ከሞተ ከበሰበሰ ቡሀላ ትንሳኤ የለውም ከሚሉት) ከሰዱቃውያን ወገን ነውና አንድም ሌሎች ሐዋርያት አየነው ብለው ሲያስተምሩ እርሱ ግን ሰማሁ ብሎ የሚያስተምር እንዳይሆን ብሎ።

እንደዚህች ባለች በእሁድ ሰንበት (ዳግማይ ትንሳኤ) በዝግ ቤት ውስጥ ሳሉ ዳግመኛም በመካከላቸው ቆሞ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ቶማስንም ተናገረው ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይⷪ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባውⷪ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው። የጌታን ጐን ቢዳስስ እጁ ከእሳት እንደገባ ቢኮማተር " ጌታዬ አምላኬ " አለ (ዮሐ 20:27-29) ዛሬ ዛሬ 'ኢየሱስ ጌታ ነው' የሚሉ በየመንገዳችን በዝተዋል አምላክነቱን ክደው 'ኢየሱስ ጌታ ነው' ይላሉ እኛ ግን ከቶማስ ተማሩ እንላለን እርሱ ጌታዬ አምላኬ ሲል ቁርጥ ንግግር ተናግሯልና ይህቺ የጌታን ጐኑን የዳሰሰች እጅ ዛሬም ድረስ በህንድ አገር ከታቦት ጋር በመንበር አለች ጌታም አለው ቶማስ ሆይ ብታየኝ አመንክ ንውዳን ክቡራንስ ሳያዩኝ የሚያምኑብኝ ናቸው።

ይህም ለኛ አብነታችን ነው። እኛ ኢትዮድያውያን የክርስቶስን ልደትⷪ

ስቅለት፤ ትንሳኤና እርገት አይተን አይደለም የምናምነው ነገር ግን እምነት ከመሰማት ነው መስማትም የእግዚአብሔርን ቃል ነው ብለን እንጂ። ደግሞም 'ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው' ይላል አማናዊ የጌታ ቃል በእርግጥም ብፁዕ ነን ሳናይ አምነናልና።

ወስብሀት ለእግዚአብሔር።

26/ የተሰሎንቄ እብዶች

Please read in PDF

በቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞዎች ከማይረሱ ከተሞች መካከል አንዷ ተሰሎንቄ ናት። ከአውሮፓ ወደእስያ ለሚዘዋወረው ሰውና ንግድ ዋና የባህር በር ሆና የሰረገላም መንገድ ተሰርቶባት ያለችግር መመላለሻ ነበረች።ከተማይቱ ብዙ የአይሁድ እምነት ተከታዮች ያሉባትና እኒህም ምኩራብ ሰርተው ያመልኩ የነበሩ ናቸው።

የሐዋርያት ሥራን የዘገበልን ቅዱሱ ተጓዥ ሉቃስ ቅዱስ ጳውሎስ ወደዚህች ከተማ መጥቶ ሦስት ሰንበት ያህል ከመጽሐፍ እየጠቀሰ " ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሣ ይገባው ዘንድ እያስረዳ፦ ይህ እኔ የምሰብክላችሁ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው" እያለ ተርጉሞ በማስተማሩ "ከእነርሱም አንዳንዶቹ ተረድተው ከሚያመልኩም ከግሪክ ሰዎች ብዙ ከከበሩትም ሴቶች ጥቂቶች ያይደሉ፣ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር ተባበሩ።" ይለናል።(ሐዋ.17÷1-4)

የክርስትና የስብከት ማዕከላዊ ርዕስ ኢየሱስ የሆነ ክርስቶስ እርሱ መሲህ ነው የሚለው ነው።ዛሬም ድረስ ይህ እውነተኛ የሐዋርያት ትምህርት "ታላላቅ" እንደሆኑ ለሚያስቡ አብያተ ክርስቲያናት ሳይቀር የመለያየት ምልክት ነው። ኢየሱስ በሚለው ስም ከአይሁድ እስከአህዛብ አይደለም ብለው አይሟገቱም። ክርስቶስ እርሱ ብቃት ያለው አዳኝ ነው የሚለው ሲጨመር ግን አብዛኛው ጉርምርምታና ጆሮውን ማከክ ይጀምራል። የሐዋርያት ሥራን ስናጠና የሐዋርያት የመከራቸውና የመሰደዳቸው መነሻና ድምዳሜው እንዲህ ብለው ጮኸው መስበካቸው ነው።

እንግዲህ ይህን ማስተማር ከውግዘት እስከመግደል ሊያደርስ ይችላል። በተሰሎንቄ የሆነው ይህ ነው። በዚህ ትምህርት ከጥቂት የዘለሉ ያመኑትን ያዩ የበዙት የተሰሎንቄ "አይሁድ ግን ቀንተው ከሥራ ፈቶች ክፉ ሰዎችን አመጡ ሕዝብንም ሰብስበው ከተማውን አወኩ..."(ቁ.5)። አስተውሉ!!! ወንጌሉን የሰሙ አምነዋል። ያልሰሙና መስማት የማይፈልጉ ግን ሁሌም ይበጠብጣሉ።ዛሬም ለቤተ ክርስቲያን ራስ ምታት የሚሆኑት ቃሉን ለሁል ጊዜ የሚሰሙትና ታጢአትን የጠሉ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሳይሆኑ በልምድ የሚመላለሱትና በንግስና በጥምቀት የሚጋፉቱ ነጠላና ቀሚስ ለባሾች ናቸው።

ወንጌልን በትክክል ስናምን በየትኛውም አይነት መንገድ ተሰዳጅ እንጂ አሳዳጅ የመሆን እድል የለንም።የዛሬዎቹን አብያተ ክርስቲያናት ዘወር ብላችሁ እዩ!!! ከአማኝ ይልቅ እንደ ተሰሎንቄ እብድ አሳዳጅና ደጋፊ ይበዛባቸዋል። አንድ ክርስቶስ የሞተለት የሥላሴ ህንፃ ክቡር ሰው በጥንቆላ ፣በዝሙት ፣በዘፈን ፣በስካር ፣...ተጠልፎ ወደቀ ተሰነካከለ ሲባል ምንም

ትርጉም የማይሰጠው፤ አንድ ሰው በሰው እጅ የተሰራውን ቤተ መቅደስ (ይበልጣል የምትሉ እንዳትቆጡ!!!)አፈረሰ አቃጠለ ሲባል ግን አንድ ቀን ቤተ ክርስቲያን ያልመጣ ሁሉ ገጀራና ቆመጥ ይዞ ሲፎክር ማየት የተለመደ ነው።በዚያው ትይዩ በሚሸነግል ምላሳቸው ተረትና እውነት ቀላቅለው" የሚያስተማሩ" ለቁጥር የሚታክት ደጋፊ ሲኖራቸው የክርስቶስን ወንጌል በቅንነትና በእውነት የሚያገለግሉ ግን ዛሬም ድረስ ካሉበት አውደ ምህረትና ከሌሉበት አደባባይ እየተገፈተሩ አካላቸው እየደማ ተፈንክተው ሲወርዱና ተሰድበው ሲወገዙም በአይኖቻችን አይተናል።

ከአፍሪካ በተለይ እኛ ሐገር በሁለት ነገር አዕላፍ ትዕልፊት ደጋፊ ያውም እብድ ደጋፊ ታገኛለህ። በሐይማኖትና በብሔርተኝነት።ብሔርተኝነት እዚያ ቤተ መንግስት መንደር ብቻ ነው ያለው ብለህ የምትከራከረኝ ጭፍን ተከራካሪ ልትኖር እንደምትችል እገምታለሁ።ግና ልትደርስበት የቀናት ጥናት ይበቃሃል።በአብያተ ክርስቲያናት ሥር የሰደደ ዘረኝነትን ያለውን ያህል በሌላ ቦታ አለ ብዬ (ከበጣም በጣም ጥቂቶች) ለማሰብ እቸገራለሁ። ከኢትዮጲያ እስከአሜሪካ ከአሜሪካ እስከ አውሮጳ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት የራስን ዘር ፈልጎ ፅዋ መመስረት ፣ዕድር መግባት ፣ጉባኤ መካፈል...እንደ በጎ ሥራ ሲቆጠር ታዝበናል። ግና በክርስቶስ ደም ከነገድ ከወገን ከቋንቋ ከህዝብ ተዋጅተናል ለማለቱ ምን ብቃት ይኖረን ይሆን?

በሌላ መልኩ ስለኃይማኖተኝነት ስናነሳ በወረሰው እንጂ ባመነው ኃይማኖቱ የሚኖረው እጅግ ከማነሱም በላይ ኃይማኖቱን የሚኖረው ብዙም አይደመጥም ቦታም የለውም።ኃይማኖት ከስሜት የዘለለ ልንኖርለትና ልንሞትለት የሚገባ ነው። "ቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጣቸውን

ኃይማኖት ተጋደሉለት" (ይሁዳ.3) ሲባል እንደቅዱስ ጳውሎስ በመገፋትና በመጠላት ብቻ ውስጥ አለፉ ማለት እንጂ ለቅጽበት እንኳ አጸፋዊ ምላሽ መስጠታቸውን ፈጽሞ አንመለከትም።

የተሰሎንቄ እብዶች ለመልካም ነገር መሸነፍ መቼም አይሆንላቸውም ። ቃሉን የማሰላሰያና የማጉተምተሚያም ጊዜም የላቸውም።ስለዚህም ስለሃይማኖታቸው መግደልም ካስፈለገ ለእነርሱ ጽድቅ ነውና ከመግደል አይመለሱም።እንዲህ ያሉትን

እብድ ደጋፊ ማፍራት ቀላል ነው።ትውውቅም አያስፈልግም።በሐገራችን ብዙ የእግር ኳስ ደጋፊ እንዳለ እሰማለሁ።"የእኛ" "እኛ" እየተባባሉም እንደሚጠራሩም። (የሩቅ ማፍቀር ስንችልበት¡¡¡)ታዲያ አንዱ ወገን ከተሸነፈ ድንገት ቢተራረቡ በጨቤ መወጋጋት ጭምር እንዳለም። (ያልታደልን!!!)

ወደቤተ ክርስቲያንም ስንመጣ ቲፎዞ ያላቸው ሰባኪዎችና ዘማሪዎች አገልጋዮች እንዳሉ እናያለን።አለማዊ ልምምዳችን አድጎ ቤተ ክርስቲያናችንን ገዝቷታል። በትልልቅ ዓለማዊ ስብሰባዎች ላይ እናይ የነበረው በንግግር መሐል ጭብጨባ ዛሬ ከዳር እስከ ዳር እግዚአብሔርን ሳይሆን ስብከት ለማድነቅ ተከነንበታል።የተሰሎንቄ እብዶች የወንጌል ልብና ጊዜ የላቸውም በእምነት ስም ግን የማሳደድና የመግደል ልብና ጊዜ ተትረፍርፎላቸዋል።

ኢየሱስን ክርስቶስ ነው ብላችሁ ስታስተምሩ ከሰማው በጣም ጥቂቱ ይረዳችኋል የሚበዛው ግን ድንጋይ ጨብጦ እስከአቴና ድረስ ይከተላችኋል። ግን እናንተ እውነተኞች ሆይ! ጨክኑ አይዟችሁ። ከፊታችሁ እነሆ የክብር

አክሊል አለና።

ጸጋ ይብዛላችሁ።አሜን።

Rodas Tadese Abebe

27/ የሰማይ ውበት

ከመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲስ መምህር

ልዑል እግዚአብሔር ሥራው በእጅጉ ድንቅ ነው፤ በተለይ የሰባቱ ሰማያት ነገርና የሰማዩ ውበት! የመዠመሪያዋ ሰማይ “ጽርሐ አርያም” ስትባል ከእሳት ብርሃኗን ነሥቶ ከብርሃን ብርሃን ጠምቆ አጥርቶ፤ ኹለንተናዋን በብርሃን ቀለም ሸልሟታል ብርሃኗን ማንም ከቶ ሊገልጸው አይችልም፤ ከርሷ ብርሃን አንጻር ሲታዩ ሌሎቹ ብርሃናት የእሳት ፍንጣሪ ያኽላሉ፤ ከሰማይ ኹሉ በላይ ስትኾን ከርሷ በላይ ምንም ሰማይ የለም፤ ከዚኽ የተነሣ “ሰማየ ሰማያት” ትባላለች (ዘዳ ፲፥፲፬፤ ፭ነገ ፰፥፳፯)።

ኹለተኛዋ ሰማይ “መንበረ መንግሥት” ስትባል እንደ ቤተ መቅደስ አራት መአዝን ሲኖራት ጽንፍ እስከ ጽንፍ አትደርስም፤ ሰባት የእሳት መጋረጃ ጋርዶ ሰባት የእሳት ዐጥር ዐጥሯታል፤ በዚኽችም ሰማይ ሥላሴ ለጻድቃን ለሰማዕታት በዘፈቀደ ይገለጹባታል፤ ከዚኽም የተነሣ “መንበር” ስትባል ርሱ በፈቀደው ክብሩን ጌትነቱን የሚገልጥባት ሰማይ ስለኾነች “መንበረ መንግሥት” ትባላለች (ኢሳ ፮፥፩-፫፤ ሕዝ ፩፥፳፮)፤ ዳግመኛም ሦስት

ስሞች አሏት ይኸውም በመላእክት የሚመሰገንባት ሰማይ በመኾኗ “መንበረ ስብሐት” ስትባል፤ ኹሉን ቻይ የኾነው አምላክ ዙፋን በመኾኗ “መንበረ ጸባኦት”፤ ዳግመኛም እውነተኛው ብርሃን የሚገለጽባት ሰማይ በመኾኗ “መንበረ ብርሃን” ተብላለች (ራእ ፬፥፪-፭)።

ሦስተኛዋ ሰማይ “ሰማይ ውዱድ” ስትባል ከእሳት ውዕየቷን ትቶ ብርሃኗን ነሥቶ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ጐዝጕዞ ዘርግቶ አንጽፏታል፤ ይኸውም ኪሩቤል የተሸከሙት መንበር ሲኾን በኪሩቤል ላይ ተዘርግቶ ለመንበረ መንግሥት እንደ አዳራሽ ወለል ኾኖ መንበረ መንግሥት እንደ ዙፋን ተዘርግቶበታል (ኢሳ ፮፥፩-፪፤ ሕዝ ፲፥፲፱-፳)።

አራተኛዋ ሰማይ “ኢየሩሳሌም ሰማያዊት” ስትባል በመንበረ ስብሐት አንጻር ትገኛለች፤ ሥራዋ እንደ ቤተ መቅደስ አራት መኣዝን ስትኾን ጽንፍ እስከ ጽንፍ አትደርስም፤ ዐሥራ ኹለት ደጆች አሏት፤ የደጆቿም ብርሃናቸው ልዩ ልዩ ናቸው፤ ይኽቺንም ኢየሩሳሌም ሰማያዊት የብርሃን አዕማድ ደግፎ የብርሃን ክዳን ከፍክፏታል፤ “ጠፈራ እሳት ወምርዋጸ ከዋክብት የዐውዱ ላዕሌሃ” ይላል በዚኽም በሦስት ረድፍ በከዋክብት አምሳል የብርሃን መርገፍ ሲያዘርባት ሰባት የእሳት መጋረጃ ጋርዶ ሰባት የእሳት ዐጥር ዐጥሯታል (ሼቆሮ ፪፥፱፤ ገላ ፬፥፳፯፤ ዕብ ፲፪፥፳፪፤ ራእ ፳፩፥፪-፲፬)።

በመቀጠልም ኢዮር፣ ራማ፣ ኤረር የተባሉ ሦስት ሰማያትን ሲፈጥር፤ እነዚኽን ሰማያት ከእሳት ውዕየቷን ለይቶ ብርሃኗን አውጥቶ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ዘርግቶ ሰባት የእሳት መጋረጃ ጋርዶ ሰባት የእሳት ዐጥር ዐጥሯቸዋል፤ “ኑኖን ወራሕቦን ለሠለስቲሆሙ ዕሩይ

ውእቱ" ይላል የሦስቱም ወርዳቸው ቁመታቸው ትክክል ሲኾን ሦስቱ የመላእክት ሰማያት የሚባሉት እነዚኽ ናቸው (፪ ቆሮ ፲፪፥፩-፫)።

ከዚያም ልዑል እግዚአብሔር በዕለተ እሑድ ሰባቱን ሰማያት ከፈጠረ በኋላ ሊቁ በአክሲማሮስ እንደገለጸው ከቅዱሳን መላእክት መኻከል፦

ከሰራዊተ ሩፋኤል ኀይት ሊቃናትን መርጦ በመንበረ ስብሐት በመጋረጃዋ ውስጥ ዙሪያዋን ክንፍ ለክንፍ ገጥሞ አቁሟቸዋል (ሕዝ ፩፥፲፩-፲፪)፤ ቍጥራቸውን ኻያ አራት ማድረጉ በኻያ አራቱ ጊዜያት ጸልየው ሌላውንም ራሳቸውንም ጠብቀው ዋጋቸውን ተቀብለው የሚኖሩ በመኾናቸው ሲኾን እነዚኽንም መላእክት "ካህናተ ሰማይ" ሲላቸው የእሳት የወርቅ ጽና ሲያሲዛቸው የብርሃን አክሊል ጻዝዮን የሚባል የብርሃን ዘውድ ደፍቶላቸዋል፤ የብርሃን ዘንግ ማኅተሙ መስቀል የኾነ ሲያሲዛቸው የብርሃን ካባ ላንቃ ሕብሩ መብረቅ የመሰለ አልብሷቸዋል።

ዮሐንስም በራእዩ በምዕ ፬፥፬-፭፤፲-፲፭ ላይ፦ "በዙፋኑ ዙሪያም ኻያ አራት ዙፋኖች ነበሩ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ኻያ አራት ሊቃናት ተቀምጠው ነበር ... ኻያ አራቱ ሊቃናት በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ኹሉን ፈጥረኻልና ስለ ፈቃድኽም ኾነዋልና ተፈጥረውማልና ክብርን ውዳሴንና ኀይልንም ልትቀበል ይገባኻል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ" በማለት ገልጾታል።

እነዚኽ ሰማያውያን ካህናት በአንድ ላይ ባጠኑ ጊዜ ዛሬ በክረምት ጊዜ ጉም ተራራውን እንደሚሸፍነው ከማዕጠንታቸው የሚወጣው ጢስ መልኩ

መብረቅ፣ ድምፁ ነጐድጓድ፣ መዐዛው መልካም የኾነና ጽርሐ አርያም፣ መንበረ መንግሥት የተባሉትን የብርሃን ሰማያት የሚሸፍንና የሚጋርድና ከጢሱ ጋር የቅዱሳን ጸሎት ዐብሮ ወደ እግዚአብሔር ፊት ይወጣል፤ “ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ኹሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ” እንዳለ ዮሐንስ በራእዩ (ራእ ፰፥፫-፭)።

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ በአክሲማሮስ ላይ “ወቦ ኪሩቤል ይቀውሙ በየማን በአምሳለ ቀሳውስት ወሱራፌል ይቀውሙ በአምሳለ ዲያቆናት ወድጎሬሆሙ ካህናተ ሰማይ ወቦ እልፍ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት መብረቅ ወነጐድጓድ ወሠረገላሆሙኒ ምሉኣነ አዕይንት” እንዳለ ኪሩቤል በቀኝ ሱራፌል በግራ ከፍ ብለው ካህናተ ሰማይ ክንፍ ለክንፍ ገጥመው በስተኋላቸው ሲታዩ በሰማይ ውዱድ ዙሪያ እልፍ አእላፋት መብረቅ፣ ነጐድጓድ፣ ሠረገላ፣ እንደ መስታየት ብሩህ የኾነ ሲኖርበት እነዚኽ ቅዱሳን መላእክትም ሳያቋርጡ “ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር” እያሉ ፈጣሪያቸውን በአንድነቱ በሦስትነቱ ያመሰግኑታል (ራእ ፬፥፰)።

ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስም ስለነዚኽ ቅዱሳን መላእክት ሲገልጽ “ወኩሎሙ ሰራዊተ መላእክት እለ ይቀውሙ ቅድሜሁ ይጸርሑ ወይባርክዎ ለእግዚአብሔር...” (በፊቱ የሚቆሙ የመላእክት ሰራዊትም ኹሉ ጨኽው ያመሰግኑታል፤ የመላእክት አለቆችም ለማይታይ ለባለዚኽ ስም ዘንበል ብለው ይሰግዳሉ፤ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑና የሚዘምሩ ዙፋኑን

የሚሸከሙ አርባዕቱ እንስሳ ጨኸው ያመሰግኑታል፤ ዕጣንን የተመሉ የወርቅ ማዕጠንት በእጆቻቸው ያለ ኻያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ይኸውም የቅዱሳን ጸሎት ነው እስከ ዘላለሙ ሕያው በኾነው ፊት የሚቀበለው መሥዋዕት አድርገው ወደ ላይ ያሳርጋሉ) በማለት የቅዱሳንን ጸሎት ቅድመ እግዚአብሔር በማዕጠንታቸው ለማሳረግ የተመረጡት መላእክት ኻያ አራቱ ካህናተ ሰማይ መኾናቸውን አስተምሯል።

የመናፍቃን መዶሻ የተባለው ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስም ስለዚኽ ታላቅ ግርማ እያመሰጠረ ሲያስተምር “ልዑል ወግኡዝ ዘበሰማያት ጠፈሩ ልብሰ እሳት ...” (በሰማይ ያለ ጠፈሩ ስዉር ልዑል ነው፤ የእሳት መጐናጸፊያ የሚጐናጸፍ በእሳት መንኰራኵርም ያጌጠ ነው፤ ዙፋኑ ከአለቆች በላይ የሚኾን ማደሪያው በማይዳሰስ በአየር ላይ፤ ጠፈሩም በልዑል ሰማይ መንኰራኵር ደመና፤ ጐዳናውም በባሕር መንኰራኵር ላይ በሚላኩት በእሳት አለቆችም ነው፤ የሚያቃጥል እሳት እንዳያቃጥላቸው በኹለቱ የእሳት ክንፋቸው እግራቸው ይሸፍናሉ፤ ግሩም የሚኾን ብርሃኑ (ነበልባሉ) እንዳይመታቸው በኹለት የብርሃን ክንፋቸው ፊታቸውን ይሸፍናሉ ረቂቅ በሚኾን ኹለት ክንፋቸው እስከ ዓለም ዳርቻ ይወጣሉ) በማለት በስፋትና በጥልቀት ሲያስተምር፤ ሊቁም አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም ከዚኽ ተነሥቶ፦-

“ጸርሐ አርያም አዳራሹ፤ የትጉሃን መኖሪያ ቦታው የሚኾን እግዚአብሔር ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ ተብሎ በአንድነት በሦስትነት ይመሰገናል፤ ካህናተ ሰማይ በዙሪያው ይቆማሉ፤ በዙፋኑ ፊት እየሰገዱ አክሊሎቻቸውን ያወርዳሉ፤ እሳትነቱ (ባሕርዩ) በሚበርቅ፣ ወገግ በሚል ጊዜ እንዳይመታቸው ይንቀጠቀጣሉ” በማለት አስተምሯል።

ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም በሰማይ ስለሚደረገው ምስጋና በቅዳሴያቸው ላይ ሲያስተምሩ፡- “መኑ ስሙ ወመኑ ስመ ወልዱ ዘከመ እፎ ብሔሩ ወዘከመ እፎ ሀገሩ፤ መንበሩ በእሳት ክሉል ወማኅደሩ በማይ ጥፋር...” (ስሙ ማነው? የልጁስ ስም ማነው? መኖሪያው እንደምን ያለ ነው? ሀገሩስ እንደምን ያለ ነው? (ምሳ ፴፥፬)፤ ዙፋኑ በእሳት የተከበበ ነው፤ ማደሪያውም በውሃ የተታጀ ነው፤ በቤቱም ዙሪያ ላይ የማይፈስስ የውሃ መርገፍ አለ (መዝ ፺፫፥፫)፤

ከዙፋኑም ብልጭልጭታ ይወጣል፤ ውስጡ እንደ ጋለ እሳት ነው፤ በውስጡ እንደ ክረምት ቀስተ ደመና ያለ ደገኛ ብርሃን አለ ዙሪያውም መብረቅ ነው (ሕዝ ፩፥፳፰)፤ በዚያም መንበር አጠገብ አራቱ እንስሳ ሕብሩ እንደ በረድ ነጭ የኾነ ሰፊ መንበር በራሳቸው እንደተሸከሙ ኾነው አሉ (ራእ ፬፥፫-፬)፤ በዚኽም መንበር ዙሪያ ኻያ አራቱ ካህናተ ሰማይ አሉ (ራእ ፬፥፬-፲፩)፤ በፊታቸውም የበጉን ሥዕል ደምን የተረጨች ልብስንም የታተመ መጽሐፍንም ያያሉ፤ ይኽንንም መንበር በዙሩ ቁጥር ለዚያ ለበጉ ሥዕልና በደም ለታለለች ልብስ ለታተመው መጽሐፍ ሦስት ጊዜ ይሰግዳሉ (ራእ ፭፥፰-፲፬)፤

በአዳራሹም ድንኳን የምስጋና ጢስ ይመላል፤ ከዚኽም መንበር በታች ጐዳናው ኹለት የኾነ ባሕር ይፈልቃል የብርሃን ባሕርና የነፋስ ባሕር (ራእ ፬፥፮፤ ፲፭፥፪)፤ የአማልክት አምላክ በዚያ አለ የአጋዕዝትም ጌታ በዚያ አለ (መዝ ፵፱፥፩፤ ፹፫፥፯፤ ፺፭፥፪)፤ በውጪ ይኖራል በውስጥም ይገኛል፤ ያገኙትም ዘንድ አይኼዱም በሹትም ጊዜ አይታጣም፤ በያዙት ጊዜ አይዳሰስም ከጎሊና ልዩ ነው...መላእክትና ሊቃነ መላእክት የሚሰግዱለት

ርሱ ነው (ፊልጵ ፪፥፲)፤ በማየት የሚሰግዱለት አይደለም ለመንበሩ ይሰግዳሉ ለጌትነቱም ይገዛሉ እንጂ፤ ፈቃዱን ኹሉ ለመሥራት ወደ አራቱ መኣዝነ ዓለም ይወጣሉ፤ ሱራፌልና ኪሩቤል በትዕቢት ጎይል ያይደለ ጩኸው ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ጎያል የማይሞት ስለ ሰው ፍቅር የሞተ ቅዱስ ሕያው ይላሉ (ራእ ፭፥፱-፲)) በማለት ድንቅ ምስጢርን ገልጠዋል።

በቅርቡ ታትሞ ከሚወጣው መጽሐፌ የተወሰደ

አቤቱ ልዑል እግዚአብሔር ሆይ የመንግሥት ወራሽ እንድንሆን በቸርነትኽ ዐስበን።

ደቀ መዛሙርት የጌታን ትንሳኤ ለምን ተጠራጠሩ?(የመጨረሻ ክፍል)

Please Read in Pdf

3. መጠራጠር ፦ ደቀ መዛሙርቱ ነገረ ትንሳኤውን ሲሰሙ የተነገራቸው “ ... ቃል ቅዠት መስሎ ታያቸውና አላመኑም።”(ሉቃ.24፥11) ደቀ መዛሙርት አርብ ዕለት በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነውን መከራ አይተነዋል። ስለዚህ ሁሉም “ተሰብስበው ... አይሁድን ስለፈሩ ደጅ ዘግተው ... ” በፍርሐት ቆፈን ውስጥ ሆነው ተቀምጠዋል። (ዮሐ.20፥19) እግዚአብሔርን የማይፈራ ፍርሃት ጥበብ የጎደለው ፍርሃት ነው። እግዚአብሔርን እስከመካድ ያደርሳልና።

ጴጥሮስ “አንተ ክርስቶስ የህያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ”(ማቴ.16፥16) ብሎ የመሰከረለትን ጌታ ከሥጋዊ ፍርሃት የተነሳ በአንዲት “ነጻነት በሌላት”ሴት ፊት በተጠየቀ ጊዜ “የምትይውን ... ሰውየውን

አላውቀውም” ብሎ ካደ።(ማቴ.26፥70፤72) “መለኮታችን” መለኮትን ፤ፍርሃታችን እግዚአብሔርን መፍራት ካልቻለ ፍርሃታችን የራሱን መለኮት ፈጥሮ መካዳችን የማይቀር ነው።ጌዴዎን የመፍራቱና የመጠራጠሩ ምንጭ የምድያማውያን ጥቃትና እግዚአብሔርም እንደተዋቸውና እንደጣላቸው ማሰቡ ነበር።(መሳ.6፥11-13)

አይሁድ ሁሉንም ሰው በክርስቶስ ሞት እንዲተባበር ኢየሱስን ግን እንዲያጠፉት ወይም እንዲገድሉት ህዝቡን እጅግ አባብለዋል።ስለዚህም ሁሉም ይሰቀል እያሉ ጩኸት አብዝተዋል።(ማቴ.27፥20፤23) ይህም በራሱ ለደቀ መዛሙርቱ ከባድ የፍርሃትና የጥርጥር ምንጭ ነው። አለሙ የተስማማበት ብዙዎች የተከተሉት ውሸት በእርግጥ ለዘመናት ብዙዎችን በጥርጣሬ መንፈስ ወደኋላ ስቧል። ዛሬም ወንጌልን በድፍረት እንዳንመሰክር የሚያደርገንና የፍርሃታችን አንዱ ዋናው ምንጭ ስህተት የሆነውን ነገር የተቀበለው ህዝብና ወገን በፍጥራዊው አይናችን ፊት በዝቶ ስለታየንና ትልቁን የጌታ ክንድ መዘንጋታችን ወይም መጠራጠራችን ነው። በመጠራጠር ወደኋላ መመለስ ደግሞ ውጤቱ ካለማመን ይበልጥ ሊከፋ ይችላል።ስለዚህም “እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና”(2 ጢሞ.1፥7) በመንፈስ አካለ መጠን ልንጎለምስ ይገባል።

ጠላት ክንዱ በበዛና ክንዱም በበረታ ጊዜ ይህ ፍጥረታዊው ሰው በፍርሃትና በጥርጣሬ ካልቀለጥሁ ይላል።የዚያን ጊዜ ግን ጠላትን ሁሉ እንደአንድ ሰው መምታት እንዲቻለን ኃይልና ጥበብን የሚሰጠንንና ለእጆቻችንም ሰልፍን የሚያስተምረውን ጌታ በብዙ ልንታመንበት ይገባናል።በእርግጥ እርሱ

ሳይታዘብ ደካማውን ይረዳልና።

4. የመጻህፍትን ኃይል መሳት ፦ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ያለማስተዋላችን ትልቁ ምስጢር “መጻህፍቱንና ኃይሉን ባለማወቅ መሳታችን” ነው።(ማቴ.22፥29) ደቀ መዛሙርቱ ጌታ ገና ከእነርሱ ጋር ሳለ “በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ...” ስለእርሱ የተጻፈውን ሁሉ በጆሮአቸው ነግሯቸው ነበር። (ማቴ.16፥21፤ማር.10፥32፤ሉቃ.4፥21፤24፥44) መላዕክቱ እንኳ በተገለጡ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገሩት “የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሳ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደተናገረ አስቡ።”(ሉቃ.24፥7) እያሉ ነበር።ደቀ መዛሙርቱ ግን ከማስተዋል የዘገዩ ይመስላል።

ሰፊው የክህደት በር እግዚአብሔር የተናገረው ቃሉን ችላ ከማለትና ካለማስተዋል ይጀምራል። እግዚአብሔር ፈቃዱንና ሃሳቡን የገለጠልን በቅዱስ ቃሉ አማካይነት ነው።እግዚአብሔር የተናገረን እንደአባት ልጆች ለምንሆን ለእኛ ነው።የሚናገረንም እንዳንጠፋና እንዳንቅበዘበዝ በዕረፍቱ ጥላ ሥር እንድንሆን ነው።(ምሳ.1፥33፤ኢሳ.48፥16)እረኛ እንደሌለን በጎች ተጨንቀን ተጥለንም ባየን ጊዜም ያዝንልናል፤ ቃሉንም በየመንደራችን ዞሮ ያስተምረናል።(ማቴ.9፥31) በፊቱም በመታዘዝ በቀረብን ጊዜ ቃሉን እናደምጥ ዘንድ ልባችንን ይከፍትልናል። (ሐዋ.16፥15)

ቃሉን በጸሎትና በማጉተምተም ማንበብና ማጥናት ከምንም በላይ የአንድ ብርቱ ክርስቲያን ትልቅ መገለጫ ነው። ህይወት አልባ ክርስቲያን

ያፈራነው፣ዘፋኝና ጨፋሪ አማኝ ያበዛነው፣ቃሉን ሳያጠኑ በድፍረት የሚሰብኩ አገልጋዮችን በጉያችን ያፈላነው፣ቃሉንና ኃይሉን የማያውቁ በቤቱ ላይ በሰበካ መንፈሳዊ፤ስብከተ ወንጌል ክፍልና ሰንበት ትምህርት ቤት ላይ የሾምነው ቃሉን ከማጥናትና ከማንበብ ባዕዳን ስለሆንን ነው።

በዘመናችን ከምንም ጊዜ በላይ የእግዚአብሔር መጻህፍትና ኃይላቸው የተዘነጋበት ዘመን ነው።የእግዚአብሔር ቃል ወደርና የሚመስለው የለም። መጽሐፍ ቅዱስ እርሱን የሚመስል የሌለው ድንቅና ትልቅ መጽሐፍ ነው። ነገር ግን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል የሚታዩ ወይም በላይ የሆኑ ጥቂት ያይደሉ መጻህፍት አሏቸው።እንደውም ቃሎቻቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃልና እውነት በላይ ይታያሉም። ይህ ነው እንግዲህ መጻህፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል መሳትና አለማወቅ ማለት።

እናም ደቀ መዛሙርቱ ይህን ቃሉን ፈጽሞ ማስተዋል አልተቻላቸውም። ስለዚህም ጌታ “እናንተ የማታስተውሉ ፥ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ...” (ሉቃ.24፥25) በማለት አብዝቶ ወቀሳቸው።አዎ! ከጌታ ክርስቶስ ኢየሱስ ቃል በምናስበልጠው በማናቸውም ቃላችንና ድርጊታችን ይህ ተግሳጽና ወቀሳ ያገኘናል።አለማስተዋል ያደነዘዘልና ካላስተዋልንበት ዘመናችን ዛሬ በቃሉ እውነትና ኃይል እንንቃ።

ጌታ በጉልበቱ ይርዳን።አሜን።

ይቆየን።

Miko ZE Ethiopia

28/ «የእክለክሙ መዋእል ዘሃለፈ ፥ ያለፈው ዘመን ይብቃችኋል» ቅዱስ ያሬድ እና ጀኛ ጴጥሮስ ፱ ፥ ፫- ፱

በመጋቢ ሀዲስ ምስጢረ ስላሴ ማናየ

«የእክለክሙ መዋእል ዘሃለፈ ፥ ያለፈው ዘመን ይብቃችኋል» ቅዱስ ያሬድ እና ጀኛ ጴጥሮስ ፱ ፥ ፫- ፱

በቅድሚያ ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ሉቃስ ያሸጋገረን፤ በመግቦቱ ያልተለየን፤ በችርነቱ የጠበቀን፤ በምህረት አይኖቹ የተመለከተን፤ በብርቱ ክንዶችሁ የደገፈን፤ የዘመናት ባለቤት የፈጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ለዚህ ኣመት ስላደረሰን ክብርና ምስጋና ይድረሰው አሜን።

በቸር አድረን የምንውለው፤ ተኝተን የምንነሳው፤ ሰርተን የምናገኘው፤ ደክመን የምንበረታው፤ ታመን የምንደነው፤ ወድቀን የምንነሳው፤ ከቸርነቱ ከጠባቂነቱ የተነሳ ነው። እግዚአብሔር አምላካችን ሰውን ከድንጋይ እና ከእንጨት ለይቶ በደማዊት ነፍስ ከእንስሳት እና ከአራዊት ለይቶ በህያው ነፍስ አክብሯታል በአርያው እና በአምሳሉም ፈጥሯታል። «ወገብሮ እግዚአብሔር ለእጓለ እመህያው እመሬተ ምድር በአሪያሁ ወበአምሳሊሁ ፤ እግዚብሔር አምላክ ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአርያውና በአምሳሉም ፈጠረው» ዘፍ ፪፥፪፯

የሚኖርበትን ምድርና የሚመገበውን ምግብ አዳምን ከመፍጠሩ አስቀድሞ አዘጋጅቶ ለዘመናትም ልክ ይሆኑት ዘንድ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብትን፣ ክረምትና በጋን፣ መዐልትና ሌሊትን ሰጠው። «እግዚአብሔርም አለ ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ ለምልክቶች፣

ለዘመናት፣ ለእለታትም ለዓመታትም ይሁኑ» ዘፍ ፩፡፲፬

እለታትን በብርሐን እና በጨለማ ለይቶ እለታትን በሳምንታት፣ ሳምንታትን በወራት፣ ወራትን በዓመታት ፣ዓመታትን በዘመናት ተክቶ ለሰው ልጅ ሰፍሮ ለክቶ ይጠቀምበት ዘንድ ሰጠው። ቀን ሳምንት ወር ዓመት የተሰጠው የሰው ልጅ ተግባረ ስጋውን ፤ ተግባረ ነፍሱን እንዲሰራበት ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጠው ስጦታ ሁሉ ዘመን ትልቁ ስጦታ ነው። ዘመን ፀሐይ ነው ለሁሉ ያበራል፤ ዘመን የጨለመበትን ፀሐይ ሊያበራለት አይችልም ከዚህ የተነሳ የቀን ጨለማ ዋጠኝ ይላል። ዘመን አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ካመለጠ፣ ካለፈ የማይመለስ ፤ ቆሞ የማይጠብቅ ፤ በባንክ የማይቀመጥ ፤በተሰጠንበት ጊዜ ብቻ ልንጠቀምበት የምንችል ልዩ ስጦታ ነው።

ዘመን ጎርፍ ነው፤ ጎርፍ ይዞት የማይመጣው የለም ዘመንም እንደዚሁ እድገትን፣ ስልጣኔን፣ እውቀትን፣ ትንሳኤን፣ ማግኘት፣ ማጣትን፣ መሾምን፣ መሻርን፣ መክበርን፣ መዋረድን ብዙ ነገርን ያመጣል። ክፉውን እየተው መልካሙን እየመረጡ ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር የሚያበቃን ርስቱን ለመውረስ፤ ስሙን ለመቀደስ፤ ዘመን የሚያመጣውን ጊዜ የሚወልደውን ክፉ ነገር ለማለፍ በዘመን ሁሉ የሰው ልጅ መንገዱን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ አለበት። ዘመን ከተጠቀሙበት ይጠቅማል ካላወቁበት ግን ያጠፋል ።

በዘመን በንፍር ውሃ ሰዎች አልቀዋል ያወቁበት እነ ኖህ ተርፈዋል፤ ጊዜውን ተጠቅመው መርከብ ሰርተው፤ ትእዛዘ እግዚአብሔርን አክብረው። ዘፍ ፮፥፩ ፣ ዘፍ ፯፥፩ ፣ ዘፍ ፰፥፩ ሙሉውን ማንበቡ ለዚህ በቂ ነው። ለኖህም ለሰብአ ትካትም የተሰጣችው ዘመን እኩል ነው አጠቃቀማቸው ግን

ይለያያል።

አሁን በዘመናችን ዘመን ለሁሉም እኩል ይሰጣል አዲስ ዘመን በመጣ ቁጥር የሰዎች አጠቃቀም ልዩ ልዩ ነው። አዲስ ዓመት ሲመጣ እንደ ሰብአ ትካት ለጭፈራ እና ለዳንኪራ የሚዘጋጁ አሉ፤ ለበደል ለኃጢያት የሚሰለፈውም በዚያው ልክ ነው። ዓለማችን ከትናንት ዛሬ እንደ ብረት ምጣድ እየተቀጣጠለች፤ በጦርነት በጥላቻ እየነደደች፤ ህዝቦቿ ሰላም እየናፈቃቸው ነው። ሰው በቁሙ እንደ በግ ተጎትቶ ሲታረድ በአይናችን አይተናል፤ በጆሮአችን ሰምተናል። ለዚህ ሁሉ ያበቃን በዘመን መጠቀም አለመቻላችን፤ ለንሰሐ ለፍቅር ለመልካም ስራ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ትእዛዙን ለማክበር የሚፈልጉ ሰዎች ቁጥር ማሽቆልቆል ነው። ከዚህ ጊዜ ያደረስከኝ ከደዌ የፈወስከኝ ብሎ ፈጣሪውን ማመስገን የሚገባው ሰው ዘመኑን በከንቱ እያባከነው ይገኛል። «ህይወትን የሚወድ ሰው ማነው? በጎውንም ዘመን ለማየት የሚወድ ማን ነው? አንደበትህን ከክፉ ከልክል ከንፈሮችህም ሸንገላን እንዳይናገሩ ከክፉ ሽሽ መልካምን አድርግ ሰላምን ተከተላትም» መዝ ፴፫፥፲፪

በዘመን የሰዶምና የገሞራ ሰዎች በእሳት ጋይተው ሞተዋል፤ ሎጥ በዛው ዘመን በከተማቸው እየኖረ ከእሳት ድኗል። ለምን ጻድቅ ነበርና። ዘመን አንድ ቢሆን ለሚጠቀምበት እና ለማይጠቀምበት ሁለት ገጽታ አለው። አዲስ ዘመን ሰለመጣ መደሰት መፈንደቅ ለንሰሐ ካልተጠቀምንበት ዋጋ ያጣል። ዘፍ ፮፱፥፯፪ - ፪፱

እስራኤል በዘመን ለግብጽ ተገዝተዋል በዘመን ነጻ ወጥተዋል። ዘመን ለሁሉም ፍጡር ወሳኝ እና አስፈላጊ ነው የባርነት ጊዜአቸውን አሳልፈው፤

ገዢዎቻቸውን ድል ነስተው፤ ባህር ተከፍሎላቸው፤ ደመና ተጋርዶላቸው እና መና ወርዶላቸው ጠላት ጠፍቶላቸው ንሴብሐ ብለው ፈጣሪያቸውን አመስግነዋል።

ዘመን እግዚአብሔር ሳይቀር የቸርነቱን ስራ የሚቆጥርበት አደባባይ ነው «አቡየሂ አስከ ይእዜ ይገብር ወአነሂ ከማሁ እገብር ፤ አባቴ አስከ ዛሬ ይሰራል እኔም አሰራለው» ዮሐ ፭፥፲፯ የሰው ልጅም ያለ ዘመን ምንም ምን ሊሰራ አይችልም። ዘመንን የሰው ልጅ በወርቅ በብር በልዩ ልዩ አልማዝ ሊገዛው አይችልም። በዘመን ግን ሁሉንም የፈለጋችውን በመዳፉ ማስገባት፤ ገንዘብ ማድረግ ይችላል፤ ቢወድቅ ይነሳል፤ ቢያጣ ያገኝል፤ ጠላት ቢነሳበት በዘመን ያልፋሉ ።

ዘመን ከእግዚአብሔር በታች ከባለስልጣናት ሁሉ በላይ ፈራጅ እና ወሳኝ ነው። ሰዎች በዘመናቸው የወሰኑትን እና ያቀዱትን የሠሩትን፤ ፈላስፎች የተራቀቁበትን ዘመን ይሸረዋል። ሁሉም ፍጡራን እና ሥራዎቻቸው ሁሉ በዘመን ይተካሉ፤ በዘመን ያልፋሉ። ስለዚህ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ አዲስ ዓመት ይባላል። ሰው በንሰሐ ከኃጢአት ፤ ተግቶ በመሥራት ከስርቆት ከስንፍና የሚታደስበት፤ ጊዜው ያመጣለትን ሥራ ለመሥራት የሚፋጠንበት መሆን ይገባዋል። መባከን የለበትም ልዩ ስጦታ ነውና። ዘመን እንደ ነፋስ ፈጣን ነው፤ አንድ ጊዜ ታይቶ እንደሚጠፋበት ጥላ ነው። «ሰው ከንቱ ነገርን ዘመኑም ይመስላል ዘመኑ እንደ ጥላ ያልፋል» መዝ ፻፵፫ ፥፬

«ሺ አመት በፊት እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን እንደ ሌሊትም ትጋት ነውና ዘመኖቹ የተናቁ ይሆናሉ። በማለዳም እንደሳር ያልፋል ማልዶ ያብባል

ያልፋል በሰርክም ጠውልጎ እና ደርቆ ይወድቃል። እኛ በቁጣህ አልቀናል በመአትህም ደንግጠናል። በደላችንንም በፊትህ አስቀመጠህ ዘመናችን ሁሉ አልፏልና እኛም በመአትህ አልቀናልና ዘመኖቻችንም እንደ ሸረሪት ድር ይሆናሉ። የዘመኖቻችን እድሜ ሰባ ዓመት ቢበዛም ሰማኒያ ዓመት ነው፤ ቢበዛ ግን ድካምና መከራ ነው» መዝ ፹፱፥፫-፲

በዘመን ጥላ ስር የማያልፍ ማንም የለም ሰው ይቅርና ዘመን የማይቆጠርለት መለኮት በስጋ ዘመን ተቆጥሮለታል፤ ፴ አመት ሆነው ተብሎ። ሰው ሁሉ በዘመን ማህጸን ይጸነሳል ይወለዳል ያድጋል፤ የተወሰኑለትን ዘመን ተጠቅሞ ፈጣሪውን ቢያገለግል ዘመን የማይሽረው ጊዜ የማይለውጠው ክብር ያገኛል። ማለት መንግስተ ሰማያት ይገባል፤ ካገኙ ማጣት ከገቡ መውጣት የሌለበት ህይወት መላእክትን መስሎ ይኖራል። በእርግጥ ጥንተ ዘመን የሌለዉ ኋላም ዘመኖቹ የማያልቁበት የማይለውጡት እግዚያአብሔር ብቻ ዘመናት በርሱ ይወጣሉ በርሱ ያልፋል እርሱ ግን ለማይቆጠሩ ዓመታት እና ዘመናት ይኖራል። «የዘመኔን አነስተኝነት ንገረኝ፤ በዘመኔ እኩሌታ አትውሰደኝ፤ ዓመቶችህ ለልጅ ልጅ ናቸው። አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሰረትክ ሰማያትም የጅህ ስራ ናቸው፤ አነርሱ ያልፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁላቸው አንደ ልብስ ያረጃሉ አንደ መጎናጸፊያ ትለውጣቸዋለህ። አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤ አመቶችህም ከቶ አያልፉም።» መዝ ፻፩፤፪፬-፪፷

ዘመን ከውቂያኖስ ይልቅ እጅግ ሰፊ ነው። በውቂያኖስ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ ፍጥረታት የበለጡ አና የበዙ ፍጥረታት በዘመን ውስጥ ይኖራል። ዘመን ከእግዚያብሔር በታች ለሁሉም አስፈላጊ ነው። ለዚህ ነው ጥበበኛው

ሰሎሞን አንዲህ ያለው «ለሁሉ ዘመን አለው ከሰማይ በታች ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለዉ» መክ ፫፤፩

ከዚህ የተነሳ የሰው ልጅ የተሰጠዉን ጊዜ በዋዛ በፈዛዛ ከማሳለፍ የተነሳ ተዘጋጅቶ ዕለተ ሞትን አያሰበ እግዚያብሔርን እያከበረ ሊኖር ይገባዋል። በከቱ ያሳለፉቸው ዘመናት ይበቃሉ። ቅዱስ ጴጥሮስ «ያለፈው ዘመን ይብቃችሁ» ያለው ዘመኖቹ ክፎዎች ናቸውና ሰው እራሱን መጠበቅ አለበት። «መንፈስ ግን በግልጽ በኋላኛው ዘመናት አንዳንድ የሚያስቱ መናፍስትና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንት ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ።» ፩ጢሞ ፬፥፩-፫

«ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን አንዲመጣ እወቅ ሰዎች እራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ። ገንዘብ የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትእቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ እርቅን የማይሰሙ፣ እራሳቸውን የማይገዙ፣ ሃሜተኞች፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ ይሆናል። »፩ጢሞ፫፥፩-፱

እነዚህ በሙሉ አሁን ያለንበትን ዘመን የሚያምለክቱ ናቸው። ሰው ሁሉ በእነዚህ እንደ ብራና ተወጥሯል፤ ሚች መሆኑን ረስቷል፤ ኃጢያት ሠርቶ አይጠግብም ።«ያለፈው ዘመን ይብቃችሁ»

«ወይእዜኒ በጽሃ ጊዜሁ ለነቂህ እምነዋም ኀለፈት ሌሊት ወመጽአት መዓልት ወንግድፍ እምላእሌነ ምግባረ ጽልመት ወንልበስ ወልታ ብርሃን ከመናንሰሉ በምግባረ ፅድቅ፤ ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ ካመንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ

ቀርቧል፤ ሌሊት አልፏል፤ ቀኑ ቀርቧል፤ እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃን ጋሻ ጦር እንልበስ፤ በቀን እንደምንሆን በአግባቡ እንመላለስ። በዘፈንና በስካር በዝሙትና በመዳራት አይሁን፤ በክርክር እና በቅናት አይሁን»ሮሜ ፲፫፥፲፩

«ያለፈው ዘመን ይብቃችሁ» በኃጢአት፣ በርኩሰት፣ በጠብ፣ በክርክር፣ በቂም፣ በቀል፣ በስካር ያለፈው ይብቃ። የተቀበልነው ዓመት የሰላም፣ የጤና፣ የብልፅግና የንስሐ ያድርግልን።

«ያለፈው ዘመን ይብቃችሁ»

ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘሃሎ በአርያም

ወለወላዲቱ ድንግል ማርያም

ወለመስቀሉ ክቡር ዕፀ ፍቅር ወሰላም

አሜን

Rodas Tadese Abebe

29/ ዕለተ ምጽአት

በመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

ክብር ይግባውና ጌታችን ዓለምን ለማሳለፍ ሙታንን ለመስነሣት ዳግመኛ ለፍርድ ሲመጣ ከርሱ ጋር መላእክቱ ዐብረውት እንደሚመጡ በማቴ 16፡ 27 ላይ “የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል” በማለት ሲያስምር፡- ዳግመኛም ከመምጣቱ በፊት በዓለም ላይ ስለሚመጣው ስለምልክቱ በተለይም የሐሳዌ መሲሕ መንገድ ጠራጊ በመኾን በኢየሱስ ስም በዓለማችን ስለሚመጡ በጣም ብዙ ስለኾኑ ስለሐሰተኞች መናፍቃን ምንፍቅና ክሕደት በዓለም ላይ ስለሚመጣው መከራ በስፋት በደብረ ዘይት ላይ ካስተማረ በኋላ በማቴ 24፡29-31 ላይም “ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሓይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ የሰማያትም ኀይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ኹሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኀይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ” በማለት በታላቅ ግርማ ስለሚደረግ ምጽአቱ አስተምሯል።

ክብር ይግባውና ጌታችን ዓለምን ለማሳለፍ እንደሚመጣ ሙታንን እንደሚያስነሣ በዘመነ ሥጋዌዉ በስፋት ሲያስተምር በተግባርም የዕለት ሬሳ የኾኑትን የኢያኢሮስን ሴት ልጅ፤ የመበለቲቱን ልጅ፤ እና ከሞተ አራት ቀን የሞላውን አልዓዛርን ከሞት አስነሥቶ አሳይቷል፤ በዮሐ 5፡28-29 ላይ “በመቃብር ያሉት ኹሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካምም ያደረጉ ወደ ሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ”

በማለት አስተምሯል።

ወደ ቢታንያ አውጥቶ ደቀ መዛሙርቱን በአንብሮተ እድ ባርኮ በክብር በምስጋና ሲያርግ ሐዋርያት በናፍቆት ኾነው ሲመለከቱት ቅዱሳን መላእክት “የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደሰማይ እየተመለከታችኁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይኽ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲኼድ እንዳያችኹት፥ እንዲኹ ይመጣል” (የሐዋ 1፡11) በማለት ዳግም ዓለምን ለማሳለፍ እንደሚመጣ መስክረዋል።

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ አትናቴዎስም ስለዚኽ ነገር በቅዳሴው ላይ፦

“አሜሃ መቃብራት ይትከሠታ ወሙታን እለ በልዩ ዘእምዓለም ይትነሥኡ ከመ ቅጽበተ ዐይን...” (ያን ጊዜ መቃብራት ይከፈታሉ ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ የፈረሱ ሙታን ፈጥነው እንደ ዐይን ጥቅሻ ይነሣሉ፤ አብ መንግሥቱንና ፍርዱን ለልጁ ይሰጣል፤ ያን ጊዜ ዐዲስ የመብረቅ ጎይል ይታያል፤ ግሩም የሚኾን የነጐድጓድም ቃል ይሰማል፤ ከመዠመሪያ (ከጥንት) ዠምሮ ዠሮ ያልሰማው ዐይንም ያላየው፤ የእሳት ክንፎች ያሏቸው ግሩማን መላእክት በፊቱ ይቆማሉ፤ ስም የሌላቸው እገሌና እገሌ የማይሏቸው በአብ መጋረጃ ፊት የሚኖሩ ባለሟሎች መላእክት ናቸው፤ የሊኽም ክንፍ ከክንፍ ጋራ ይሳበቃል ይሰማሉ ያንጐደጕዳሉ ሰይፋቸውንም ይመዝዛሉ የጽናታቸውን ጎይል ያሳዩ ዘንድ ይበርራሉ፤

ያን ጊዜ የእሳት ባሕር እስከ መሠረቷ ትገለጣለች፤ በበታቿ ያለ የውርጭ ነጐድጓድም የእሳት ወንዝም ይፈስሳል፤ ኹሉ ተጠብቆለት ያለውን ያይ ዘንድ፤ ያን ጊዜ መጻሕፍት ይገለጣሉ ሥራም ይገለጣል አንደበትም ዝም ይላል የተከፈተ አፍም ድዳ ይኾናል፤ ፍጥረቱም ኹሉ በመፍራት

በመንቀጥቀጥ በታላቅ ጸጥታም ይቆማሉ፤ ምድር ኹላ ከእግር መኼጃ ልክ በቀር አትበቃም ኹሉም እንደ ጽፍቀተ ሮማን ይጨናነቃል፤ ያን ጊዜ ጥቁርና ቀይ ዐጪርና ረዢም የለም አንድ አካል አንድ መልክ ነው እንጂ፤

ያን ጊዜ የነፍስ ቤዛ የለም ወንድ በሚስቱ መለወጥም ቢኾን አባት በልጁ እናትም በልጇ አንዱም አንዱ የሥራውን ፍዳ ይቀበላል እንጂ፤ ባለጸጋውን ስለ ባለጸጋነቱ አያፍረውም እንደ ተገመገመለት ነው እንጂ፤ ለድኻውም ስለ ድኽነቱ አይራራለትም ርሱን ደስ ካላሰኘው፤ ያን ጊዜ ጻድቃን ደስ ይላቸዋል፤ በሕይወታቸው አልቅሰዋልና፤ ኃጥኣን ያለቅሳሉ ሣቅንና ሥላቅን ስለ ወደዱ የፍርድና የፍዳ ቀን ደርሳባቸዋለችና፤

ያን ጊዜ ባለጸጎች ይደኸያሉ ተድላ ደስታቸውን በዐመፅ ጨርሰዋልና፤ ነዳያንም ባለጸጎች ይኾናሉ ንዴታቸውን በምስጋና ተቀብለዋልና፤ ያን ጊዜ ተርበው የነበሩ ይጠግባሉ በሕይወታቸው ተቸግረው ነበሩና፤ ያን ጊዜ ተናጋሪዎች የነበሩ ዝም ይላሉ ከንቱና ብላሽን ነገር ተናግረዋልና፤ ትዕግሥተኞች የነበሩ ይናገራሉ አንደበታቸውን ወደ ሐሜት ይርጥ ዘንድ አልተዉትምና ባልንጀራቸውንም ፈጽሞ አላሰዘኑምና፤

ያን ጊዜ ጽኑዓን የነበሩ ይደክማሉ ሥጋቸውን በዝሙት አድክመዋልና፤ ደክመው የነበሩት ይጸናሉ ኀይላቸውን በሰጊድ በመዓልትና በሌሊትም በመትጋት አድክመዋልና፤ ያን ጊዜ ኀያላን ልምሾ ይኾናሉ እጃቸውን ለመቀማት ዘርግተዋልና፤ ባልቴትንና አባት እናት የሞቱበትን አስለቅሰዋልና፤ ያን ጊዜ የተናቁት እንደ አንስርት ይበራሉ ክንፎቻቸውም ይወጣሉ ጕልማስነታቸውም ይታደሳል (ኢሳ ፵፥፴፩)፤

ያን ጊዜ ትዕቢተኞችና ኵሮች ይገለጻሉ ኀፍረታቸውም ይገለጻልና፤ ያን ጊዜ

የተራቈቱት ይለብሳሉ የዝናምና የጠል ካፊያ አርሷቸዋልና ብርድና ውርጭ አስቸግሯቸዋልና የፀሓይ ሐሩርም አቃጥሏቸው ነበርና፤ ያን ጊዜ ንጉሥ አድልዎ በሌለበት በቅን ፍርድ ይፈርዳል፤ ያን ጊዜ ኃጥኣን ከጻድቃን መኻከል ይለያሉ፤ ርኩሳንም ከንጹሓን መኻከል ይለያሉ፤ የዚያን ጊዜ አውያት የዚያን ጊዜ ጩኸት የዚያን ጊዜም ልቅሶ ምን ያኽላል ርሱ ቅሉ ፈጣሪ ወደ ጥፋት መንገድ ሲኼዱ ባያቸው ጊዜ እጁ ስለ ፈጠራቸው ፍጥረቶቹ እስኪያለቅስ ድረስ፤ ያን ጊዜ ኃጥኣን ስለ ራሳቸው ያለቅሳሉ ጻድቃንም ስለ ዘመዶቻቸው ያለቅሳሉ የሰማይ መላእክትም ስለ ሰው ፍጥረት ያዝናሉ፤ ኹሉ ከተፈጸመ በኋላ ያን ጊዜ ለመረጣቸው ለወዳጆቹ ለጻድቆቹ የብርሃን ድንኳን ይተከላል ሰባት መሰወሪያ ያለው የእሳት መጋረጃ ይዘረጋል፤ የካህናት አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስም ከዚያ ወደዚኽ ምስጢር ይገባል፤ ለግብር ሥራት ቀሳውስትን በቀኙ ዲያቆናትንም በግራው ያቆማቸዋል፤ የምስጢርን ሥራት ያሳያቸው ዘንድ፤ ምን ይመስላል? ስሙስ ምንድር ነው? የዚያን ጊዜውስ ምስጢር ምን ይባላል? ዛሬ ሊናገሩት አይቻልም በሰው ልቡናም የለም) በማለት ዓለም ሲያልፍ ሙታን ሲነሡ ያለውን የግርማውን ታላቅነት አስተምሯል።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማሳለፍ ሲመጣ በበግ የተመሰሉ ጻድቃንን በቀኝ በፍየል የተመሰሉ ኃጥኣንን በግራ እንደሚያቆማቸው ራሱ ጌታችን በማቴ 25 ላይ አስተማረ። ጌታችን ሲመጣ በግና ፍየልን ለይቶ እንዲያቆም ያቆማቸዋል ቢሉ ለይቶስ አያቆማቸውም ግብራቸው ይመራቸዋል እንጂ “እስመ ስሙ ይመርሐ ኀበ ግብሩ” እንዲል፤ ደግሞም ምሳሌ አላቸው የበግና የፍየል ግልገል ከቤተ

ታሥረው ይውላሉ፤ እናቶቻቸው ሲመጡ ይለቋቸዋል፤ የበጊቱ ግልገል ወደ እናቷ ትኼዳለች እንጂ ወደ ፍየሊቱ አትኼድም፤ የፍየሊቱ ግልገልም ወደ እናቷ ትኼዳለች እንጂ ወደ በጊቱ አትኼድም እንደዚኹ ኹሉ ጻድቃንም ተነሥተው በቀኝ ቢቆሙ እንጂ በግራ አይቆሙም ኃጥኣንም ተነሥተው በግራ ቢቆሙ እንጂ በቀኝ አይቆሙም።

ምነው ጻድቃን በቀኝ ይቆማሉ ቢሉ ምሳሌያቸው ነውና፤ ቀኝ ቅን፣ፈጣን፣ ብርቱ ነው ጻድቃንም ሃይማኖት ለመማር ምግባር ለመሥራት ቅኖች፣ ፈጣኖች፣ ብርቱዎች ነበሩና ነው። ምነው ኃጥኣን በግራ ይቆማሉ ቢሉ ምሳሌያቸው ነውና፤ ግራ ጠማማ፣ ዳተኛ፣ ሰነፍ ኃጥኣንም ሃይማኖት ለመማር ምግባር ለመሥራት ጠማሞች፣ ዳተኞች፣ ሰነፎች ነበሩና ነው። አንድም የማን ማለት ክብር ጸጋም ማለት ጎሣር ማለት ነውና ጻድቃን በክብር ኃጥኣን በጎሣር ይኖራሉ ሲል ነው።

ስለምን ጻድቃንን በበጎች መሰላቸው ቢሉ በጎች በዘመነ ኦሪት ለመሥዋዕተ ነግኅ ለመሥዋዕተ ሰርክ ይቀርቡ ነበር የጻድቃንም ጸሎት በየጊዜው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይደርሳልና፤፤

አንድም በጎች በደጋ እንጂ በቆላ አይኖሩም ጻድቃንም በመከራ ሥጋ እንጂ በተድላ በደስታ አይኖሩምና፤፤

አንድም የበግ ሥጋ ይጣፍጣል ደዌ አይቀሰቅስም የጻድቃንም ጸሎት በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ የተስማማ ነውና፤፤

አንድም በጎች ጥቂት ሳር ቢያገኙ ርስ በርሳቸው ተስማምተው ይበሉታል ይፈቃቀራሉ፤ ጻድቃንም ጥቂት ገንዘብ ቢያገኙ ከሌሎች ጋር በፍቅር ተካፍለው ይበሉታልና፤፤

አንድም የበጎች ጸጉር ለብዙ ነገር ይኾናል የጻድቃንም ጸሎት ለኹሉ ይጠቅማልና፤፤ አንድም በጎች ጭቃውን አይጸየፉትም ጻድቃንም በሃይማኖት ምክንያት የሚመጣውን መከራ አይሰቀቁትምና፤፤

አንድም የበጎች ላታቸው የወደቀ ጎፍረታቸው የተሰወረ ነው የጻድቃንም የግል ጎጢአትን በንሥሓ የወንድማቸውን ጎጢአት በትዕግሥት ይሰውራሉና፤፤

አንድም በጎች አቄልቊለው እንጂ አሻቅበው አያዩም ጻድቃንም ሞትን ገሃነምን ዐስበው በትሕትና በመንኖ ጥሪት ይኖራሉ እንጂ እንሾም እንሸለም በማለት በፍቅረ ንዋይ አይኖሩምና፤፤

አንድም ከበጎች ውስጥ አንዷን ዐውሬ የነጠቃት እንደኾነ "በግ ከበረረ የሰው ልጅ ከተመረረ" እንዲሉ በረው በረው ከዱር ይገባሉ ይቀራሉ፤ ከገቡም በኋላ እንዳይመለሱ ጻድቃንም ከባልንጀራቸው የሞተባቸው እንደኾነ ትላንት እንደኛ ሰው ነበር አኹን ሥጋው ወደ መሬት ገባ ነፍሱም አምላኳ ፊት ቀረበች በማለት "ጎድግዎ ወመንንዎ ለዝ ዓለም" ብለው ዳዋ ጥሰው ደንጊያ ተንተርሰው ግርማ ሌሊቱን ድምፀ አራዊቱን ጸብዐ አጋንንቱን ችለው ታግሰው ይኖራሉና፤ ከመነኑም በኋላ አይመለሱምና ጻድቃንን በበጎች መሰላቸው።

ስለምን ኃጥኣንን በፍየል መሰላቸው ቢሉ፤ ፍየሎች በቆላ እንጂ በደጋ አይኖሩም ጎጥኣንም በተድላ ሥጋ እንጂ በመከራ ሥጋ (በጾም በጸሎት በትሕርምት) አይኖሩምና፤ ዳግመኛም ኑሯቸው በቆላ በተመሰለ ገሃነም ነውና፤

አንድም የፍየል ሥጋ ደዌ ይቀሰቅሳል የጎጥኣንም ምግባር በሰውና

በእግዚአብሔር ዘንድ ያልተስማማ ነውና፤፤

አንድም ፍየሎች እረኛቸው ባሰማራቸው ቦታ ረግተው አይኖሩም ጎጥኣንም ቤተ ክርስቲያን ባስተማረቻቸው መልካም ምግባር ጸንተው አይኖሩምና፤፤

አንድም ፍየሎች የማይበሉት ቅጠል የለም ጎጥኣንም የማይሠሩት ጎጢአት የለምና፤፤

አንድም ፍየሎችን እረኛቸው ከብዙ ሳር ከብዙ ቅጠል ቢያሰማሯቸው ያነን ትተው ከሰው እኽል እየገቡ እረኛቸውን ሲያሳዝኑ ይኖራሉ፤ ጎጥኣንም መምህራነ ወንጌል ያስተማሯቸውን የቀና ትምህርት ትተው ሲሰርቁ፣ ሲቀሙ፣ ሕግ ሲያፈርሱ ይኖራሉና፤፤

አንድም ፍየሎች ብዙ ሳርና ቅጠል ቢያገኙ ተስማምተው አይበሉም ሲዋጉ፣ ሲያጉረመርሙ ሲጋደሉ ይኖራሉ ጎጥኣንም የዓለሙን ኹሉ ገንዘብ ቢሰጡዋቸው ተስማምተው አንበላም ብለው በራስ ወዳድነት ሲዋጉ ሲጋደሉ ይኖራሉና፤፤

አንድም ፍየሎች ጭቃውን ይጸየፉታል ጎጥኣንም በሃይማኖት ሲኖሩ የሚመጣባቸውን መከራ ሥጋ ይሰቀቁታልና፤፤

አንድም ፍየሎች ጅራታቸው የተሰቀለና ጎፍረታቸው የተገለጠ ነው ጎጥኣንም የራሳቸውን ጎጢአት በንሥሓ የወንድማቸውን ጎጢአት በትዕግሥት አይሠውሩትምና፤፤

አንድም ፍየሎች አሻቅበው እንጂ አቈልቍለው አያዩም ጎጥኣንም በፍቅረ ንዋይ ተታልለው እንሾም እንሽለም እንጂ ይላሉ እንጂ ሞትን ገሃነምን አያስቡምና፤፤

አንድም ከፍየሎች አንዷን ዐውሬ የነጠቀ እንደኾነ ለጊዜው ይሸሻሉ ኋላ

ግን ተመልሰው ወደርሱ እንደገና ይሰበሰባሉ፤ ነብርም አንድ አንዱን ነጥቆ ይፈጃቸዋል ጎጥኣንም ከባልንጀራቸው አንዱ ቢሞት ለጊዜው ልብሰ ጎዘን ይለብሳሉ፣ ያለቅሳሉ ያነባሉ ወዲያውን ግን የባልንጀራቸውን ሀብት ንብረት ርስት ለመውረስ ርስ በርሳቸው ሲጋደሉ ይኖራሉና ጎጥኣንን በፍየል መስሏቸዋል።

በፍየል የተመሰሉት ሕጉን ያላከበሩ ከእውነተኛዋ ሃይማኖት የወጡ ከምግባረ ጽድቅ ያፈነገጡ ሰዎችን ባለቤቱ ክርስቶስ በዕለተ ምጽአት "እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ኺዱ" ብሎ ዘላለማዊ መከራ ያለባትን ገሀነመ እሳትን የሚያወርሳቸው ሲኾን፤ ዮሐንስም በራእዩ ላይ "ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ፤ ታላቅና ነጭ ዙፋንን በርሱም ላይ የተቀመጠውን አየኑ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም፤ ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየኑ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ ርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ፤ ባሕርም በርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፤ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፣ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ፤ ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ፤ ይኽም የእሳት ባሕር ኹለተኛው ሞት ነው፤ በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ" (ራእ ፳) በማለት በዲያብሎስ መንገድ የኼዱ ኃጥኣን ከሞት ተነሥተው በዚኽ ጊዜ ያልፋል

ይጠፋል የማይባል የዘላለም ቅጣት እንደሚያገኛቸው ጽፏል።

ንጉሠ ሰማይ ወምድር ክርስቶስ በበግ የተመሰሉ ለቅዱሳኑ “እናንተ የአባቴ ቡሩካን ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ ያለውን መንግሥተ ሰማያትን ትወርሱ ዘንድ ወደኔ ኑ” በማለት መንግሥተ ሰማያትን የሚያወርስ ሲኾን ዮሐንስም ይኽቺን ዓለም አሳልፎ ለወዳጆቹ በዕለተ ምጽአት ስለሚያወርሳት መንግሥተ ሰማያት ተገልጾለት በራእዩ ላይ፦

“ፊተኛው ሰማይና ፊተኛዪቱ ምድር ዐልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም ቅድስቲቱም ከተማ ዐዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባሏ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየኹ ታላቅም ድምፅ ከሰማይ እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መኻከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይኾናሉ፤ እግዚአብሔርም ርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ኾኖ አምላካቸው ይኾናል፤ እንባዎችንም ኹሉ ከዐይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲኽ ወዲኽ አይኾንም፥ ሐዘንም ቢኾን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲኽ ወዲኽ አይኾንም፥ የቀደመው ሥርዐት ዐልፏልና ብሎ ሲናገር ሰማኹ ...ለከተማዪቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራቷም በጉ ስለ ኾነ፥ ፀሓይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም ነበር፤ አሕዛብም በብርሃኗ ይመላለሳሉ፥ የምድርም ነገሥታት ክብራቸውን ወደ ርሷ ያመጣሉ፤ በዚያም ሌሊት ስለሌለ ደጆቿ በቀን ከቶ አይዘጉም፤ የአሕዛብንም ግርማና ክብር ወደ ርሷ ያመጣሉ፤ ለበጉም በኾነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር፥ ጸያፍ ነገር ኹሉ ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ ርሷ ከቶ አይገባም” በማለት ጻድቃን ከሞት ተነሥተው በዕለተ ምጽአት ስለሚወርሷት መራብ፣

መጠማት፣ መጨነቅ፣ ሕማም ሞት እርጅና ስሌለባት ስለመንግሥተ ሰማያት ገልጽዋል።

አዘጋጅ፡- መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

አቤቱ ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ዓለምን ለማሳለፍ በታላቅ ግርማ ዳግመኛ ስትመጣ ሙታንን ስታስነሣ ከቅዱሳንኽ ጋር በቀኝ እንድታቆመን እንለምንኻለን። አሜን —

Miko ZE Ethiopia

30/ የምእመናን ድርሻ በቤተ ክርስቲያን

መግቢያ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በተለያየ ጊዜ ካህናት እና ምእመናን የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት በተባለች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊኖሩ እንደሚገባ ድርሻቸውም ምን እንደሆነ ያስተምራቸው ነበር:: ለምሳሌ የመንፈስ ልጁ የሆነ ቅዱስ ጢሞቴዎስን በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት ሲኖር ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲህ በማለት መክሮታል:-"በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም የእውነት ዐምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው::" (1 ጢሞ 3፥15)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቅዱስ ጢሞቴዎስን ብቻ ሳይሆን ሁላችንን እንዴት መኖር እንደሚገባን መክሮናል:: ለአብነት ያህል የሚከተሉትን

እንመልከት:- "እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ ... ልከኛ፥ ራሱን የሚገዛ፥ እንደሚገባው የሚሠራ፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ለማስተማር የሚበቃ ፥ የማይሰክር፥ የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ፥ የማይከራከር፥ ገንዘብን የማይወድ። (1ጢሞ 3 : 2-3) በማለት ኤጲስ ቆጶሳትን የመከረ ሲሆን፤ ዲያቆናትን ደግሞ "እንዲሁም ዲያቆናት ጭምቶች፥ በሁለት ቃል የማይናገሩ፥ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገመጁ፥ ነውረኛ ረብ የማይወዱ፥ በንጹሕ ሕሊና የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል::" (1ጢሞ 3 : 8-9) በማለት መክሯል:: ስለ ምዕመናንንም "እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ ፣ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ፣ መልካምን እንዲያደርጉ በበጎም ሥራ ባለጠጎች እንዲሆኑ፣ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው::" (1ጢሞ 6 : 18-19) ሲል ለጢሞቴዎስ ጽፎለታል ::

የእውነት ዓምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የተባለች መጠለያችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተመስርታ ፣ በቅዱሳን ተጋድሎና ሰማዕትነት ከብራ፣ በካህናትና ምእመናን አንድነት ጸንታ ላለንበት ዘመን ደርሳለች:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሥጋ ልደታችን 40ኛ እና 80ኛ ቀን ጀምሮ የምንኖርባትና ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልገሎት የምናገኝባት ቤታችን ናት:: በጥምቀት የእግዚአብሔር ልጅነትን ያገኘንባት ፣ በወንጌል የምንታነጽባት፣ ዝማሬ የምናቀርብባት፣ በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ ሕይወት የምናገኝባት፣ በአብርሃምና ሳራ ሕይወት ለመኖር ብንወስን በቅዱስ ጋብቻ

የምንከብርባት፣ በእንጦንስና በጳውሊ ሕይወት ለመኖር ብንወስን በምንኩስና እና በብህትውና የምንከብርባት ቤታቸን ናት:: ስለእኛ ከእመቤታቸን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስን ነስቶ የተወለደበትን ልደቱን፣ እንዲሁም የከበረ ጥምቀቱን፣ መከራ መስቀሉን፣ ሞቱን እና ትንሣኤውን ፣ዕርገቱንና ዳግም ምጽአቱን እያዘከርን በረከት የምናገኝባት ቤታችን ናት:: ስለ ስሙ የተጋደሉና ሰማያዊ አክሊል የተቀዳጁ በዘለዓለም ሕይወት የከበሩ ቅዱሳንን ስማቸውን ጠርተን ፣ በታቦታቱ ተማጽነን፣ በሥዕላቸው ተማጽነን ፣ በጸበላቸው ተፈውሰን በማይመረመር መንፈሳዊ በረከት የምንኖርባት የእውነት ቤት ናት:: ከልደት እስከ እርግና ቆይተንባት በሞታችንም ጊዜ ሥጋችን የሚያርፍባት ነፍሳችንም በጸሎተ ፍትሐት ወደዚያኛው ዓለም የምንሸኝባት የመጨረሻ ማረፊያችን ናት:: ከሞት በኋላ ስመ ክርስትናችን እየተወሳ በጸሎት የምንታሰብባት ጽድቅን የምናገኝባት አማላጃችን ሕያዊት የእግዚአብሔር ቤት ናት:: ለዚህ ነው ልበ አምላክ የተባለ ቅዱስ ዳዊት ቤተ ክርስቲያንን "ይህች የእግዚአብሔር ደጅ ናት ፤ ወደ እርስዋም ጻድቃን ይገባሉ::" (መዝ 117:20) ብሎ በሚገባ የገለጻት:: ይህ የብዙ ዘመናት የተቀደሰ መንፈሳዊ በረከትን የመቀበል ሕይወት ቀጣይነቱ ዘላቂ እንዲሆን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፍሬ የሆንን ካህናትና ምእመናን ተገቢ ድርሻችንን መወጣት ይጠበቅብናል:: እንኳን በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት ይቅርና በየግላችን ጎጆ ስንኖር እንዴት መኖር እንዳለብን ካልተረዳን አወዳደቃችን የከፋ ይሆናል:: ጎጆአችንም በላያችን ላይ ይፈርሳል:: ስለዚህም በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት እንዴት እንኑር እያልን? የመጻሕፍትን

ምስጢር መመርመር፣ በቤቱ ጸንተው ለዘለዓለም ሕይወት የበቁትን ቅዱሳን ገድል በማንበብ፣ በመስማትና ከሕይወት ልምዳቸው ትምህርት በመውሰድ፤ እነርሱንም በመምሰል የሚጠበቅብንን ድርሻ በመወጣት ልንኖር ይገባናል::

የዚህ መልእክት ዓላማ የቤተ ክርስቲያን ዕንቁ የተሰኘን ምእመናንን በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት ያለንን ድርሻ ማሳየት በመሆኑ በዚሁ ላይ ያተኩራል::

የምእመናን ድርሻ በቤተ ክርስቲያን ዘርፈ ብዙ ቢሆንም ዓበይት የሆኑትን በዚህ ጽሑፍ እንቃኛለን:-

1. የክርስትና ሕይወት የሚጠይቀውን ምግባር በማከናወን አርአያ ሆኖ መኖር:-

ከሁሉ አስቀድሞ በቤተ ክርስቲያን ጥላ ስር የተሰባሰብን ምዕመናን በውጭ ካሉት የሚለየን ክርስቲያን የሚለው የከበረ መጠሪያ ስማችን ብቻ ሳይሆን ስሙ የሚጠይቀውን ቤተ ክርስቲያን ያቆየችልንን ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ወይም ሕይወት መተግበርና መኖር መቻላችን ነው:: ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ልጅነትን ክብር በጥምቀት ወይም ከውኃና ከመንፈስ በመወለድ ያገኘን ምእመናን ልጅነታችንን የሚያረጋግጥ መንፈሳዊ ሕይወትን መኖር ይጠበቅብናል:: አይሁድ የአብርሃም ልጆች ነን በማለት ዋጋ እንዳላገኙ ሁሉ ክርስቲያን ነን ማለታችን ብቻውን ዋጋ አያስገኝልንም:: ለመዳን ከአይሁድ ተሽሎ ከፈሪሳውወያን በልጦ ከአጋንንት ማታለል ወጥመድ ተጠብቆ መገኘት ያስፈልጋል:: የእውነተኛ ክርስትና መገለጫው ሥነ ምግባር ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ "ምግባር የሌለው ሃይማኖት በራሱ የሞተ ነው::" (ያዕ 2፣ 17) እንዳለ:: ስለዚህ ዕለት

ዕለት በጸሎት የምንተጋበት፣ ለንስሐ የምንፈጥንበት፣ በአገልግሎት የምንበረታበት፣ በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ ታንጸን የምንኖርበት ሕይወት ሊኖረን ያስፈልጋል:: በሥነ ምግባር ያጌጠ የክርስትና ሕይወት ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ያሉትን ኢአማንያን በምግባር በመስበክ ወደ ውስጥ ለማስገባት በውስጥ ሆነው የደከሙትን ደግሞ ለማበርታት አርአያነቱ ታላቅ ነውና ቀዳሚ ድርሻችን ይህንኑ ማጠናከር ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን::" (1 ጢሞ 4፣ 11-12) እንዳለ ትህትናን እና የዋህነትን ከጥበብ ጋር በመልበስ የፍቅርን ብርሃን በቤታችን፣ በጎረቤታችን፣ በሥራ ገበታችን እንዲሁም ለመንፈሳዊ በረከት በምንሰበሰብባት ቤተ ክርስቲያናችን በማብራት ሌሎች በሕይወታችን ተማርከው በቤተ ክርስቲያን ጥላ ስር እንዲሰባሰቡና ለዘለዓለም ሕይወት እንዲበቁ ምሳሌ መሆን ከእኛ ይጠበቃል::

2. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል:-

የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሀብቶች የሆንን ምእመናን እግዚአብሔር በሰጠን ልዩ ልዩ ጸጋ ቤተ ክርስቲያንን በትጋት ማገልገል ይጠበቅብናል:: ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ "እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን... አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ::" (ሮሜ 12: 7) በማለት በግልጥ አስተምሮናል::በሰንበት ትምህርት ቤት ፣ በአውደ ምሕረት ጉባኤያትና፣ በሰበካ ጉባኤ ከሚጠበቅብን ሰፊ የአገልግሎት ድርሻ በተጨማሪ ፤

በየተሰለፍንበት የትምህርትና የሞያ ዘርፍ ከዓለም የቀሰምነውን ጠቃሚ ዕውቀት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማዋል ታላቅ በረከት የምናገኝበት ድርሻችን ነው:: አብዛኞቻችን አገልግሎት የሚለውን ቃል ከስብከት እና ከመዝሙር ጋር ብቻ በማያያዝ በየሞያችን የተቀበልነውን መክሊት ቤተ ክርስቲያንን ሳናገለግልበት ቀብረነው እንገኛለን:: በምህንድስና፣ በህክምና፣ በትምህርት፣ በሕግ ፣በሕዝብ አስተዳደር፣ በኮምፒዩተር ሳይንስ፣ በቋንቋዎች ጥናት፣ በሂሳብ ሥራ እና በመሳሰሉት የዕውቀት ዘርፎች የሰለጠንን ምእመናን ይህንን ጥበብ ላደለን ለልዑል እግዚአብሔር ምሥጋና የምናቀርብበት፣ የጥበቡን ዐሥራት በማውጣት በረከት የምንቀበልበት፣ ቤተ ክርስቲያን ከዘመኑ ጥበብ ጋር እንድትጓዝና የተቀላጠፈ አገልግሎት እንድናገኝ የሚኖረው አስተዋጽኦ ታላቅ ነውና ወደ ቤተ እግዚአብሔር በመቅረብ በሞያችን ድርሻችንን ልንወጣ ያስፈልጋል:: በገንዘብ ቢተመኑ ከፍተኛ ዋጋ ሊያስከፍሉ የሚችሉ ሥራዎች በዕውቀታቸው ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ላይ ባሉ ጥቂት ምእመናን እየተከናወኑ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያናችን ካላት በርካታ ምእመናን እና ከምእመናኑ ካላቸው የሞያ ስብጥር አንጻር ምንም አልተሠራም ለማለት ያስደፍራል:: ስለዚህ በእውቀታችንና በሞያችን ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል የምንነሳበት ወቅት አሁን ነውና ወደ እናት ቤተ ክርስቲያናችን ቀርበን የድርሻችንን እንወጣ::

3. የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የኢኮኖሚ ዐቅም ማጎልበት:-

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያላት ወይም የሚኖራት የኢኮኖሚ አቅም የተሟላና ዘላቂ የሆነ መንፈሳዊ አገልግሎትን ያለማቋረጥ በሰፊው መስጠት መቻልዋን ሊያረጋግጡልን ከሚችሉ መለኪያዎች አንዱ ነው:: በሚሊዮኖች

የምንቆጠር ምእመናን ከልደት እስከ ሞት ለእኛው ሕይወት የሚቀደሰው ቅዳሴ፣ የሚበራው ጧፍና ሻማ ፣የሚታጠነው እጣን ፣ የምንቀባው ሜሮን፣ የምንጠጣው ጸበል፣ የምንባረክበት መስቀል፣ በአጠቃላይ በውስጥ በአፍአ ለአገልግሎት የሚውሉ ንዋየ ቅድሳት በሙሉ ዘወትር ሊገኙ የሚችሉት በልጅነታችን አምነን ለቃሉ ታዛዥ ሆነን የሚጠበቅብንን ዐሥራት አውጥተን ስንገኝ ነው:: በተጨማሪ በክህነትና በተለያዩ የቤተ ክርስቲያኒቱ የአስተዳደር ዘርፍ የተሰማሩ በርካታ ባለሞያዎች ወርሃዊ ደመወዛቸውን አግኝተው አገልገሎታቸውን በትጋት እንዲወጡ ለማስቻል ከምናወጣው ዐሥራት በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያኒቱን የገቢ አቅም ማጠናከር በሚያስችሉ ሥራዎቹም ላይ መረባረብ ግድ ይለናል:: በበርካታ ምእመናን ዘንድ ዐሥራት የማውጣት ልምድ የተዳከመ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን ዛሬም በ 21 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደቀደመው ሁሉ ጀንጥላ ዘቅዝቆ ከመለመን ነጻ መሆን አልቻለችም:: ለዚህ የሚጠቀሱ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም በተለይ ማእከላዊ የፋይናንስ አስተዳደር አለመኖሩ ትልቁን ድርሻ ይይዛል። ይህ ደግሞ የአገልጋዮችዋን የዕለት ጉርስ እንኳን መሸፈን የማይችል በመሆኑ በርካታ አገልጋዮች የዕለት ጉርስ ፍለጋ ከአገልግሎት እንዲለዩ እያደረገ ነው:: በአብዛኛው በልመና በሚተዳደሩ የአብነት ትምህርት ቤቶችም ተተኪ የሆኑ ዲያቆናት ካህናትና ሊቃውንትም እንዳይኖሩ አሉታዊ ተጽዕኖ እያስከተለ መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም:: ስለዚህ ዘመናዊ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በመፍጠር የቤተ ክርስቲያኑን አገልግሎት ዘላቂ ማድረግ ከሁላችንም ይጠበቃል:: በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ያለውን የኢኮኖሚ አቅምን የማጠናከር በጎ ጅምር ለምሳሌ ዘመናዊ ትምህርት ቤት፣

ክሊኒክ፣ ዳቦ ቤትና ወፍጮ ቤት ግንባታ፤ የንብ ማነብና የከብት ማድለብ ሥራ፣ የእደ ጥበብ ሥራ ፣ የንዋየ ቅድሳት ሱቆች የመክፈት ሥራ የመሳሰሉትን ማጠናከር እና ሌሎችም ልምድ ቀስመው ይህንኑ ሥራ እንዲያከናወኑ ዐቅም ለመፍጠር መረባረብ ያስፈልጋል:: በየዓመቱ አገራችን ኢትዮጵያን ለመጎብኘት የሚመጡ በርካታ አገር ጎብኝዎች(tourists) በአብዛኛው የሚጎበኙት እንደ ቅዱስ ላሊበላ ያሉ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትን እና ቤተ ክርስቲያናችን ለዘመናት ጠብቃ ያኖረቻቸውን ጥንታውያን መጻሕፍት፣ ሥዕላት እና ሌሎች ንዋየ ቅድሳት ሲሆን ከዚሁ አገልግሎት ቤተ ክርስቲያኒቱ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንድትሆን የማድረግ ሥራ መሥራትም ይጠበቅብናል:: ለምሳሌ ጎብኝዎቹ ጎብኝተው ሲጨርሱ ሊገዙት የሚገባ ነገር በተመጣጠነ ዋጋ ሊያገኙ ይገባል። ቤተ ክርስቲያኒቱ በእነዚህ ተግባራት እና በሌሎችም አዋጭነት ባላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች (investments) ላይ መዋዕለ ንዋይ ብታፈስ ሊገኝ የሚችለው የኢኮኖሚ ዐቅም ደመወዝተኛ ሠራተኞችን ከማስተዳደር ባሻገር ቤተ ክርስቲያኒቱን በሁሉም መስክ እንድትጠነክር የሚያደርግ ነውና ትኩረት ሰጥተን የበኩላችንን አስተዋጽኦ ልናበረክት ያስፈልጋል::

4. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከአጽራረ ቤተ ክርስቲያን መጠበቅ:-

ቤተ ክርስቲያንን ዘወትር ከውስጥና ከውጭ ጠላቶች ፈተና መከላከልና መጠበቅ ከእያንዳንዱ ምእመን ከሚጠበቁ የሥራ ድርሻዎች አንዱ ነው:: ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የሚታዩ ምንጫቸው የአጽራረ ቤተ ክርስቲያን እጆችና ሀብት የሆኑ በርካታ ፈተናዎች/ችግሮች ሁላችንም ድርሻችንን

በተገቢው መንገድ ካለመወጣታችን የተወለዱ ናቸው:: በርካታ ምእመናን ድርሻችን ቅዳሴውን አስቀድሶ፣ በዐለ ንግሱን አክብሮ ወደየጎጆአችን መሄድ ብቻ ስለሚመስለንና የአጽራረ ቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ የካህናት ጉዳይ ብቻ አድርግን ስለምንመለከት በአጭሩ ሊቀጨ የሚገባቸው ፈተናዎች በየቦታው ተስፋፍተው ቤተ ክርስቲያንን እስከማዘጋት ምዕመናንንም እስከ መከፋፈል ደርሰዋል:: በዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከአጽራረ ቤተ ክርስቲያን የመጠበቅ ሥራ ምእመኑ ያለው ተሳትፎ እጅግ በጣም አናሳ መሆኑን የተረዱ የተሐድሶ አቀንቃኝ መናፍቃንም በቤተ ክርስቲያን አውደ ምሕረት እየተገኙ የኑፋቄ መርዛቸውን ለመትፋት ደርሰዋል :: ከእናት ቤተ ክርስቲያን የተወለድን የተዋሕዶ ልጆች በዚህ ፈተና ወቀት እናታችን ቤተ ክርስቲያንን ከጠላት ለመከላከል ድርሻችንን መወጣት ሲገባን ወይ ጉድ እንዲህ ሆነ?! እንዲህ ተፈጠረ?! እንዲህ አደረጉ?! በማለት ዳር ሆኖ መመልከት መፍትሔ አያመጣም:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የእኔ እናት ናት፤ ለእናቴ ችግር ከእኔ በላይ ማን ቀድሞ ይደርሳል? በማለት በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጭም ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ጉዳይ ላይ ሁላችንም በባለቤትነት ልንንቀሳቀስ ያስፈልጋል:: ዳር ሆነን የምንመለከትበት ጊዜ ከእንግዲህ አብቅቷል::

የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ ዳር ሆኖ በመመልከት ያሳለፍነው ጊዜ ስመ ሥላሴ እንዳይጠራ የሚሹ የተሐድሶ አራማጆች በየአውደ ምሕረቱ ሲፏልሉ ለማየት አድርሶናል፣ የአጋንንትን ስም እየጠሩ የሚያሚርቱ አስማተኞች በጸበል አጥማቂነት ስም በየጸበሉና በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ምእመናን ሲዘርፉ ለማየት አድርሶናል፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል ያልሆኑ አታላዮች በቤተ

ክርስቲያኒቱ ቆብ፣ቀሚስ፣ መስቀልና ጃንጥላ ተከልለው በየጎዳናው የምእመኑን ገንዘብ ሲዘርፉና አመሻሽ ላይ በየመሸታው ሲጨፍሩበት ለማየት አድርሶናል:: በየደብሩ ወደ ግለሰቦች ኪስ የሚገቡ ሙዳየ ምጽዋት ሲሰለፉና ሲዘርፉም ለማየት ደርሰናል:: ከድሀ ምእመናን በንግስ፣ በቅዳሴ ፣በስዕለት የተሰበሰበ ገንዘብ ወርቅና ሌሎችም ውድ ስጦታዎች ቤተ ክርስቲያን ባለቤት የሌላት እስኪመስል ድረስ ወደ ግለሰቦች ቤት ሲገባ ለማየት በቅተናል:: በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማገልገል የተሰየሙ የሰበካ ጉባኤ እና የሕንጻ አሠሪ ኮሚቴዎች በቡድን በመደራጀትና በመመሳጠር የቤተ ክርስቲያንን ሀብት ሲዘርፉ ለማየት በቅተናል:: ከሀገር ውጭም አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በዘር ከፋፍሎ የትግሬ፣ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የጉራጌ ፣የወላይታ ፣የሰሜን ፣የደቡብ በማለት ምእመኑን ግራ የሚያገባና አንገት የሚያስደፋ ኢክርስቲያናዊ ሥራ ሲሠራ ለማየት አድርሶናል::ሐጢኣት በገንዘብ የሚሰረይ ይመስል እንድንጸልይልሽ፣ ለነዳያን እንድንሰጥልሽ ይህን ያህል ሺህ ብር አምጪ የሚሉ፤ ለዚህ ሐጢአት ንስሐ መስጠት አስቸጋሪ ስለሆነ ይህን ያህል ብር አምጣ በማለት የማይገባ ነውር ሲፈጽሙ የሚገኙም አሉ። ምእመናንን ከአባቶቻቸው ካህናት ለመለየት ሻሽ ጠምጥመው ቆብ ደፍተው ቄስ መነኩሴ መስለው እየሰከሩ፣አጽዋማትን እየሻሩ ሌላም ጸያፍ እና ክፉ ሥራ በመስራት የተጠመዱ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች አሉ። በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን የማፍረስ ተልዕኮ ያነገቡ አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በተለያየ መልክ የማፍረስ ሥራ ላይ ተሰማርተዋልና ቤተ ክርስቲያንን ከዚህ እኩይ ተግባር ለመታደግ እያንዳንዱ ምእመን ሊረባረብ ያስፈልጋል::

"በውኑ ይህ ቤት ፈርሶ ሳለ እናንተ ራሳችሁ በተሸለሙ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን?" (ሐጌ 1፣4) የሚለው ጥያቄ ይመለከተናልና ድርሻችንን እንወጣ::

5. ተተኪ ትውልድ ማፍራት:-

ለአንዲት ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዘላቂነት የተተኪ ትውልድ መኖር እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው:: ካለንበት ዘመን ባሻገር በቀጣይ ዘመናት ቤተ ክርስቲያኒቱን ከነተቀደሰ ሥርዓቷ ሊረከባት፣ ሊያቆያት፣ ሊያገለግላት፣ ሊገለገልባት እና ሊድንባት የሚችል ተተኪ ትውልድ እንዲኖር ምዕመናን ድርሻችንን ልንወጣ ያስፈልጋል:: ከአብራካችን የተከፈሉ ልጆቻችንን በቤተ ክርስቲያን ይዘን በመገኘት ስርዓቱን ማስተማር፣ ማስባረክ ፣ፍቅሩን ማስረጽ እና ቤተ ክርስቲያኒቱ የእነርሱ መሆኗን እያሳወቁ ማሳደግ ያስፈልጋል:: በሰንበት ትምህርት ቤት እና በቤተ ክርስቲያን በሚዘጋጁጉባኤያት የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት እንዲከታተሉና ራሳቸውን ከመናፍቃን እንዲጠብቁ በምግባርም እንዲልቁ ማድረግ ከወላጆች ይጠበቃል:: በዘመናችን በአብዛኛው ወላጆች ለራሳቸው መንፈሳዊ ማንነት ብቻ በከፊል በመሮጥ ላይ ሲሆኑ የልጆች መንፈሳዊ ሕይወት ጉዳይ ግን በእጅጉ ተዘንግቷል:: ይህም በአንድ ጎጆ ስር የሚኖሩ የተለያየ እምነት ያላቸው የቤተሰብ አባላት መኖር ፤ ወይም በርካታ እምነት የለሽ ዘር በመብቀል ላይ ያለባቸው ቤተሰቦች መበራከት ከሚጠፉት ነፍሶች ባሻገር የወደፊቱን የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ ትውልድ ጉዳይ አሳሳቢ ያደርገዋል:: ስለዚህ ምእመናን ዘሮቻችን የወደፊት የቤተ ክርስቲያን ዕንቁ መሆናቸውን እያስተዋልን ልጆቻችንን በመንፈሳዊ ሕይወት ልንቀርጽ

ያስፈልጋል::

ማጠቃለያ:-

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከአምላካችን ከልዑል እግዚአብሔር ጋር የምንገናኝባት የጽድቅ ቤት ናት:: በክርስትና ሕይወት የምንኖር የተቀደሰች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ምእመናን የመንፈስ ቅዱስ ግምጃ ቤት በተሰኘች የመንፈሳዊ በረከት ቤታችን በሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስንኖር ከሚጠበቁብን በርካታ የቅድስና ሥራዎች መካከል፤ የክርስትና ሕይወት የሚጠይቀውን ምግባር በማከናወን አርአያ ሆኖ መኖር፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በተሰጠን መክሊት ሁሉ ማገልገል፣ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የኢኮኖሚ ዐቅም ማጎልበት እና በጎ ጅምሮችን ማጠናከር፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ በጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ ሊያፈርሷት እየታገሉ ካሉ የውስጥ እና የውጭ ጠላቶች ነቅቶ መጠበቅና መከላከል እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኒቱን ከነሙሉ ሥርዓቷ የሚረከብ ተተኪ ትውልድ የማፍራት ሥራን መሥራት እና በትጋት ማከናወን ይጠበቅብናል:: በአጠቃላይ ዘመኑ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በሩቅ ሆነን የምንሳለምበትና ሲሞላልን ብቻ የምንጎበኝበት ሳይሆን ጠጋ ብለን ድርሻዬ ምንድን ነው? ብለን ጠይቀን ለሥራ የምንነሳበት ወቅት ነውና ድንገት ዐረፍተ ዘመን ሳይገታን ወይም ሳይቀድመን ቤተ ክርስቲያን የምትጠብቅብንን ድርሻ ለመወጣት እንትጋ:: ለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ ከሁላችንም ጋር ይሁን:: አሜን::

Miko ZE Ethiopia

በዲን. ብርሃኑ ታደሰ

31/ አባታችን አብርሃም እውነተኛውን አምላክ ለሚያመልኩ ሁሉ ታላቅ የእምነት አባት ነው። በእርግጥም አምላኩን ፍጥረትን በመመርመር ማግኘቱ፣ አምላኩን ብሎ ቤተሰቡን ተለይቶ መውጣቱ፣ ልጁን ለመሰዋት ፍጹም ፈቃዱን ማሳየቱ ሁሉ ለእምነት አባትነቱ ማሳያዎች ናቸው። ከሁሉ የሚልቀው ከእርሱ አስቀድሞ ከሙታን መካከል የተነሱ ሳይኖሩ፣ ዘርህ በይስሐቅ ይጠራልሃል ከተባለ በኋላ ልጅህን ሰዋልኝ ሲባል፣ እነዚህን ሁለት የሚጣሉ የሚመስሉ ሐሳቦችን በእምነቱ አስታርቆ ማለት ቢሞት እንኳን ያስነሳዋል ብሎ አምኖ ልጁን ሊሰዋ ወደ ተራራ መውጣቱ ነው።(ዕብ 11፥19) የሰው ሕሊና ጊዜ ሲያገኝ አንድን ነገር ደጋግሞ ማሰቡ አይቀርም፤ አብርሃም ግን የሦስት ቀን መንገድ ሲሄድ ይህ እምነቱ ንውጽውጽታ አልነበረውም - እፁብ ነው።Lideta_Le_Mariam_1

እኛ ክርስቲያኖች - የእግዚአብሔር ወልድን ሰው መሆን፣ ለኛ ብሎ መከራ መቀበል፣ በኋላም የቤዛነቱን ሥራ ሲፈጽም በአባቱ ክብር መቀመጡን ስለምናምንና ስለተጠመቅን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል። ይህ ልጅነት በፊት እንደነበረው ከሥጋ የመጣ አይደለም፤ መጽሐፍ - “ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደ ግን መንፈስ ነው።” እንዲል፤ ልጅነታችን በጸጋ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሳ ነው። (ዮሐ 3) ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ ይህንን ሲያጸናው የተወለድነው ከሚጠፋ ዘር አይደለም ይለናል። (1 ጴጥ 1፥22) ክርስቲያኖች የመሆናችን ምንጭ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ደግሞ

የተወለደው ንጽሕት ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ነው። ከድንግል ማርያም የተወለደው እርሱ እኛን በጸጋ ልጆች የምንባልበትን ስልጣን ሰጠን፤ ስለዚህም እናታችን ማርያም እንላለን፣ በሙሉ ጥብዐትም የቅድስት ማርያም ዘር ነን እንላለን። እንግዲህ ሰው የትኛውን ይጠራጠራል? በክርስቶስ ክርስቲያን መሰኘቱን ነው ወይስ ክርስቶስ ከቅድስት ማርያም መወለዱን? ወይንስ ክርስቶስ በሥጋ መገለጡን? በአንድ ስፍራ ቅዱስ ጴጥሮስ ጸጋው ለሁሉም እንደተሰጠና የሚሰጥበትን ምክንያት ሲገልጽ “እንግዲህ እግዚአብሔር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላመነው ለእኛ ደግሞ እንደ ሰጠን ያን ስጦታ ለእነርሱ (ለአሕዛብ) ከሰጠ፥ እግዚአብሔርን ለመከልከል እችል ዘንድ እኔ ማን ነበርሁ?” ይላል። (ሐዋ 11፥17) ዳግመኛም “ማርያም ሆይ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ።” ይላል።(ሉቃ 1፥30) በሌላም ስፍራ “ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ።” ይላል። (1 ዮሐ 4፥3) ስለዚህ ተጠራጣሪ አይኑር ይመን እንጂ።

አቡቀለምሲስ ወይም ባለ ራዕይ የሚባለው ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ካያቸው ራእዮች መካከል አንዱ የክርስቲያኖች እናት እና መመኪያ ስለሆነች ቅድስት ድንግል ማርያም ነው። ይህንንም በአስራ ሁለተኛው ምዕራፍ ላይ አስቀምጦታል። የሚጀምረውም ስለክብሯ፣ ከዚያም ስለወለደችው ልጅ፣ በዚህም ምክንያት ስለመጣባት መከራ፣ መከራውም

ወደ ዘሮቿ እንደዞረ ያስረዳል። ስለክብሯ፦ “ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች።”(ቁጥ 1) ይላል። ስለወለደችው ልጅም፦ “አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ወንድ ልጅ ወለደች” (ቁጥ 5) ይላል። አሕዛብን ሁሉ የሚገዛ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱን የወለደች ደግሞ ቅድስትና ድንግል ማርያም ናት። ስለዚህም ምክንያት “ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።” (ቁጥ 13) ይለናል - ወደ ግብጽ ስለመሰደዷ። በመጨረሻም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጠብቁትን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች የሆኑትን እንደሚያሳድድ ሲገልጽ፦ “ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፤” ከዘርዋ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሴቲቱን ዘር ነው፤ ይህች ደግሞ የመመኪያችን ዘውድ ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። ዘርዋ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች የሆኑትን ነው። ንዋየ ሳሩይ ቅዱስ ጳውሎስም፦ “በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።” ብሎ፣ በእርሱዋ የደረሰ በዘሮቿም እንደሚደርስ አስረግጦ ተናግሯል። (2 ጢሞ 3፥12)

በአብርሃም ልጅ በይስሐቅ ደም ዓለም እንደማይድን ተነገረ፤ በእመ አምላክ ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ግን ክብርን አገኘን። በሥጋ ተወልደው የአብርሃም ዘር የሆኑት ከነዓንን ለመውረስ ተስፋ አደረጉ፤ እኛ በመንፈስ ከአብርሃም ተወልደን የድንግል ማርያም ዘር የሆንነው ደግሞ መንግስተ

ሰማያትን ተስፋ እናደርጋለን። እነርሱ ከነዓንን ለመውረስ ብዙ ሰልፍ አደረጉ፤ እኛ መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ መንፈሳዊ ውጊያ እናደርጋለን። እነርሱ በመገረዛቸው ይመካሉ፤ እኛ ግን በጥምቀት ባገኘነው የጸጋ ልጅነት እና የድንግል ልጅ በመስቀል ላይ ባደረገልን ውለታ እንመካለን። እነርሱ ማመን ለሥጋ ዘመዶቻቸው ብቻ እንደሆነ ያስባሉ፤ እኛ መዳን ለሁሉ እንደተሰጠ እናምናለን። እነርሱ ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት መሲህ ወደ ዓለም አልመጣም ይላሉ፤ እኛ የነቢያት እውነተኝነት ይገለጽ ዘንድ ሰውን ለማዳን የመጣውን ኢየሱስ ክርስቶስን ድንግል ማርያም ወልዳልናለች ብለን እንመሰክራለን። እነርሱ በሥጋ የአብርሃም ዘር ነን እያሉ ይመካሉ፤ እኛ በመንፈስ የአብርሃም ልጆች፣ የድንግል ማርያም ዘር በመሆናችን እንመካለን።

እናታችን ማርያም ሆይ ልጅሽ ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሳን ለምኝልን። አሜን።

Rodas Tadese Abebe

32/ የአዳምና የሔዋን ተስፋ .....

..... በመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ .....

አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር አምላክ የሰጣቸውን ሕግ በዲያብሎስ ክፉ ምክር አፍርሰው ዕፀ በለስን ከበሉ በኋላ፤ ለስሕተታቸው ምክንያት የኾናቸውን በእባብ ያደረ ዲያብሎስን ታላቅ እርግማንን ረግሞታል፤ ይኽም ዲያብሎስ የተረገመው ርግማን ለአዳምና ለሰው ዘር ታላቅ የተስፋ ቃል ሲኾን በኋለኛው ዘመን አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀሉ ዲያብሎስን ድል እንደሚነሣው የሚያሳውቅ የመዠመሪያው የድኅነት ተስፋ ነበር፤ ይኸውም በዘፍ ፫፥፲፭ ላይ እንደተጻፈ በእባብ አንጻር ዲያብሎስ የተረገመው እርግማን ይኽ ነበር “በአንተና በሴቲቱ መኻከል በዘርኽና በዘሯም መኻከል ጠላትነትን አደርጋለኁ፤ ርሱ ራስኽን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለኽ” ብሎታል።

ይኸውም “ባንተና በሴቲቱ” ማለት በሔዋን መኻከል ጠላትነትን አደርጋለኁ ብሎ፤ በዲያብሎስና በሔዋን መኻከል የሚኾነውን ታላቅ ጸብና ክርክር ነግሮታል። እኹን እግዚአብሔር እንዲኽ ማለቱ ሔዋን ከዲያብሎስ ጋር ተጣልታ ድል የምትነሣው ኾኖ አይደለም፤ ኾኖም ግን ከሔዋን ባሕርይ ከተገኘች ዳግሚት ሔዋን ከምትባል ከቅድስት ድንግል ማርያም የዲያብሎስ ምክሩን የሚያፈርስ፣ ጎይሉን የሚያደክም፣ አሸክላውን የሚቈርጥ፣ መርዙን የሚያጠፋ ቤዛ ኩሉ ክርስቶስ የመወለዱን ነገር ሲናገር ነው (ገዮ ፫፥፲፭-፲፱)።

“በዘርኽና በዘሯም መኻከል ጠላትነትን አደርጋለኁ” በማለት የዲያብሎስ የግብር ልጅ በተባሉት ዲያብሎስ ባደረባቸው በአይሁድ መኻከልና፤ ከሔዋን

ባሕርይ ከተገኘ ከዳግሚት ሔዋን ከድንግል ማርያም በድንግልና በተወለደው በባሕርይ ልጁ በክርስቶስ መኻከል ጸብና ክርክር እንደሚኾን አስቀድሞ ገልጧል። ይኽ የሰጣቸው ተስፋ ሊፈጸም አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከእመቤታችን ከተወለደ በኋላ ዲያብሎስ በአይሁድ ልቡና ዐድሮ ጌታን እንዲሰቅሉት ያነሣሳቸው ነበር፤ ጌታም አይሁድን “ንግግሬን የማታስተውሉ ስለምንድር ነው? ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው፤ እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችኹንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ፤ ርሱ ከመዠመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር፤ እውነትም በርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም፤ ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራልና፤ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና፤ እኔ ግን እውነትን የምናገር ስለኾንሁ አታምኑኝም” (ዮሐ ፰፥፵፬-፵፮) በማለት ማኅበራነ አይሁድ የግብር አባታቸው የዲያብሎስን ፈቃድ ፈጻሚዎች መኾናቸውን ነግሯቸዋል።

ይኸውም ኅጢአት በመሥራት የተጐዱ ኹለቱ (አዳምና ሔዋን) ሲኾኑ ተስፋውም የአዳምና የሔዋን ሲኾን “ማእከለ ዘርዖሙ” (በዘሮቻቸው) አላለም፤ ነገር ግን ሔዋንን ብቻ ለይቶ “በዘርዋ” ብሎ ተስፋውን የሰጠበት ምክንያት አካላዊ ቃል ክርስቶስ ተወልዶ የሚያድናቸው ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት እንደተወለደ ኹሉ፤ ድኅረ ዓለም ያለ አባት ከዳግሚት ሔዋን ከድንግል ማርያም ብቻ በድንግልና ተወልዶ ነውና ለሔዋን ብቻ ሰጥቶ ተስፋውን ገልጾለታል። ይኸውም አካላዊ ቃል በሰጠው ተስፋ መሠረት ከሔዋን ዘር ይወለድ ዘንድ ስላለው ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር “እንግዲኽ ሕግ ምንድር ነው? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ” (ገላ ፫፥፲፱) በማለት የሰጠውን ተስፋ አጕልቶ ከተናገረ በኋላ፤ በሰጠው ተስፋ መሠረት

ከቅድስት ድንግል የመወለዱን ነገር ሲገልጽ “ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ፤ ከሴትም ተወለደ” (ገላ ፬፥፬) ሲል ጌታ የተሰጠውን ተስፋ እንደፈጸመው አስተምሯል።

“ርሱ ራስኽን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለኽ” በማለት የተናገረው ሊፈጸም አካላዊ ቃል ወልደ እግዚአብሔር ሰው በኾነ ጊዜ ዲያብሎስ በገዳመ ቆሮንቶስ በአካል በመምጣት በመፈተን፤ ከዚያም በልበ አይሁድ በማደር ሰኰና ትምህርቱን፣ ሰኰና ተአምራቱን በመቀዋወም በመስቀል ሲያሰቅለው፤ ጌታም በመስቀል ተሰቅሎ በመስቀሉ የእባቡ የዲያብሎስን ራስ ቀጥቅጦ ድል ነሥቶት ዓለምን አድኖ ለአዳምና ለሔዋን የሰጠውን የተስፋ ቃሉን ፈጽሞታል። በማእከለ ምድር በቀራንዮ በመስቀል ተሰቅሎ የእባብ የዲያብሎስን ራስ ቀጥቅጦ ሥልጣኑን እንደሚያጠፋ፤ ክቡር ዳዊት በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በመዝሙሩ ላይ ‹‹እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፤ በምድርም መኻከል መድኀኒትን አደረገ፤ አንተ ባሕርን በኀይልኽ አጸናኻት፤ አንተ የእባቦችን ራስ በውሃ ውስጥ ሰበርኽ፤ አንተም የዘንዶውን ራሶች ቀጠቀጥኽ›› (መዝ ፸፫፥፲፪-፲፬) በማለት ለአባታችን አዳም በሰጠው ተስፋ መሠረት፤ በመስቀሉ ዲያብሎስን ሰራዊተ አጋንንትን ድል የማድረጉን ነገር ተናግሯል።

በኦርቶዶክስ የነገረ እግዚአብሔር ትምህርት ታላቅ አባት የተባለው ሄሬኔዎስም ለመናፍቃን ምላሽ በሰጠበት መጽሐፉ እግዚአብሔር በዘፍ ፫፥፲፭-፲፮ ላይ ለዲያብሎስ መርገም የኾነ ለአዳምና ለሔዋን ግን በረከትና ተስፋ አድርጎ የሰጣቸው ዐዲስ ተስፋ በክርስቶስ ስለመፈጸሙ ሲያስተምር ‹‹Christ completely renewed all things...››

(ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ኹሉንም ነገር ለወጠ፤ እናም ከጥንት ዠምሮ በአዳም ምክንያት እስረኛ ያደረገን ርሱን (ሰይጣንን) አደቀቀ፤ ራሱን ረጋገጠ፤ በኦሪት ዘፍጥረት ላይ ጌታ ለእባቡ እንዲኽ እንዳለ ‹‹በአንተና በሴቲቱ መኻከል በዘርኽና በዘርዋም መኻከል ጠላትነት አደርጋለኹ፤ ርሱ ራስኽን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለኽ›› (ዘፍ ፫፥፲፭)፤ ከዚያ ጊዜ ዠምሮ በአዳም አምሳል ከድንግል የሚወለድ ርሱ፤ የእባብን ራስ የሚቀጠቅጥ መኾኑ በግልጽ ታየ(ታወጀ)፤ ይኽ ዘር ሐዋርያው በገላትያ መልእክቱ ላይ ‹‹እንግዲኽ ሕግ ምንድር ነው? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ›› (ገላ ፫፥፲፱)፤ በማለት የተናገረለት ነው፤ ይኽንን በግልጽ በተመሳሳይ መልእክቱ ላይ ‹‹ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ›› (ገላ ፬፥፬) በማለት ተናግሯል፤ ጠላት በትክክል አይሸነፍም፤ ርሱን ለመማረክ ሰው ኾኖ ከሴት ካልተወለደ በቀር፤ ሰውን ከጥንት ዠምሮ ለመቃወም በሴት በኩል ጎይል አግኝቶ ነበር በዚኽ ምክንያት ጌታ ራሱን የሰው ልጅ በማለት ተናገረ) ሲል ተንትኖ ገልጾታል።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስም እንደ ሄሬኔዎስ የተፈጸመውን የድኅነት ምስጢር እያነጻጸረ በመጽሐፉ ምስጢር ላይ ሲያብራራ ‹‹ቀደመ እግዚአብሔር ረጊሞታ ለአርዌ ምድር ወኢተሰአላ በእንተ አበሳሃ ዘከመ ተስእሎሙ ለአዳም ወለሔዋን ...›› (እግዚአብሔር እባብን በመርገም ዠመረ አዳምንና ሔዋንን እንደጠየቃቸው ስለ በደሏ አልጠየቃትም፤ የኅጢአት መሠረት ከእባብ እንደወጣ ዐውቋልና፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር ሰይጣንን ተቃወመ፤ እናታችን ሔዋንን በመምከር ሰይጣን ሞትን እንዳመጣ፤

እንዲኹ በእመቤታችን በማርያም ሕይወትን አመጣ፤ በሴት ምክንያት እንደተሰደድን በሴት ምክንያት ወደ እግዚአብሔር ቀረብን፤ ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን አምላክ መኾንን እንዳስመኛቸው፤ እንዲኹ ገብርኤል ለድንግል ማርያም በሥጋዋ አምላክን እንደምትወልድ አበሠራት፤ የክሕደትን ዛፍ በመብላት እግዚአብሔር እንደነቀፈን በዕፀ መስቀሉ ይቅር አለን፤ በገነት ዛፎች መኻከል የአዳም ራቁትነት እንደተገለጠ እንዲኹ የመድኀኒታችን የሰውነት ራቁትነት በእስራኤል ሕዝብ ጉባዔ መኻከል ተገለጠ) በማለት በዘመነ ሥጋዌ የተደረገውን የተስፋው ቃል የድኅነት ምስጢርንና የተፈጸመውን ካሳ አብራርቷል።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም ሔዋን እና እባብ በፈጠሩት ስምምነት የሰው ኹሉ ዘር ቢወድቅም፤ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ የጠላታችን የዲያብሎስን ምክሩን አፍርሶ ድል ነሥቶ ያጣነውን ገነትን ዳግመኛ እንደመለሰልን ሲተነትን ‹‹In Eden Eve wrote out...›› (በዔደን ሔዋን ጠንካራ የዕዳ ሰነድ በጽሑፍ ገለጸች (ቆላ ፪፥፲፬)፤ ውጤቱም በርሷ ልጆች ላይ ሰቈቃውና ሁከት ኾነ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድም ሞትን አመጣ፤ እባቡ ሸረኛው ጸሐፊ በተንኰሉ ጽፎ ፈርሞ አተመው፤ ጥንት የነበረ ዘንዶ በምክሩ ዕዳው እንዲሰፋ አደረገ፤ የሰው ዘር በማራኪው ጉድን (ባልንጀራነት) ፍቅር እንዲወድቅ ኾነ፤ ዘንዶውን በመስማቱ አዳምም ከገነት ለመውጣቱ ምክንያት ኾነ፤ የሔዋን ኀጢአት የዕዳውን ስምምነት ዐደረገ... ዘለዓለማዊቷ ድንግል የርሷን እናት ዕዳ ከፈለችላት ለርሷ ምስጋና ይግባት፤ ትውልዱን ኹሉ ያሳመመ (ያስለቀሰ) ሰነድ ተቀዷልና፤ እባቡ በመርዘኛ እቅዱ በደካማዪቱ በሔዋን

ዝሮ መርዝ ተነፈሰ፤ ይኽ ከመግደል የማይመለስ ውጤት ከትውልድ ወደ ትውልድ ተሻገረ፤ ከድንግል ማርያም የተወለደው ሕፃን ያን እባብ እስኪገድለው ድረስ፤ የአብ ቃል ርደቱን ክፉው በገባበት በዚያ ዝሮ ዐደረገ፤ የእባቡን መሥመር ተመልክቶ ዱካውን ተከተለ፤ በንጽሕት ድንግል ዝሮ ፈጣን ርደቱ የእባቡን መርዝ ጠርጐ ጣለ፤ ጥፋትን ያስከተለ የእባቡ ጥቆማ በዝሮ በኩል ገባ፤ ሞት በገባበት በዚያ በር ሕይወት ሊገባ ይገባዋልና፤ ጎጢአት በተቀመጠበት በዚያ ስፍራ ጸጋ ሊነግሥበት ሊትረፈረፍ ይገባዋል (ሮሜ ፭÷፳)፤ አብ ለቃሉ ታማኝ መልእክተኛ ገብርኤልን ላከ፤ ዐላማውም ለወጣቷ ድንግል ለኹሉ ደስታን የሚሰጥ ሰላምታን ለማቅረብና ያ ርጉም በገነት ያስተዋወቀው የከረረ ኹኔታ ፍጻሜውን ሊያመጣ ነው፤ ያ መንፈሳዊ ፍጥረት ወደታች በረረ፤ ወደ እመቤታችን ማርያም ሲደርስ ወደ ታች እጅ ነሥቶ ብሥራቱን አሰማ፤ አፉን ከፍቶ ለርሷ ደስታ ሰላምታውን በዝሮዋ ዘራ፤ አብ ልጁን በሚመለከት ለርሷ የላከውን ረዥሙን ደብዳቤ አውጥቶ ለርሷ ሰጠ፤ የእግዚአብሔር የኾነ ይኽ ስዉር ምስጢር በተላከው ጠባቂ ምክንያት በግልጽ ወጣ፤ በዐዲሱ ዐዋጅ በእሳታዊ ፍጡር አፍ በነበልባላዊ ልሳን ስዉሩ ምስጢር ተነገረ) በማለት ዲያብሎስ ከሥጋ ከይሲ ሥግው ኾኖ በሔዋን ዝሮ ለትውልድ ኹሉ ፍዳን ያስከተለ ሞትን ቢያመጣም ክብር ይግባውና ጌታ በመልአኩ አማካኝነት በቅድስት ድንግል ማርያም ዝሮ እውነትን ልኮ ሥጋዋን ተውሕዶ ዲያብሎስን ድል የነሣ መኾኑን አስተምሯል።

የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴ የበዛለት ይኸው ሊቅ የተረገመው እባብና ሔዋን የፈጠሩት ስምምነት ያመጣውን ሞትና፤ የቅዱስ ገብርኤልና

የድንግል ማርያም ስምምነት ያመጣውን ሕይወት ሲገልጽ፥- ‹‹The serpent and Eve had dug a grave for Adam...›› (እባብና ሔዋን ለአዳም መቃብርን ቆፈሩ፤ በሲኦልም እንዲጣል ዐደረጉት፤ ገብርኤልም ወደ ድንግል ማርያም መጣ ተናገራትም፤ ከዚኽም ነገር ምስጢር ተገኘ፤ ይኸውም የሞቱትን ኹሉ የሚያነሣ ኾነ (ነው)፤ የአዳም ድንግሊቱ ሚስቱ በተንኰል ያታለላትን ውሸታሙን ተቀበለች፤ አጥፊውን ሰማችው በጅልነት አመነችው፤ እናም በገነት በነበረ መራራ ፍሬ አዳም እርቃኑን እንዲኾን አደረገች (ዘፍ ፫፥፩-፯)፤ ወደ ዳዊት ልጅ ወደ ድንግል ማርያም ስንመጣ የጠባቂውን ሰላምታ ተቀብላ የክብር ካባን አዘጋጅታ አዳም ለዕርቃኑ ልብስ እንዲኾነው አቀረበችለት፤ አኹን ሙሽራው በሰርግ ክፍሉ አሸብርቆ ቆመ፤ ኹለት ደናግል አሉ ምግባራቸው የተለያየ፤ አንዷ ባሏን የጣለች ሌላዋ ለአባቷ ረዳት የኾነች፤ በሔዋን ምክንያት አዳምን ሞት አገኘው፤ በእመቤታችን ማርያም ግን ገነትን ተሰጠው፤ ኹለት መልእክተኞች ወደ ዓለም ተላኩ፤ አንዱ ሰይጣን ሌላው መልአክ፤ እባብ ወደ ሔዋን ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም፤ በኹለቱም የሞትና የሕይወት ምርጫ ያለበት፤ የእትክልቱ ቦታ ብልኑ ጠባቂ ኹለት ዛፎችን ተከለ፤ በአንዱ ሞትን አንጠልጥሎ በሌላው ሕይወትን ደብቆ፤ በዚኽም ለአዳም ፈተናን ሰጠው፤ ከዚኽ ፈተና ክብርን ይቀዳጅ ዘንድ፤ ጌታም ለአዳም ሕግን ሰጠው፤ በውስጡም ሞት ካለበት ከዕውቀት ፍሬ እንዳይበላ ከለከለው፤ እባብና ሔዋን ተስማምተው በፈጠሩት ውሸት ምክንያት ተዋጊው በትግሉ ተሸንፎ ከክብሩ ተዋረደ፤ በሔዋን ምትክ ድንግል ተተካች፤ ከርሷም አምላክ ተገኘ፤ ፍሬውንም አቀየልን፤ በገነት

ያልቀመሱትን ከድንግል ማርያም አገኙት፤ ከፍቅሩ የተነሣ ራሱ የሰጠው ለበሉትም ጥንካሬን የሚሰጥ፤ ዛፉም በፍቅሩ ነደደ ከርሱም ለበሉት፤ ነገር ግን በሰይጣን ተታለው በገነት ያገኛቸውን ውርደት የሚያስቀር፤ ዛፉ ሲሸሻቸው ርሱ በታላቅ ርኅራኄ ተከተላቸው፤ በራሳቸው ቦታ እንዲበሉት የተሰጣቸው፤ ከዕውቀት ዛፍ ጎይልን ተራቡ ተመኙ፤ ነገር ግን ድንግል ካለመሻት ያንን ፍሬ ፀነሰች፤ በዚኽም በመመኘት ምክንያት ወደ አዳም ዘሮ የመጣ ሞት፤ በርሷ ምክንያት ከኹሉም ትውልድ እንዲወገድ ኾነ፤ ድንግል ማርያም የዕውቀት ዛፍ በውስጧ ሳይኖር፤ እንደ ሔዋን ያለ ሞትን የሚያመጣ አሳሳች እባብ የሌለባት የአምላክ ገነት ናት፤ ከርሷም ሕይወትን የሚሰጥ በቅጣት ያለውን ከግዞቱ ወደ ገነት የሚመልስ የሕይወት ዛፍ (ክርስቶስ) ወጣ፤ ኹለት ደናግል አሉ ምግባራቸው የተለያየ፤ አንዲ ባሏን የጣለች ሌላዋ ለአባቷ ረዳት የኾነች፤ በኪሩቤልና በእሳት ሰይፍ ሲጠበቅ የነበረ ያ ዛፍ ከንጽሕቲቷ ድንግል ተገኘ (ዘፍ ፫፥፳፬)) በማለት በእባብ ተንኰል ምክንያት በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ፣ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነም ተፈርዶባቸው ለሺሕ ፷፪ ዘመን በመንጸፈ ደይን ወድቀው በእግረ አጋንንት ተረግጠው የነበሩ የሰው ልጆችን ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፤ የእባብ የዲያብሎስን ራስ በመስቀል ቀጥቅጦ፤ ለእኛ ሕይወትንና መድኀኒትን ሊኾነን በገነት ያጣነውን የሕይወት ዛፍ ማለት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን በዚኽ ዓለም የሰጠን መኾኑን በጥልቀት አስተምሯል።

በመኾኑም እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያን ታላቅ ተስፋ ለአዳምና ለሔዋን የሰጠ፤ የሰጠውንም ተስፋ የፈጸመ የጌታችን እናቱ ናትና

እንወዳታላን፣ እናመሰግናታላን፣ እናከብራታለን፣ እናገናታለን፤ አዳምና ሔዋን ለነርሱ የድኅነት ተስፋ ለዲያብሎስ ግን የሽንፈት ዜና የኾነውን ይኽነን የተስፋ ቃል ከሰሙ በኋላ እንኳ አዳም የቤተ ፈት ልማድ አላገኘውም፤ ቤተ ፈት በዚኽ ጊዜ እበላ እጠጣ፤ በዚኽ ጊዜ ተድላ ደስታ አድርግ ነበር ብሎ ያዝናል፤ ርሱ ግን ፈጣሪዬ አትብላ ያለኝን ዕፀ በለስን በልቼ በደልኑ ብሎ በኀጢአቱ ፲፱ ሱባዔ ፮፮ ዓመት መሪር ልቅሶን አለቀሰ ‹‹ወአልቦቱ ካልዕ ኀሊና ላዕለ ኀጢአቱ ዘእንበለ ብካይ ወላህ›› እንዲል መቅድመ ወንጌል ያን ጊዜ ‹‹በአንተና በሴቲቱ መኻከል በዘርኽና በዘርዋም መኻከል ጠላትነትን አደርጋለኑ›› ሲል የተናገረውን የተስፋ ቃል በማጒላት ‹‹ወእምድኅረ ኀሙስ መዋዕል ወመንፈቀ መዓልት እምሕረከ ወእሣሃለከ በብዝኀ ሣህልየ ወምሕረትየ፤ ወእወርድ ውስተ ቤትከ ወአኀድር ውስተ ከርሥከ ወበእንቲኣከ ኦ አዳም እትወለድ ከመ ሕፃን ወበአንቲኣከ ኦ አዳም አሐውር ውስተ ምሥያጥ፤ ወበእንቲኣከ እጸውም ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ፤ ወበእንቲኣከ እትዌከፍ ወእትዔገሥ ሕማማተ ወበእንቲኣከ እሰቀል ዲበ ዕፀ መስቀል›› (በፍጹም ይቅርታዬ ከዐምስት ቀን ተኩል በኋላ በፍጹም ምሕረቴ ይቅር እልኻለኑ፤ ወደ ቤትኽም ወርጄ በባሕርይኽ ዐድራለኑ፤ አዳም ሆይ ስለ አንተ እንደ ሕፃን እወለዳለኑ፤ ስለ አንተ ወደ ገበያ እኼዳለኑ፤ ስለ አንተም አርባ ቀን አርባ ሌሊት እጾማለኑ፤ ስለ አንተ መከራ መስቀልን በትዕግሥት አቀበላለኑ፤ ስለ አንተም በዕንጨት መስቀል ላይ እሰቀላለኑ)ብሎ ተስፋውን ነግሮታል (መጽሐፈ ቀሌምንጦስ፣ ፫መቃ ፱፥፳፫-፳፱፤ ዕዝ ሱቱ ፱፥፭፤ ሲራ ፳፱፥፯፤ ገላ ፱፥፱)

ይኽነን ተስፋ ይዞ ሊቁ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው በቍ፴፯ ላይ ‹‹እንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እምገነት›› (ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም ተስፋው አንቺ ነሽ) በማለት ነበር ያመሰገናት፤ ምክንያቱም አዳም በኃቀን ተኩል ያለውን የተስፋ ቃል እንደሱ አቈጣጠር መስሎት ዐምስት ቀናትን ጠብቋል፤ ኋላ ግን ዘመኑ ፭ሺሕ፭፻ መኾኑን ተረድቶ ይኽነን ተስፋ በመትከፈ ልቡናው ይዞ ይኖር ነበር፤ ዛሬ ነጋይ ሥንቁን ይዞ እየበላለት ከዚኽ እስከዚያ ያደርሰኛል እያለ በተስፋ እንዲጓዝ፤ አዳምም በዐጸደ ሥጋ በዐጸደ ነፍስም ሳለ ፈጣሪዬ እንዲኽ ብሎኛል ይምረኛል፤ እያለ ተስፋውን አጽንቶ ሲጠባበቅ ኖረ፤ ይኽነን ተስፋውን ለልጆቹ አስቀድሞ ነግሯቸዋልና ልጆቹ አንዱ ሲቀበር አንዱ ሲወለድ፤ የአካላዊ ቃል ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ዓለምን የማዳኑ ምስጢር እየተገለጸላቸው ፭ሺሕ፭፻ ዘመን እስኪፈጸም ትንቢት እየተናገሩ ሱባዔ እየቈጠሩ ኖሩ (ማቴ ፲፫÷፲፯፤ ዮሐ ፭÷፵፯፤ ፰÷፶፮፤ ዕብ ፩÷፩-፪፤ ፯ዮሐ፩÷፩-፪)። የተናገረውን የማይረሳ የሰጠውን ተስፋ የማይነሣ አምላክ ፭ሺሕ፭፻ ዘመን ሲፈጸም ቀን ቢደርስ አምባ ይፍረስ እንዲሉ፤ በልዩ አመጣጡ በጽኑ ቀጠሮው ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፤ ፴፫ ዓመት ከ፫ወር የጌትነቱን ወንጌል አስተምሮ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ፤ በለበሰው ሥጋ ሞቶ በደሙ ክሶ፤ አዳምን ከነልጅ ልጆቹ ወደ ጥንት ቦታው ወደ ገነት መልሶታልና፤ ተስፋውን የሰጠውና የፈጸመው ጌታን በመውለዷ የአዳም አለኝታ ተስፋው ተብላ ትመሰገናለች። ሊቃውንቱም ይኽነን ታላቅ የድኅነት ሥራ በማድነቅ ‹‹ተፈጸመ ተስፋ አበው በማርያም ድንግል ወበቀራንዮ ተተክለ መድኀኒት

መስቀል›› (በድንግል ማርያም የአባቶች ተስፋ ተፈጸመ በቀራንዮ መድኀኒት መስቀል ተተከለ) እያሉ በያሬዳዊ ዜማ ይኽነን ምስጢር ያሰማሉ።

.....ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን ክፍል አንድ ከሚለው መጽሐፌ የተወሰደ (መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ). ....

..... እመቤታችን ትባርካችኁ። .....

Ethiopian Orthodox Tewahdo Books

33/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ መጻሕፍት አንባብያን ቡድን ዘፈን ለምን ይከለከላል?

. . . ዘፋኝነት የተከለከለበትን ምክንያት በግድ ማወቅ አለብኝ ለምን ትላለህ? ምክንያቱን ማወቅህ አያፀድቅህም አለማወቅህም አያስኮንንህም። ነገር ግን ዘፋኝ ብትሆን ትጠየቅበታለህ። ባትዘፍን ደግሞ ታዛዥ ተብለህ በእግዚአብሔር ዘንድ ትመሰገነበታለህ። ስለዚህ የሚመለከትህን ለምን አታደርግም? ...

. . . ዘፈን ለምን እንደተከለከለ መዘርዘሩ ምስጢሩን እንደሚያጠበው መገለጹ ጽክክል ነው። ቢሆንም ይሕ እንዳለ ሆኖ የተወሰኑ ነጥቦችን በማንሳት የዘፈንን ጎጂ ገጽታ ማሳየት ይገባል።

››› ሀ. ዘፈን የአጋንንት ስራ ነው። አጋንንት ይዘፍናሉና። ለዚህ ምንም ማስተባበያ አያስፈልገውም። መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹በዚያም አጋንንት

ይዘፍናሉ›› በማለት ስለ አጋንን ዘፋኝነት ይናገራል። ኢሳ 13፥21 አትዘፈኑ ማለት የአጋንትን ሥራ አትሥሩ ማለት መሆኑን ተረዳ።

ይህን በተመለከተ መጽሐፈ መቃብያን ደግሞ እንዲህ ይላል፦ ‹‹ . . . እየዘፈኑም ከአጋንንት ጋር ይጫወቱ ነበር። አጋንንትም ጫወታቸውንና ዘፈናቸውንም ሁሉ ያደንቁላቸው ነበር።›› 1 መቃ 36፥27-28 የዚህ ስፍራ አገላለጥ ደግሞ ለየት የሚለውን አጋንንትን ዘፋኞች ብቻ ሳይሆኑ ከዘፈን አድናቂዎች ጎራ መሰለፋቸው ነው።

ዘፈን የአጋንንት ስራ መሆኑን ስታውቅ አይንህ ተገልጦ አንድ ምሥጢር መመርመር ይጀምራል። እስኪ ሀገራችንን ጨምሮ የጃማይካውያንንና የአንዳንድ የአፍሪካንና የሌሎችንም አህጉራት ዘፋኞችን ድርጊት ልብ ብለህ መርምር። ደግሞም ፀጉራቸውን አንጨብርውና በመናጥና በአሸሽ ጦዘው አንገታቸውን በማወናጨፍ የሚዘፍኑት ዘፈን መገኛው ም እንደሆነ ማስተዋል ሞክር። የባለ ዛሮች ዝየራ አይተህ የምታውቅ ከሆነ ፍፁም ተመሳሳይ ሆኖ ታገኘዋለህ።

ባለውቃቤዎችስ ሲደነፉ ተመልከተህ አታውቅምን? የባለ ውቃቤዎች ድንፋታ ደግሞ ቁርጥ እዋኽ፣ እዋኽ እየተባለ የሚዘፈነውን ባህላዊ ዘፈን ይመስላል። ፍከራው ቀረርቶውና በየብሄረሰብ የምትመለከተውን ዘፈንና ጭፈራ ብትመረምር ከዚህ የቀረበ መመሳሰል አታጣበትም። ቅዱስ ሐዊ እንደተናገረው ‹‹ዘፈንና ዳንስ ከሰይጣን የተገኘ›› ነውና።

አጋንንት ዘፋኞች ብቻ ሳይሆኑ የዘፈንና የጭፈራ ዓይነት ሁሉ ምንጮች ናቸውና። ከዚህ በኋላ የእኔ ስጋት ዘፋኞች እና ጨፋሪዎች አዳዲስ የዘፈን እና ጭፈራ መንገድ (ስታየል) ለመከረጅ ሲሉ አጋንንት ያደሩባቸው ሰዎች

ፍለጋ በየፀበል ስፍራው መዞር እንዳይጀምሩ ነው። ምክንያቱም እንዲህ ያሉ ሰዎች የሚሹት ገንዘብንና ዝናን ብቻ እንጂ ሃይማኖት እና ምግባርን አይደለምና።

››› ለ. ክርስትያን የሆነ ሁሉ ዘፋኝነት በቅዱሳን መጻሕፍት የተከለከለ ተግባር መሆኑን ማወቅ አለበት። ዘፋኝነት እንደ መተዳደርያ ስራም ተደርጎ መታየት የለበትም። በዘፋኝነት ‹‹ሥራ›› የተሰማሩ ክርስትያኖች በሃይማኖት ለመኖር ከወደዱ በንስሐ እንደተመለሱ ዝሙት አዳሪዎችና ቀማኞች ሁሉ እነርሱም ሌላ የሰለሰራ አማራጭ መፈለግ ይኖርባቸዋል።

በዘመናችን የሐጢያት ተግባራት በሙሉ ገቢ ማግኛ እየሆኑ መጥተዋል። ገቢ ያስገኘ ተግባር በሙሉ ገቢ ማግኛ እየሆኑ መጥተዋል። ገቢ ያስገኘ ተግባር በሙሉ ግን እንደ ሙያ (ፕሮፌሽን) መቆጠር የለበትም። ‹‹መተዳደሪያዬ ነው›› እያሉ ሕሊናን የሚቆጠቁጥና መንፈሳዊነትን የሚጋፋ ስራ ከመስራት መቆጠብ ያስፈልጋል።

አትሰረቅ አታመንዝር ያለ እግዚአብሔር ‹‹አትዝፈን›› ደግሞ ብሏል። ታዲያ በመንፈሳዊ ጎዳና ለሚመለከተው ዘፈን ከስርቆትና ከምንዝር በምን ይለያል? ሁሉም የእግዚአብሔርን ሕግ በማፍረስ አንድ ናቸውና። ምን ላድርግ? መተዳደሪያዬ ነው እያሉ በዘፋኝነት ጸንቶ ከመኖር አማራጭ መሻት ይበጃል።

በዚህ ዓለም ስጦታው ዘፋኝነት ብቻ የሆነና ሌላ ምንም ዓይነት ተውህቦ (ስጦታ) የሌለው ሰው የለም። እንዲህ ቢሆን ኖሮ ፈጣሪም ዘፋኝነትን ባላወገዘ ነበር። አንበሳ ምግቡ ሥጋ ብቻ ነው። ስለዚህ አንበሳ ሳር እንዲበላ ማድረግ እንደማያቻል ሁሉ ዘፋኞች እንደሌላው ሰው በሌላ የሥራ ዘርፍ

ተሰማርተው መኖር የማይችሉ ቢሆኑ ኖሮ ፈጣሪ ዘፋኝ አትሁኑ የሚል ትእዛዝ አይሰጥም ነበር። ስለዚህ ካሰቡበት እንደሌላው ሰው ሁሉ ዘፋኞችም ሌላ የሰራ አማራጭ አላቸው።

ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ ሥራን አስመልክቶ ሲናገር ‹‹ስለ ተግባረ እድ ግን በዓለም ከሚሠሩ ሥራዎች መንፈሳዊ ህግን ከሚቃወም ሥራ በቀር ሁሉንም ሊሰሩ ይገባል። . . . እንደ ዘፋኝነት፣ እንደ መጥፎ ጨዋታ፣ በእግር አንደማሸብሸብ (ዳንስና ጭፈራ) ካልሆነ በቀር።›› ፍት.ነገ.መን.አን 23፡ 820 ይሕ የአበው ቃል ዘፋኝነት በመንፈሳዊ እይታ እንደስራ መቆጠር እንደሌለበት ያስረዳል።

››› ሐ. ዘፋኝነት ‹‹የስጋ ስራ›› በመሆኑ ሀጥያት ነው። ገላ 5፡21 ስለዚህ ዘፈን መዝፈን በመጽሐፍ ቅዱስ በእጅጉ ይከለከላል። ክርስትያኖች በመንፈሳዊ ሀሳብ መመላለስ እንጂ እንደ ዘፈን ያለውን ስጋዊ ስራ መስራት የለባቸውም። በመንፈስ ተመላለሱ፤ የስጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ›› ተብሏልና። ገላ 5፡16

››› መ. ዘፈን በመንፈሳውያን መጻሕፍት ተወግዟል ዘፋኝነትም ተከልክሏል። ሐመር መጽሔት ይህን ሲያስረዳ ‹‹ዛሬ የአለም ሕዝብ የሚያዘወትረውን ዘፈን ሐዋርያት በትምህርታቸው ደጋግመውና አጥብቀው ተቃውመውታል። ይላል (ሐመር 2ኛ ዓመት ቁ 4 ገጽ 27) በእርግጥም ሐዋርያት በዲድስቅልያ ‹‹አትኩሉ ዘፋንያነ››፤ ‹‹ዘፋኝ አትሁኑ›› ብለዋል። ዲድስ አን 7

ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በቀን እንደምንሆን በአግባቡ እንመላለስ። በዘፈንና በስካር አይሁን›› ብሏል። ሮሜ 13፡13 ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ በስካር እና

በዘፈን የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃል።›› ይለናል 1ኛ ጴጥ 4፡3

በላይኛው አንቀጽ በሰፈረው የሮም ክታቡ ቅዱስ ጳውሎስ ዘፋኝነትን ከዝሙትና ከስካር ጋር አስተካክሎ አስቀምጦታል። ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ ‹‹በቀን ሲዘፍኑ እንደ ተድላ ይቆጥሩታል። ነውረኞችና ርኩሳን ሆነው ከእናንተ ጋር ሲጋበዙ በፍቅር ግብዣ ይዘፍናሉ።›› በማለት ዘፋኝነትን የርኩሳንና የነውረኞች ተግባር አድርጎታል። 2 ጴጥ 2፡13-15

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እነዚህን የዘፈን ሰዎች በሌላ ማንነታቸው ሲገልጻቸው ደግሞ ‹‹ምንዝር የሞላባቸው ኃጢአትን የማይተዉ ዓይኖች አሏቸው። የማይፀኑጽንም ነፍሳት ያታልላሉ። መመኘት የተለመደ ልብ አላቸው። የተረገሙ ናቸው።›› ይላል 2 ጴጥ 2፡13-15

መጽሐፈ ሐዊ ደግሞ ‹‹ከሰይጣን የተገኘ ነውና ዘፈንንና ዳንስን ከኛ ማራቅ ይገባናል።›› ይለናል። መጽ ሐዊ አን 50 ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ደግሞ ከማዘዝ አልፎ ዘፈንን አንተው ዘንድ ‹‹ዘፈንን ትተዉ ዘንድ እማልዳችኋለሁ›› በማለት የማፀናል ተግ ዘዮሐ አፈ 28

ዘፈንን አንተውም ላሉ ደግሞ መጽሐፈ ሐዊ በዘፈን ፀንተው የሞኖሩ ይፈረድባቸዋል›› በማለት ሲያስጠነቅቅ እናገኛለን። መጽ ሐዊ አን 12 ይህ የሐዊ ቃል ሐዋርያው ‹‹የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው። እርሱም ዝሙት .. ስካር፣ ዘፋኝነት እንደነዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም›› ማለት በምን ይለያያሉ?

››› ሠ. ዘፈን በራሱ ኃጢአትና የሥጋ ፍሬ ከመሆኑም ባሻገር በዜማው በግጥሙና ከእርሱ ጋር በተጓዳኝ ባሉ ነገሮች ማለትም በስካር ፣ በዳንስ፣

በጭፈራ በእስክስታና በአጠቃላይ ውዝዋዜን በመሳሰሉ አጋሮቹ በመታገዝ ወደ ዝሙትና ወደ ክፉ ሀጢአት የሚመራ ምንጭ ነው::>> ተብሏልና። እንዲያውም <<ኃጢአት በሰዎች ልቡና ለመንገስ ሲመጣ ከሚያቀርብልን እጅ መንሻዎች አንዱ ዘፈን ነው።>> ሐመር 2ኛ ዓመት ቁ 4 ገጽ 27

የዘፈን ኃይል የሚገፋፋው ወደ ዝሙት ብቻ አይደለም። ማንኛውም ሥጋዊ ስሜት እንዲያይልና ወደ ውጭ እንዲወጣ ያደርጋል። ዘፈን በውስጥህ የሚገኘውን አንድ ዓይነት ሥጋዊ ምሪት ሊያበረታታ ወይም ሊያጠፋን ይችላል። ብታዝን ሆድ እንዲብስህ ያደርጋል ስትደሰት ደግሞ ደስታህን ያለ መጠን ሊያጋንነው ይችላል። ሌላው ቀርቶ አረማመድህን እንኳን ሊቀይረው እንደሚችል አትዘንጋ።

ለምሳሌ፦ ዘፈን መጠጥን በልክህ እንዳትጠጣ መኪናህንም በፍጥነት እንድትነዳ ወይም እንድን የጭካኔ ተግባር ያለ አንዳች ርኅራሄ እንድትፈጽም ሊገፋፋህ ይችላል። በአንዳንድ አገሮች በጣት የሚቆጠሩ ዘፋኞችን የተመረጠ ዘፈን እየሰሙ መኪና ማሽከርከር እስከመከልከል መድረሱ ከላይ ለተጠቀሰው ሐሳብ ምስክር ይሆናል።

>>> ረ. ከላይ በተዘረዘረው መልኩ ዘፈን በአንተ ላይ ምንም ዓይነት ጫና እንደማያደርስብህ ይሰማህ ይሆናል። ነገር ግን አንተ ከብዙዎች ሰዎች የተለየ ማንነት እንደሌለህ ዕወቅ። ያነተ ዘፋኝነት ሌሎች ሰዎችን እንደሚያሰናክል ተረዳ። ስለዚህ ዘፋኝ በመሆንህ ዕውቀትና መንፈሳዊ ጥንካሬ የሌላቸው ሰዎች ሊሰናከሉብህ ስለሚችሉ ስለ ሌሎች ሰዎችም ብለህ አለመዝፈን ጠቃሚ ነው። እንዲህ ከተጠነቀቅህ <<መሰናክልን ለሚያመጣው ለዚያ ሰው ወዮለት!>> በሚለው የአምላክ ቃል ከመውቀስ

ትድናለህ። ማቴ 18፡7

››› ሰ. ዘፈን ስሜትን በመግዛት ሱስ ወደመሆን ይለወጣል። ወደ ሱሰኝነት መለወጡም ሱስ ከሚሆኑ ከሌሎች ነገሮች ማለትም እንደ ጫት ሲጋራ መጠጥና ከመሳሰሉት የማይተናነስ ነው። ይህንንም አንድ ግዜ ከገቡ በኃላ ለማጣት በሚዳክሩ ሰዎች መረዳት ይቻላል። በአጠቃላይ ዘፈን ራስን ከመግዛት ይልቅ ስሜትን በመንካት የስሜት ተገዢነትን ያዳብራል።

ብዙዎች ስለ ዘፈን የሚከራከሩት የዘፈን መልካምነት ከሀይማኖታቸው መልካምነት በልጦ ስለታያቸው ሳይሆን ዘፈን ሱስ እስከመሆን ደርሶ ስለገዛቸውና የገንዘብም ምንጫቸው ስለሆነ ነው። የዘፈን ሱሰኛ መሆን በህይወታችን ውስጥ ማከናወን ያለብንን ብዙ መሠረታዊ ጉዳዮች ቸል እንድንላቸው ሊያደርገን የችላል። በዚህ ምክንያት እኛ ክርስትያኖች ዘፈንና ዘፋኝነት በክርስትና ሕይወታችን ውስጥ ዘልቆ እንዲገባ አንፈቅድም።

››› ሸ. ዘፈን መንፈሳነት ይፈልጋል። ለጸሎት ፣ ለመዝሙር እና ለምስጋና፣ ለመንፈሳዊ ነገር ሁሉ ያለንን ፍቅርና ትጋት እንዲባረድ ያደርጋል። ከዚሕም በላይ ለበጎ ነገር ያለንን ጊዜ በሙሉ ይሻማል። ለዚህም በቤታችን ያለ የቴፕ ማጫወቻ በቀን ለምን ያህል ሰዓት ሲጮህ ይውላል ? ከዚያም ውስጥ መንፈሳዊ ነገሮችን የምንሰማበት ጊዜ ቢሰላ ምን ያህሉን እጅ ይይዛል? ብሎ መጠየቅ ብቻ በቂ ነው።

››› ቀ. ዘፈን መንፈሳዊነትን የሚገፋው ጊዜ በመሻማት ብቻ አይደለም። ሥጋዊ ስሜቶችን በማበረታትና ለመንፈሳዊ ነገር አንዲቀዘቅዝ በማድረግም ጭምር ነው። የዘፈን ተገዢዎች ብዙ ጊዜ ወደ ስጋ ፍቃድ ያዘነብላለሉ።

በቀላሉ ለመግለጽ አንዳንድ የቤተ ክርስትያን ወጣቶች የጸሎት የጸሎት

ሰአት እስኪፈፀም ተሰላችተው ከደጅ ይቆሙና ለመዘመር ብቻ ሲሉ ወደ አዳራሽ ይገባሉ። ይህም ሆኖ በመዝሙር ሰዐት ደግሞ ክንስሐ መዝሙር ይልቅ የቸብቸቦ መዝሙርን ይመርጣና ከበሮ ለመምታት ይሽቀዳደማሉ። ይህም የዘፈን እርሾ ብባቸው መኖሩን ይጠቁማል።

ቀሪውን ከመጽሐፉ እንዲያነቡ እንጋብዛለን

ምንጭ፡-ሕይወተ ወራዙት ክፍል ሁለት

በዲያቆን ጎብረት የሺጥላ

ጎዳር 1999 ፣ አ.አ

I Am Proud To Be A Member Of Sunday School"

34/ ሕፃናትን በውርጃ መግደል እቃወማለሁ !!!

..... ‘መጽሐፍ ቅዱስና ውርጃ’ .....

"""""""

እንደዚኽ አክብሮ የፈጠረውን የሰው ልጅ ዘሩ እንዲቀጥል ፈቃዱ ነውና “ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሏት” (ዘፍ ፩÷፳፯)፤ በማለት የበረከትን ቃል ለወላጆቻችን ለአዳምና ለሔዋን ሰጥቷልና ፅንስ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ፍሬ በረከት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ለመዝመሪያ ጊዜ የሰው ሕይወት የሚዝምረው ከተፀነሰበት ጊዜ ዝምሮ መኾኑን ቢገልጽም ብዙ ሰዎች ግን ይኽን የተፈጥሮ ጸጋ በመቃወም በራሳቸው ስሜት በጎጢአትና በድንቁርና በመጓዝ በብዙ ሚሊየን የሚቈጠሩ ሕፃናትን በአሰቃቂ መልኩ ከእናታቸው ማሕፀን በውርጃ መልክ ወጥተው እንዲሞቱ አድርገዋል።

በዓለም ላይ እጅግ አሰቃቂ መከራን ያደረሰው ኹለተኛው የዓለም ጦርነት ሲኾን በዚኹም ምክንያት 50 ሚሊየን ሰዎች አልቀዋል፤ ይኽነንም መከራ ሲታሰብ በእጅጉ የሚዘገንን ቢኾንም ከዚያ ጦርነት በከፋ መልኩ በዓለማችን በየዓመቱ 50 ሚሊየን የሚደርሱ ሰዎች ውርጃን ሲያኪያኺዱ፤ የዓለም ጤና ድርጅት እንደገለጸው በእኛው አህጉር አፍሪካ ውስጥ እንኳ ከሚከሠተው እርግዝና 15% በውርጃ በመፈጸሙ ምክንያት በየዓመቱ ዐምስት ሚሊየን ሕፃናት በውርጃ መልክ እየተገደሉ ሠላሳ አራት ሺሕ የኾኑ እናቶቻቸውም ለሞት ይዳረጋሉ፤ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት በአጠቃላይ ውርጃ በሕግ ከተፈቀደ በኋላ እስከ አኹን ድረስ በውርጃ መልክ በግፍ የተገደሉ የሕፃንነት ቀጥር አንድ ቢሊየን (1,000,000,000) ይደርሳል (ፅንስ ማቋረጥና መዘዙ፤ ገጽ 1)::

እነዚኽ ኹሉ በሕፃናት ላይ በውርጃ ሰበብ የሚፈጸሙ ዘግናኞች የኾኑ ጭፍጨፋዎች ሲደረጉ አልትራሳውንድን የሚመስሉ ረቂቅ መሣሪያዎች

ተሠርተው ጥንቱን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው እውነት መኾናቸውን እስካሳዩበት ጊዜ ድረስ ፅንስ እስከ ሦስት ወር ድረስ ደም ነው እንጂ ሕይወት የለውም በሚል የተሳሳተ የጎጢአት ሽፋን በመስጠት ነበር። ለምሳሌ ያኽል በዓለም ዐቀፍ ደረጃ በርሳቸው መሪነት ስሳ ሺሕ ውርጃ የተፈጸመ በመኾኑ "የውርጃ ንጉሥ" ተብለው ይጠሩ የነበሩት ፕሮፌሰር በርናንድ ናታን የፅንሱን ኺደት የሚያሳዩ መሣሪያዎች እውነቱን ካወጡ በኋላ እስካኹን ያደረጉት ድርጊት ታላቅ ጎጢአት መኾኑን ተረድተው፤ ንስሓ ገብተው እንዲኽ በማለት ተናግረዋል፦ "እኔ በምሠራበት ዘመን የረቀቁ የሕክምና መሣሪያዎች ባለመኖራቸው ምክንያት ፅንሱ ሕይወት ያለው አይመስለንም ነበር፤ ዛሬ ሳይንስ ኹኔታውን ግልጽ አድርጎታል፤ ታዲያ ከአኹን በኋላ ወዴት ይሸሻል? ምክንያቱም ሳይንስ ከሦስት ወር በታች ያለው ፅንስ ሕይወት እንዳለው በግልጽ አስቀምጦታል" ብለዋል።

በመኾኑም ሰው አስቀድሞ መጽሐፍ ቅዱስን ቢረዳው ኖሮ እስከ ሦስት ወር ድረስ ደም ሊኾን ይችላል ከሚል የስሕተት መላ ምት የተነሣ ይቆጠብ ነበር፤ ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ከተፀነሰን ጊዜ ዠምሮ ነፍስና ሥጋ የሚኾነንን ዘር ከአባት ነፍስም ሥጋም የሚኾነንን ደም (እንቍላል) ከእናታችን እንደምንነሣ ያስተምረናልና ነው። ይኸውም እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከፈጠራቸው በኋላ "ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሏት" (ዘፍ ፩፥፳፰)፤ ብሎ ባዘዛቸው መሠረት ለመዠመሪያ ጊዜ አዳም ሔዋንን በግብር ባወቃት ጊዜ ከአዳም ዘር ከሔዋን ደም ሲከፈል ነፍስም ዐብራ ተከፈለች፤ ደምና ዘር ተቀላቅለው ተዋሕደው ቀስ በቀስ ሥጋ፣ ዐጥንት፣ ዠማት፣ ጠጕር፣ ጥፍር ወደ መኾን ሲራመዱ፤ ነፍስም በበኩሏ ቀስ በቀስ

ሥጋዊ አካል ወይም ገላ ወደ መኾን መራመድ የዠመረውን ፅንስ በማንቀሳቀስ የሕይወት ሥራዋን ትሠራለች፤ ይኽ ከእናት ከአባት ተከፍሎ የዕለት ፅንስ የኾነው ዘርና ደም በዚያኑ ጊዜ ነፍስ አብራው የተከፈለች ባትኾንስ በገበታ ላይ እንደተቀበሉት ደም ለጊዜው ቢረጋም ወደ መድረቅ ይራመድ ነበረ እንጂ ሕያው ወደ መኾን ሊራመድ ባልቻለም ነበር፤ በዚኽ አኳኋን ይኽ ፅንስ በነፍስ ሕያውነት እየተረዳ ቀስ በቀስ አካል ዘየአክልን ገንዘብ አድርጎ የፅንስ ጊዜውን ሲፈጽም ተወለደ፤ ቃየል ተባለ (ዘፍ 4÷1)።

ይኽ የሰው ዘር ኹሉ የሚገኝበትን ድንቅ የእምላክ ሥራን የትዕግሥት መምህር ኢዮብ በምዕ ፲÷፲-፲፩ ላይ “በውኑ እንደ ወተት አላፈሰስኸኝምን? እንደ ዕርጎስ አላረጋኸኝምን? ቍርበትና ሥጋ አለበስኸኝ፤ በዐጥንትና በሽማትም አጠነከርኸኝ፤ ሕይወትና ቸርነት አደረግኽልኝ፤ መጐብኘትኽም መንፈሴን ጠበቀኝ” በማለት ነፍስም ሥጋም የሚኾነውን ዘር ከአባት አብራክ ሲከፈል፤ ነፍስም ሥጋም የሚኾነውን ደም ከእናቱ ነሥቶ በተፀነሰ ጊዜ እናቱ የበላቸው ተጭኖ የጠጣቸው አንዝዞ ሕይወቱ እንዳያልፍ ፈጣሪው የጠበቀው መኾኑን አስተምሯል።

በማሕፀን ያለው ፅንስ ልክ እንደኛው ሥጋና ነፍስ ያለው የእግዚአብሔር ፍጥረት ስለመኾኑ ከሦስት ሺሕ ዓመት በፊት ነቢዩ ዳዊት በመዝ ፺፱÷፪ ላይ፡- “እግዚአብሔር ርሱ አምላክ እንደኾነ ዕወቁ፤ ርሱ ሠራን እኛም አይደለንም” በማለት እንዳስተማረ የእግዚአብሔር ሥራ የኾኑትን ሕፃናትን በማሕፀን ሳሉ በውርጃ መልክ በጭካኔ መጨፍጨፍ በእግዚአብሔር መንግሥት ያስጠይቃል።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠሩ ሰዎችን መግደል ክፉ ኀጢአት መኾኑን በሮቤ ፫፥፲፮-፲፯ ላይ፡- “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ኾናችኁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችኁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር ርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችኁ” በማለት የሕይወትና የሞት ሥልጣን በአምላክ ተይዞ ሳለ ሰዎች ግን በርሱ ሥልጣን በመግባት የንጹሓንን ደም የሚያፈስሱ ኹሉ ተጠያቂ መኾናቸውን አስተምሯል።

በመኾኑም ነፍስና ሥጋችን ተዋሕደው ስላሉ ሰው ተብለን በዚኽ ዓለም ስንመላለስ እንደምንኖር ኹሉ ሕግናትም ከተፀነሱበት ጊዜ ዠምሮ ልክ እንደኛ ነፍስም ሥጋም ስላላቸው ፍጹም ሰው ናቸውና፤ በእግዚአብሔርም ዘንድ የታወቁና የተመረጡ ስለመኾናቸው ክቡር ዳዊት በመዝ ፻፴፰፥፲፫-፲፮ ላይ፡- “አቤቱ አንተ ኵላሊቴን ፈጥረኻልና በእናቴም ኾድ ሰውረኽኛል፤ ግሩምና ድንቅ ኾኜ ተፈጥሬአለኹና አመሰግንኻለኁ ሥራኽ ድንቅ ነው፤ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች፤ እኔ በስዉር በተሠራኁ ጊዜ፤ አካሌም በምድር ታች በተሠራ ጊዜ፤ ዐጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም፤ ያልተሠራ አካሌን ዐይኖችኽ አዩኝ የተፈጠሩ ቀኖቼ ኹሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍኽ ተጻፉ” በማለት ምስክርነቱን ሲሰጥ፤ የእግዚአብሔር ምርጫና ጥሪ ከማሕፀን የሚዠምር መኾኑን ራሱ ጌታ “በኾድ ሳልሠራኽ አውቄኻለኁ፤ ከማሕፀንም ሳትወጣ ቀድሼኻለኁ፤ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌኻለኁ” በማለት ለኤርምያስ ነግሮታል (ኤር ፩፥፭)።

ሰማይ ምድር የማይወሰኑትን አምላክ ፱ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ

የተሸከመች፤ ኪሩቤልና ሱራፌል መንበሩን በፍርሀት ኾነው የሚሸከሙትን ርሱን በዝርባዋ ያዘለች በክንዷ የታቀፈች ቅድስተ ቅዱሳን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በግብረ መንፈስ ቅዱስ አምላክን ፀንሳ ሳለ ወደ ኤልሳቤጥ ቤት በመኼድ ሰላምታን በሰጠቻት ጊዜ ገና በእናቱ ማሕፀን ያለው ዮሐንስ በታላቅ ደስታ ኾኖ እየዘለለ ምስጋናን አቅርቧል፤ እናቱ ኤልሳቤጥም በአድናቆት ኾና “የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይኾንልኛል? እነሆ የሰላምታሽ ድምፅ በዝሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማሕፀኔ በደስታ ዘሏልና ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት” በማለት እውነተኛ ምስክርነቷን ሰጥታለች (ሉቃ ፩፥፵-፵፭)።

ዮሐንስ ገና በእናቱ ማሕፀን ሳለ የተሰጠውና ያገኘውን እውቀት ከ1450) ዓመት በፊት የነበረው ቅዱስ ያሬድ “እምከርሠ እሙ አእመረ ሰገደ ወአንፈርዐጹ” (ዮሐንስ ከእናቱ ማሕፀን ዐወቀ፤ ሰገደ ዘለለም) በማለት የፅንሱን ዐዋቂነት ይኽ በጥበብ መንፈሳዊ የተራቀቀው ሊቅ ቢያስተምርም፤ ዓለም ግን ለብዙ ሺሕ ዘመናት ይኽነን ባለመረዳት በተለይም በ (1690) ዓ.ም እንግሊዛዊዉ ፈላስፋ ጆን ሎክ ሕፃናት ምንም የማያውቁ እንደ ባዶ ነጭ ወረቀቶች ናቸው፤ ከተወለዱ በኋላ በኼደት ከማኅበረሰቡ ጋር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዕውቀትን እያገኙ ይኼዳሉ፤ እውነታን የማወቂያው ብቸኛ መንገድ በሕዋሳት የሚደረገው ልምምድ ሲኾን፤ የእያንዳንዱ አእምሮ ባዶ መጻፊያ ነው፤ በልምምድ ምክንያት ዕውቀት በላዩ ላይ ይሣላል፤ የሚለውን “ታቡላራሳ” በመባል የሚታወቀውን የፍልስፍና ትምህርት ሙጥኝ ብሎ ሲኖር ቆይቶ፤ ነገር ግን በቅርብ ጊዜያት ስለ ፅንስ ኼደት በሚያጠናው የፊቶሎጂ ጥናት ሕፃናት

በተፀነሱ በአራተኛው ወራት የእናታቸውን ድምፅ ለይተው ማወቅ መቻላቸው በመታወቁ ምክንያት በሰለጠኑ ዓለማት ወላጆች በማሕፀን ላሉ ልጆቻቸው ለነርሱ የተዘጋጀ የተረት መጽሐፍ የሚያነቡበት ጊዜ መጥቷል።

በጀርመን ሆስፒታሎች ውስጥ ለረዥም ጊዜ የሠሩት የማሕፀን ስፔሻሊስት ዶ/ር ሔኖክ ገ/ሕይወት በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ውርጃን አስመልክቶ ለሦስት ቀናት በሰጡት ጥናታዊ ማብራሪያ ላይ በጀርመን የተደረገውን ምርምር መሠረት በማድረግ ሲገልጹ፦ በዚያ ሀገር የፀነሱ ሴቶች ገና በማሕፀን ያሉትን ፅንሶች ሰዓት ወስነው በተከታታይነት ሰዓቱ ሲደርስ ልክ እንደተወለደ ልጅ በቃላቸው እንዲያጫውቷቸው ከተደረገ በኋላ በአልትራሳውንድ መሣሪያ በማሕፀን ያሉት ሕፃናት ሲታዩ፤ ያቺ ወላጆቻቸው የሚያጫውቱባት ሰዓት ስትደርስ በደስታ ብድግ ቁጭ የሚሉ መኾኑን ገልጠዋል። በተጨማሪም አንዳንድ የፀነሱ ሴቶች በማሕፀን ያሉ ልጆቻቸውን "ምነው ፀነስኹት" እያሉ የሚያማርሩትና የሚጠሉት ከኾነ፤ ያ ሕፃን ከተወለደ በኋላ አካለ መጠን ሲደርስ ያ ተጽዕኖ አሳድሮበት የአእምሮ ሕመምና የብቸኝነት ስሜት ሊሰማው እንደሚችል በአኹኑ ዘመን የተደረጉትን ጥናቶች መሠረት በማድረግ ከፍ ያለ ትንታኔ ሰጥተዋል።

ይኽነን እውነታ ስናይ ሰው አስቀድሞ መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት ቢረዳው የእግዚአብሔርን ሕግ ቢያከብር ኖሮና ሕፃናት ገና ከተፀነሱባት ቅጽበት ዠምሮ ፍጹም ሰው መኾናቸው ታውቆ በቢሊየን የሚቈጠሩ ሕፃናት በግፍ ከመሞት ይተርፉ ነበር። ዛሬ ግን ለጥቂት ሽርፍራፊ ገንዘብ ሲሉ እውነቱን በሐሰት በመለወጥ እንደ ሄሮድስና እንደ ሰራዊቱ ሕፃናትን በውርጃ መልክ የሚጨፈጭፉ አንዳንድ ሐኪሞች ሰው አያውቅብንም በማለት ሳይንሱን

ለማያውቀው ሕዝብ አጣምመው በማቅረብ የሰውን ጎሊና በማድከም አሰቃቂና አስጸያፊ የጎጢአት ሥራን በሳይንስ ሽፋኝ ይሠራሉ፤ በእውነት ዓለም አኹን የደረሰበት ሳይንስ ይኽነን ይል ይኾን? እስኪ እንመልከት፦

የሳይንስ እውነተኛ ማስረጃ ዘላለማዊ የኾነውን የእግዚአብሔር ቃል የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ሕይወት የሚዘምረው ከተፀነሰበት ጊዜ ዠምሮ እንደኾነ ቢገልጽም ሰዎች ግን ባለማስተዋል ለብዙ ሺሕ ዘመናት በስሕተት መስመር ከተጓዙ በኋላ በቅርብ ዘመናት በተደረጉ የፊቶሎጂ (የዕድገተ ፅንስ) ጥናቶች ሕይወት ሰው በተፀነሰበት ቅጽበት የሚዘምር መኾኑን አረጋግጠዋል። ዘመናዊዉ ሳይንስ በረቀቁ የአልትራሳውንድ መሣሪያዎች እየታገዘ ባደረገው ጥናት ሕይወት የሚዘምረው ልክ በተፀነሱበት ቅጽበት ሲኾን፤ ይኸውም በማሕፀን ውስጥ የሴቷ እንቁላልና የወንዴው ዘር ውሕደት ውሕደ ሕዋስ በመመሥረት ይዘምራል፤ በዚያ ቅጽበት ወንድ ወንድ የሚያሰኝውን ሴትም ሴት የሚያሰኛትን ባሕርይ ሙሉ በሙሉ ታገኛለች፤ ጾታቸው ሳይቀር በተፀነሱበት ቅጽበት ትወሰናለች ትታወቃለች፤ ይኸውም በአንድ ነባ ዘር (46) X ና Y የተሰኙ ሐብለ በራሂ ሲገኙ፤ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ጊዜ X ሐብለ በራሂ (ክሮሞዞም) የያዘ የወንድ ነባ ዘር ከሴቷ እንቁላል በተገናኘ ጊዜ X+X= XX ስለሚኾን የምትፀነሰው ሴት ትኾናለች፤ ዳግመኛም ከሴትዋ እንቁላል የሚዋሐደው የወንድ ነባዘር Y ሐብለ በራሂ ከኾነ X+Y= XY ስለሚኾን ወንድ ይፀነሳል፤ በመኾኑም የወንዱና የሴቷ 23 ሐብለ በራሂ ውሕደት በአጠቃላይ (46) ውሕደ ሕዋስ ያለው ፍጹም ሰው ይኾናል ይላሉ።

በዓለም ያሉት ታላላቅ ሳይንቲስቶች የሥነ ባሕርያት ተመራማሪዎች ኹለት

ጊዜ ማለትም በ (1971) ዓ.ም እ.ኤ.አ ኹለት መቶ ኻያ ሳይንቲስቶች፤ በ(1981) ዓ.ም እ.ኤ.አ (51) ሳይንቲስቶች በአሜሪካ ኮንግረንስ ፊት ቆመው ሕይወት ከፅንስ እንደሚዠምር የእምነት ቃላቸውን እንዲኽ ሲሉ ሰጥተዋል፡-“In biology and medicine, it is an accepted fact that the life of any individual organism reproducing by sexual reproduction begins at conception, or fertilization” (Dr. Micheline M. Matthews-Roth) (በሥነ ፍጥረትና በሕክምና ተቀባይነት ያለው እውነታ የእያንዳንዱ ሕይወት የሚዠምረው ፅንሱ በተፀነሰበት ቅጽበት ነው) ዶ/ር ማሽሊን ኤም. ማቲው ሮዝ ከሐርቫርድ ዩኒቨርስቲ “ሳይንሳዊ የኾነው ተመክሯዊ ማስረጃ የሚያስተምረን ፅንስ በተዠመረ ቅጽበት ሕይወት መጀመሩን ነው” (የዓለማችን ዝነኛው የፊረንሳይ የሥነ ባሕርያት ተመራማሪ ዠሮም ለዠዌን)

“ውርጃን እቃወማለኹ ምክንያቱም በመዠመሪያ ደረጃ በሥነ ሕይወት እንደሚታየው ሰብኣዊ ሕይወት ከጽንስ ስለሚዠምር በኹለተኛ ደረጃ ደግሞ በማንኛውም ኹኔታ ንጹሕ የሰው ደም ማፍሰስ ስሕተት እንደኾነ ስለማምን ነው” (ዶ/ር ላንድራም ሼትልስ በወንድ ዘር ባዮሎጂና በወላድነትና መካንነት ምርምር ላይ ቀዳሚ ተመራማሪ) በመኾኑም የነዚኽ ዓለም ዐቀፍ ታላላቅ ተመራማሪዎች ምስክርነት ሕይወት የሚዠምረው ከተጸነሰበት ጊዜ ዠምሮ እንደኾነ በትክክል ያረጋግጣል።

... የየወራቱ የፅንስ ዕድገት ....

የተፀነሰውን ፍጹም ሰው ከተፀነሰበት ጊዜ ዠምሮ በየወራቱ ያለውን ኺደት

ኖርማን ጌስለርና ፍራንክ የተባሉ ምሁራን “Legislating Morality” (ሌጂስሌቲንግ ሞራሊቲ) በሚለው አስደናቂ መጽሐፋቸው ላይ እንዲኽ ሲሉ ገልጸውታል፡-

የመዝመሪው ወር- መፀነስ

☻ሰብኣዊ ባሕርዮቹ ኹሉ ይፈጠራሉ።

☻በማሕፀን ውስጥ ትክክለኛ ቦታውን ይይዛል (በመዝመሪው ሳምንት)።

☻የፅንሱ የልብ ትርታ መሰማት ይዝምራል።

☻በሕፃኑ የደም ሥሮች ውስጥ ደም ይዘዋወራል፤ አብዛኛውን ጊዜ የሕፃኑ የደም ዐይነት ከእናቱ የደም ዐይነት ይለያያል።

ኹለተኛው ወር- ዕድገት

☻አንጐሉ ኤሌክትሮኢንሴፋኖግራም (electroencephalogram) በሚባል መሣሪያ ሊለካ የሚችል ንዝረት (ሞገድ) ይፈጥራል።

☻አፍንጫው፣ ዐይኑ፣ ዦሮውና የእግር ጣቶቹ መታየት ይዝምራሉ።

☻አካላዊ ሥርዐቱ በትክክል መሥራት ይዝምራሉ።

☻የራሱ የኾነ የእጅ አሻራ ይኖረዋል።

☻ምላሱን መንካት ይችላል።

☻የራሱ የኾነ የእጅ አሻራ ይኖረዋል።

☻ምላሱን መንካት ይችላል።

ሦስተኛው ወር- እንቅስቃሴ

☻መዋጥ፣ መመልከት፣ መንቀሳቀስ ይችላል።

☻በእጅ ለመያዝ እንዲኹም ምላሱን ለማንቀሳቀስ ይችላል።

☻እጁን መጥባት ይችላል።

☻ሕፃኑ በማሕፀን ውስጥ የሚገኘውን አሚኒዮቲክ ፈሳሽ መዋጥ፣ መተንፈስና መሽናት ይችላል (ከ 10-11 ሳምንት)።

☻የሕፃኑ የፊት ጡንቻዎች እንቅስቃሴ ይዘምራሉ፤ እንዲያውም ፈገግታን ሊፈጥሩ ይችላሉ (በ 11 ሳምንት)።

☻አካላዊ ሕመም ሊሰማው ይችላል (ከ 8-13 ሳምንት)።

አራተኛው ወር- ፈጣን ዕድገት

☻ክብደቱ ስድስት ዕጥፍ ያድጋል።

☻ከ 8-10 ኢንች ዕድገት ያሳያል።

☻የእናቱን ድምፅ ሊሰማ ይችላል (ለይቶ ያውቃል)።

አምስተኛው ወር- ከማሕፀን ውጪ መኖር ይችላል

☻ቆዳው፣ ጠጉሩና ጥፍሩ ያድጋል።

☻ሕልም ያልማል (REM sleep)።

☻ማልቀስ ይችላል (አየር ካለ)።

☻ከማሕፀን ውጪ መኖር ይችላል (Legislating Morality, Norman Gesiler p.150 ሚኒሊክ አስፋው፤ 1999፤ “ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳዮችና ተግዳሮቶች” ገጽ 207-208፤ ፅንስ ማቋረጥና መዘዙ፤ ገጽ 4) ።

የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ሊታወቅ፤ የሕፃናቱ ፍጹም ሰው መኾን ሊመሰከር በአራት ወር ተኩል፤ በዐምስት ወር ተወልደው ያደጉም አሉ፤ ለምሳሌ ኬንያ ኪንግ የተባለችው ሕፃን የተወለደችው በ፲፱ (19) ሳምንቷ ሲኾን፤ ሊዛ ኪንግ ኬንያ (እናቷ)በፍሎሪዳ ሰኔ ፲፯/ ፲፱፻፹፭ (1985)

ስትወልድ የሕፃኗ ክብደት ዐሥራ ስምንት አውንስ (ounces) ብቻ ነው።

ዳግመኛም የካቲት ፲፫/ ፲፱፻፺፱ (1999) ዓ.ም በአሜሪካ ሀገር ማያሚ በተባለችው ክፍለ ግዛት የዐምስት ወር ሕፃን በሰላም ተወልዳ፤ ዜናው በቢቢሲና በእኛም የዜና ማሰራጫዎች ተላልፏል፤ ይኽነን ኹሉ እውነታና የስመ ጥሮቹ ሳይንቲስቶች ግኝት ፅንስ ከተፀነሰበት ቅጽበት ዠምሮ ፍጹም ሰው መኾኑን የሚያስተምረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያረጋገጠ ነው። እውነቱ ይኽ ኾኖ ሳለ በጊዜያችን አንዳንድ ሰዎች ከአጋንንት በተማሩት መጠን ሐሰትን ገንዘብ በማድረግ ለነላፊ ገንዘብ ሲሉ በግፍና በጭካኔ ለሕልውናቸው መከራከር የማይችሉ ሕፃናትን በውርጃ መልክ ልክ እንደ ሄሮድስ ሰራዊት በጭካኔ እየጨፈጨፉና እያስጨፈጨፉ ይገኛሉ፤ ጥንቱን ዲያብሎስ በጨካኙ አምላኩን በማይፈራው በቃኤል ዐድሮ የዋሁ አቤል እንዲሞት እንዳደረገ ዛሬም ከቢሊየን በላይ ሕፃናትን በውርጃ መልክ ደማቸው እንዲፈስስ አድርጓል።

ይኽ ጭካኔና ነፍሰ ገዳይነት አስቀድሞ የተገኘው ከዲያብሎስ ነውና፤ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ ክፉዎች አይሁድን በዮሐ ፰፥፵፬ ላይ “እናንተ ከአባታችኁ ከዲያብሎስ ናችኁ፤ የአባታችኹን ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችኁ፤ ርሱ ከመዠመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመምና፤ ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራልና፤ ሐሰትና የሐሰትም አባት ነውና” በማለት ገሥጿቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ እንደምናነበው የሴት ልጆች እግዚአብሔርን ማመስገን ትተው ከደብር ቅዱስ ወርደው ከቃየል ልጆች ጋር ተቀላቅለው ብዙ የዝሙት ሥራና የክፋት ሥራን

በሚሠሩ ጊዜ አጋንንት እጅግ ክፉ የኾነ የጎጢአትን ሥራ አስተምረው ነበር፤ ከእነዚኽ መኻከል ካዕድያዕ የተባለው ጋኔን በናቱ ማሕፀን ያለ ፅንስ ወጥቶ ይወድቅ ዘንድ ፅንስ ማስወረድን ነፍስን መግደልን ለሰዎች አስተምሯልና ውርጃን ለመዘመሪያ ጊዜ ለሰዎች ያስተማረው ሰይጣን ነው (ሔኖ ፲፱÷፭፯-፭፰)።

ያን ጊዜ ዲያብሎስ ያስተማረው ሕፃናትን የመግደል ኺደት ዛሬም በመቀጠል በቢሊየን የሚቈጠሩ ሕፃናት በውርጃ መልክ በግፍ ሲያልቁ፤ ውርጃ በተፈቀዱባቸው ሀገራት አውሬው ዲያብሎስ ሥራውን የሚስፈጽምባቸው ሰባት አሰቃቂ ከባድ የውርጃ መንገዶች አሉ። በተጨማሪም ከውርጃ ጋር የሚመሳሰል ፅንስ ከተፈጠረ በኋላ የተፈጠረውን ፅንስ የሚገል ሉፕ የተባለ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ ሲኖር ምሁራኑ “ፅንስ ማቋረጥና መዘዙ” በሚለው መጽሐፋቸው የሉፕን ገዳይነት በትክክል እንዳስቀመጡት፦ “አብዛኛውን ጊዜ የወንዱ ዘርና የሴቷ እንቁላል ተገናኝተው ፅንስ የሚፈጥሩት በሴቷ የዘር መተላለፊያ ቱቦ ላይ ነው፤ እስካኹን እንደተረዳነው ይኽ ግንኙነት ውሕደ-ሕዋስ ይፈጥራል፤ በዚኽ ቅጽበት የፅንስ ሕይወት ዠመረ ማለት ነው፤ ይኽ ውሕደ-ሕዋስ ከቱቦው ወደ ማሕፀን ይጓዝና በማሕፀን ውስጥ ከገባ በኋላ በአንደኛው የማሕፀን ግድግዳ ላይ ስፍራን በመያዝ ያድጋል፤ ሉፕ ባለበት ማሕፀን ግን ይኽ ውሕደ-ሕዋስ በማሕፀን ግድግዳ ላይ ስፍራ እንዳይዝና እንዳያድግ ሉፕ በመከላከል ፅንሱን ያፈርሰዋል፤ ይገድለዋልም፤ ይኽ የፈረሰ ውሕደ-ሕዋስ ደም መስሎ ከማሕፀን ይወጣል፤ በውጪ ሀገር የክርስቲያን ሆስፒታሎች ሉፕ አጥብቆ የተከለከለና የተወገዘ ነው፤ ስለዚኽ ሉፕና ውርጃ ውሕደ-

ሕዋስ (ፅንስ) ከተፈጠረ በኋላ የሚሠሩ ዘዴዎች ስለኾኑ ከነፍስ ግድያ ተለይተው አይታዩም፤ ለምሳሌ ሉፕ (በማሕፀን ውስጥ የሚገባ ፕላስቲክ መሰል ነገር) የሚሠራው ፅንሱ በማሕፀን ውስጥ የሚገባውን ስፍራ ይዞ እንዳያድግ በመከላከል ነው፤ ስለዚኽ ይኽን መሰል አሠራር ያላቸው የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች ሳይኾኑ ፅንስ አፍራሾች ወይም ነፍሰ ገዳዮች በመኾናቸው ልንጠቀምባቸው አንችልም ማለት ነው።" በማለት የሉፕን አደገኛነት ጠበብቱ እውነታውን ገልጸውታል (ፅንስ ማቋረጥና መዘዙ፤ ገጽ 53)።

እውነታው ይኽ ከኾነ አንዳንድ የሕክምና ሰዎች ግን ለጥቅማቸው በማሰብ ትክክለኛውን ሳይንሳዊ እውነታ አጣምመው በማቅረባቸው ምክንያት በርካቶች የሀገራችን እናቶች ባለማወቅ ሉፕን በመጠቀም ብዙዎች ፅንሶች እንዲሞቱ አድርገዋል ማለት ነው፤ ኾኖም ግን ታላቅ ከኾነው ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍርድ ለመዳን ሳያውቁ በሠሩት ኀጢአት በመጸጸት ንስሓ ገብተው እግዚአብሔርን መማጸን ይገባቸዋል፤ ልዑል እግዚአብሔርም አስቀድሞ በነቢዩ በኢሳይያስ ዐድሮ "እጃችኹንም ወደ እኔ ብትዘረጉ ዐይኔን ከእናንተ እሰውራለኁ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችኹም እጆቻችኁ ደም ተመልተዋል፤ ታጠቡ ሰውነታችኹንም አንጹ የሥራችኹን ክፋት ከዐይኔ ፊት አስወግዱ ክፉ ማድረግን ተዉ፤ መልካም መሥራትን ተማሩ፤ ፍርድን ፈልጉ፤ የተገፋውን አድኑ፤ ለድኻ አደጉ ፍረዱለት ስለ መበለቲቱም ተሟገቱ፤ ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኀጢአታችኁ እንደ አለላ ብትኾን እንደ ዐመዳይ ትነጻለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች፤ እሺ ብትሉ ለእኔም

ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችኁ፤ እምቢ ብትሉ ግን ብታምፁም ሰይፍ ይበላችኁል የእግዚአብሔር አፍ ይኽን ተናግሮአልና ፍርድ መልቶባት የነበረው የታመነችዪቱ ከተማ እንዴት ጋለሞታ ኾነች! ጽድቅ ዐድሮባት ነበር፤ አኹን ግን ገዳዮች አሉባት" በማለት አስጠንቅቋልና ከዘላለማዊ ቅጣት ለመዳን የእግዚአብሔር ልጆች ሆይ በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠሩ ሕፃናትን በውርጃ ከመግደል ከዚኽ አስከፊ ከኾነ የኀጢአት ሥራ ኹሉ እንድንቆጠብ ሕያው ቃሉ ያስተምረናል (ኢሳ ፭፣፲፭-፳፩)።

መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

'ከመጽሐፍ ቅዱስና የሕክምና ሳይንስ' መጽሐፍ የተወሰደ —

Miko ZE Ethiopia

POSTED BY ADDIS ALEMAYEHU

35/ ቃልህ ለጕሮሮዬ ጣፋጭ ነው ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ።

(መዝ 119፣103)

«መጽሐፍ ቅዱስ »

††

እሳት (ኤር.23፡29)

መዶሻ (ኤር 23፡24)

መብራት (መዝ 119፡105)

መስታዎት (ያዕ 1፡23)

ወተት (1 ጴጥ.2፡2)

በትር (ራዕ 11፡1-2)

ዘር (1 ጴጥ.1፡23)

(ሉቃ.8፡22)(ያዕ.1፡18)

ሰይፍ (ዕብ.4፡12)

ውሃ (ኤፌ.5፡26) (ዮሐ 15፡3)(17፡17)(መዝ.119፡5፣9)

ወርቅ (መዝ.19፡10)(ራዕ.10፡10)

ማር (መዝ.19፡10)

ሚስማር (ችንካር) (መክ.12፡11)

ዳቦ (ዘዳ.8፡3) (መዝ.119፡103) (ኢሳ.55፡10)

ዕንቁ (ማቴ.7፡6)

መልኣክ (ዕብ.6፡18-19)

ኮከብ (2 ጴጥ 1፡19)(ራዕ.2፡28)

ስጋ (ዕብ.5፡14)

ነው።

ስለ ቅዱስ ቃሉ ልዑል እግዚአብሔር ይመስገን አሜን።

Gebre Egziabher Kide

36/ ††† ተወዳጅ ሆይ! አምላክህ እንዴት እንደሚወድህ አስተውል፤ ፍቅሩንም ተረዳለት። እርሱ ሲፈልግህ አንተ ለምን ትሸሻለህ? እርሱ ሲጠራህ ለምን አቤት አትልም? አንተን ለማዳን ርሱ ከአንተ ከባርያው ጋር ሲከራከር አንተ ለምን ትርቃለህ? እስኪ ለማዳመጥ እንኳን ጥቂት ጊዜ ስጥና የተደረገልህን ጥቂት አሰላስለው። ላንተ፣ ለእኔ፣ ለአንቺ፣ ለኹላችንም በቀራንዮ የተከፈለውን እስኪ ቆም ብለህ አስበው፤ ኹላችንም እናስበው። እስኪ አባቶች ይንገሩን፤ እኛም እንስማ፡-

“... ያን ጊዜ ነፍሴ እስከ ሞት ደርሳ አዘነች አለ። ይኸውም ያዘኑትን ደስ የሚያሰኛቸው ነው። በዚያች ሌሊት ያዙት። በነጋም ጊዜ የአይሁድ መምህሮችና የካህናት አለቆች ከገዢ ከጲላጦስ ጋር ሊፈርዱበት በአደባባይ ተቀመጡ። የመላእክት ሠራዊት በመንቀጥቀጥ የሚቆሙለትን በፊታቸው አቆሙት።

ክፉ ባርያ እርሱን ያልበደለውን በጥፊ ይመታው ዘንድ እጁን አጸና። የመላእክት አለቆች በፍጹም ድንጋጤ ለሚሰግዱለት ለርሱ በትዕቢት ይሰግዱ ዘንድ አጐነበሱለት። የሕይወትን ራስ የሾኽ ዘውድ ደፋበት። ብርሃንን እንደ ልብስ የሚጐናጸፈውን ልብሱን ገፈው ቀይ ግምጃ አለበሱት።

ወደሚሰቅሉበት ስሙ ቀራንዮ ወደሚባል አገር ወሰዱት። መስቀሉን አሸከሙት። ኢየሱስም መስቀሉን በመሸከም ደከመ፤ ወዛ፤ ከባድ ነውና። ከወንበዴዎች ጋራ ቈጠሩት። ወደ እንጨትም አውጥተው ምሕረት የሌለው ስቅለትን እንደ ሕጋቸው ሰቀሉት።

አዳምን የፈጠሩ እጆች ወዮ በመስቀል ችንካር ተቸነከሩ። በገነት የተመላለሱ እግሮች ወዮ በመስቀል ችንካር ተቸነከሩ። በአዳም ፊት የሕይወትን መንፈስ እፍ ያለ አፍ ወዮ ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ መጻጻንና ከርቤን ጠጣ።

ኢየሱስም በመከራው ጮኸ። ወደ አባቱ ጮኸ። ራሱን ዘንበል አደረገ። ያን ጊዜ ነፍሱ ወጣች (ተለየች)። ለርሱ ብለው ባሠሩት በጥቁር ጦር ጐኑን ወጉት። ከእንጨት አውርደው በመቃብር አኖሩት። በነርሱ መቃብር ያኖሩት አይደለም። ከከተማ ውጪ ሦስት ክንድ በሚኾን በስደተኛ መቃብር ነው እንጂ። በደንጊያም ገጠሙት። በዚያም ሳለ ወደ ባርያው ወደ አዳም ወደ ልጆቹም ኹሉ ጮኸ። ይኽንን ለባርያው ለአዳም በተናገረ ጊዜ አዳም ደስ አለው። ከልጆቹ ኹሉ ጋር ወጥቶ ወደ ቅድስት አገር ገባ።" /ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት ቁጥር 88-91/።

ወዳጄ ሆይ! የአኹኑ አዳም እኮ እኔና አንተ ነን። እኅቴ ሆይ! የአኹኗ ሔዋን አንቺ ነሽ። ታድያ ለምን አባታችንን አቤት አንለውም? እናቱ ስትጠራው አቤት የማይል ልጅ ማን ነው? ታላቅ ወንድም ሲጣራ አቤት ጋሼ የማይል ልጅ ማን ነው? ሚስት ስትጣራ አቤት የማይል ባል ማን ነው? ባል ሲጣራ አቤት የማትል ሚስት ማን ነች? ታድያ እግዚአብሔር እኮ ከእነዚኽ ኹሉ ነው።

ወዳጄ! ከንፈርህን ብቻ በመምጠጥ አትዘን። ከዚያ ባለፈ የሚጠቅምህን አድርግ እንጂ። ወስንና አባትህን አቤት በለው። ንስሐ አባት ካልያክ ዛሬ ነገ አትበል። ንስሐ አባት ከያዝክ ወደ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ቅረብ። ወደ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ከቀረብክም ቅድስናኽን አጽንተህ ያዝ።

ክርስትና ነጻነት እንጂ ባርነት አይደለም፤ በመኾኑም ራስኽን ነጻ አውጣ። እመነኝ ስትቀምሰው ትመሰክራለህ!!!

"የምናስተውል ካለን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል"፤

37/ በሚሞት ስጋችሁ ሐጢያት አይንገስ

ብልቶቻችሁን የፅድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ (ሮሜ 6፥12-14)

ከሴት ጋር አለመገናኘት መልካም ነው ካልተቻለ ዝሙትን ለመከላከል በአንድ ይፅና ከዚህ ውጭ ጉዞ ወደ እሳት ነው (1ኛ ቆሮ 7፥1)

ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱ ያፈርሰዋል ቤተ መቅደሱም እናንተው ናችሁ (1ኛ ቆሮ 3፥17)

ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእረፍትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸፍኑ (1ኛ ጢሞ 2፥9)

የወንድ ልብስ የለበሰች ሴት በእምላክ ዘንድ የተጠላች ናት (ዘዳ 22፥5; ዘፀ 39፥28)

ፀጉሯን ሳትሸፍን የምትፀልይ ሴት እራሷን ያዋረደች ናት(1ኛ ቆሮ 11፥5)

የወይን ጠጅ ከሚጠጣ ጋር አትቀመጥ (ምሳ 23፥20)

ዘፈን የሰነፎች ዜማ ነው (መክ 7፥5)

በዛም አጋንንት ይዘፍናሉ (ኢሳ 13፥21)

መምህር ዲያቆን ፋሲካ ደመቀ

38/ ዲያቢሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ እናንተ ወርዷል። የዮሐንስ ራዕይ 12÷12

ውድ የተወደዳችሁ የፌስቡክ ወዳጆቼና በአንድም በሌላም መንገድ ይህ ፅሁፍ የሚደርሳችሁ ሁሉ የእግዚአብሔር ሰላምና ፍቅር ይብዛላችሁ!!!

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው ዲያቢሎስ ጥቂት ዘመን እንደቀረው አውቆ ነው የሚለው። ዲያቢሎስ እኮ ከቅዱሳን መላዕክት እኩል የተፈጠረና ጌትነትን በመሻቱ የተነሳ የተጠለ፣ የትላንትው እባብ የዛሬው ዘንዶ ነው። እንግዲህ አስተውሉ ወገኖቼ የዲያብሎስ ትልቁ ጥበቡ ጊዜን ማወቁ ነው። የእኛ ደግሞ ትልቁ ስንፍና ጊዜን አለማወቃችን ነው። ዲያቢሎስ እኮ ትላንትና የነበረ ፣ ነገም የሚኖር የተሸነፈ እንጂ የሞተ ያይደለ ጠላት ነው። እኛ ግን ትላንት ታይተን ዛሬ፣ ዛሬም ታይተን ነገ የማንታይ ዘመናችንም እንደ ጠዋት ጤዛ ጥቂትም ታይቶ ቶሎ እንደሚጠፋ እንደ እንፋሎት ነው። ታዲያ እረጅም ዘመን የኖረውና ገና ወደፊት የሚኖረው ዲያቢሎስ የቀረኝ ጥቂት ዘመን ነው ብሎ በታላቅ ቁጣ ከወረደ ምናለ እኛም ዘመናችን ቢበዛ ከሃምሳ እስከ ሰባና

ሰማኒያ የሆንን ትውልዶች እከሌና እከሊት ተጋቡ፣ እከሌና እከሊት ተፋቱ። እከሌ ዘመረ፣ እከሌ ዘፈነ። እከሌ ታሰረ፣ እከሌ ተፈታ... በሚሉና በመሳሰሉት እርዕሰ ጉዳዮች ጊዜያችንን ከምናባክን ምን አለበት ከእውነት ጋር ተሰልፈን ስለእውነት ብናልፍ። ምናለበት ዲያቢሎስ በታላቅ ቁጣ እንደወረደ እኛም ትንሽ ጊዜ እንደቀረን አውቀን በታላቅ ፍቅር ወደ ባልንጀሮቻችን ዘንድ በይቅርታ መንፈስ ብንወርድ። ምናለበት እግሮቻችን የታመሙትንና የታሰሩትን ለመጠየቅ ቢፈጥኑ። ምናለበት እጆቻችን ደም ለማፍሰስ ሳይሆን ለምፅዋት ቢዘረጉ። ምላሶቻችንስ ከአሜት ይልቅ ምስጋናና ቢለምዱ የተሻለ እንደሆነ አትቆጥሩም? በእውነት ስለ እውነት ምዬ እነግራችኋለሁ ዘመናችን አጭር ነውና ከአሁን እንንቃ። ዘመናችንን እየተገረምንበት ሳይሆን እንደ ቃሉ እየኖርንበት እንለፍ። በዘመናችን በሚሆነው ነገር መገረም ሳይሆን ከእኛ የሚጠበቀው፣ ቤተሰብንና ሀገርን፣ ህዝብና መንግስትን የሚያስገርም ስራ መስራት ነው፣ ከሁሉ በላይ ቤተክርስቲያንና እግዚአብሔርን የሚያስደስት ስራ ሰርተን በእሊናችን እንረፍ፣ ከመቃብር በላይ የሆነ ተግባር በፈፅምና አንድ ሀዲስ ታሪክ በመስራት ስማችንን ተክለ እንለፍ የቀረን ጥቃት ዘመን ነውና። ቀሪው ዘመናችንን እንደ ጌታ ሀሳብና ፍቃድ እንድንኖር እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን። የቀረውን ነገር ሁሉ ሳልቆጥር የእግዚአብሔር አባታችን ሰላምና ፍቅር እንዲበዛላችሁ የዘወትር ምኞቴ ነው። ጌታ እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ህዝቧን ይባርክ!!!

ይህንን ፅሁፍ አንብባችሁ አንዳች ቁምነገር አግኝተንበታል የምትሉ ብቻ ለሌሎች ሼር አድርጉላቸው።

Like . ገኒ የማሪያም ልጅ

Amen Amen Amen

kale hiwet yasemaln tesfa mengste semayatn yawursln amen

በእውነት እንደ እንጀራ ተፈትፍቶ የሚጎረስ ቃል ነው እግዚአብሔር በነገሮች ሁሉ ይቅደምልን ማስተዋልና ጥበቡን ያድለን አሜን

Like . Tsiyon Sileshi

Andamlak Wolde ትክክለኛአውን መልስ መልሰህለታአል ። መምህር ግርማ ወንድሙ እግዚያብሄር ከሁሉ በላይ መርጦ ይህን የመሰለ ፀጋ ሥለሰጣአቸው ብዙ የህይማኖት መሪዎች እንዲሁም አገልጋአዮች ይቀኑባአቸዋአል እግዚያብሄር የተሰጣአቸውን ፀጋ ማንም ሊቀማቸው አይችልም ። እኚ አባአት ፈውሥ መፈወሥ ከጀመሩ ከ 11 አመት በላይ ሆኑአቸዋል ። በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላአው አለም እምነታአችን ህይማአኖታአችን ፈዋአሽ እና አዳኝ መሆኑን እግዚያብሄር በሳአቸው ላይ አድሮ ድቅ ታአምራቱን አሳይቱል !! ሥለዚህ መላአው የክርሥትእና ህይማኖት ተከታዮች ይህንን ፍትህ የጎደለው ክሥ ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ ልንቃወም ይገባል ። አባታችን መምህር ግርማአንም እግዚያብሄር አምላክ ጠብቆ በሰላም ያሥፈታአልን አሜን !!

Yeshiber Fentahun-የሸበር ፈንታሁን

39/ ‹‹አትፍረድ ይፈረድብሃል››

ቆይ እኔ የምለው! የውጨ መናፍቅና ሰይጣን አባታችን መምህር ግርማን ቢቃወማቸውና በሀሰት ቢመሰክርባቸው አይገርመኝም ነገር ግን የህዝብ አስተማሪና የሀይማኖት ሰው ነን የምትሉ ለምን ይሆን አባታችንን "የሀሰት አጥማቂ ነው" እያላችሁ ራሳችሁን ብቻ ምሁርና አዋቂ አድርጋችሁ የዋህ የሆነውን ምዕመናን ግራ የምታጋቡት? እስኪ ራሳችሁን እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ "እውነት በአውደምህረቱና በየአዳራሹ ቁሜ ለምእመናኑ የምሰብከውንና የማስተምረውን ትምህርት፣በኢንተርኔቱና በሚድያው ለህዝቡ የምለቀውን ብሎግ በህይወቴ ውስጥ እተገብረዋለሁ ወይ?"

መልሱን ለእናንተ እተወዋለሁ ምክንያቱም ማንነታችሁንና ስራችሁን ከማንም የበለጠ ራሳችሁ ታውቁታላችሁ!

አይደለም እኛ ሀጢያተኞቹ ፍፁምና ፃድቅ የሆነው እየሱስ ክርስቶስ በሀጢያተኞች ላይ አልፈረደም ታዲያ እኛ እነማን ሁነን ነው በመምህራችንና በአባታችን የምንፈርደው? በእግዚአብሔር ፊት ሀጢያትና በደላችን በዝቶ ሳለ ስለራሳችን በደል ንሰሀ በመግባት ፋንታ በሌሎች ላይ እየፈረድን ራሳችን ላይ ፍርድን እናበዛለን።አውደምህረቱ ላይ የምትቆሙት ምህረቱ ስለበዛላችሁ እንጂ ፃድቅ ስለሆናችሁ አይደለም። በእግዚአብሄር ፊት ማንም ፍፁም የለም ስለዚህ ማናችንም በማናችንም ላይ ልንፈርድ ወይም ልንዘባበት አይገባንም የሌሎችን ፍርድ እንዳንሸከም እንጠንቀቅ።

ፍቅር የሆነ እግዚአብሔር ፍቅርን ነው ያስተማረን እንጂ በሰው ላይ በሀሰት መፍረድን አይደለም እናንተ ግን ስለፍቅር ምእመናኑን እየሰበካችሁ ነገር

ግን እርስበርስ ፍቅር የሌላችሁ! በአንደበታችሁ እየኖራችሁ በተግባር የሞታችሁ! ሌላ ምን ይባላል እግዚአብሔር ልቦናውን ይስጣችሁ!

የእግዚአብሔር የሆነ ሰው በመከራ እንዲያልፍ ግድ ነውና አባታችንን ብቻ አይደለም ሌሎችም ስለሀይማኖታቸው ሲሉ በእስራትና በመከራ በአለም ዙሪያ የሚገኙትን ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር ይጎብኝልን! ዛሬ ቀኑ ገብርኤል ነው እርሱ መላእክቱን ልኮ ሰንሰለታቸውን ይበጥስልን! እመቤቴ ዋስ ጠበቃ ትሁንልን!

እኔ ከብዙ ጠንካራ ምዕመናን አንድ ተራ የማልረባ ደካማና ሀጢያተኛ ስሆን የማመልከውም ሰውን ሳይሆን በመስቀሉ ስለኔ ቤዛ ሊሆን በሀሰተኛ ፈራጆች በፈሪሳውያን እጂ በገዛ ፍቃዱ ተይዞ በቀራንዮ የዋለውንና የተሰቀለውን፣በሶስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጎ የተነሳውን፣ በፍርድ ቀን በጌትነቱ የሚመጣውን የወላዲተ አምላክ የቅድስት ድንግል ማርያም ልጂ እየሱስ ክርስቶስን፣የሁሉ ፈጣሪ ስላሴን፣እግዚአብሄርን ብቻ ነው።

ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምሩትን፣የሚሰብኩ ትን፣ስለድንግል ማርያም፣ስለሰማዕታትና ስለቅዱሳን መላእክት የሚመሰክሩትን፣በስማቸው ጥንተ ጠላታችን ሰይጣንን የሚያሳድዱትን፣በፀበላቸው የሚፈውሱትንና ባጠቃላይ የተዋህዶ ኩራት የሆኑትን ሁሉንም አስተማሪወችና የእግዚአብሔር ፀጋ የበዛላቸውን አባቶች አከብራለሁ፣እወዳለሁ ነገር ግን በጥላቻና በቅናት መንፈስ ወደ ሌላው እጃቸውን የሚቀስሩትንና እርስበርሳቸው የማይዋደዱትን አጥብቄ እቃወማለሁ።

ይህ የእኔ አመለካከት ነው (This is my personal opinion

and it may not necessarily reflect the opinion of you or others) በዚሁ መልእክት ከተስማማችሁ ለሚመለከታቸው እንዲደርስና እንዲያነቡት ይልቁንም ራሳቸውን እንዲመለከቱና እንዲፈትሹበት ሼር አድርጉት!

(ለወንድሞቹ:-ከምስሉ ላይ የተፃፈውን መልእክትም አስተውለን እንተግብረው)

ተዋህዶ አንዲት ናት ፈራጁም እግዚአብሔር ብቻ ነው!

እግዚአብሔር እንደ ሰው ለመፍረድ አይቸኩልም!ያለምክንያትም ዝም አይልም!

ያለድንግል ማርያም አማላጅነት አለም አይድንም!

የሸበር ፈንታሁን(ሀይለ ጊዮርጊስ)

ጥቅምት 19(እለተ ገብርኤል),2008

Pawlos Kukuyu

40/ ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ እነሆ

1: ስለ ሥላሴ

የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት:-

ዘፍ 1:26 ዘፍ 3:22

ዘፍ 11:18 ዘፍ 18:1-2

ኢሳ 48:26 ማቴ 3:16-17

ማቴ 28:19 ሉቃ 1:35

ዮሐ 7:28-29 ዮሐ 14:25-26

ሐዋ 3:14 1 ኛ ቆሮ 12:4-7

2 ኛ ቆሮ 13:14 ኤፌ 4:4-7

2: ስለ እመቤታችን ቅድስናዋ ፣ ክብሯ ፣ ድንግልናዋና አማላጅነቷ:-

መዝ 9:11 መዝ 13:10

መዝ 44:9 መዝ 86:5

መዝ 131:13 መዝ 44:2

መኃ 4:12 ኢሳ 7:14

ኢሳ 49:23 ኢሳ 60:14

ማቴ 1:23 ሉቃ 1:28

ሉቃ 1:42 ዮሐ 2:1-11

ዮሐ 19:16 ሮሜ 11:26-27

2 ኛ ቆሮ 11:2 ራዕ 12:16

3: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም፥-

ዘፍ 3:22 1 ኛ ሳሙ 16:1

ኢሳ 9:6 ዳን 7:14

ሆሴ 13:4 ዘካ 9:9-10

ሚክ 5:2 ሉቃ 1:32-33

ዮሐ 10:30 ሉቃ 2:12

ዮሐ 14:7 ሮሜ 9:5

ቆላ 2:9-10 ቲቶ 2:11-13

ዕብ 1:3-4 ዕብ 1:10-11

1 ኛ ጴጥ 3:23 1 ኛ ዮሐ 2:23

ራእ 3:22 ራእ 22:12-13

4: ስለ ታቦትና ጽላት

ዘፀ 24:12 ዘፀ 25:10

ዘፀ 25:21 ዘፀ 26:34

ዘፀ 31:18 ዘፀ 32:15

ዘፀ 34:1 ዘፀ 34:28

ዘፀ 37:1 ዘፀ 40:20

መኃ 7:89 ኢያ 3:3

ኢያ 7:6 2 ኛ ቆሮ 6:16

5: ስለ ጾም የመጽሐፍ

ቅዱስ ማስረጃ:-

ዘፀ 34:28 ዘፀ 9:9

ሳሙ 20:26 1 ሳሙ 7:6

1 ሳሙ 31:13 2 ኛ ሳሙ 1:12

2 ኛ ሳሙ 12:16 ዕዝ 8:21

ዕዝ 68:10 ዕዝ 108:24

ኢሳ 48:3 ኤር 36:9

ዳን 9:3 ዳን 20:2-3

ኢዩኤ 2

:14 ኢዩኤ 2:12

?ዮና 3:5 ማቴ 4:2

ማቴ 6:16:18 ማቴ 9:14-15

ማቴ 17:21 ማር 2:18

ማር 9:29 ሉቃ 2:37

ሉቃ 18:12 የሐ.ስራ 13:3 ሐዋ

14:23 2ኛ ቆሮ 11:17

6: ስለ መስቀል በመጽሐፍ

ቅዱስ:-

ማቴ 10:38 ማቴ 16:20

ማር 8:34 ሐዋ 5:30

1ኛ ቆሮ 1:18 ገላ 3:13

ገላ 6:13 ፊል 2:8

ፊል 3:18

7: ጥምቀትን በተመለከተ:-

ሕዝ 36:25 ማቴ 3:5-6

ማቴ 26:19-20 ማር 1:4-5

ማር 16:16 ሉቃ 3:21

ዮሐ 3:5 ዮሐ 3:22

ኤፌ 4:5 ገላ 3:26-27

ሐዋ 19:4 ሐዋ 18:8

ሐዋ 13:24 ሐዋ 10:47 የሐዋ 9:18 1ኛ ቆሮ 1:16

1ኛ ቆሮ 10 :2 1ኛ ቆሮ 12:13

8:ስእለትን በተመለከተ:-

ዘኁ 28:20 ዘኁ 21:2

ዘፀ 23:21 መሳ 11:30

መዝ 49:14 መዝ 75:11

 1 ኛ ሳሙ 1:11 መክ 5:4-5

ዮና 2:10 ናሆ 1:15

ሐዋ 18:18

9: ጻድቃን ሰማዕታት ያማልዳሉ:-

 ዘ ፍ 18:17-18 ዘፍ 18:23:24

 ዘፍ 20:7 ዘፍ 33:3

ዘፍ 42:6 1 ኛ ሳሙ 28 :14

 2 ኛ ሳሙ 1:2 2 ኛ ነገ 1:13

 2 ኛ ነገ 2:15 2 ኛ ነገ 4:9

2 ኛ ነገ 4:32-35 መዝ 88:34

ማቴ 18:18 ዮሐ 20:23

 ሐዋ 10:25 ሐዋ 16 :29

1 ቆሮ 6:1-2 ፊሊ 4:6

1 ኛጢሞ 5:17 ያዕ 5:14

ራእ 14:13

10: መላእክት ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ:-

መዝ 148:2 ኢሳ 6:3

ማቴ 4:12 ማቴ 18:10

ማቴ 25:31 ማር 8:38

ራእ 1:11 ሉቃ 1:19

11: መላእክት ጸሎታችንን ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ:-

ጦቢ 12:15 ሉቃ 15:10

የሐዋ 10:4 ኢዮ 25:3

ኤር 33:22 ዳን 7:10

ሄ ኖ 10:1 ራእ 5:11

12:ለመላእክት የአክብሮት ስግደት ይገባል:-

ዘ ፍ 19:1 ዘኁ 22:31

ኢያ 5:14 ዳን 8:16-17

13:መላእክት አብሣሪያን ናቸው:-

ዘፍ 16:11 ሉቃ 1:13

ሉቃ 1:19 ሉቃ 1:30-31

ሉቃ 2:10-11

14:መላእክት በአደጋ ጊዜ ፈጥነው ይደረሳሉ:-

ዘፍ 22:11-12 መዝ 90:11-12

ዳን 6:22 ዳን 10:13

ማቴ 2:13 ሐዋ 5:19-20

ሐዋ 12:7

15: ፀበል መርጨት ያስፈልጋል:-

ዘ ኁ 19:20

Miko ZE Ethiopia

ተከታታይ ትምህርት (ክፍል ሃያ)

41/ ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዬሐንስ ራዕይ ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ዋና ሃሳባቸውና ምን ምን ዋና ዋና ነገሮችን ያነሳሉ?

መጽሐፈ መቃብያን ካልዕና ሣልስ

ዋና ሃሳብ

በቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት አንድ መጽሐፍ ሆነው ይቆጠራሉ።

31 ምዕራፎች አሉት።

ልዩ ጠቃሚ ሐሳቦች

መጽሐፉ በዋናነት የዲያብሎስን ማንነትና በሰው ልጆች ላይ የሚያደርሰውን የክፉት ሥራ በዝርዝር ያስረዳል፣

ትንሣኤ ሙታን ለማያምኑ ስለ ትንሣኤ ሙታን ጽድቅና ኩነኔም እንዳለ ሰፊ ትምህርት ይሰጣል;;

Miko ZE Ethiopia

42/ መዳን በሌላ በማንም የለም.....‘በሌላ የተባሉት እነማን ናቸው?’

ይህ ትምህርት የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ትምህርት ሲሆን የተላለፈውም በወቅቱ ለነበሩት የካህናት አለቆች እና የመቅደስ አዛዦች ሰዶቃውያን

እንዲሁም በስፍራው ለተሰበሰቡት ህዝብ ነበር።በሐዋ.ሰራ ምዕ.3 ላይ እንደምናነበው ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ዮሐንስ በቤተ መቅደስ ደጃፍ አንድ ድውይ ሰው በእግዚአብሄር ኃይልና ጥበብ በማዳናቸው በወቅቱ በነበሩ ባለስልጣናት እና ነዋሪዎች መካከል አነጋጋሪ ሆኖ ነበር።በዚህ ምክኒያትም ሁለቱም ሐዋርያት ወደ ወህኒም ተወርውረው ነበረ። ሐዋርያቱም በሸንጎ ፊት ቀርበው "እናንተ ይህንን በምን ኃይል ወይስ በማን ስም አደረጋችሁት?"ተብለው ተጠየቁ።ቅዱስ ጴጥሮስም "እናንተ የህዝብ አለቆችና ሽማግሌች እኛ ዛሬ ለድውዩ ሰው ስለተደረገው መልካም ሥራ በምን እንደ ዳነ ብንመረምር እናንተ በሰቀላችሁት....በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደህና ሆኖ በፊታችሁ እንደቆመ...እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት የማዕዘን ራስ የሆነው ይህ ድንጋይ ነው።መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና"ብሏል።ለመሆኑ መዳን ስንል ምን ማለትችን ነው?መጀመሪያ ሰው ልጅ ዳነ ስንል እግዚአብሄር አምላክ የሰውን ልጅ ሲፈጥረው የእግዚአብሄር ስምን እንዲያመሰግን እና ክብሩን እንዲወርስ ሆኖ ሳለ "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉውን ከምታሳውቀው ዛፍ አትብላ፤ከእርሱ በበላህ ቀን ትሞታለህና" ሲል ፈጣሪው ያዘዘውን ህግ በመተላለፉ ከክብሩ ወረደ፤ከፀጋው ተለየ ለሞትም ተዳረገ።ይሁንና ከአምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን በኃላ እግዚአብሄር አምላክ ከልጅ ልጁ ተወልዶ አዳነው።ሰው ዳነ ስንል ጠቅለል አድርጎ ለማስቀመጥ ከላይ የዘረዘርኳቸው መርገመ ስጋ እና መርገመ ነፍስ በአምላክ ሰው መሆን ተወገደለት በምትኩ ድኅነተ ሥጋ እና ድኅነተ ነፍስን ገንዘብ አደረገ

ማለታችን ነው።እንግዲ እዚህ ላይ በደንብ ከተማመንን ከቅዱስ ጳጥሮስ ትምህርት ተነስተን ‘በሌላ’ የተባሉት እነማናቸው የሚል መሰረታዊ ጥያቄ እናነሳለን።ሌላ ማለት በአማርኛ ፍቺ ‘ልዩ የሆነ፤እንግዳ’ ማለት ነው። የክርስትና ሊቅ ነን የሚሉት ፕሮቴስታንቶች ብዙ ጊዜ ስለማርያም፤ስለመለአክት፤ስለቅዱሳን፤ስለሐዋርያት ማዳን ስንናገር መዳን በሌላ ምናምን እያሉ የሚጨቀጭቁን እንግዲ ‘ሌላ’ ማን እንደሆነ ጠንቅቀው ስለማያውቁ ነው።ይህን ቃል ከመ/ቅዱስ አንባር ብንመረምረው ግን የማያድኑ ሌሎች የሚባሉት ወደ ፕሮቴስታንቱ ስህተት ያመዘኑ ሆነው እናገኛቸዋለን።የማያድኑ ሌሎች 1ኛ. ‘ገንዘብ’ ነው።እኛ የዳነው በእግዚአብሄር ሥላጣንና ጥበብ ነው እንጂ ‘ኃጥያት ስር’ በተባለው ገንዘብ አይደለም።ፕሮቴስታንቶች ግን ገንዘብን ቀን ከሌት ሲዘክሩት ይኖራሉ አምላካችን ክርስቶስ “የሰው ሕይወት በገንዘብ ብዛት አይደለምና ከመጎምጀትም ሁሉ ተጠበቁ” ብሎ ቢያስተምርም እነሱ ግን በየፀሎታቸው ሁሉ ትልልቅ ቤቶችን እያለሙ፤መኪና በሀሳባቸው እየነዱ እየጎመጁ ይኖራሉ ሉቃ 12፤ 16።ገንዘብ ማካበትንም እንደ እግዚአብሄር ስጦታ ይቆጥሩታል ወንጌሉ ግን “የእግዚአብሄርን ስጦታ በገንዘብ ማግኘት አይቻልም የእግዚአብሄርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሀል እና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ” ይላል የሐዋ.8፤20 ።ወንድሞቼ ፕሮቴስታንቶች ለሁለት ጌታ መገዛት ከቶ አትችሉምና መዳን በገንዘብ እንደሌለ አውቃችሁ ተመለሱ ማቴ.6፤20 “ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ወይም አንዱን ይጠላል ወይም አንዱን ይወዳል፤ወይም አንዱን ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ለእግዚአብሄርና ለገንዘብ መገዛት

አትችሉም።”(በነገራችን ላይ ይሁዳም አምላኩን በገንዘብ እንደሸጠ እንዳትዘነጉ

Miko ZE Ethiopia

43/ ትምሕርተ ሃይማኖት ሥነ ፍጥረት (የዓለም አፈጣጠር)

እግዚአብሔር በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠራቸው ፍጥረታት በየወገናቸው ሲቆጠሩ ሃያ ሁለት ሲሆኑ :: በመጀመሪያው ቀን እሑድ የተፈጠሩት ፍጥረታት ስምንት ናቸው ::

1 ጨለማ 3 ውሃ 5 ነፋስ (አየር) 7 መላእክት

2 መሬት 4 እሳት 6 ሰባቱ ሰማያት 8 ብርሃን

ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ የሚታየውም ከማይታው እንደሆነ (እንደተፈጠረ) እናምናለን ። ዕብ 11 ፣ 3 በማለት ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረ:: እነዚህም ዓለሞች የተባሉት (ዓለመ ምድር ፤ ዓለመ ሰማይ) ተብለው በሁለት ይከፈላሉ ።

ዓለመ ምድር

1 ጨለማ (ጊዜ) ፤ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው ጨለማን ነው ። ጨለማንየፈጠረውም ከምንም (ካለመኖ ወደ መኖር አምጥቶ በአምላክነት ጥበቡ በማስገኘት) ነው ። እኛ ሰዎች አንድን ነገር ለመስራት ጥሬ ዕቃ

የግድ ያስፈልገናል ከምንም ተነስተን ምንም ነገር መስራት አንችልም በዓለም ላይ የምናያቸው የሰው ልጅ ሥራዎች (ታሪካውያን መዛግብትና የሳይ ንሰ ውጤቶች) ሁሉ የተለያዩ ንጥረ ነገሮችን በማሰባሰብ የተሠሩ ናቸው ። ሰው ምን ቢያውቅ መሥራት የሚችለው ካለው ነገር ላይ ተጠቅሞ ነው ። እግዚአብሔር ግን ዓለማትን የፈጠራቸው (ያስገኛቸው) ያለምንም ነገር (እምኅበ አልቦ) ከምንም ነው ።

ይህም ጊዜ መቆጠር የተጀመረበት ሲሆን ፤ ሌሎቹ ፍጥረታት የተፈጠሩትም በጊዜ ውስጥ ነው ። ጊዜ ከመፈጠሩ በፊት ስለ ነበረው ሁኔታ ለሰዎች የማወቅ ችሎታ የላቸውም ። ሰዎች እንዲያውቁና እንዲመራመሩ የተፈቀደላቸው ከሥነ ፍጥረት በኋላ ያለውን ብቻ ነው ። ያንም ቢሆን የቻሉትን ያህል ይሞክራሉ እንጅ ሁሉንም ተመራምረው አይደርሱበትም ።

2 መሬት (ምድር)፤ በውስጡ ለሚገኙት ሁሉ መኖሪያ እንዲሆን የተፈጠረውና ከአራቱ ባህርያት አንዱ የሆነው መሬት ተፈ ጥሮው ከምንም ነው ። መሬት ብትን (አፈር) ሲሆን ፤ ምድር የተባለውና ዛሬ እንደምናየው የፀና የሆነው ከውሃ ጋር ተዋህዶ በመጠንከሩ ነው መሬት በዓይን ይታያል ፣ በእጅ ይጨበጣል ፣ በውስጡ ሶስት ባህርያት አሉት ።እነሱም ደረቅነት (የብስነት) ፤ ክብደት (ግዙፍነት) ፤ ጥቁርነት (ጽልምነት) ፤ ናቸው ።

3 ውሃ ለፍጥረታት ሁሉ ሕይወት የሆነውና ከአራቱ ባህርያት አንዱ የሆነው ውሃ የተፈጠረው ከምንም ነው ። ውሃ በምድር

ለሚኖሩ ፍጥረታት ሕይወታቸው ነው ። ከእሳት በቀር በሁሉም ፍጥረታት ውስጥ አለ ። ውሃ በዓይን ይታያል ፣ በእጅ ይዳሰሳ

ል ፣ ግን አይጨበጥም ። በባህርዩ ከመሬት ረቂቅ ነው ። በውስጡ ሶስት

ባህርያት ፥ ቅዝቃዜ ፣ እርጥበት ፣ ብርሃን ፤ ናቸው

4 እሳት ከአራቱ ባህርያት አንዱ ሲሆን የተፈጠረው ከምንም ነው ። በዓይን ይታያል ግን በእጅ አይጨበጥም አይዳሰስም ከመሬትና ከውሃ ይረቃል ። የእሳት ሶስት ባህርያት ፤ ብርሃን ሙቀት (ዋዕይ) ደረቅነት (ይብሰት) ናቸው ።

5 ነፋስ (አየር) ከአራቱ ባህርያት የመጨረሻ የሆነው ነፋስ በባህርዩ ከመሬት ከውሃና ከእሳት ይረቃል ። እንቅስቃሴው ይሰ ማል ። ነገር ግን በዓይን አይታይም ። በእጅ አይዳሰስም ። ዮሐ 3 ፥ 8 ። የነፋስ (አየር) 3 ባህርያት እርጥበት (ርጡብነት) ፣ ረቂቅነት ፣ ጸሊምነት (ጥቁርነት) ናቸው ።

ጥቁርነት የነፋስ ባህርይ ነው መባሉ ፤ በዓይን ታይቶ ሳይሆን ፤ ከጨለማ ባህርይ ጋር በመስማማቱና ተለይቶ ባለመታወቁ ነው ። እስመ ነፋስ ጸሊም በአርአያሁ እንዲል ። ነፋስ የተፈጠረው ከምንም ነው ።

የአራቱ ባህርያት የየራሳቸው ዋና ባህርይ መሬት ደረቅነት ፣ ውሃ ቀዝቃዛ ነት ፣ እሳት ብሩህነት ፣ ነፋስ ረቂቅነት ፣ ነው ።

አራቱ ባህርያት ለፍጥረታት ሁሉ መሠረት ናቸው ። እግዚአብሔር በምድር ያሉ ፍጥረታትን የፈጠራቸው ከአራቱ ባህርያት

ሲሆን ፤ እነሱን ግን ያስገኛቸው ከምንም (ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ) ነው ።

ዓለመ ሰማይ

ሰባቱ ሰማያት ፤ እግዚአብሔር ሰማያትን ከእሳት ዋዕዩን (የማቃጠል ባህርዩን) ትቶ ብርሃኑን ብቻ በመውሰድ ፈጠራቸው ስማ ቸውም ከላይ ወደ

ታች በሚከተለው መልኩ ይገለጻል ።

1. ጽርሐ አርያም 3. መንበረ መንግሥት 5. ራማ

2. ሰማይ ውዱድ 4. ኢየሩሳሌም ሰማዊት 6. ኢዮር 7. ኤረር ናቸው ።

1. ጽርሐ አርያም ለሰባቱም ሰማያት የመጨረሻ ክፍል ሲሆን ፤ ከላይ ወደታች ሲቆጠር የመጀመሪያ ደረጃ ያለው ነው ።

2. መንበረ መንግሥት እግዚአብሔር በወደደው መጠን ለወዳጆቹ የሚገለጥበት ፤ የክብሩ ዙፋን የተዘረጋበት ፤ ቅዱሳን መላ እክት በፊቱ እየሰገዱ ምስጋና የሚያቀርቡበት ፤ የሞቱ ሰዎች ነፍሳቸው ሰግዳ ፍርድ የምትቀበልበት ነው ። ኢሳ 6 ፥ 1 ። ሕዝቅ 1 ፥ 22 - 27 ። ራዕ 4 ፥ 2 ።

3. ሰማይ ውዱድ በአራቱ መዐዝን ቁመው ዙፋኑን የተሸከሙ አርባዕቱ እንስሳ (የሰው ፤ የላም ፤ የንሥር ፤ የአንበሳ) ምስል ያላቸውና ዘወትር ዙፋኑን የሚያጥኑ ፸፬ ካህናተ ሰማይ ያሉበት የሰማይ ክፍል ነው ። ሕዝቅ 1 ፥ 4 - 75 ። ራዕ 4 ፥ 4

4. ኢየሩሳሌም ሰማያዊት (መንግስተ ሰማያት) በመጀመሪያ ሳጥናኤል (የዛሬው ዲያብሎስ) የነበረባት ፤ ጻድቃን ከምጽአት በኋላ የሚወርሷት ርስታቸው ናት ። ገላ 4 ፥ 26 ። ዕብ 12 ፥ 22 ። ዮሐ 14 ፥ 2 ።

5. ኢዮር ፤ 6 ራማ ፤ 7 ኤረር ፤ ሦሥቱም የመላእክት ዓለማት (መኖሪያዎች) ሲሆኑ ፤ ከዳግም ምጽዓት በኋላ ወዳለመኖር ሲያልፉ ቅዱሳን መላእክት ከጻድቃን ጋር በመንግስተ ሰማያት ይጠቃለላሉ (ይኖራሉ) ። ማቴ 22 ፥ 30 ። ከሰባቱ ሰማያት ቀጥሎ ያለውና ምጽንዓት የሚባለው የሰባቱ ሰማያት መሠረት ነው ።

እነዚህን ሰማያት በሃይማኖት እንጅ ዛሬ በሥጋ ዓይን ልናያቸው አንችልም ። በሰማያት ይቅርና በዓለማችን ያሉ በዓይናችን የማናያቸው ብዙ ጥቃቅን ነገሮች መኖራቸው ይታወቃል ።

ቁሳዊ አስተሳሰብ ላላቸው ሰዎች ይህ ምሥጢር ይከብዳቸል ፤ የሃይማኖት ሰዎች ግን ሁሉንም ሳይጠራጠሩ በሃይማኖት እውነት ነው ብለው ይቀበላሉ ። ሃይማኖት ለብዙ እንቆቅልሾች መልስ ስለሚሰጥ ለሚያምኑ ሰዎች ታላቅ እፎይታ ነው ።

ቅዱሳን መላእክት

መልአክ የሚለው ቃል ተመልአከ አለቃ ሆነ ካለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ይህም ቃል ቅዱሳን መላ እክት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ክብሩን ወርሰው ለመኖር የተመረጡና የተሾሙ መሆናችውን ይገልጻል ።

በሌላም በኩል ለአከ ፡ ላከ ካለው ግሥ የተገኘ ሆኖ መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች መሆናቸውን ያስረዳል ።

የመላእክት አፈጣጠር

መላእክት የተፈጠሩት ከምንም ነው ። በመዝ 103 ፡4 ። እና በዕብ 1 ፡ 7 ። ላይ ከእሳትና ከነፋስ እንደተፈጠሩ የተገለጠው ረቂቅነታቸውንና ለአገልግሎት ፈጣን መሆናቸውን ለማስረዳት ነው ። ከእሳትና ከነፋስ ተፈጥረው ቢሆን ኖሮ የሚሞቱ ይሆኑ ነበር ።

መላእክት ግን - አይይሞቱም የሥጋ ባህርይ የላቸውምና ።

- ፆታ የላቸውም ፤ ነገር ግን የሚጠሩት በወንድ ፆታ ነው ።

- ረቂቃን(መናፍስት) ስለሆኑ በዓይን አይታዩም ።

የመላእክት አገልግሎት

ያለ እረፍት እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ ። መዝ 148 ፥ 2 ። ኢሳ 6 ፥ 3 ።

- ከእግዚአብሔር ወደ ሰዎች ይላካሉ ። ሉቃ 1 ፥ 11 ። ሐዋ 10 ፥ 3 ። ዘፍ 19 ፥ 1 ።

- የሰዎችን ጸሎት ያሳርጋሉ ። ዘካ 1 ፥ 14 ። ራዕ 8 ፥ 3 ።

- የእግዚአበሔርን ወዳጆች ይጠብቃሉ ። መዝ 90 ፥11 ። 2 ነገ 19 ፥ 35

መላእክት የተፈጠሩት በመጀመሪያው ቀን እሑድ ነው ። ከብዛታቸው የተነሳ ቁጥራቸው አይታወቅም አይወሰንም ። በመቶ ነገድ የተከፋፈሉ ሲሆኑ ለየነገዱ አለቃ አለው ። ሳጥናኤል የዛሬው ዲያብሎስ ለመጀመሪያው ነገድ አለቃ ነበረ ። ሳጥናኤል የመጀመሪያ የክብር ስሙ ነው ። ሲክድ ስሙም ተወሰደበትና ‹‹ዲያብሎስ (ፈታዌ አምላክና አምላክነትን ፈላጊ ፤ ዖፍ ሰራሪ ለማሳት የሚፋጠን በራሪ ወፍ)ጋኔን(ዕቡይ ትዕቢተኛ ውዱቅ የተጣለ) ሰይጣን (ባለጋራ ከሳሽ) ። የሚባሉና ግብሩን የሚገልጹ ስሞች ተሰጡት>> ።

እግዚአብሔር መላእክትን ፈጥሮ በተሰወራቸው ጊዜ አእምሯቸው ጠያቂ አገናዛቢ ነውና ማ ን ፈጠረን ከየት መጣን ? እያሉ እርስ በእርሳቸው ሲጠያየቁ በቦታና በመዓርግ ታላቅ የነበረው ሳጥናኤል ማንም ሳያሳስተውና ሳይመክረው ሐሰትን ለመጀመሪያ ጊዜ ከልቡ (ከአእምሮው) አንቅቶ እኔ ፈጠኋችሁ ብሎ በድፍረት ተናገረ ። ዮሐ 8 ፥ 44 ። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል (ንቁም በበጎላዌነ እስከንረክቦ ለአምላክነ) የፈጠረን አምላካችንን እስክናገኘው (እስኪገለጥልን) ድረስ በያለንበት እንጽና

በማለት ብሎ ባረጋጋቸው ጊዜ በመላእክት መካከል መለያየት ተፈጠረ ይህም ዲያብሎስ በመላእክት መካከል የዘራው የመጀ መሪያ መከፋፈል ነው ። ማቴ 13 ፥ 28 ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን ብሎ ብርሃንን ፈጠረ ። ዘፍ 1 ፥ 3 ።

ብርሃን በተፈጠረ ጊዜ ሳጥናኤል ምንም መፍጠር የማይችል የውሸት (የምኞት)አምላክ መሆኑ ተገለጠበት ። በስህተቱም ተፀፅቶ ሊመለስ ስላልቻለ ቅዱሳን መላእክት በሰልፍ (በጦርነት) ተዋግተው መዓርጉን ተነጥቆ ከነበረበት የክብር ቦታ ከመንግስተ ሰማያት ከነሠራዊቱ (ከነተከታዮቹ) ወደ ጥልቁ ተጣለ ። ራዕ 12 ፥ 6 ። ኢሳ 14 ፥ 12 ። ይሁ 1 ፥ 13 ።

አጋንንት መልካቸውን እየለዋወጡ በብርሃን መልአክና ፣ በተለያየ የሰው መጠን ፤ መስለው ሰዎችን ከእግዚአብሔር መንገድ ያሳስታሉ ። ኢዮ 1 ፥ 6 ። ሉቃ 22 ፥ 3 ። 2 ቆሮ 11 ፥ 14 ። 1 ዮጥ 5 ፥ 8 ።

እሑድ ፦ ሌሊቱ አሥራ ሁለት ፣ ቀኑ አሥራ ሁለት ፣ በድምሩ 24 ሠዐታት አንድ ቀንተብሎ የመጀመሪያ ቀን ተቁጠረ ።

ሰኑይ (ሰኞ)

ሰኑይ (ሰነየ አማረ ፤ በጀ ፤ ተስተካከለ) ፤ ካለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ቃል ሲሆን እግዚአብሔር በዚህ ቀን የፈጠረው አንድ ፍጥረት ጠፈርን (ሰማይ) ብቻ ነው ። ከመሬት (አፈር) ጋር ተዋህዶ የነበረውን ውሃ ከሶስት ከከፈለ በኋላ አንደኛውን ባለበት እንዲረጋ አድርጎ፤ ጠፈር (ሰማይ) አለው ፤ ሁለተኛውን ከመሬት ጋር እንደተቀላቀለ (ድፍርስ እንደሆነ) ከጠፈር በላይ አደረገው ስሙም ሐኖስ ይባላል ። ዘፍ 1 ፡ 6 ። ሶተኛውንም ከውሃ ጋር

እንደተቀላቀለ ከጠፈር በታች ተወው ።

ሰሉስ (ማክሰኞ)

ሰሉስ ሰለሰ ሶስት አደረገ ፤ ካለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሆኖ ለፍጥረት ሶስተኛ ቀን ማለት ነው ። ይህ ቀን እግዚአብሔር ከአፈር ጋር ተቀላቅሎ የነበረውን ውሃ በምድር ዙርያ ከወሰነው በኋላ ፤ የመሬት ገጽ የታየበት እና ሰማይና ምድር ዛሬ በምናየው ሁኔታ የተዘጋጁት ፤ ምድርም የዛሬ ቅርጿን የያዘችበት ብሩህ ዕለት (ቀን) ነው ። እሑድ የተፈጠሩት ፍጥረታት (ሃያውን ዓለ ማት) በየቦታቸው የተከናወኑትም በዚሁ ቀን ነው ። ሃያው ዓለማት የሚባሉትም ።

- ዓለማተ መሬት 5 የጋራ ስማቸው ዱዳሌብ
- ዓለማተ ማይ 4 የጋራ ስማቸው ናጌብ
- ዓለማተ እሳት 9 የጋራ ስማቸው ኮሬብ
- ዓለማተ ነፋስ 2 የጋራ ስማቸው አዜብ ናቸው ።

ገሐነመ እሳት ፥ ሲኦልና ገሃነ ት ፥ ብሔረ ህያዋን ብሔረ ብፁዓን ። ተብለው የተሰየሙት በዚህ ቀን ነው ። እግዚአብሔር አስቀድሞ እነዚህን ዓለማት በየቦታቸው ካዘጋጀ በኋላ ፤ በመሬት ላይ ሶስት ፍጥረታትን ብቻ ፈጥሯል ። እነዚህም

- በእጅ የሚለቀሙ አትክልት (በመሬት ውስጥ የሚያፈሩ እንደ ካሮት ድንች ...)
- በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕት (የአገዳ እህሎች እንደ ገብስ ስንዴ በቆሎ ጤፍ ...)
- በመጥረቢያ የሚቆረጡ ዕፀዋት (የዛፍ ዓይነቶች እንደ ዋርካ ወይራ

ሾላ...) የመሳሰሉት ናቸው ።

የተፈጠሩትም ከአራቱ ባህርያት ነው ። ከመሬት እንደ መፈጠራቸው ሲጣሉ አፈር ይሆናሉ ። ከውሃ እንደ መፈጠራቸው በውስጣቸው ፈሳሽ አላቸው ። ከእሳት እንደመፈጠራቸው ይቃጠ ላሉ ። ከነፋስ እንደመፈጠራቸው አየር (ነፋስ) ያስገባሉ ያስወጣሉ ፤ ከአራቱ ባህርያት አንዱ ከተጓደለ ግን ይደርቃሉ እነዚህም የምድር ጌጦች ሲሆኑ ሰውም ለምግቡም ሆነ ለሚፈልገው አገልግሎት ይጠቀምባቸዋል

ረቡዕ

ረቡዕ “ረብዐ አራት አደረገ“ ካለው ግሥ የተገኘ ሲሆን ፤ ለፍጥረት አራተኛ ቀን ማለት ነው ። እስከዚህ ቀን ድረስ እሑድ

የተፈጠሩት ብርሃንና ጨለማ በየ 12 ሰዓት ቀንና ሌሊት እየተፈራረቁ ከቆዩ በኋላ ብርሃኑን ወደ ሰባቱ ሰማያት ፤ ጨለማውን ወደ ከርሰ ምድር (ወደ እንጦርጦስ) አጠቃሎ በጠፈር (በህዋ) ላይ ሆነው የሚያበሩ ሶስት ፍጥረታትን ፈጠረ ።

እነዚህም ፀሀይን ፈጥሮ ከእሳት ብርሃኑንና ሙቀቱን ከሳለበት በኋላ በቀን እንዲያበራ ሾመው።

ጨረቃን ሰሌዳውን አዘጋጅቶ በፀሀይ ብርሃን ነፀብራቅ በሌሊት እንዲያበራ አደረገው ።

ከዋክብትን በተለያየ መጠን ካዘጋጃቸው በኋላ ብርሃን ስሎባቸው በሌሊት እንዲያበሩ ሾማቸው ።

ጨረቃና ከዋክብት በሌሊት በማብራታቸው ሌሊቱን ማስቀረት አይችሉም ። ሁሉም ሥርዓታቸውን ጠብቀው የሚገኙ ሲሆን እነዚህም ለሠዓታት ፤

ለወራትና ፤

ለዓመታት ፤ መታወቂያና መለያ ናቸው ። ዘፍ 1 ፡ 14 - 20 ።

ሐሙስ

ሐሙስ ፤ ሐመሰ አምስት አደረገ ካለው ቃል የተገኘ ሲሆን ፤ ለፍጥረት አምስተኛ ቀን ነው ። በዚህ ቀን እግዚአብሔር ከባህር በደመ ነፍስ ህያዋን ሆነው የሚኖሩ ፤ ሶስት ተንቀሳቃሽ ፍጥረታትን ፈጠረ ። ዘፍ 1 ፥ 20 ፡ 23 ።

እነዚህም - በልብ የሚሳቡ እንስሳትና አራዊት

- በእግር የሚሽከረከሩ እንስሳትና አራዊት

- በክንፍ የሚበሩ አእዋፍ ናቸው ።

ከነዚህም ውስጥ ከባህር ውጭ መኖር የማይችሉ እንደ ዓሣ ያሉና ፤ በባህርም በየብስም መኖር የሚችሉም አሉባቸው ።

ዐርብ

ዐርብ ፤ ዐረበ ፤ ገባ ፤ ተካተተ ፤ ካለው የወጣ ሲሆን ፤ መካተቻ ማለት ነው ፤ ለፍጥረት ስድስተኛ ቀን ነው ። እግዚአብሔር በዚህ ቀን በመጀመሪያ ከየብስ በደመ ነፍስ ህያዋን ሆነው የሚኖሩ ሶስት ተንቀሳቃሽ ፍጥረታትን ፈጠረ ። ዘፍ 1 ፡24 ።

እነዚህም - በልብ የሚሳቡ እንስሳትና አራዊት

- በእግር የሚሽከረከሩ እንስሳትና አራዊት

- በክንፍ የሚበሩ አእዋፍ ናቸው

በመጨረሻም እግዚአብሔር “ ሰውን በመልካችንና እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር ” ብሎ ከሰባቱ ባህርያት ፈጠረው ። ሰባት ባህርያት የሚባሉት

አራቱ ባህርያተ ሥጋ(መሬት : ውሃ: እሳት : ነፋስ) ሲሆኑ ሶስቱ ባህርያተ ነፍስ የሚባሉት ደግሞ ልብ (ማሰብ) ቃል (መናገር) እስትንፋስ (በሕይወት መኖር) ናቸው ። ዘፍ 1 ፥26 ።

ሰው በሥጋው እንደ እንስሳት ይበላል ይጠጣል ይተኛል ይነሳል ። በነፍሱ እንደ መላእክት ረቂቅ (መንፈስ) ነው ። ፈጣሪውን ያመሰግናል ። የነፍስ ምግቧ የእግዚአብሔር ቃል ነው ። አሞ 8 ፥ 11 ። ነፍሱ አትሞትም ለዘለዓለም ህያው ሆና ትኖራለች ። ስለዚህም ሰውን የፈጠረው በሥጋው እንደ እንስሳት ፤ በነፍሱ እንደ መላእክት ረቂቅ አድርጎ ነው ።

በመጀመሪያ የተፈጠረው ሰው ስሙ አዳም ይባላል ፤ አዳም ማለት ያማረ የተዋበ.. ፍጡር ማለት ነው ። አዳም ሲፈጠር የሰላሳ ዓመት ያህል ሆኖ ነው ። ሌሎቹ (ሐሙስና ዐርብ የተፈጠሩ እንስሳት አራዊትና አእዋፍ) የተፈጠሩት ሁሉም ወንድና ሴት ዖታ እየሆኑ ነው ። አዳም ግን ሲፈጠር ረዳት ስላልነበረው ። ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም...። ዘፍ 2 ፥ 18 ። ብሎ በአዳም ላይ እንቅልፍ በማምጣት ከግራ ጎኑ አንዲት አጥንት ወስዶ እሱን ከፈጠረው ከአንድ ሳምንት በኋላ ፤ በተ ፈጥሮ የምትመስለው ፤ በዖታ የተለየች ሴት ፈጠረለት ፤ አዳምም ስሟን ሄዋን አላት ። ትርጉሙም የህያዋን (የሰው ልጆች) ሁሉ እናት ማለት ነው ። ሄዋን የተፈጠረች የአስራ አምስት ዓመት ያህል ሆና ነው ። ሴት ልጅ ለአቅመ ሄዋን ደረሰች የሚባለውም ከዚህ ዕድሜ ጀምሮ ነው ።

ሔዋንን ከጎኑ የፈጠረበት ምክንያት ከወገብ በላይ ቢፈጥራት የወንድ የበላይ ፤ ከወገብ በታች ቢፈጥራት ደግሞ የበታች ፤ እንዳትሆን ጎን (ወገብ) መካከለኛ እንደሆነ ሁሉ በተፈጥሮ ከወንድ እኩል ሙሉ ሰው መሆኗን

ለማስረዳት ነው ። አዳምና ሄዋን የሚቆጠሩት እንደ አንድ ሲሆን ከእሑድ እስከ ዐርብ የተፈጠሩት ፍጥረታት ሃያ ሁለት ናቸው ። ይህም ዝርዝር ቁጥራቸው ሳይሆን ፤ በዓይነታቸው (በየወገናቸው) ተቆጥረው ነው ።

ሰውን በመጨረሻ የፈጠረበት ምክንያት

1 ኛ አምላክ ፤ ለሰው ልጅ የሚያስፈልገውን ሁሉ ስለሚያውቅ አስቀድሞ በማዘጋጀት ፍቅሩን ለመግለጽ ፤ ማቴ 6 ÷ 32 ።

2 ኛ ሰው አስቀድሞ ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ሌሎችን ፍጥረታት ሲፈጥር ረድቻለሁ አማክሬያለሁ እንዳይል ። እግዚአብሔር ዓለማትን ሲፈጥር የማንም አማካሪነት ሳያስፈለገው ፤ በራሱ ጥበብና ማስተዋል ሁሉን አዘጋጀ ። ኢሳ 40 ÷12 ። እግዚአብሔር አዳምን በተፈጠረ በአርባ ሄዋንን በተፈጠረች በሰማንያ ቀናቸው በልጅነት አክብሮ ብርሃን አልብሶ በይባቤ መላእክት (በመላእክት አጅቦ) ወደ ገነት አስገባቸው ። ገነት ከገቡ በኋላ በገነት ያለውን አትክልትና ፍራፍሬ ሁሉ ብላ ፤ ክፋና በጎ የምታስታውቀውን ዕፀ በለስን ግን አትበላ ፤ እሷን በበላህ ቀን ትሞታለህ ብሎ አዘዘው ። ዘፍ 2 ÷ 16 ። ይህን ያለበት ምክንያት አዳም ፍጡር (ተገዢ) ፤ እግዚአብሔር ፈጣሪ (ገዢ) መሆኑን ለማስረዳት ነው ።

ቅዳሜ (ቀዳሚት ሰንበት)

ቅዳሜ ይህ ቀን የሳምንቱ መጨረሻ ሰባተኛ ቀን ነው ። እግዚአብሔር በዚህ ቀን ምንም አልፈጠረም ። አረፈ ይህም ማለት እንደ ፍጡር የሚደክምና እረፍት የሚያስፈልገው ሆኖ ሳይሆን መፍጠሩን ተወ ፡ ማለት ነው ። ይህንም ቀን ሰዎች የሚያርፉበት የእረፍት ቀን ሰንበት አደረገው ። ለእረፍታችን ሳይቀር የሚያስብ አምላክ ነውና ። ዘፍ 2 ÷ 1 ። ለሙ ሴ

“ሰንበትን አክብር” ብሎ ያዘዘውም ይህንኑ ቀን ነው ። ዘፀ 28 ፥ 11 ።
ቀዳሚት ሰንበት ፤ ቀዳሚት፤ የግዕዝ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙ የመጀመሪያዋ (ፊተኛዋ)ማለት ነው ። ሰንበተ አይሑድ ተብላም ትታወቃለች ፤ እለተ እሑድ (ሰንበተ ክርስቲያን) በሐዲስ ኪዳን ሰንበት ሆና መከበር ስትጀምር ቀዳሚት ሰንበት (ቅዳሜ) ተባለች በሐዲስ ኪዳን ሁለቱም ቀናት (ቅዳሜና እሑድ) ሰንበታት ሆነው ይከበራሉ ።

Miko ZE Ethiopia

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

44/ ‹‹ መዳንም በሌላ በማንም የለም...›› ሐዋ 4፡12 +++ +////++++

ክፍል አንድ 02/03/07 ሳሚ ዘቂርቆስ

የምትናፍቁኝና የምናፍቃችሁ ወዳጆቼ በወደደን እስከሞት ድረስ ባፈቀረን በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ፍቅር እንደምን ቆያችሁ? የማያልቅበት ባለጸጋ፤ ፍጥረቱን የሚጠብቅ አልፋና ኦሜጋ፤ሕይወት እንዲበዛልን የመጣ፤ከማንም እና ከምንም ጋር የማይስተካከል፤በመዳፉ የቀረጸን፤መቼም የማይተወን ስሙ መድኃኒት፤እጁ ፈውስ፤እውነተኛ ሐኪም፤ዳግመኛ በማንሞትበት ድኅነት ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን አምላካችን እና አባታችን እግዚአብሔር ይመስገን።

ሰማይና ምድር የማይችሉትን አምላክ በድንግልና ጸንሳ በድንግልና የወለደች የድህነታችን ምክንያት ወላዲተ አምላክ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም በፍጥረት ሁሉ አንደበት የተመሰገነች ትሁን፤ለቅዱሳን መላእክት፤ለጻድቃን፤ለሰማእታት እንደየክብራቸው ምስጋና ይድረሳቸው። መዝ 32፡1፤ሉቃ 1፡48፤ሮሜ 2፡10

በዚህ ርዕስ ሶስት መሰረታዊ ነገሮችን እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ እንማማራለን 1.ድኅነት ምንድን ነው? 2. መዳን በሌላ በማንም የለም ምን ማለት ነው? 3. ለመተርጎም ምን ያስፈልጋል?

ወዳጆቼ አንዳንድ ጊዜ የመዳን ምስጢርን በእምነት ልናየው ካልቻልን እና ሁሉን በዓይናችን ካላየን አናምንም የምንል ከሆነ ሁሉ ነገር ከንቱ መስሎ ሊታየን ይችላል። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ሰው የጻፈው ነው፤ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰቀል አላየውትም፤የወለደችሁ ማን እንደሆነች አላውቅም፤መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ ይጋጫል፤ቃሉ አማረኛ ስለሆነ ትርጉም አያስፈልገውም ፤እንደፈለኩት መረዳት እችላለሁ...የሚሉትን አስተሳሰቦች ልባችን የሚያሰሳስበን ካላየን አናምንም በምንልበት የጥርጣሬ ሕይወት ስንኖር ነው።

ይህ ደግሞ እምነት ከዕውቀት በላይ አይደለም ከሚሉት ከዕውቀት ሰዎች እንድንመደብ ያደርገናል ፍጻሜውም ክህደት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እምነት ዕውቀት ሊደርስበት ከሚችለው በላይ የራቀ እና የረቀቀ እንደሆነ ይመሰክራል። << እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው...ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።>>እንዳ

ለ።ዕብ 11፡1 አምላካችን እግዚአብሔር በእምነት እየኖርን ፍቃዱን እየፈጸምን የምንመላለስበትን ሕይወት ይሰጠን ዘንድ ቅዱስ ፍቃዱ ይሁን።

1.ድኅነት ምንድን ነው?

ድኅነት ማለት የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ያጣውን የዘላለም ሕይወት መልሶ ያገኘበት መንገድ ነው።እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለስም አጠራሩ ክብር ይሁን። አሜን። ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና››እንዳለ።ዮሐ 3፡16

የመዳን ትምህርት ወይም ነገረ ድኅነት(soteriolog

y) የቤተክርስቲያን ትምህርት መሰረትና የማዕዘን ድንጋይ ነው። ማንኛውም ትምህርት የሚመዘነው እና የሚለካው በነገረ ድኅነት ትምህርት ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ አልዳነም ብሎ ማስተማር በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የተወገዘ እና የተለየ ነው። ይህ ማለት ግን አንድ ጊዜ ድኖለው እና በኃጢአት ብኖር ችግር የለውም እንድንል ሳይሆን ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሳችሁ፤ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።›› እንዳለ በጽድቅ ልንኖር ይገባል። ምክንያቱም ‹‹አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበተበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልዳልና በገዛ ስጋው የሚዘራ ከስጋ መበስበስን ያጭዳልና በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል። ገላ 6፡7-8፤ዳን 12፡2፤

ቆላ 3፡1፤ሮሜ 2፡6

የሰው ልጅ ዳነ ሲባል ሞቱ በሕይወት ተለወጠለት ማለት ነው። ዘፍ 2፡17 የተፈረደበት ሞት ነበር ነገር ግን ‹‹...እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ስልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው፤በሕይወታቸው የተፈረደበትም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሀት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በስጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።››እንዳለ።ዕብ 2፡14-15 ክብር ለእርሱ ይሁንና ሞቱን በሕይወት ለወጠለት።

የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ጸጋ የዳነበትን ድኅነት ለመፈጸምና በዚሁ የድኅነት አገልግሎት ተካፋይ ለመሆን የሚያስፈልጉት ሦስት መሰረታዊ ነገሮች

1. በእውነት ማመን ፡- ‹‹ በወልድ ያመነ የዘላለም ሕይወት አለው፤በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።›› እንዳለ።ዮሐ 3፡36 እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ያዳነበትን መንገድ ማመን መቀበል ያስፈልጋል።ዮሐ 5፡24 የማያምን ግን አሁኑኑ ተፈርዶበታል።እንዳለ። ዮሐ 3፡18፤1 ዮሐ 4፡15፤5፡10

2. የቤተክርስቲን ምሥጢራትን መፈጸም፡-

2.1. ምሥጢረ ጥምቀት ‹‹የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችኋልና›› እንዳለ።ገላ 3፡27፤ማር 16፡16፤1 ጴጥ 3፡21

2.2. ምሥጢረ ሜሮን ‹‹ እናንተ ከቅዱሱ ቅባት ተቀብታችኋል፤ሁሉንም ታውቃላችሁ።...እናንተስ ከእርሱ የተቀባችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፤ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንዲያስተምራችሁ፤ እውነተኛም እንደሆነ፤ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ።››1 ዮሐ 2፡20-27

2.3. ምሥጢረ ቁርባን ‹‹...እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ስጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም ። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው።እኔም በመጨረሻው ቀን እስነሳዋለሁ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።››ዮሐ 6፡53-56

ወዳጆቼ እነዚህን ሦስት ምስጢራት ያልፈጸመ ሰው በእግዚአብሔር ጸጋ በተሰጠው የመዳን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን አይችልም።ድኅነትም የለውም እነዚህን የፈጸመ ክርስቲያን እንጨት ሆኖ የማይጤስ እንዲሉ ቢበድል እንኳ ዘወትር ንሰሐ ሊገባ ይገባል።

3. ትሕዛዛቱን መጠበቅ፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንድ ወጣት ባለጸጋ ‹‹ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ትህዛዛትን ጠብቅ››ማቴ 19፡16 እንዳለ ትህዛዛቱን መጠበቅ ለመዳናችን በጎ ፍጻሜ ነው። በዚህ ውስጥ መልካም ስነ ምግባር ያብባል፤ ይህ ካልሆነ ለመዳናችን የተከፈለውን ዋጋ ውለታ መዘንጋት ነውና መንግስቱን መውረስ አንችልም። አንዳንድ ሰዎች በጸጋው ስለዳንን ምግባር አያስፈልግም ብለው ሲሟገቱ ይገኛሉ ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ሲመልስ ‹‹ ወይስ ዓመጸኞች የእግዚአብሔርን መንግስት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀራጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሰሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም የሚሰክሩ ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም።›› እንዳለ። 1 ቆሮ 6፡9-10

2. መዳን በሌላ በማንም የለም ምን ማለት ነው?

ይቆየን ይቀጥላል

ምንጭ፡- - መጽሐፍ ቅዱስ(ሰማንያ አሐዱ)

- ኢየሱስ ፈራጅ ወይስ አማላጅ በዲያቆን አሐዱ አስረስ

- ቃል ኪዳን በነገረ ድኅነት በዲያቆን ያረጋል አበጋዝ

- ኦርቶዶክስ መልስ አላት በዲያቆን ዳንኤል ክብረት

- Christology note by father doctor Jossi Jacob

- የነገረ ቅዱሳን ኖት በሳምሶን ጣሰው

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ

Miko ZE Ethiopia

45/ እንጀራ ሳንበላ ስንት ቀን መቈየት እንችላለን? ውኃ ሳንጠጣ ስንት ቀን መቈየት እንችላለን? አዲስ ልብስ ሳንገዛስ? ይኼ ኹሉ ግን ስለ ምድራዊ ቆይታችን የምናደርገው ነው። ነፍሳችንስ ኀብስተ ሕይወት ክርስቶስን ከበላች ስንት ዘመን አለፋት? ስቴ ሕይወት ክርስቶስን ከጠጣች ስንት ጊዜያት አለፉ? የኃጢአት ካባ ከደረብን ስንት ዘመናት አለፉ? አብዛኖቻችን በሕግንነት ዘመናችን እንደቈረብን ግልጽ ነው። ግን ለምን? ተወዳጆች ሆይ! ለምን እንፈራለን? መድኃኒት መውሰድ እንደምን ያስፈራናል? እንኪያስ ምንም ምክንያት አንስጥ። ደስተኛ ሕይወትን

ለመምራት ወደ መጠጥ ቤት፣ ወደ ዳንኪራ ቤት ከመሔድ ወደ ክርስቶስ እንምጣ። እኛ በክርስቶስ፤ ክርስቶስም በእኛ ይኹን። እስከማገባ፣ ወጣት ስለኾንኩ የሚለው ኋላ ቀር አስተሳሰብን ጥለን ወደ ሕይወት ክርስቶስ እንምጣ። በድፍረት ሳይኾን፤ “ጌታዬ ሆይ! ኃጢአተኛ እንደኾንኩ ዐውቃለኹ። ነገር ግን ያላንተ ሕይወት እንደሌለኝም ዐውለኹ። ስለዚኽ ቸርነትኽን ተማምኜ ወደ አንተ እቀርባለኹ” ብለን እንምጣ። አባቶቻችን ያስተማሩን እንደዚኽ ነው። ኦርቶዶክሳዊነት እንደዚኽ ነው። ካልኾነ ግን የሕይወት ትርጒሙ ምንድነው? የሕይወት ዓላማው ምንድነው?

መቅረዝ ዘተዋሕዶ ይኽን መልዕክት አበክራ ታስተላልፋለች።

- ንስሐ አባት ያልያዝን ንስሐ አባት እንያዝ። ንስሐ አባት ስንይዝም “አለኝ” ብለን የሕሊና እርካታ ለማግኘት ብቻ መኾን የለበትም። በትክክል ንስሐ ገብተን ወደ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ለመድረስ እንጂ።

Miko ZE Ethiopia

46/ የማይስማሙትን እንዲስማሙ አድርጎ ፈጠራቸው

ሊቀ ሊቃውንት ስምዐኮነ መልአክ

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ከሰባት እርስ በርሳቸው ከማይስማሙ ነገሮች ፈጥሮታል:: አራቱ ባሕርያት እግዚአብሔር በጥበቡ ካላስማማቸው በቀር መቼም የማይስማሙ ባላንጣዎች ናቸው። ምን አልባት ተስማምተው ከተገኙም በጽርሐ አርያም ባለው የእግዚአብሔር ማደሪያ ብቻ ሊሆን

ይችላል። በዚያ ግን ባለጠጋው እግዚአብሔር የውኃ ጣራ፤ የእሳት ግድግዳ ያለው አዳራሽ ሠርቷልኽ ዓለም ከተፈጠረ እስከ ዛሬ ተስማምተው ይኖራሉ እንጂ አንዱ ባንዱ ላይ በክፋት ተነሳስቶ ውኃው እሳቱን አሙቆትኽ እሳቱም ውኃውን አጥፍቶት አያውቅም። ይህ ትዕግስታቸው በፍጥረት ሁሉ አንደበት ሠሪያቸውን እንዲመሰገን አድርጎታል::

በታች ባለው ምድራዊ ዓለምም ያለው ብቸኛው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሰው ልጅ ነውና እነዚህ እርስ በእርስ የማይስማሙ መስተጻርራን ነገሮች ተስማምተው የሚኖሩበት ዓለም ሆኗል። እሳት ከውኃ፤ ነፋስ ከመሬት ጋር የሚያጣብቃቸውን የፍቅር ሰንሰለት የሰው አዕምሮ ተመራምሮ ሊደርስበት የማይችል ታላቅ ምሥጢር ነው። ግን እንዴት ይሆናል? ነፋስ መሬትን ሳይጠርገው፤ መሬትም ነፋስን ገድቦ ይዞ መላወሻ መንቀሳቀሻ ሳያሳጣው፤ ተስማምተው እንዲኖሩ ያደረገ እግዚአብሔር ታላቅ ነው። ውኃና እሳት ተቻችለው አንድ ቤት ውስጥ መኖር ችለዋልኽ የጥንት ጠላትነታቸውን በጥበበ እግዚአብሔር አስታራቂነት እርግፍ አድርገው ትተው ከሞት በቀር ማንም ላይለያቸው በቃል ኪዳን ተሳስረዋል።

አሁን እሳት ውኃን በቁጣ ቃል አይናገረውም ውኃም በእሳት ፊት ሲደነግጥ አይታይም እንዲያው ሰው በሚባለው ዓለም ውስጥ በሰላም ይኖራሉ እንጂ። የነቢዩ ዳዊት ቃል ለነርሱ ያለፈ ታሪክ ማስታወሻ ቃል ነው። “ከመጸበል ዘይግህፎ ነፋስ እምገጸ ምድርኽ ከምድር ገጽ ላይ ነፋስ እንደሚበትነው አፈር.....” ይባል ነበር አባቶቻችንም ስለ ወንጌላዊው ማቴዎስ ሲተርኩልን “ሶቤሃኬ ተንሥአ ማቴዎስ ወንጌላዊ ከመ ተንሥኦተ ማይ ላዕለ እሳትኽ ውኃ በእሳት ላይ በጠላትነት እንዲነሣ ወንጌላዊው ማቴዎስም ተናዶ

ተነሣ" በማለት ወንጌልን ለመጻፍ የተነሣበትን ምሥጢር አጫውተውናል። ማንኛውም ነገር አጥፊና ጠፊ ሆኖ ከተነሣ በእሳትና በውኃ መመሰል የተለመደ ጉዳይ ነው። የእግዚአብሔር ልዩ ሥነ ተፈጥሮ ባረፈበት የሰው ሕይወት ግን እንዲህ አይደለም። እሳትና ውኃ እስከ መቃብር የሚዘልቅ የፍቅር መንገድ ጀምረዋል ነፋስና መሬትም እስከ ፀኣተ ነፍስ ላይለያዩ ወስነዋል። ይህ የፍቅር ኑሯቸው ደግሞ ሌላ አዲስ ነገር ፈጠረላቸው ለመላእክት እንኳን ያልተደረገ አዲስ ነገር እግዚአብሔር በሰው ሕይወት ላይ እንዲያደርግ አስገድዶታል፤ የማትሞትና የማትበሰብስ ነፍስን በሥጋ ውስጥ አኖራት። ሌላ አስደናቂ ነገር ነው። የአራቱ መስተጻርራን መዋሐድ የፈጠረው ሌላ አስደናቂ መዋሐድ።

በጥቂቱም ቢሆን ከመላእክት ጋር ዝምድና ያላት ነፍስ በእጅጉ ከማይስማማት የሥጋ ባህርይ ጋር ተስማምታ መኖሯ አስደናቂ ነገር ነው። አራቱ ባህርያት ልዩነታቸውን አጥፍተው በፍቅር ተስማምተው ብታይ እሷም ሁሉን ረስታ ከሥጋ ጋር ተስማምታ ለመኖር ወሰነች እናም ሥጋ ብዙ ድካሞች እንዳሉበት ብታውቅም ከነድካሙ ታግሳው አብራው ትኖራለች። ሥጋ ይተኛል ያንቀለፋል፤ እሷ ግን በድካሙ ሳትነቅፈው እንዲያውም ተኝቶም በሕልም ሌሎችን የሕልም ዓለማት እንዲጎበኝ በተሰጣት ጸጋ ይዛው ትዞራለች። በሕልም ሠረገላ ተጭኖ በነፍስ መነጽርነት አነጣጥሮ የተመለከተውን አንዳንዱን ሲደርስበት ሌላውንም በሩቅ አይቶ ተሳልሞ ሲተወው ይኖራል።

ያዕቆብ እንዳየው የተጻፈው ሕልም አስገራሚ ከሚባሉት ሕልሞች ዋናው ነው። ምክንያቱም በምድር ያለ ሰው የእግዚአብሔርን ዙፋን በሕልም

ያየበትና የሰማይ መላእክትን የአገልግሎት ሕይወት የተካፈለበት ሕልም ስለሆነ ነው ዘፍ 28÷10። ያዕቆብ በነፍሱ ያየው ይህ አስደናቂ ሕልም ከሦስት ሺህ የሚበዙ ዓመታትን አሳልፎ ፍጻሜውን በክርስቶስ ልደት አይተናል ዮሐ 1÷50። ታዲያ ነፍሳችን በዘመን መጋረጃ የተጋረዱ ምሥጢራትን ሳይቀር አሾልካ መመልከት የምትችል ኃይል ናት ማለት ነው፤ እሷም የፍቅር ውጤት ናት። ተፈጥሮአችን ከምታስተምረን ነገሮች አንዱ ትዕግስት ነው። ሁልጊዜ ትዕግስት ፍቅርን፤ ፍቅር ደግሞ ሁሉን ሲገዛ ይኖራል ሰማያዊም ሆነ መሬታዊ ኃይል ለነዚህ ነገሮች ይሸነፋል ምን አልባት ሰው ሁሉን አሸንፎ የመኖሩ ምሥጢር ይህ ሊሆን ይችላል። ተፈጥሮው ትዕግስትን፤ ትግስት ደግሞ ፍቅርን ወልዳለታለች ከዚህ የተነሣ ተፈጥሮን መቆጣጠር የቻለ እንደሰው ያለ ማንም የለም። እስኪ ልብ በሉት ሞትን በቃሉ የሚገስጽ፣ ደመናትን በእጆቹ የሚጠቅስ፣ የሰማይን መስኮቶች የሚመልስ፤ እስከ ሰባተኛው ሰማይ ወጥቶ የሚቀድስ የሰው ልጅ አይደል? ባንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሁሉም ነገር ለሰው አገልግሎት ሲባል የተፈጠረ ነው። የማይስማሙትን አስማምቶ ባንድ ላይ ማኖር መቻል ትልቅ ጥበብ ከመሆኑም በላይ ትዕግስት ካለ ሁሉም ፍጥረት ተቻችሎ ባንድነት መኖር እንደሚችልም አመላካች ነው።

ተቻችለው የመኖራቸው ምሥጢር፡-

እያንዳንዳቸውን ብንመለከት አራቱም ባህርያት ለያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ባሕርያት አሏቸው፡- የእሳት ባህርይ ውእየትና /ማቃጠል/ ይብሰት /ደረቅነት/ ሲሆን፤ የውኃ ደግሞ ቀሪርነትና /ቀዝቃዛ/ ርጡብነት /ርጥብነት/ ናቸው። እነዚህ ሁለቱም ባህርያት በምንም ይሁን በምን

መስማማት አይቻላቸውም እግዚአብሔር ግን በሌላ በኩል የእርቅ መንገድ ፈልጎ ሲያስታርቃቸው እንመለከታለን። ይሄውም በነፋስና በመሬት በኩል ነው፤ የነፋስ ባህርያት ውእየትና ቆሪርነት ሲሆን የመሬት ባህርያት ደግሞ ይቡስነትና ርጡብነት ናቸው። አሁን ዝምድናውንና ማንን በማን እንዳስታረቀ ስንመለከት እሳትና ውኃን በነፋስ አስታርቋቸዋል። ነፋስ በውዕየቱ ከእሳት፤ በቆሪርነቱ ከውኃ ጋር ተዘምዶ አለው፤ በመካከል ለሁለቱም ዘመድ ሆኖ በመገኘቱ እሳትን ከውኃ ጋር አንገቱን ደፍቶ እንዲኖር አድርጎታል። የመሐል ዳኛ ባይኖራቸው ኖሮ እሳቱ ውኃውን እንደ ክረምት ነጎድጓድ አስጨሆት ውኃውም እሳቱን እንደ መብረቅ ሳይታሰብ በላዩ ላይ ወርዶበት ተያይዘው በተላለቁ ነበር።

ነፋስና መሬትን ደግሞ ውኃን ሽማግሌ አድርጎ ሲገላግላቸው እናያለን ውኃ በቀዝቃዛነቱ፤ ነፋስን በርጥበቱ መሬትን ይዘመዳቸዋል ይህን ዝምድናውን ተጠቅሞ ሁለቱን መስተጻርራን በትዕግስት አቻችሏቸው ይኖራል። አብረው በመኖራቸው ደግሞ ነፋስ ከመሬት ትእግስትን ተምሯል አብሮ መኖር ከሰይጣን ጋር ካልሆነ ከማንኛውም ፍጥረት ጋር ካወቁበት ጠቃሚ ነው፤ አብሮነት የለወጣቸው ህይወቶች ብዙ ናቸው። ዐስራ ሦስቱን ሽፍቶች ያስመነነው አንድ ቀን ከናፍርና ከሚስቱ ጋር የተደረገ ውሎ ነው፤ ያውም ገንዘብ ሊዘርፉና አስካፍን ሊማርኩ ሄደው ህይወታቸውን አስማረኩ፤ የጦር መሣሪያ ታጥቀው ሄደው ላልታጠቀው ተንበረከኩ። ክርስትና እንዲህ ሲሆን የእውነተኛነቱ ማረጋገጫ ነው ምክንያቱም ክርስትና ማለት አንዱ ብዙዎችን የሚያሸንፍበት፤ ወታደሩ ንጉሡን የሚማርክበት፤ ገረድ እመቤቷን የምታንበረክክበት ያሸናፊዎች ሕይወት ነውና። ሳይታኮሱ ደም ሳያፈሱ

አብሮ በመዋል ብቻ ከህይወታቸው በሚወጣው የሕይወት መዓዛ ብቻ የሰውን አካሉን ብቻ ሳይሆን ልቡን ጭምር መማረክ ያስችላል። ዐስራ ሦስት ሰው ባንድ ጊዜ እጅ የሰጠውም ከዚህ የተነሣ ነው እናም አብሮነት የሚጎዳው ከሰይጣን ጋር ብቻ ከሆነ ነው። ከዚያ ውጭ ግን የአትናስያን ሕይወት የለወጠ፤ ኃጢአቷን ከልቧ እንደ ሰም ያቀለጠ፤ ላንዲት ሰዓት ከዮሐንስ ሐጺር ጋር የነበራት ቆይታ ነው። እነ ማርያም ግብፃዊትን ከዘማዊነት ወደ ድንግልና ሕይወት የለወጠስ ላንድ ቀን ብቻ ወደ ኢየሩሳሌም ከሚሄዱ ሰዎች ጋር የተደረገ ውሎም አይደል? ያን የመሰለ የቅድስና ሕይወት ባንድ ጀንበር የገነባ አብሮነት በመሆኑ የሕይወት ትምህርት ቤት ነው።

በእርግጥ እግዚአብሔር ያልባረካት ሕይወት ከማንም ጋር ብትውል ለውጥ እንደሌላት በይሁዳ፣ በዴማስ፣ በግያዝ ሕይወት ማወቅ ይቻላል። ይህ ማለት ግን የተሰበረ መንፈስ ለሌላቸው ቅንነት ለጎደለባቸው ማለት እንጅ አብሮ በመኖር የሚገኘውን ጥቅም የሚተካ ሌላ ነገር አለ ማለት አይደለም። ነፋስን በቅጽበት ዓለማትን መዘሩን ትቶ ባህሩን የብሱን መቆጣቱን ረስቶ ተረጋግቶ እንዲኖር ያደረገው ከመሬት ጋር አብሮ መኖሩ እኮ ነው ።

መሬትም በአንጻሩ ከነፋስ ጋር በመኖሩ ፈጣን ደቀ መዝሙር ሆኗል። መሬትን የምናውቀው የማይንቀሳቀስ ፅኑ ፍጥረት መሆኑን እንጂ መሬት ሲንቀሳቀስ የምናውቀው አይደለምን? በሰው ባህርይ ውስጥ የመሬትን ባህርይ ተንቀሳቃሽ ያደረገው ከነፋስ ጋር አብሮ መሠራቱ ነው እንጂ ሌላ ምን አለው መጽሐፍ ስለ መሬት ሲናገር የተናገረው እንዲህ ነበር። "ዘአጽንኣ ለምድር ዲበ ማይ፤ ምድርን በውኃ ላይ ያጸናት" መዝ

135÷6 በማለት የምድርን ፅናት ይመሰክራል። ሰውን ስንመለከተው ሌላ አዲስ ፍጥረት ይመስለን ይሆናል እንጂ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ሁለት ፍጡራን አንዷ ከሆነቸው ምድር የተገኘ ምድራዊ ፍጥረት ነው። ነገር ግን የሚንቀሳቀስ ምድር መሆኑ አስገራሚ ፍጥረት ያደርገዋል የዚህ ምሥጢር ደግሞ የተሠራበትን ምድር በነፋስ ሠረገላ ላይ ጭኖ የፈጠረው መሆኑ ነው የተጫነበት ሠረገላ ፈጣን ከመሆኑ የተነሣ የማይንቀሳቀሰውን እንዲንቀሳቀስ ያደርገዋል።

መሬትም ለፈጣኑ የነፋስ እግሮች ጭምትነትን ያስተምርለታል። ባጭር ጊዜ አድማሳትን ማካለል የሚቻለው ነፋስ ጭምትነትን ገንዘብ ሲያደርግ ትዕግስትን ለብሶ ሲመላለስ ማየት ምንኛ ድንቅ ነው። ከዚያም በላይ አራቱንም በሌላ ሁለት ነገር እንከፍለዋለን፦ ቀሊልና ክቡድ ብለን። ቀሊላኑ እሳትና ነፋስ ሲሆኑ ክቡዳኑ መሬትና ውኃ ናቸው። እንደ ውኃና ነፋስ ምን ቀላል ነገር ይኖራል? እንደ መሬትና ውኃስ ማን ይከብዳል? ቢሆንም ግን አብረው ይኖራሉ እንዲያውም ክቡዳኑ መሬትና ውኃ ከላይ የተቀመጡ ሲሆን ቀሊላኑ እሳትና ነፋስ ግን ከስር ሆነው ክቡዳኑን ሊሸከሙ ከእግዚአብሔር ተወስኖባቸዋል፤ ሁለቱም እርስ በእርስ ተጠባብቀው ይኖራሉ። ነፋስና እሳት ቀላል ከመሆናቸው የተነሣ ወደ ላይ እንዳይወጡ መሬትና ውኃ ከላይ ሆነው ይጠብቃሉ፤ መሬትና ውኃ ደግሞ ከባዶቹ ናቸውና ወደታች እንውረድ ሲሉ ነፋስና እሳት ሐላፊነቱን ወስደው ከመውደቅ ይታደጓቸዋል። ይህ የተፈጥሮ ስጦታ ሰውን ወደታች ወርዶ እንጦርጦስ እንዳይገባ፤ ወደ ላይም ወጥቶ እንዳይታበይ ማእከላዊ ፍጡር አድርጎ ሲጠብቀው ይኖራል። ፈጡራንን ሲፈጥር በመካከላቸው መረዳዳትን

የግድ ባያደርገው ኖሮ ማንኛውም ፍጡር አብሮ ለመኖር ባልተስማማ ነበር። ምንም ላንጠቅመው የሚወደንና የሚጠብቀን የሰማዩ አምላክ ብቻ ይሆናል። ፍጥረታት ግን እርስ በእርስ ተጠባብቀው የሚኖሩት አንዱ ያለ አንዱ መኖር ስለማይችል ብቻ ነው።

እንደዚያማ ባይሆን ኖሮ ነፋስ እሳቱን አግለብልቦ አንድዶት እሳቱም በፋንታው ውኃውን አንተክትኮት ውኃም መሬትን ሰነጣጥቆ ጥሎት አልነበረምን? ግን ይህ ሁሉ ከመሆኑ አስቀድሞ ከእግዚአብሔር የተሰወረ አልነበረምና አራቱንም ኑሯቸውን እርስ በእርስ የተሳሰረ አድርጎታል። መሬትና በውስጧ የሚኖሩ አራቱ ባህርያት ተስማምተው መኖራቸው ከመሬት በላይ የሚኖሩ ፍጥረታት ተስማምተው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። አንዱ ሌላውን በመታገሱ የተከሰተ ነውና ለሁሉም ነገር መሠረቱ ትዕግስት መሆኑ የማይካድ ሀቅ ነው።

ከዕለታት አንዳንድ ቀናት አሉ አራቱ ባህርያት የማይስማሙባቸው። ታዲያ በነዚህ ቀናት ሰው ተኝቶም እንኳን አይተኛም፤ የነፋስ ባህርይ የበረታ እንደሆነ ሲያስሮጠው ከቦታ ቦታ ሲያንከራትተው ያድራል፤ የመሬት ባህርይ ቢጸና ደግሞ ከገደል ሲጥለው፤ ተራራ ተንዶ ሲጫነው ያያል፤ እሳታዊ ባህርይም በእሳት ተከበን፤ እሳት ቤታችንን በልቶ ሲያስለቅሰን ያሳያል፤ ውኃም እንደሌሎቹ ሁሉ ሰውን በባህሩ ሲያጠልቀው ውኃ ለውኃ ሲያመላልሰው ያድራል። እያንዳንዳቸው ተስማምተው እንዲኖሩ ባያደርጋቸው ሰው በመኝታው እንኳን እረፍት ማግኘት እማይችል ፍጡር ነበር ማለት ነው። ስለዚህ ትዕግስት ለማንኛውም ነገር መሠረት ነው።

ሁሉም በጎ ነገሮች በሰማይም በምድርም የሚገኙት የትዕግስት ውጤቶች

መሆናቸውን ልብ ይሏል። ሰው በራሱ የትዕግስት ውጤት መሆኑን ካየን የምንጠብቀው አዲሱ ዓለም መንግሥተ ሰማይ የትዕግስት ስጦታ ነው፤ ምክንያቱም መጽሐፍ የሚለው “እስከ መጨረሻው የታገሰ ይድናል” ነውና። ሞታችንን የገደለው፤ ጨለማን የሳቀየው ማነው? ክርስቶስ በዕለተ አርብ በህማሙ ወቅት ያሳየው ትእግስትም አይደል! ይሄ ትዕግስት ፍጥረቱን ሁሉ ያስደነቀ ትዕግስት ነበር። ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አንዱ “አ! ትዕግስት ዘኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ በቅድመ እለ ይረግዝዎ፤ በመከራው ወቅት በሚወጉት ሰዎች ፊት የማይናገር ትዕግስት” ሲል በቅዳሴው ያደንቃል። በዚህ አስደናቂ ትዕግስቱ እኮ ነው ኃይለኛውን እስከ ወዲያው ጠርቆ ያሰረው ማቴ 12÷29። ኃይለኛውን አስሮ ቤቱ ሲያልን በርብሮ አወጣን። እንግዲያውስ ትዕግስት ጉልበት ነው፤ ትዕግስት ውበት ነው። በዓለም ላይ በጦርነት ከተሸነፉት በትዕግስት የተሸነፉት ይበዛሉ፤ ባለ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ጦር የነበረው ሰናክሬም በሕዝቅያስ ትዕግስት መሸነፉን አንዘነጋውም።

Miko ZE Ethiopia

POSTED BY Sewaferawe Alene

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

ትምሕርተ ሃይማኖት/ክፍል አንድ/

በተከታታይ ስለማቀርብላችሁ ተከታተሉ

47/ ሃይማኖት

መግቢያ

1 ሃይማኖት ፤ ሃይመነ አሳመነ ፤ ካለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም በአንድ አምላክ ማመን እ ለአንድ አምላክ መታመን ማለትን ያመለክታል ፤ በዓይናችን ለምናየው ለግዙፉ ዓለምና ለማይታየው ለረቂቁ ዓለም ፈጠሪ አስገኝ ፣ መጋቢ... አለው ፤ እሱም እግዚአብሔር ነው ብሎ ማመን የሃይማኖት የመጀመሪያ ክፍል ነው ።

እምነት ማለትም ፤ አምነ አመ ነ ፣ ካለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሆኖ ትርጉሙ ም ለእግዚአብሔር መታመንነና በእግዚአብሔር ማመንን ይገልጣ ል ነው ። ቅዱስ ጳውሎስ “ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ የሚታየውም ከማይታየው እንደሆነ እናውቃለን” ዕብ 11 ፥ 3 ። በማለት እንደተናገረ ። የሰው ልጅ የሃይማኖት ትምሕርት ከመማሩ አስቀድሞ በህሊናው በመመራት የእግዚአብሔርን መኖር ማመን ተገቢ ነው ።

የሃይማኖት ትምሕርት ፤ የሚ ነገረው የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን በመቀበል የምናምነው ን የምንማርበት እንጅ ፣ እንደ ዓለማዊ የሳይንስ ዕውቀት የተማርነው ን ሁሉ በዘመናዊ መሳሪያ አረጋግጠን የምንደርስበት አይደለም ። ሃይማኖት ቁስ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ታምነቀው ኢየሚኖሩት ሕይወት ነውና ። የእግዚአብሔር መንግሥት ተቃዋሚዎች አጋንንት ሳይቀሩ አይጠቀሙበትም እንጅ የአምላክን መኖር ያምናሉ ይንቀጠቀጣሉም ። ያዕ 2 ፥19 ።

በዚህ ዓለም በራሱ የተገኘ ምንምነገር እንደሌለና ለሁሉም አስገኝ ፤ ፈጣሪ እንዳለው ይታወቃል ። የሳይንሱ የምርምር ውጤ ት፣ ሁሉን የፈጠረው ን ታይል በሥጋዊ ጥበብ ተመራምሮ አልደረሰበትም ። በሃይማኖት ትምሕርት ግን ሁሉን ያስገኘ እግዚአብሔ ር መሆኑን መረዳት ይቻላል ። የሰው ልጅ የሠራቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚያንቀሳቅስ ባለሞያ እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ ይህን ዓለምም የሚያንቀሳቅሰውና የሚመራው ፤ አስገኝው (የፈጠረው) አምላክ ብቻ ነውና ። ሰው ይህን የአምላክ ሥራ አይቶ ፈጣሪውን ማመስገን ሲገባው “የተፈጥሮ ክስተት ነው” ሲል ይደመጣል ።

ለምሳሌ ጨለማና ብርሃንን ፣ ወቅቶችንና ዘመናትን ፣ የሚያፈራርቅ ፣ የሰውን ልደትና ሞት የሚወስን ፤ ሌሎችም ፍጥረታት ሥርዓታቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ የሚያደርግ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠራቸው አምላክ ብቻ ነው ፤ የሰው ልጅ የተደረጉና ያለፉ ታሪኮችን ከመመዝገብ ያለፈ ችሎታና አቅም የለውም ።

2 እምነት ፤ ቅዱስ ጳውሎስ “በሥጋ ዓይን የማናየውንና ተስፋ የምናደርገውን የሚያስረዳና የሚያስረግጥ መሳሪያ ነው ። ዕብ 11 ፥ 1 ።” በማለት እንዳስተማረ ፤ በሃይማኖት የሚኖር ሰው ዕለት ዕለት በሚ ያደርግለት የቸርነት ሥራው አምላኩን ያየዋል ለማ ያምንና ፍረጥረታዊ ለሆነ ሰው ግን የሃይማኖት ነገር ለእሱ ሞኝነት ስለሆነ ለህሊናው ሊረዳውና ፥ ሊቀበለው ኤይችልም ። 1 ቆሮ 2 ፥ 9 ።

3 ሃይማኖት ፤ ሰዎችና እግዚአብሔር የሚገናኙባት መንታነት የሌለባት አንዲት መንገድ ናት ። ኤፌ 4 ፥ 4 ። በዓለማችን የሚገኙት የተለያዩ

የሃይማኖት ተቋማት የግል ጥቅምና የሥልጣን ሱስ የተጠናወታቸው ፣ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ ለራሳቸው ክብርና ዝና ቅድሚያ የሚሰጡ ፤ አዲስ ነገር በመሥራት ታዋቂነትን ለማትረፍ የሚፈልጉ ግለሰቦች የመሠረቷቸው ድርጅቶች መሆናቸው ግልጽ ነው ። ምክንያቱም ፤ ሁሉም እየተለዩ የወጡት ከመጀመሪያዋ አንዲት ሃይማኖት ነውና ፤

ሃይማኖት ከቅዱሳን መላእክት ጀምሮ ፀንቶ የሚኖር የአምላክና የፍጡራን ግንኙነት ነው።

ለምሳሌ ቅዱሳን መላእክት ፤ ሰይጣን ፡ዲያብሎስ “ፈጣሪ ነኝ” ባለበት ወቅት ቅዱስ ገብርኤል “አምላካችን እስኪገለጥልን ድረስ በእምነ ታችን እንጽና” ብሎ የተናገረውን ቃል ፤ መሪ በማድረግ በሃይማኖት ጸንተው ተገኝተዋል ። ራዮ.ሐ 12 ፡7 ።

ከአዳም እስከ ሙሴ ፤ የነበሩ ቅዱሳን ሰዎች ፤ የተጻፈ ህግ ሳይኖራቸው በህገ ልቡና እየተመሩ በሃይማኖት ጸንተው ኖረዋል ።

ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ፤ የነበሩ ቅዱሳን ሰዎች ፤ ቃሉን ሰምተው በመጠበቅ በሃይማኖታቸው ተመስክሮላቸው አልፈዋል ።

ሐዋርያት ፤ ቃሉን ሰምተው ፣ ተአምራቱን አይተው ፣ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ሃይማኖታቸውን ጠብቀው ፣ ለሌላውም አስተምረው ክርስትናን በዓለም አስፋፍተው በክብር አልፈዋል ።

ከሐዋርያት በኋላ የተነሱና እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚቀጥሉ ክርስቲያኖች ፤ ከቅዱሳን ሕይወትና ከመጻህፍት ተረድተው ፣ ከመም ህራን እየተማሩ ፣ በየዘመናቱ የሚደረገውን ተአምራት እያዩ ፤ በሃይማኖት ጸንተው ኖረዋል ፣ ይኖራሉም ። ስለዚህም ሃይማኖት በአምላክ ፈቃድ የሆነና በዘመናት ሁሉ

የነበረ ያለና የሚኖር ሕይወት ነው ።

4 ሃይማኖት ፤ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ሆነው ምሥጋና በማቅረብ ክብሩን ወርሰው እንዲኖሩ የሚያችል ሕይወት ነው

ከዚህ ከተቀደሰና ከትትክለኛው መንገድ የወጡ ሰዎች ከመጠራጠር ተነስተው እኛ ትንንሽ ከርስቶሶች ነን እስከ ማለት ደርሰ ዋል ። ሰው ለህሊናው ገደብ ካላበጀለትና ለእግዚአብሔር ክብር መስጠትን ከረሳ መጨረሻው ጥፋት መሆኑን እንረዳለን ።

5 ሃይማኖት ፤ በዘመናት ብዛት የማታረጅ ፣ የማትታደስ ፣ በየዘመኑ በሚነሳ ሥልጣኔ የማትለወጥ ሁሌም አዲስ ናት ። ሃይማ ኖት ፤ በልብ አምኖ በአንደበት መስክሮ የሚዳንበት ህይወት ነው ። ሮሜ 10 ÷ 10 ። ሃይማኖታችን በምግባር የሚገለጥ መሆን አለበት ። በሥራ የማይገለጥ ሃይማኖት ነፍስ የተለየችው ሥጋ “በድን” ማለት ነውና ። ያዕ 2 ÷ 26

Miko ZE Ethiopia

POSTED BY ASHENAFI MENGISTU "

48/ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው።" 1 ኛ ቆሮ. 1፡23

ክፍል 2

ክርስቶስን መስበክ ለአንዳንዶች እንደሚመስላቸው ስሙን እየጠሩ መጮኽ አይደለም፤ ራስን ከፍ ማድረግም አይሆንም፤ ጻድቅ ነኝ ብሎ መመጻደቅም አይደለም፤ ቅዱሳኑን መናቅም ሊሆን አይችልም።

ክርስቶስን መስበክ እምነትን ከምግባር ጋር አጣምሮ መያዝ ነው፦

(((ጾምን ቀድሱ ጉባኤውንም አውጁ ሽማግሌዎችንና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሰብስቡ ወደ እግዚአብሔርም ጩኹ። ትን. ኢዮ. 1፡14)))

ስለ ጾም መልካምነት ዕለት ዕለት ብናወራ ካልጾምን ምን ትርጉም አለው??? እናት ቤተክርስቲያን ግን ስለጾም አስተምራ ዝም አትልም ስርዓት አበጅታ፤ ቀኑንም ወስና ጾምን ታውጃለች ልጆቿንም ወደ ቤቷ ሰብስባ ያስተማረችውን በተግባር እንዲገለጥ ታደርጋለች።

(((ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ። ማቴ. 26፡41)))

ስለ ጸሎት ኃይል ቀኑን ሙሉ ብንመሰክር ካልጸለይን ምን ዋጋ እናገኛለን??? ቅድስት ቤተክርስቲያን ስለ ጸሎት ነግራን ዝም አትልም የጸሎት ስርዓትን አዘጋጅታ፤ ሰዓቱንም አሳውቃ ዕለት ዕለት በጸሎት እንድንተጋ ታደርጋለች።

(((ንስሀ ግቡ ኃጢያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። ሐዋ. 2፡38)))

እናት ቤተክርስቲያን የንስሀን ትምህርት በሚገባ ካስተማረች በኋላ ንስሀ እንድንገባ፤ ቀኖናም እንድንቀበል በማድረግ የንስሀ ጥምቀትን አጥምቃ ለታላቁ ክብር ታዘጋጀናለች።

(((ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለው። ዮሐ. 6፡54)))

ይህ ታላቁ ክብር ነው፤ የዘላለማዊ ሕይወት ቁልፍ ነው የተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በሚገባ አስተምራ ብቻ ዝም አትልም ኃጢያታቸውን በንስሀ ያጠቡና እንደ እግዚአብሔር ቸርነት ይህን የሕይወት ምግብ ለመቀበል የቀረቡትን ልጆቹዋን ቅዱስ ሥጋውን አብልታ ክቡር ደሙን ታጠጣቸዋለች።

እንግዲህ ስለ ስንቱ እንናገር ስለ ሌሎቹ እንዳልናገር ጊዜ ያጥርብኛል አለ ቅዱስ ጳውሎስ እናት ቤተክርስቲያናችን እንዲህ ናት በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም የተሰቀለውን ክርስቶስን የምትሰብክ፤ ልጆቿም ሕይወት ያለው (ምግባር ያለው) እምነት እንዲኖራቸው ዕለት ዕለት የምትተጋ።

የቅዱሳኑን ሥራ(ገድል) መመስከር ክርስቶስን መስበክ ነው፡-

የቅዱስ ጳውሎስ ጨርቅ ታላቅ ነገርን አደረገች ብንል የተሰቀለውን ክርስቶስን መስበክ ነው። የሐዋ. 19፡11

ስለ ቅዱስ ጴጥሮስ ጥላ ድውያንን መፈወስ ብንናገር የተሰቀለውን ክርስቶስን መስበክ ነው። የሐዋ. 5፡15

የነቢዩ ኤልሳ አጥንት ሙት ማስነሳቱን ብንመሰክር የተሰቀለውን ክርስቶስን መስበክ ነው። 2ኛ ነገ. 13፡21

ይህ ሁሉ ነገር በእርሱ ሆኗልና ስለ ቅዱሳኑ ክብር ብንናገር፣ ብንመሰክርም አንድ ክርስቶስን እየሰበክን ነው።

ቅዱሳን መጽሐፍት ሁሉ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ይናገራሉ፤ የቅዱሳኑም ክብር ክርስቶስን ያሳየናል፤ ሥራቸውም ክርስቶስን ይሰብካል ስለዚህም ቅድስት

ቤተክርስቲያን በአንድም በሌላም መንገድ የተሰቀለውን ክርስቶስን ስትሰብክ ኖራለች፤ አሁንም እየሰበከች ነው፤ ወደፊትም ትሰብካለች።

ቅድስት ቤተክርስቲያን ይህን ክርስቶስን በቃልም በተግባርም ስትሰብክ ፕሮቴስታንቱ ተሰናከሉ፤ ለአህዛብም ሞኝነት ሆነባቸው።

ፕሮቴስታንቱ ቢሰናከሉበትም፤ ለአህዛብም ሞኝነት ቢሆን እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን!!!

የእግዚአብሔር ቸርነት፤ የእመቤታችን አማላጅነት፤ የመላእክት ጥባቆት፤ የጻድቃን ሰማዕታት ተራዳኢነት ከሁላችን ጋር ይሁን፤ በእውነተኛይቱ መንገድ በተዋህዶ ያጽናን። አሜን!!!

Miko ZE Ethiopia

ወደ ገላትያ ሰዎች

6፥14

49/ ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።

ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

3፥18

ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና፤ ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ፥ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ።

ወደ ቆላስይስ ሰዎች

2፥14

በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው። እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል።

ወደ ዕብራውያን

12፥1-2

እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልከተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።

1 ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1

18

የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።

Miko ZE Ethiopia

2 ኛ፡ጢሞቴዎስ፥ምዕራፍ፡4።_____

ምዕራፍ፡4፤

1፤በእግዚአብሔር፡ፊት፡በሕያዋንና፡በሙታንም፡ሊፈር

ድ፡ባለው፡

50/በጌታ፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ፊት÷በመገለጡና፡በመንግሥቱም፡

እመክርኻለኹ፤

2፤ቃሉን፡ስበክ÷በጊዜውም፡አለጊዜውም፡ጽና÷ፈጽመኽ

፡እየታገሥኽና፡እያስተማርኽ÷ዝለፍና፡ገሥጽ፡

ምከርም።

3፤ሕይወት፡የሚገኝበትን፡ትምህርት፡የማይታገሡበት፡

ዘመን፡ይመጣልና፤ነገር፡ግን÷ዦሮዎቻቸውን፡

የሚያሳክክ፡ስለ፡ኾነ÷እንደ፡ገዛ፡ምኞታቸው፡ለራሳቸው፡አስተማሪዎችን፡

ያከማቻሉ።

4፤እውነትንም፡ከመስማት፡ዦሮዎቻቸውን፡ይመልሳሉ÷ወደ፡ተረትም፡ፈቀቅ፡

ይላሉ።

5፤አንተ÷ግን፡ነገርን፡ኹሉ፡በልክ፡አድርግ÷መከራን፡ተቀበል÷የወንጌል፡

ሰባኪነትን፡ሥራ፡

አድርግ÷አገልግሎትኽን፡ፈጽም።

6፤በመሥዋዕት፡እንደሚደረግ÷የእኔ፡ሕይወት፡ይሠዋል

ና÷የምኼድበትም፡ጊዜ፡ደርሷል።

7፤መልካሙን፡ገድል፡ተጋድያለኹ÷ሩጫውን፡ጨርሻለኹ÷ሃይማኖትን፡

ጠብቄያለኹ፤

8፤ወደ፡ፊት፡የጽድቅ፡አክሊል፡ተዘጋጅቶልኛል÷ይህንም፡ጻድቅ፡ፈራጅ፡የኾነው፡

ጌታ፡ያን፡ቀን፡ለእኔ፡

ያስረክባል÷ደግሞም፡መገለጡን፡ለሚወዱት፡ኹሉ፡እንጂ፡ለእኔ፡ብቻ፡አይደለም።

Miko ZE Ethiopia

51/ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን !!! አሜን (ኢዮብ 1:21)

አዲሱን ዓመት ስንቀበል ያሳለፍነው ዓመት የስኬትም ይሁን የጉድለት ፣ ያዘንንበትም ይሁን የተደሰትንበት ፈጣሪአችንን እያመሰገንን መሆን አለበት ። ክርስቲያን እግዚአብሔርን የሚያመሰግነው በሙላቱ ብቻ ሳይሆን በጉድለቱም ጭምር ነው ። እንዲያውም የክርስቲያን አመስጋኝነቱ የሚጎላና የሚወጣው የዲያብሎስ ፈተና በተደራረበበት ተስፋ የሚያስቆርጡ መከራዎች በጠነከሩበት ወቅት ነው ።

ክርስቲያን በመሆናችን ብቻ መከራ አያጋጥመንም ብለን አንዋሽም ፤ ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ፤ አይዞአችሁ ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ (ዮሐ 16:33) ስላለን ፤ ከተደቀነብን መከራና ፈተና በድል እንደምንወጣ ፣ ችግሩም ጊዜያዊና የምናሸንፈው መሆኑን አምነን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን እንጅ ። በህመምና በስቃይ ያሳለፍንም ወገኖች ብንኖር ፣ ህመማችን ለጥቅማችን መሆኑን ተረድተን እግዚአብሔርን ተመስገን ልንለው ይገባል ። ህመምና መከራ እንዴት ለጥቅማችን ይሆናል የሚል ሰው አይታጣምና የሚከተሉትን ማስረጃዎች አመለክታለሁ ።

ሀ/ በስጋ ደዌ (Leprosy) የተጠቁ ሰዎች ፣ ህመምን የሚረዳው የስሜት ህዋሳቸው ክፍል ስለተጎዳ ስለት ቆረጣቸው ፣ እሳት አቃጠላቸው አይሰማቸውም ። ዓይናቸው አይቶ ሰውነታቸውን ካላሸሸላቸው በስተቀር

እሾክና ሚስማር ላይ ቢቆሙ ፥ እጃቸውን እሳት መቆስቆሻ ቢያደርጉ / የጋለ ብረት ድስት ቢጨብጡ ወይም መጋዝ ቢያገኛቸው አሚቸው አያርቁትም ። ይህም በመሆኑ ጥንቃቄ የማያደርጉት ህሙማን ከደዌአቸው በተጨማሪ ቁስልና ሌላም ጉዳት ያገኛቸዋል ። ስለዚህ ህመምን መስማታችን ለጥቅማችን ነው መባሉ ትክክል ነው ።

ለ/ አንድ ሰው ሆዱን የሚሰነጥቅ ቁርጠት ካላመመው ሆዴ ውስጥ ችግር አለ ብሎ ወደ ኃኪም መሄድ አይፈልግም ። ሆዱን ያሳመመው ችግር ግን ሙያተኛ የሚለየው ገዳይ የሆነ ትርፍ አንጀት ወይንም የአንጀት መታጠፍ ሊሆን ይችላል ። ስለዚህም ህመምን መስማታችን አሁንም ለጥቅማችን ነው ።

ሐ/ የሚፈልጥ ራስ ምታት ባይሰማን ሙያተኛ አናማክርም ። ራሳችንን የሚያሳምመን ምክንያት ሊገድለን የሚችል ማጅራት ገትር ወይንም ጭንቅላታችን ውስጥ የፈሰሰ ደም ሊሆን ይችላል ። ስለነዚህና ሌሎች አያሌ ምክንያቶች ህመምን መስማታችን ለጥቅማችን መሆኑን ተረድተን ሳንበሳጭበት እግዚአብሔርን በህመም ውስጥም ሆነን እናመሰግነዋለን ።

መጽሐፍ ማንም ሲፈተን ፥ በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል ፤ እርሱ ማንንም አይፈትንም። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል (ያዕ 1:13-14) ስለሚለን ፥ መከራና ፈተናም ሲመጣ የራሳችን አጉል ምኞትና ፍላጎት የፈጠረው ፥ ለጥቅማችን እንደሆነም መቀበል ይኖርብናል ። ምክንያቱም በመቸገራችንና መከራ በመቀበላችን የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት ስንል ፊታችንን ወደርሱ መልሰን ስሙን እየጠራን ጸሎት ጀምረን ሊሆን ስለሚችል ።

በመከራ ሳለሁ ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፥ እርሱም ሰማኝ ። (ዮናስ 2:3) አሜን

እግዚአብሔር መልካም ነው፥ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው በእርሱ የሚታመኑትንም ያውቃል። ናሆም 1:7

ምሳሌ :-

1. ጻድቅ ኢዮብ የወንዶችና ሴቶች ልጆቹን መሞትና የንብረቱን መውደም በሰማ ጊዜ ፥ ራቁቴን መጣሁ ራቁቴንም እመለሳለሁ ብሎ በሃዘኑ እግዚአብሔርን አመሰገነ (ባረከ) እንጅ አልተበሳጨም። ኢዮ 1:13-21

2. ጳውሎስና ሲላስ እግራቸውን በግንድ አጣብቀው አስረው ወኅኒ ሲጥሏቸው እግዚአብሔርን ተግተው ያመሰግኑ ነበር (ሥራ 16:24-25)።

የመጽሐፍ ምክር :-

** በተስፋ ደስ ይበላችሁ፤ በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ፤ ሮሜ 12:12

** መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ፤ ደስ የሚለውም ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር። ያዕ 5:13

ስለዚህም በዓሉን ስናከብር ሁላችን በአንድ ልብ ሆነን አውሎ አሳድሮ እዚህ ላደረሰን አምላካችን ምስጋና እያቀረብን በመዘመር እንዲሆን እላለሁ ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

Diacon Ankets Tekola

52/ የነፍስ ሕልም

በውስጣችሁ ሳለሁ ምናልባት ስሜን ለማታውቁት ነፍስ እባላለሁ።

በዘመናት ሁሉ ስሻውና ስመኝው የነበረው ጊዜ በአምላኬ ፊት ቀርቤ

በልቤ የተቀበሩ ጥያቄዎችን አንስቼ እርሱን መጠየቅ ነበር ያሳሰቡትን

የማይረሳ የጠየቁትን የማይነሳ አምላክ ፈቅዶልኝ በፊቱ ቀረብሁ።

ከሙሴ ጀምሮ እስከ ባለራዕዩ ወንጌላዊው ዮሐንስ ያሉት እና የእነርሱም

መንገድ የተከተሉት አበው እየረዱኝ ዓለምን በያዘበት ክንዱ ተደግፌ

ጌታን ፊት ለፊት ማናገር ጀመርሁ።

ነፍስ፡- ጌታ ሆይ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደሆንና ጥቂት ጊዜ ቢኖርህ

አንተን መጠየቅ የምፈልጋቸው ልቡናዬን የሞሉ ብዙ ጥያቄዎች አሉኝ።

ጌታ፡- ልጄ ሆይ ጊዜን የፈጠርኩ የጊዜ ባለቤት መሆኔን ረሳሽ? ወይስ

እኔም እንደ ምድራዊ አባት ከአንቺ ጋር ለመሆን ጊዜ ያቆመኝ ዘመን

ይገድበኝ ዘንድ አሰብሽ? በእኔ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት ሺሁም

እንደ አንድ ቀን መሆኑን አታውቂምን? ከጊዜ ሁሉ በላይ የሆንሁ ጊዜን

የፈጠርሁ ጊዜን የምገድብ ነኝና የምትሺውን ጠይቂኝ ይሰጥሽማል።

1 ጴጥ 3፡8

ነፍስ፡- ጌታ ሆይ የማስተዋል ድክመቴን ታውቀዋለህና ይቅር በለኝ። ስለ

አንተ ከብዙዎች ብዙ ነገር ሲባል ሰምቻለሁ ይሁን እንጂ አሁንም እኔን

ማሳረፍ ጥማቴንም ማርካት የሚቻለውን ቃልህን እናፍቃለሁ ዛሬ አንተ

ስለራስህ ንገረኝ።

ጌታ፡- ልጄ ሆይ ስለ እኔ ምንም ያህል አልሰማሽም ምክንያቱም ሰዎች

ብዙ ጊዜ ይሳሳታሉና ነው አንዱ እንዲህ አንዱም እንዲያ ይላል።
ሌላው ቀርቶ ምንም በቃላቸው ስህተት ባይኖርባትም የነቢያትና
የሐዋርያት አንደበት እንኳ እኔን እንደሚገባው መግለጽ አይችሉም። ሰው
በሚገባው በሰው ቋንቋና ምሳሌ ተናገሩ እንጂ ስለ እኔ ሙሉ በሙሉ
ለመናገር የሚችል የለም። ምድር ሰሌዳ ባህር ቀለም ብትሆንም ስለ
እኔ የጠብታን ያህል ማንም ሊናገር አይችልም። እኔን ለማወቅ ስላለሽ
ጉጉትና ጥያቄሽን ለመመለስ ግን <<ያለና የሚኖር እኔ ነኝ>> ዘጸ 3፡14 ፣
ራዕ 1፡8
ነፍስ፡- እነሆ በፊትህ ሞገስን ካገኘሁ ዘንድ እኔ ባሪያህ ሌላ ጥያቄ
አለኝ ብዙ ጊዜ ሳስበው የሚደንቀኝ ማሰብ እስከማልችል የምደርስበት
ነገር አለ። እርሱም ለምን ሰው መሆን አስፈለገህ?
ጌታ፡- ልጄ ሆይ ሰው መሆንማ ያስፈለገኝ ስለ አንድ ነገር ነው። ስለ
አንቺ ስለ አንቺ ብቻ
ነፍስ ፡- አባት ሆይ እኔ ግን እኮ ሀጢዓተኛ ነኝ እንደተባለው የተፈረደብኝ
ሞት እንኳ ሳይቀር የሚገባኝ ነበር። አንተ ግን በአደባባይ ስለ እኔ በጥፊ
ትመታ መከራን ትቀበል እስከሞት ደርሰህ ሕማሜን ትቀበል ዘንድ ምን
አተጋህ? ከእኔ የሚገኝ በጎ ነገር ሳይኖር ሁሉ ያንተ ሆኖ ሳለ ወንደቤው
ተፈትቶ አንተ ትታሰር ዘንድ እኔ ነጻ ሆኜ አንተ ትያዝ ዘንድ ለምን ጌታ ሆይ
ለምን?
ጌታ፡- ልጄ ሆይ በቅድሚያ ስለራስሽ ደግና እውነት ብለሻል። ቦታሽንም
አውቀሻል እንደ አንቺ ቢሆን ሞት ቢያንስሽ እንጂ አይበዛብሽም በዘመኑ
ሁሉ ሌሎች ፍጥረታት ቦታቸውን ሲያውቁ ትዕዛዜን ሲያከብሩ አዘንቺ ግን

በብዙ ነገር ታምሚ ነበር። ነገር ግን ልጄ ሆይ አንድ ያልተረዳሽው ደግመው ደጋግመው ቢነግሩሽ ያልገባሽ ነገር አለ እርሱም ፍቅር ነው ልጄ ሆይ ማንም ከእኔ ጋር ታግሎ ማሸነፍ አይችልም ሁሉን በመዳፌ ጨብጬ ይዣለሁና። አህዛብ ሁሉ በገንቦ ውስጥ እንዳሉ ጠብታ ናቸው ይሁን እንጂ አንድ ሃይል ጠራኝ ከዙፋኔም ስቦ ለሞት አደረሰኝ እርሱም ለአንቺ ያለኝ ፍቅር ነው ልጄ ሆይ አንድ ነገር እወቂልኝ በጣም ነው የምወድሽ በእኔ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ ነሽ ራስን አሳልፎ ለሚወዱት ከመስጠት በላይ ምንም የሚበልጥ ፍቅር የለም እንጂ ስለ አንቺ የማልሆነው አልነበረም። እናት አባትሽ ላንቺ በጣም የሚቀርቡ የሚመስሉሽ ሁሉ እንደሚወዱሽ ታስቢያለሽ? እነርሱ ቢወዱሽ ጉድለትሽን ድክመትሽን ሀጢዓትሽን እስኪያውቁ ድረስ ነው። ያውም እኔ በሰጠዋቸው ጸጋ እኔ ግን እስከ ኃጢዓትሽ ነው የተቀበልሁሽም ወደድሁሽም አባቴም ስለአንቺ መዳን እኔን አሳልፎ እስከመስጠት ደርሶ ስለ አንድያ ልጁ አልራራም። ኢሳ 1፡3 ፣ ዮሐ 15፡1 ዮሐ 4 ሮሜ 5፡6 ፣

ሮሜ 8፡32

ነፍስ፡- ባሪያህ እናር ዘንድ ከፈቀድህልኝ አሁንስ በእኔ ላይ ዓላማህ ምንድን ነው?

ጌታ፡- ልጄ ሆይ ባንቺ ላይ ያለኝ ዓላማ ለዘላለሙ ፍቅር ነው። መኃል 2፡ 4

ነፍስ፡- ለምንድን ነው ታዲያ እንዲህ እየወደድከኝ ሳለ መከራና ፈተና በዝቶ የሚያስጨንቀኝ?

ጌታ፦ ልጄ ሆይ መከራና ፈተና ስለብዙ ነገር ወዳንቺ ይመጣል። እኔን እንዳትረሽ ከበፊቱ ይልቅ ጸጋን አበዛልሽ በተለይ ደግሞ ብዙ ጊዜ ቀናውን መንገድ ስለምትሸሽ ይመጣል። በቃሌ ብነግርሽም በሰው አድሬ ብመክርሽም አትሰሚኝም ስለዚህ ልጄ ስለሆንሽ እንድትጠፊብኝ ስለማልሻ በጥቂቱ እንደቸርኑቴ አቀጣሻለሁ። አባት ልጁን እንዲቀጣ ማለት ነው። ስጋዊ አባት ለጊዜያዊ ጥቅም ይቀጣል እኔ ግን ከክብሬ እንድትካፈይ በመጠን እገስጽሻለሁ። ‹‹ምነው አባቴ ጨምሮ በቀጣኝ የት በደረስሁ›› የሚሉ ያንቺ ወገኖችን አልሰማሽምን? እኔማ ብትመለሽ ምን ያህል ክብር እሰጥሽ ዘንድ አዘጋጅቻለሁ መሰለሽ?። ስለዚህ ልጄ ስለሆንሽ ለመቀጣት ታገሽ አባቱ የማይቀጣው ግን ልጅ አይደለም። ዕብ 12፡5

ነፍስ፦ ጌታዬ እሺ እርሱስ ይሁን ግን መልካም እያደረግሁ በጎ እየሰራሁም ሳይቀር ብር ሲገባኝ ብዙ ጊዜ መከራ ደርሶብኛል ይህስ ለምን ይሆናል?

ጌታ፦ ልጄ ሆይ በመጀመሪያ ይህን አወቂ አንቺ ስለ ክብርሽ እደሜ ልክሽን የሚደርስብሽ ፈተናና መከራ እኔ አንዲት ሰዓት ስለ አንቺ የተቀበልኩትን ስቃይ እንኳ አያህልም። ልጄ ሆይ በሚመጣው ዓለም ካዘጋጀሁልሽ ክብርና ደስታ ጋር ሲተያይ የዚህ ዓለም መከራሽ ምንም ማት አይደለም። ደግሞ ኃጢዓት አድርገሽ ስትጎሰሚ መከራ ቢደርስብሽና ብትታገሽ ምን ክብር አለው? በጎ አድርገሽ መከራን ብትታገሽ ግን ከእኔ ዘንድ ክብር አለሽ። እሳት ባይኖር ወርቅና መዳቡ እንዴት ይለያሉ? እንዲሁ ለእኔ ያለሽ ታማኝነትና ፍቅር በመከራ ውስጥ

ታምነሽ ካልገለጽሽው እንዴት ትገልጪዋለሽ? ወርቅን እሳት
አያሳስበውም ምክንያቱም በእሳት ውስጥ ሲያልፍ ነው ወርቅነቱ
የሚታወቅለትና የሚመሰከርለት። እንዲሁ መከራ በጎ የሚያደርጉትን
ሊያሳስባቸው አይገባም በመከራ በመታገሳቸው ጽድቃቸው ትወጣለች
በጎነታቸውም በሁሉ ይታወቃል ይልቅስ መከራን ይሹታል ጸጋዬ
ይበዛላቸው ዘንድ። በእነርሱም ድካም የእኔ ሃይል ይገለጥ ዘንድ ስለዚህ
በሁሉ ታጋሽ ሁኚ እንጂ ቶሎ አትሰልቺ አትታክቺም። የውጪው ሰውነትሽ
ቢጠፋም ውስጥሽ ዕለት ዕለት ይታደሳልና ምን ጊዜም ግን ክብር
ይገባኛል ብለሽ አታስቢ።
ፍቅሬንም ደግሞ በሚያልፍ መከራና ፈተና አትመዝኚው። እኔ ለንቺ
ያለኝን ፍቅር የሚለውጠው ምንም ነገር የለምና። 1 ጴጥ 4፡12 ፣ ሮሜ
8፡18 ፣ ዕብ 12፡10
ነፍስ፡- ይህ መከራና ፈተና ሀዘኑስ እስከ መቼ ነው?
ጌታ፡- ልጄ ሆይ በዓለም እስካለሽ መከራ አለብሽ ግን አትፍሪ እኔ
ዓለምን አሸንፈዋለሁና ዓለምን የሚያሸንፈው በእኔ ላይ ያለ እምነትሽ
ነው። በእኔ በአባቴ በመንፈሴም እመኚ ከእጄ ማንም አይነጥቅሽም ወደ
እኔ የመጣውን በፍጹም ወደ ውጪ አልጥልምና። ዮሐ 16፡33 ፣ ዮሐ
5፡4 ፣ ዮሐ 10፡29
ነፍስ፡- እንዲህ ከሆነ ጌታ ሆይ ለእንደ እኔ አይነቱ ኃጢዓተኛስ ምን
ተስፋ አለ?
ጌታ፡- ስለ በደልሽ ታልፊ በመሰጠሪ ደሜን በማፍሰሴ ያቆምኩልሽ
ንስሐ አለ። ንስሐ ፍጹም ወደ እኔ መመለስ ነው ትወጅው የነበረውን

ኃጢዓት በእ ፍቅር መለወጥ ነው ሰው ለሁለት ጌቶች ሊገዛ አይቻለውም። አንዱን ይተዋል ሌላውንም ይከተላል አንቺም እንዲሁ ለእኔና ለዓለም መገዛት አትችይም ወይ የኔ አልያም የዓለም ነሽ። ብዙ ጊዜ የምትወድቂው ለእኔ ያለሽ ፍቅር ሲቀንስ ሰውን ከእኔ አብልጠሽ ስትወጂ ነው። ግን ብትወድቂም በንስሐ ከእኔ ጋር ትታረቂያለሽ እኔም ስለስሜ ስል በደልሽን እፍቃለሁ። ልጄ ሆይ መቼም በዓለም ውስጥ ብዙ አሳቾች አሉ ያንቺም ስጋ ምድራዊውን ወዳጅ ስለሆነ ወደ ኃጢዓት ያመዝናል። በሌላ በኩል ጠላትሽ ዲያብሎስም አይተኛልሽም ስለዚህ ምናልባት ደግመሽ ኃጢዓት ብትሰሪ እንኳ የንስሐን መንገድ ሰርቼልሻለሁ። እርሷም ዘማዊውን ድንግል ሌባውን መጽዋች አሳዳጁን ተሳዳጅ ታደርጋለች ስለዚህ ብትወድቂ እንኳ ተስፋ ባለመቁረጥ በንስሐ ተመለሽ። እኔም ያለፈውን ኃጢዓትሽን ከቶ አላስብም ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ምሶ ግን ይነሳል እንጂ ተስፋ ቆርጦ አይቀርም። ወድቆ መቅረት ዲያብሎሳዊ ነው ወድቆ መነሳት ግን አዳማዊ ነው። ንስሐን ያዘጋጀሁት ኃጢዓትን ለማይሰሩ ለማይበድሉም አይደለም መድኃኒት ለጤነኞች አያስፈልጋቸውም ለበሽተኞች እንጂ እንዲሁ ንስሐ በኃጢዓት ለወደቁት ነው እኔም እንኳ ወደ ዓለም የመጣሁት የጠፋውን ላድንና ልፈልግ ነው። ንስሐ መግባት በማያስፈልጋቸው በመላእክቶቼ ፊት በአንድ ኃጥዕ መመለስ ምክንያት ታላቅ ደስታ ይደረጋል። ያለፈው ዘመንሽ ምንም ቢሆን አላስበውም የመጨረሻሽን እንጂ የመጀመሪያውን ስራሽን አላይምና። ብቻ በመንፈስ ጀምረሽ በስጋ እንዳትፈጽሚ ተግተሽ ጸልይ። ሌላ ሽክም አልጭንብሽም እስክመጣ ግን ያለሽን አጽንተሽ

ያዥ። ማቴ 6፡24 ፣ ሕዝ 33 ፣ ማቴ 9፡12 ፣ ራዕ 2

ነፍስ፡- ግን ብዙ ጊዜ እሰነካከላለሁ ስራዬን ብናዘዝም መልሼ ያንኑ ኃጢዓት እሰራለሁ ምን ላድርግ?

ጌታ፡- መልሰሽ ንስሐ ግቢ ደግመሽም ኃጢዓትን አትስሪ። ዮሐ 8፡11

ነፍስ፡- እስከመቼ እንደዚህ እኖራለሁ?

ጌታ፡- ከዚህ ከመከራና ከፈተናው ዓለም እስክትለይ ድረስ።

ነፍስ፡- ጌታ ሆይ (በውስጣችሁ ያለሁ የእኔ የነፍስ ጥያቄስ የሚያልቀው መች ይሆን)

‹‹በጠራሁህ ቀን ቀርበህ አትፍራ አልህ ጌታ ሆይ ስለ ነፍሴ ተሟግተህ ሕይወቴን ተቤዠህ›› ሰቆ. ኤር 3፡57

ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው ለእርሱ ቸር ከሚሆን አባቱ ሕይወትን ከሚሰጥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለዘላለሙ ክብር ይሁን። አሜን!!!

Miko ZE Ethiopia

POSTED BY SAMUEL AYALNEH አዲሱ ዓመት - ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳስተማረው (ክፍል ፩)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

የምወዳችኁ

53/ ልጆቼ! አዲሱ ዓመት የደስታ የሰላምና የጤና እንዲኾንላችኁ ትሻላችሁን? እንኪያስ ገና ከዥመሩ በስካር፣ በዘፈን፣ በገቢረ ኀጢአት

ለማሳለፍ አታቅዱ። የአዲሱ ዓመት የመዝመሪያውን ዕለት ብቻ ሳይኾን እያንዳንዱን ቀን በገቢረ ጎጢአት አትዝምሩት። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ፣ ምግባር ትሩፋት በመሥራት አሐዱ በሉ እንጂ። ዕለታት ክፋዎች ወይም ጥሩዎች የሚኾኑት በተፈጥሮአቸው እንደዚያ ኾነው አይደለም። ዕለቱን ክፉ ወይም ደግ እንዲኾን የምናደርገው እኛው ነን። የአምናው ማግሰኞ ከዘንድሮ ማግሰኞ የተለየ አይደለም። የተለየ የሚያደርገው የእኛ ብርታት ወይም ስንፍና ብቻ ነው።

የጽድቅን ሥራ የምንሠራበት ከኾነ አዲሱ ቀን ብቻ ሳይኾን አዲሱ ዓመት ለእኛ መልካም ነው። ጎጢአት የምንሠራበት ከኾነ ግን ቀኑ ብቻ ሳይኾን አዲሱ ዓመትም ክፋና መከራ የመላበት ይኾንብናል። አዲሱን ዓመት በበጐ ሥራ የምንዝምረው ከኾነ በዓመቱ በምናደርገው ማንኛውም ክንውን ላይ በጐ ተጽዕኖ ያሳድርብናል። በትግሃ ሌሊት፣ በቀዊም፣ በጾም በጸሎት እንድንበረታ ስንቅ ይኾነናል። በስካር፣ በዘፈን፣ በጎዘን የምንዝምረው ከኾነ ግን ዓመቱ ሙሉ እንዲኽ የተጐሳቈለ ዓመትን እናሳልፋለን። ሕይወታችንን በከንቱ እንገፋለን። ዲያብሎስም ይኽን ጥንቅቅ አድረጐ ስለሚያውቅ ዓመቱን በገቢረ ጎጢአት እንድንዝምረው እየቀሰቀሰ ነው። ፈቃዳችንን አጥፍቶ፣ ዓይነ ልቡናችንን አሳውሮ በዘፈን፣ በስካር፣ በዋይታ እንድንዝምረው በተለያየ መንገድ እየለፈፈ ነው።

ሰነፍ ሰው “ቀኑ ክፋ ወይም መልካም የሚኾነው በእኔ ምክንያት አይደለም” ብሎ ያምናል። እንዲኽ በማመኑም ክፋ ነው ብሎ በሚያስበው ቀን ገቢረ ጽድቅ መሥራት እንደሚቻል አያስብም። ቢያደርግም ትርጕም እንደሌለው አድርጐ ይቈጥራል። የጽድቅ ሥራ ለመሥራት በተመቻቸለት

ቀንም ልል ዘሊል ከመኾኑ የተነሣ ምግባር ትሩፋት ለመሥራት አይሸቀዳደምም። ስንፍናው ምን ዓይነት ጉዳት እንደሚያመጣበት አይረዳም። ድኅነቱን ሳይፈጽም ዕድሜውን ኹሉ በከንቱ ይገፋል። እንዲኽ ያለ የሥጋም የነፍስም ጕዳት እንደሚያገኘው ዲያብሎስ ዓይነ ልቡናውን ስለሚያሳውርበት ከአጋንንት ወጥመድ ለመሸሽ ዓቅምን ያጣል።

ዲያብሎስም ዕለት ዕለት ይኽን እንዳንገነዘብ በተለያየ ማጥመጃ መንገዶች እኛን ለመጣል ይሯሯጣል። አንዱ መንገድም ስለ ክርስትና ሕይወታችን ግድ እንዳይኖረን ማድረግ ነው። በዚኽም ክርስቲያናዊ ተፈጥሮአችንን ያሳጣናል። የእግዚአብሔርን ሥራ በገቢር እንድንሰድብ ያደርገናል። ነፍሳችንን በቆሸሸ ስፍራ ተወሽቃ እንድትቀር ያደርጋታል።

የምወዳችኁ ልጆቼ! እኛ ግን ይኽን ልናውቅ ልንረዳ ይገባናል። በዓለም ላይ ከኀጢአት በቀር ክፉ ነገር እንደሌለ ልናውቅ ልንረዳ ይገባናል። ከምግባር ከትሩፋት በቀርም መልካም ነገር እንደሌለ ልናውቅ ልንረዳ ይገባናል። በዚኽም ዘወትር እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተን ልንኖር እንዲገባን ማወቅ መረዳት ይገባናል። መጠጥ ደስታን አያመጣም፤ ደስታን የሚያመጣው ጸሎት ነው። ደስታን የምናገኘው ቃለ እግዚአብሔርን ከመስማት እንጂ ከስካር አይደለም። ስካር የነፍስ መታወክን ያመጣል፤ ቃሉን መስማት ግን ተመስጦን ያመጣል። ስካር ሁካታን ያመጣል፤ ቃሉን መስማት ግን ሁካታን ያርቃል። ስካር ዓይነ ልቡና እንዲጨልም ያደርጋል፤ ቃለ እግዚአብሔር ግን የጨለመው ዓይነ ልቡናችን ብሩህ እንዲኾን ያደርጋል። ስካር የኀጢአት ኀዘ ይዞ ይመጣል፤ ቃለ እግዚአብሔር ግን አዲስ የሚመጡትን ብቻ ሳይኾን የነበሩትንም ያስወግዳል።

ልጆቼ! የዚኽን ዓለም ደስታ ንቆ ሰማያዊ ደስታን እንደመሻት ያለ ጥበብ ምንም የለም ብዬ እነግራችኋለኹ። ይኽን ገንዘብ የምናደርግ ከኾነ፣ ለሰማያዊ ሕይታችን ቅድሚያን የምንሰጥ ከኾነ የዚኽ ዓለም ዝባዝንኬ ቢቀርም አይከፋንም። አንድ ሰው ባለጸጋ ስለኾነ ቅናት አይይዘንም። ምንም ምድራዊ ሀብት ባይኖረንም ድኾች እንደኾንን አናስብም። ባለ ጸጋውን ክርስቶስ የያዘ ሰውስ እንዴት ድኻ ይባላል? በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይኾን በየዕለቱ በዓል ማድረግ ማለትም ይኸው ነው።

እግዚአብሔር የሚወዳችኁ አንድም እግዚአብሔርን የምትወዱት ሆይ! አንድ ክርስቲያን በዓልን ሲያከብር ሳምንትን ወይም ወርን ወይም ዓመትን ጠብቆ መኾን የለበትም። ከክርስቲያናዊ ተፈጥሮው ጋር እንደሚስማማ አድርጎ ዕለት ዕለት በዓል ሊያደርግ ይገቧል እንጂ። ከክርስቲያናዊ ተፈጥሮው ጋር የሚስማማ በዓል ማለትስ ምን ማለት ነው? ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ምን እንደሚለን አብረን እናድምጠው፦ “በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን እናድርግ እንጂ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ እርሾም አይደለም” /1 ኛ ቆሮ.5፡8/። ንጽሐ ልቡናን ገንዘብ ያደረገ ሰው ዕለት ዕለት በዓልን ያከብራል። ተስፋ መንግሥት ሰማያት የተጠበቀለት ነው። ከሰማያዊው ማዕድና መጠጥ ተካፍሎ ሐሴት ያደርጋል። በዚኽ ምድር ላይ የሚደረጉ ጊዜያዊ ክንውኖች ስለቀረበት የኾነ ነገር እንደቀረበት አያስብም፤ ርሱ ያገኘው ከዚኽ በእጅጉ የሚልቅ ነውና። ነፍሱን ከሚያቆሽሹ ገቢረ ኀጢአቶች ራሱን ይጠብቃል።

በገቢረ ኀጢአት ተሰማርተን ሳለ ሺሕ ጊዜ በዓላትን ብናከብር ግን እንዳከበርን ልንቈጥረው አይገባንም። ያከበርነው የበዓል ቀን (በዓል ማለት

ደስታ ማለት ነው) ሳይኾን የኀዘን ቀን ነውና። ነፍሴ በኀጢአት ቀንበር ተይዛ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሳለች የደስታን ቀን ባከብር ለእኔ ምን ጥቅም ያመጣልኛል?

እግዚአብሔር የሚወዳችኁ እናንተም የምትወዱት ልጆቼ! አዲሱ ዓመት የእውነት አዲስ ዓመት እንዲኾንላችኁ ካሻችኁ ነፍሳችኁን ከኀጢአት ቀንበር አላቋት እንጂ ድጋሜ በኀጢአት ሸክም አትጫኗት። አሮጌው ዓመት እንዳለቀ ስታዩ እግዚአብሔርን አመስግኑት። ወደሌላ ዘመን አሸጋግሯቸዋልና እግዚአብሔርን አመስግኑት። ልቡናችኁንም ውቀሱት። በዕሜአችኁ ስንት ጊዜ እያለፈ እንደኾነ እያሰባችኁም ራሳችኁን እንዲኽ ብላችኁ ጠይቁት፦ “ቀናት እየሮጡ ነው። ዓመታቱም እየነጐዱ ነው። የዕድሜዬ መንገድም እየተጋመሰ ነው። ታድያ ምን በጐ ምግባር ያዝኩ? ከዚኽ ምድር የማልፍበት ቀን እየቀረበ ነው። ታድያ ምን የጽድቅ ሥራ ሠራኹ? በዚኽ ዕድሜዬ መሥራት የነበረብኝ ምግባር ትሩፋት ዕድሜዬ ሲገፋ ማድረግ አልችልም። ታድያ ዕድሜዬ ሲገፋ ማድረግ የማልችላቸውም የጽድቅ ሥራዎች (ፆም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ አገልግሎት፣... ዕድሜ ሲገፋ ይከብዳሉና) እንዳቅሜ እያደረግኩ ነውን?”

ተወዳጆች ሆይ! አዲስ ዓመት ሲመጣ እነዚኽን ነገሮች በጥንቃቄ ልናስብባቸው ይገባናል። ይኽን እያደረግንም ስለቀጣዩ ዓመት እናስብ። ይኽን የምናደርግ ከኾነ “ቀኖቻቸውም በከንቱ አለቁ፤ ዓመቶቻቸውም በችኰላ” አይባልብንም /መዝ.78፡3/። ዕለት ዕለት በዓልን እናድርግ ብዬ የገለጥኩላችኹም ይኸው ነው። የእኛ በዓል ዘወትር መኾን ይገባዋል። የክርስቲያኖች በዓል በዓመታትና በቀናት ብቻ መወሰን የለበትም። ቤተ

ክርስቲያንም በሳምንት፣ በወር፣ በዓመት የሚከበሩ በዓላት እንዲኖሩ ማድረጓ ዘወትር ከዚኹ ልንርቅ እንደማይገባ ማሳሰቧ እንጂ ሌላ አይደለምና። ይኽን በዓል በየዕለቱ ማድረግም ለኹሉም ይቻላል፤ ለድኻውም ለባለጸጋውም ይቻላል። በዓልን ለማድረግ (የጽድቅ ሥራን ሠርቶ ሐሴት ለማድረግ) የሚያስፈልገው ቅን ልቡና እንጂ ገንዘብ አይደለምና። ወዳጄ ሆይ! ገንዘብ የለኽምን? ፈሪሐ እግዚአብሔርን ገንዘብ አድርግ። ፈሪሐ እግዚአብሔርን ገንዘብ የምታደርግ ከኾነ ገንዘብ ካላቸው በላይ ባለጠጋ ነኽ። “እንዴት?” ትለኝ ይኾናል። እኔም እንዲኽ ብዬ እመልስልሃለኹ፦ የእነዚያ (የባለጠጐቹ) ገንዘብ ያልቃል። ያንተ ግን ብል አይበላውም። ጊዜ አይለውጠውም። አያልቅም። ወደ ሰማያት፣ ወደ ሰማየ ሰማያት፣ ወደ ምድር፣ ወደ አየራት፣ ወደ እንስሳቱ ዓይነት፣ ብዙ የብዙ ብዙ ወደሚኾኑት ዕፅዋት፣ ወደ ደቂቀ አዳም በጠቅላላው፣ ወደ መላዕክት፣ ወደ መላዕክት አለቆች፣ ወደ ጎይላት ተመልከት። እነዚኽ ኹሉ የአምላክኽ ፍጥረቶች ናቸው። የእነዚኽን አምላክና መጋቢ ባርያ መኾን ድኻ መኾን አይደለምና ድኻ አይደለኽም ብዬ እነግርኻለኹ።

ተወዳጆች ሆይ! ቀናትን ቈጥሮ በዓል ማድረግ የክርስቲያን ግብር አይደለም፤ የአሕዛብ ግብር እንጂ። እንዴት? የክርስቲያኖች ተፈጥሮ በቀንና በወር የተገደበ አይደለምና። አገራችን ሰማይ ነው። ግብራችን ሰማያዊ ነው። ኅብረታችንም ከሰማያውያን መላዕክት ጋር ነው። በዚያ መዓልት ለሌሊት ስፍራውን አይለቅም። ሌሊትም በተራው ለመዓልት አይለቅም። እዚያ ኹሌ መዓልት ነው። እዚያ ኹል ጊዜ ብርሃን ነው። ስለዚኽ “ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችኹ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን

እሹ” እንደተባልን ኹል ጊዜ ማሰብ ያለብን ይኽንን ነው /ቈላስ.3፡1/። ክርስቲያናዊ ተፈጥሮአችን ከዚኽ ምድራዊ አቈጣጠር በላይ ነው። በንጽሕና በቅድስና እየኖርን ዘወትር በዓልን የምናከብር ከኾነም የዚኹ ዓለም ሌሊት ለእኛ ሌሊት አይደለም፤ መዓልት ነው እንጂ። ዘመናችንን በሙሉ በገቢረ ኀጢአት፣ በስካር፣ በዘፈን የምናሳልፈው ከኾነ ግን መዓልቱ ለእኛ መዓልት አይደለም፤ ሌሊት ነው እንጂ። ፀሐይዋ ብትወጣም ልቡናችን ገና በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ይኖራልና ቀን እንደወጣ አይቈጠርም።

Miko ZE Ethiopia

54/ ማንነቱ ያልገባው ትውልድ

ሰላም ጤና ይስጥልኝ እንደምን አላችሁ?

እንዴት ከረማችሁ እንዴትስ ዋላችሁ?

እንዴት አደራችሁ እንደምን አላችሁ?

ለነገሩ... ለእናንተ የማቀርበው ሰላምታ፣

ሆኖባችሁ ጨዋታ “አለን” ነው የምትሉኝ በእርጋታ።

ለመሆኑ ማን አኖረህ?

እስካሁንስ ማን አቆየህ?

በኃይልህ ነው እንዴ የምትኖረው?

ወይስ በምግብ ብቻ ነው ያለኸው?

በእርግጥ... አንተ ከበላህ ከጠጣህ ከተነፈስህ፣

በቃ! “አለሁ!” ትላለህ እንደፈለግህ።

ኧረ ስማ ወገኔ! ይህ ነው ወይ መኖር ይህ ነው ወይ ማለት?

“አለሁ!” የምትል በድፍረት።

በዝናብ አብቅሎ በነፋስ አሳድጎ በፀሐይ አብስሎ ይመግብሃል፣

ሲበርድህም ያሞቅሃል፣

ሙቀት እንዳይጎዳህ ቀዝቃዛ አየራትን ለግሶሃል።

ስትበድለውም ይምርሃል፣

ይባስ ብሎ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ይወድሃል፣

ለመሆኑ ላንተ ምንድን ነው ያጎደለው?

“አለሁ!” ብቻ የምትለው።

አንተ ተራ! አንተ ከንቱ!

አመስግን እግዚአብሔርን ስለቸርነቱ።

እንደምን ዋልክ፣እንዴት አደርክ፣እንዴት ከረምክ ሲሉህ “አለሁ!”

አትበል፣

“እግዚአብሔር ይመስገን” በል።

ቆይ እስኪ....! በቸርነቱ ያኖረህን ብታመሰግነው፣

ኃፍረቱ ምኑ ጋር ነው?

ሁሉን ሲሰጠን ሲያደርግልን፣

እኛ ሁልጊዜ “አለን!” ብቻ ለምን እንላለን?

“እግዚአብሔር ይመስገን” እንዳንል ማነው አዚም የጣለብን?

ለነገሩ...! ዝሙት ርኩሰት መዳራት፣

ጣዖት ማምለክ ምዋርተኝነት፣

ጥል ክርክር ቅንዓት፣

ቁጣ አድመኛነት፣

መለያየት መግደል መናፍቅነት፣

ምቀኝነት ስካር ዘፋኝነት፣

ይህን የመሰለ ነው ግብርህ፣

የሁልጊዜ ተግባርህ፣

ታዲያ! የትኛው አንደበትህ፣

“እግዚአብሔር ይመስገን” ይበልልህ።

አንተ ከንቱ! ዕድሜህ እንደ አበባ ታይቶ የሚጠፋ፣

ምግባርህ እጅጉን መራራ የከፋ፣

መሆኑን ብታውቀው፣

ፈጣሪህን ባወቅኸው።

አንተ እኮ! ማን ፈጠረህ ሲሉህ እናትና አባቴ፣

ማን አኖረህ ሲሉህ ጽድቅ ደግነቴ።

የሚለው ነው መልስህ፣

ማንም ሲጠይቅህ።

ግሩም ነው...! በጣም የሚገርም፣

የሚያስደንቅ የሚያስደምም።

ታችህ ጣዖት፣

ላይህ ታቦት።

አፍህ ቅቤ፣

ልብህ ጨቤ።

በብርሃን ቤተክርስቲያን፣

በምሽት ከጠንቅ ዋይ ቤት።

በጨለማ ቤት ሰርሳሪ፣

ሲነጋጋ ሥራ ሠሪ።

ብቻ... ያንተ ነገር! የተደባለቀ የተጨማለቀ፣

የተመሳቀለ የተቀላቀለ።

ኧረ ሰው ጠፋ! ደግ ሰው አለቀ፣

ለጠንቅ ዋይ ተገዛ ለጣዖት ሰገደ።

የአጋንንትን ጽዋዕ ከእግዚአብሔር ጋር ቀላቀለ።

በውኑ! እግዚአብሔር ማዳን አልችል አለን?

ከጠንቅ ዋይ ከአጉሪ ከመተተኛ ዘንድ መሄዳችን፣

ገና! የሕመም ምልክቱ ሲታየን የሕመም ስሜቱ ሲሰማን።

ኧረ! ሌላም አለ! ምቀኝነት ጎለቶብን፣

እገሌን ግደልልኝ እገሊትን ድሃ አድርግልኝ፣

እገሌን አሳብደው እገሌን ጨርቅ አስጥለው

እያልን ለጠንቅ ዋይ የምንሰግደው ለምንድን ነው?

የእኛስ ጥቅም ምኑ ጋር ነው?

አንተ ጠንቅ ዋይ መተተኛ በዚህ ደባ፣

ወዮልህ ወዴት ይሆን የምትገባ?

አምላክ በግርማው ሲመጣ፣

ከየት ይሆን ያንተስ ዕጣ?

አልሰማህም እንዴ? የጠንቅ ዋዩን የመጥቁልን ታሪክ፣

ድንግል ማርያምን በስረዩ አጠፋለሁ ብሎ ሲደፍር፣

የደረሰበትን የመከራ ክምር።

የአጋንንት ሥልጣን ስለማይበልጥ ከእግዚአብሔር፣

መጥቁል ተዋጠ በዚች ምድር።

ይህን ባወቅህ ጠንቅ ዋይ ባልሆንህ፣

ማንነትህን በተረዳህ።

ነገሩማ! ትዕቢትህስ መቼ ያልቃል?

አእምሮህስ መቼ ያስተውላል?

ልብህስ መቼ ያስባል?

ታዲያ! ካሰብክ ፈርዖንን አስበው ናቡከደነጾርን ልብ በለው።

ትዕቢታቸው ወዴት ገባ እነርሱስ የት ደረሱ?

እሽ! እንቀጥል ይህ ነው መልሱ፣

ፈርዖን በትዕቢት ልቡ ቢደነድን፣

አልለቃቸውም ቢል እስራኤላውያንን፣

አልተሻገራትም ባሕረ ኤርትራን።

ሰጥሞ ነው የቀረው ከነሠራዊቱ ፈርዖን በትዕቢቱ።

ሌላስ! ናቡከደነጾር ቢነሣ በትዕቢት፣

ቢሰግድ ቢንበረከክ ለሰው ሠራሽ ጣዖት፣

ሣር ጋጠ እኮ እንደ ከብት ለሰባት ዓመታት።

ታዲያ! የእኛ ትዕቢት በባሕር ሰጥሞ ለመቅረት፣

ወይስ ሣር ለመጋጥ እንደ ከብት?

እባክህ ወገኔ! አድምጠኝ እባክህ፣

ጥንቆላው ይቅርብህ።

ሥር መማሱ ቅጠል መበጠሱ አያጓጓህ፣

ትዕቢት ድፍረት አይሰማህ፣

ትሕትና ነው የሚያዋጣህ።

ኧረ ስማኝ ወገኔ! ላስተምርህ፣

ለነገሩ...! ከኔ በላይ ማን አለ?

እንደእኔ አዋቂ እንደእኔ ጠቢብ የት ይገኛል?

ነው የምትል። ለመሆኑ...!

ፊደል ቆጥረሃል? ዳዊትን ደግመሃል?

መጻሕፍትን አንብበሃል?

ውሸት! ኧረ ባዶ ደንቆሮ ነን፣

ባዶ ሆነን ሁሉ ያለን የሚመስለን።

ታዲያ...! ዛሬ ኢትዮጵያዊ መለያ ፊደላችንን ሊቀንሱ፣

አላዋቂዎች ሲነሱ፣

ፊደላችን በዝቷል! አንዱ ይብቃን ሲሉህ፣

አዎ ትላለህ አብረህ ልዩነታቸው ስላልገባህ፣

ትርጉማቸውን ስላላወቅህ።

ታዲያ...! የቱ ነው ትምህርቱ?

አውቄያለሁ ነቅቻለሁ ማለቱ።

ኧረ ተነሣ ወገኔ! ግዕዝ ሞተልህ!

ሀገራዊ ትልቅ ሀብትህ።

በባዕድ ቋንቋ ከንፈርህን ስታጣምም፣

የአንተ የሆነውን ንጹሕ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ቀበርከው፣

ዳግም እንዳይነሣ ልታደርገው።

አቤት ኃፍረት! አቤት ውርደት!

ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖርን፣

ለግዕዝ ቋንቋ ባዕድ መሆን።

ያ! ያማረው የተዋበው የቅኔ መፍለቂያ፣

የመጻሕፍት መጻፊያ የአዳም ቋንቋ መግባቢያ፣

“ሞተ” ሲባል በይፋ ዛሬም “አለሁ!” እያልክ ልትደነፋ?

በባዶው ሳናውቅ አወቅን እያልን፣

አስጠፋነው ግዕዝ ሐብታችንን።

አንተ በውኑ ኢትዮጵያዊ ነህ፣

ወይስ...ደግሞ የሌላ ነህ?

ለግዕዝ ቋንቋ ባዕድ የሆንህ።

ለፊደላችን የሌለህ ፍቅር ሲቀነሱ ያላለህ ቅር።

የራስህን ወዲያ ጥለህ በሌሎቹ ተገንዘህ፣

አእምሮህን መርዘህ በከንቱነት ትኖራለህ፣

የእናት የአባትህን አደራ ዘንግተህ።

በዓለማዊ ፍልስፍና በሥጋዊ ብልጽግና፣

ገነት መግባት ከተቻለ እስክንድርን ጠይቀው፣

ማን እንዳባረረው?

በእውነት አሁን...! የእኛ ሥጋዊ ፍልስፍና፣

ዕድሜ ያስጨምራል ወይስ ጤና?

ከንቱ! ብቻ ሁሉም ከንቱ!

ኧረ ተማር ወገኔ! አላወቅህም!

አዋቂ ብትሆንማ ኢትዮጵያን ባወቅህ፣

የምትኖርባትን አገር ታሪኳን በመረመርህ፣

እንደእንስሳት ስትመስል አለባበስህ ሲከፋ፣

ዕርቃነ ሥጋህ ሲታይ በይፋ፣

የለበስክ የሚመስልህ “አውቃለሁ!” አትበለኝ አላዋቂ ነህ፣

አንተ ራስህ አላዋቂነትህን ታውቃለህ፣

ልትቀልድ ነው “አውቃለሁ!” ማለትህ።

አንቺ የሔዋን ልጅ! ስሚኝ እህቴ፣

አድምጭኝ ዛሬን ብቻ በሞቴ፣

ልብስሽ አጠረች ተቀደደች።

አለባበስሽ ተቀየረ ወደ ባዕድ አገር ተሻገረ።

ፀሐይ አይምታው አይቃጠል ሰውነትሽ፣

አልብሽው ሞልቷል ጥሩ አልባሽ፣

አንቺ መልበሻ ካጣሽ።

ያንቺ ሱሪ ያንቺ ቁምጣ፣

ኧረ እህቴ ከየት መጣ?

ያን ረዥም ቀሚስ ወዴት ጣልሽው?

የት ቀበርሽው የት ደበቅሽው?

አንቺ ጉደኛ በይ ስሚኛ!

መልሽልኝ ዝም አትበይኝ!

እሽ በቃ...!

ሱሪ ወይስ ቁምጣ ወይስ ቀሚስ ያሳየችሽ?

ያቺ ምስኪን ደግ እናትሽ።

ታዲያ...! ከየት አመጣሽው ይህን ቆራጣ ቁምጣሽን፣

ያጋለጠ ዕርቃነ ሥጋሽን።

ኧረ አስተውይ ተመለሽ!

የእናትሽን ልብስ ልበሽ፣

ያ ስለሆነ ውብ ባሕልሽ ስትለብሽውም የሚያምርብሽ።

ነገሩ እኮ በጣም ያሳዝናል! ያስለቅሳል ያበሳጫል፣

ማንነታችን ጠፍቶብናል፣

አኩሱምን ቀርጾ ያቆመውን፣

ፍልፍል ዋሻ ላሊበላ ያነጸውን፣

አጠፋነው ከአእምሯችን፣

ያንን ጀግና ያን ገናና ያኮራንን፣

ክብር ሞገስ ያደለንን።

በጸሎቱ በእምነቱ በብርታቱ በትዕግስቱ፣

ዳሯን እሳት መሐሏን ገነት፣

አድርጎ ኢትዮጵያን የጠበቃት ያ ጀግና ሕዝብ!

ልጅ መስለነው ለእኛ ቢሰጥ፣

ከፋፈልናት በቋንቋ በሰፈር በጎጥ።

በውኑ አንተ አገርህን ትወዳለህ?

ሕዝቦቿንስ ታከብራለህ ለባሕሏስ ትገዛለህ?

በቋንቋዋስ ታወራለህ?

እስኪ ስማ! የአባቶች ደም ዕዳ አለብን፣

የማንጨርሰው ሁሌም ከፍለን፣

ለባዕድ አገር ባሕል እንዳትገዛ ቢገዝቷት፣

አቡነ ጴጥሮስ ተገደሉ በፋሽስት ጥይት

ደማቸውም ፈሰሰ ከመሬት።

ታዲያ! እርሳቸውን ብርቅዬ አባት ለገደለ እጅ ትሰጣለህ?

ተላላ፣ ሞኝ! ቂል እንዴት ትሆናለህ?

ልጅ ሲያደርጉህ እንዴት ባርነትን ትመርጣለህ?

ነብር ዝንጉርጉርነቱን እንዴት ሊለውጠው ቻለ?

ኢትዮጵያዊስ በባዕድ መርዝ ባሕል እንዴት ተታለለ?

አንተ! የእመ ብርሃንን የአሥራት አገር አስደፈርካት፣

አንተ ደካማ ግዴለሽ ከንቱ ፍጥረት።

ሳይወጉህ ተሸንፈህ ሳይማርኩህ ተማርከህ፣

ለባዕድ ባሕል ባሪያ ሆነህ መኖር መስሎህ ትኖራለህ።

አቡነ ተክለሐይማኖት ዘረው የባረኳት፣

ገነትን የሚያጠጣ የግዮን ባለቤት፣

በረከትን ያልነፈጋት ፈጣሪ አምላክ የጠበቃት፣

ኢትዮጵያ እኮ ድንቅ አገር ናት።

እኛ ግን! ድንበሮቿን አፍርሰን ባሕላችንን ቀይረን፣

ሥማችን ኢትዮጵያዊ ሥራችን አውሮፓዊ፣

ፊታችን ሀገራዊ ልቡናችን ባዕዳዊ፣

የሆነብን አእምሯችን የዞረብን፣

እጅግ በጣም ብዙዎች ነን።

አይ እማማ...! የወላድ መካን አደረግንሽ፣

ተደፈረ ያ! የባሕል የእምነት ድንበርሽ፣

“ጠብቂኝ ልጆቼ አደራ” እያልሽ፣

ድንግል ማርያምን በእንግድነት ተቀብለሽ፣

ያለሽን አሰናድተሽ ድግስሽን ደግሰሽ፣

በረከትን ተቀብለሽ ስትኖሪ እኛን ወለደ ማኅፀንሽ፣

አሳልፈንም ሰጠንሽ።

መቼም...! ላናብስ እንባሽን፣

ያንችን ሥራ ዘንግተን።

አስለቀስንሽ አሳዘንሽ፣

ንፋጋን ልጆች ሆነንብሽ፣

እንግዳ መቀበልን ጠልተንብሽ፣

አንቺ ግን አሁንም እንዲህ እያልሽ ትመክሪያለሽ፣

ሎጥ እንግዳ መቀበልን ልማድ ቢያደርግ፣

መላእክትን መቀበሉን ልብ እናድርግ፣

አብርሃም ለእንግዶቹ ክብር መስጠቱ፣

ሥላሴን ተቀበለ በቤቱ።

ታዲያ...! ምን ተጎዱ እነ ሎጥ እነ አብርሃም እንግዳ መቀበልን የጠላነው?

ከቅዱሳኑ ያልተማርነው?

ለነገሩ...! ታሪክህን ስለማታውቅ ማን ይፈርዳል?

ማንስ ምን ብሎ ይወቅስሃል?

ኧረ ንቃ እባክህ!

ዛሬ የመኝታ ጊዜ አይደለም ተደፍረሃል ተወርረሃል፣

የማንነትህ አሻራ ጠፍቶብሃል።

አይ አንቺ ምድር!

ስንቱን መከራ ተቀበልሽ ስንቱን ሰቆቃ አየሽ፣

ስንቱን ክፉና ደግ በላሽ ስንቱን መጥፎና ጥሩ ቀበርሽ።

አብርሃምን የዋጠ አፍሽ ይሁዳን ዋጠ፣

የናቡቴን ደም የጠጣ አፍሽ የኤልዛቤልን ደም ጠጣ።

ስንቱ ይዘረዘራል መዘርዘርስ ማን ይችላል?

ኧረ ስማኝ! አንተ ጠማማ የማታስተውል ያንቀላፋህ፣

የማን ልጅ ነኝ ትላለህ?

የሚኒልክ ነኝ አትለኝ አገርህን አስደፍረሃል፣

በባዕድ እጅ ተማርከሃል፣

የአቡነ ጴጥሮስም ልጅ ነኝ አትል፣

እርሳቸው የገዘቷትን አንተ ፈትተሃታል፣

ለባዕድ ባሕል እንዳትገዛ ቢሞቱላት፣

አንተ ለአውሮፓውያን ተገዝተህ ሙት ሆንክባት።

የአቡነ ተክለሐይማኖት ልጅ እንዳልልህ፣

የት አለ ቅድስናህ በረከት ማግኘት ማስገኘትህ?

ብኩርና እምነትህን በምሥር ወጥ በድቃቂ ሳንቲም የምትለውጥ፣

ተረፈ ኤሳው እምነትህን ከምንም የማትቆጥረው።

የቅዱሳን መገኛ ኢትዮጵያን የታጥአን መፈንጫ፣

የባዕዳን መሮጫ የሰይጣን ማላገጫ፣

አደረግሃት! አንተ ከንቱ ፍጥረት።

ታዲያ...! የማን ልጅ ነህ ኧረ ንገረኝ ልጠይቅህ?

አባቱን የገደለው እናቱን ያገባው፣

አምላኩን የሸጠው የዚያ! የይሁዳ ልጅ ነህን?

ወይስ! እምነት ብኩርናውን የሸጠው የኤሳው?

ልክ ነው! ይህ ያስማማል! አንተስ እናትህን ገድለህ አባትህን ሰልበህ፣

ሚስትህን ቆራርጠህ አሰቃቂ ድርጊት ፈጽመህ፣

ወንድምህን ለአውሬ ጥለህ አምላክህን በገንዘብ ለውጠህ፣

ወልደ ማርያም የተባለ ሥምህን "መሐመድ" አላስባልክም?

አመተ ማርያም የተባልሽ እህቴስ ከድጃ አላስባልሽም?

የጆሮ ያለህ! ኧረ ስሙኝ! ከጊዜያችሁ ትንሽ ስጡኝ፣

ለነገሩ! ጊዜ ለእናንተ ወርቅ ነው።

የፊልም ማየቻ የአረቄ የጠላ መጠጫ፣

የኳስ መጫወቻ፣

ዓይንህን አፍጥጠህ ጆሮህን አውሰህ፣

አፍህን ከፍተህ ልቡናህን ሰቅለህ፣

የምታየው የአውሮፓውያንን እርግጫ፣

የዐረባውያንን ሩጫ ነው።

የእግር ኳስ ክለቦችን ሁሉ! ከነተጫዋቾች ሥም ሸምድደህ ትይዛለህ፣

ፊልም ሠሪዎችንም አንድ በአንድ ታውቃለህ፣

ስለ አንተ ግን ብጠይቅህ መልስ አለህ?

ክርስትና ሥምህን ታውቀዋለህ?

አላውቅም ነው መቼም መልስህ።

ታዲያ! ራስህን ሳታውቅ ሌላ ለማወቅ ምን ያባክንሃል?

መጀመሪያ ራስህን ማወቅ ይሻልሃል ይበጅሃል።

ከተራ ፍልስፍና ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይጠቅማሃል።

የዘፋኝ ሥም ከመሸምደድ የዜማውን አባት አንድ ያሬድን ብታውቅ ይሻልሃል።

ወደ ጠላ ቤት ከምትሮጥ ቤተክርስቲያን መገስገስ ያተርፍሃል።

ለጊዜዬ ዋጋ እሰጣለሁ ትላለህ ተሰብስበህ ታወራለህ።

ስትስቅ ስትቀለድ ትውላለህ፣

ታዲያ...! የምትቀልድበት ጊዜ አይደለም?

መጽሐፍ ቅዱስ ማንበቢያ ጊዜ ያጣህ፣

ቤተክርስቲያን ለመሄድ የደከመህ፣

ለመጸለይ ያንቀላፋህ።

ይመሻል ይነጋል፤ ይነጋል ይመሻል፣

አንተ ግን ዛሬም ተኝተሃል።

ኧረ ንቃ እባክህ ይበቃሃል!

ጊዜህን በአግባቡ ተጠቀመው መቀለጃ አታድርገው።

በሳቅ በጨዋታ አትጨርሰው፣

ሞት እንዳይጠራህ ማንነትህን ሳትረዳው፣

አንተነትህን ሳታውቀው።

ስካር ይብቃህ ዝሙት ይቅርብህ፣

በበሽታ ትቀጣለህ በዘላለም መከራ ትወድቃለህ፣

የሲዖል እራት ትሆናለህ።

ኧረ ቆይ እንጅ! ገንዘብህንስ ምን አደረግኸው?

አሥራት በኩራቱን ከፈልከው፣

ወይስ በጠላ በሲጋራ ጨረስከው?

ለቤተክርስቲያን እርዳታ ሲጠይቁህ የተራቡት ሲለምኑህ፣

ለአምስት ሣንቲም ዕቅድ አለኝ ትላለህ፣

ይባስ ብሎም ስድብ ትቀላቅላለህ፣

ነገር ግን ከጠላ ቤት ለሰከረው ሳይቀር ትከፍላለህ፣

አንተም ሰክረህ ትወድቅበታለህ፣

ለዝሙትም ትከፍላለህ፣

ታዲያ ...! ዕቅድህ ተዘነጋህ፣

ለአምስት ሣንቲም ዕቅድ አለኝ ስትል መቶ፣ ሽህ ብር ማጥፋትህ።

ኧረ ስማኝ ! የአዳም ልጅ ምንድኑ ነው ያስጨነቀህ?

የምትበላው የምትጠጣው ወይስ የምትለብሰው?

የሰማይ ወፎችን አታይም?

የምድር አበቦችን ልብ አትልም?

የወፎች እርሻ የወፎች ቁፋሮ አለ እንዴ?

ጠግበው ከዛፍ ዛፍ የሚበሩት በሰላም የሚኖሩት።

ማን አለበሳቸው ማንስ መገባቸው?

ታዲያ ! አንተ የምትጨነቀው ፈጣሪ አይመግበኝም ብለህ ነው?

ከነፍስና ከምግብ የሚበልጥ ማነው?

ነፍስ የሰጠን ምግብ መስጠት ይሳነዋልን?

ለምግብህ ስትጨነቅ የምትውለው የምታድረው።

ኧረ ተፈጥሮው በቂ ነው አስተውል፣

ያስተምራል ይመክርሃል።

ተመራምረህ ድረስበት አእምሮህን ከንቱ ነገር አትሙላበት፣

ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፣

እርሱም ይደግፍሃል ይላል ያ! ያላነበብከው መጽሐፍ።

ኧረ ማነህ! ማንነትህ ተሸፍኖ፣

ኢትዮጵያዊነትህ ተከድኖ፣

በአውሮፓ ባሕል ትዋኛለህ ማንነትህ ተዘንግቶህ።

ለንስሓ እንብቃ እባካችሁ ያለፈው ጊዜ ይብቃችሁ።

ዛሬን ለሰጠን ፈጣሪያችን ምስጋና እናቅርብ ከልባችን።

ለንስሓ ነው የጨመራት ይኽን ጊዜ በእውነት፣

የእኛ ጓደኞች የት አሉ?

አልሞቱም እንዴ ምድር አልገቡም እንዴ?

ኧረ ይብቃን እባካችሁ ይኽ ምድር ሳትውጣችሁ።

ከንፈር መምጠጡ አያዋጣም ገነትን አያወርስም።

ንስሓ ነው መፍትሔያችን የገነት መክፈቻ ቁልፋችን።

የታደሉት! በንስሓ ነጽተው በቅተው ሥጋና ደሙን ተቀብለው፣

የዘላለም ሕይወት አግኝተው ይኖራሉ፣

አንተ ደግሞ ዳልቻ ዶሮ ጥቁር ፍየል ወ.ዘ.ተ

እያልህ ጊዜህን በከንቱ ታጠፋለህ በምክረ ከይሲ ተታልለህ።

የክርስቶስ አማናዊ ሥጋና ደም ተዘጋጅቶ፣

አልበላም አልጠጣም አልህ ኃጢአትህ እጅግ በዝቶ።

ኧረ እባክህ ተመለስ! ጹም ጸልይ ስገድ አልቅስ፣

ንስሓ ነው መድኃኒቱ፣ ገነት መግቢያ ብልሐቱ።

Miko ZE Ethiopia

55/ ድንጋይ በድንጋይ ላይ

ነቢዩ ዕንባቆም ሊያስተምር ሲሄድ የይሁዳ አባት ከባልንጀሮቹ ጋር በድንጋይ ላይ ተቀምጦ ባልንጀሮቹ ነቢዩን አክብረው ከመቀመጫቸው ተነሥተው ሲያሳልፉት እርሱ ግን ተቀምጦ ክብር ሳይሰጥ አሳለፈው። አስተምሮ ሲመለስም ከዚያው ድንጋይ ላይ ተቀምጦ እንዳይነሣ ኮርቶ እንዳይቀመጥ ፈርቶ ተሸፋፍኖ ሊያሳልፈው በሞከረ ጊዜ “እብን ላዕለ እብን ነቢሮ”። ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተቀምጧል ከዚህ ሰው የሚወለደው ልጅ "አባቱን የሚሰልብ፣ እናቱን የሚያገባ፣ ጌታውን የሚሸጥ ነው" በማለት ትንቢት ተናገረበት። ክብር ለሚገባው ክብር አለመስጠት ምን ያህል እንደሚጎዳ ተመልከቱ። የነቢዩ ቃል ይፈጸም ዘንድ የይሁዳ እናትና አባት ያደረጓቸው ሥጋዊ ጥበቦች ይሁዳን ከመወለድ ማስቀረት አልቻሉም። ትንቢት የተነገረበት ልጅ በተወለደ ጊዜም ቢሆን እናትና አባቱ የወሰዱት እርምጃ ትንቢቱን አላስቀረውም። ይሁዳን ወላጆቹ ከባሕር ቢጥሉትም የሌላ አገር ሰዎች አግኝተው ከባሕር እውጥተውት በሌላ አገር አደገ። እናትና አባቱ በባሕር ስለጣሉት ለጊዜው የሞተ ቢመስላቸውም ይሁዳ ግን የነቢዩን ቃል

ሳይፈጽም ሊሞት አይችልም። የነቢዩ ቃልም ተፈጸመ አባቱን ጦር ሜዳ ላይ ገደለው፣ እናቱንም ከሰፈር ፈልጎ ሚስት አደረጋት በመጨረሻም አምላኩን ኢየሱስ ክርስቶስን በሠላሳ ብር አሳልፎ ለአይሁድ ሸጠው። ይህ ታሪክ ብዙዎቻችንን ከንፈር የሚያስመጥጥ ነው። ነገር ግን በሕይወታችን ከዚህ ያልተሻለ ሥራ ላይ ተሰማርተን ልብሱ ላማረ፣ ሰውነቱ ለወፈረ፣ መልኩ ለጠራ፣ ቦርሳ ላዘለ ወዘተ... በማድላት ፈርተን አክብረን ዝቅ ብለን እንቀበላለን። በጣም ጥሩ ነው። በአንጻሩ ግን ምንም ለሌለው ድሃ፣ ልብሱ ላደፈ፣ መልኩ ለጠቆረ፣ ድሪቶ ለለበሰ ወዘተ... በማክበር ፈንታ ምራቃችንን እስከመትፋት ድረስ እንጸየፋለን። ለምን? የሰው ልጅ የሚያየው ፊትን፣አለባበስን፣አረማመድን አነጋገርን ወዘተ... ነው። እግዚአብሔር ግን ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ ነው። ፈሪሐ እግዚአብሔር በውስጣችን ስላልሰረጸ የምንሠራው ሥራ ሁሉ በማድላት ላይ የተመሰረተ ነው። በየቢሮው ስትገቡ የአብዛኞች የዕለት ከዕለት ተግባር አድርገው የያዙት ፍርድን የመንፈግና የማድላት ሥራ ነው። ምናልባትም ጎንበስ ብላችሁ ሰላምታ ስታቀርቡለት በኩራት ተሸከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጦ መልስ ላይሰጣችሁ ይችላል። የደረሰባችሁን ችግር እያነባችሁ አስረድታችሁትም ከምንም ሳይቆጥራችሁ መፍትሔ ሊነፍጋችሁ ይችላል። የተበደላችሁትን ነገር ምርር ብላችሁ እየነገራችሁት እንደ ሞኝ ቆጥሮም የሚስቅባችሁ ቢሆን በዚያ ሰው አትበሳጩ ያ ሰው በወንበር ላይ የተቀመጠ ግዑዝ ነገር እንጂ ሰው ሊባል ከቶ አይችልም። ያልተደረገውን ተደረገ፣ የተደረገውን አልተደረገም፤ የሆነውን አልሆነም፣ ያልሆነውን ሆነ እያለ ሊሸነግልና ሊያታልል የሚሞክር ሰው በዋዘኞች ወንበር የተቀመጠ ድንጋይ

ነው። ምክንያቱም ፍርድ የመስጠት አቅሙ በአለባበስ፣ በዘር፣በወገን፣በቋንቋ ወዘተ... ላይ የተመሠረተ ነውና በተጨማሪም ሰው ሊባል የሚችልበትን ሥራ በአግባቡ እየሠራ አይደለምና። ፈሪሐ እግዚአብሔር በውስጡ የሌለው ሰው መቼም ቢሆን ሰውን ለማክበር የሚችል ትሑት ልቡና ሊኖረው አይችልም። ሳይማር ያስተማረውን የወገኑን ገንዘብ እየበላ ያረጀ ልብስ የለበሰ ወገኑን ከወገን የማይቆጥር ሰው በግብር የይሁዳን አባት ይመስለዋል። የእግዚአብሔር ክቡር ፍጡር የሆነን ሰው መቀበል፣ማክበር በረከት የምናገኝበት እንጅ የምንዋረድበት አይደለም። ስለዚህ የይሁዳ አባት በሄደበት መንገድ ተጉዘን ከመጎዳት ለመዳን ክብር ለሚገባው የሰው ልጅ ሁሉ ክብርን መስጠት ያስፈልጋል። ከዚያ ውጭ ግን "ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተቀምጧል" የሚለው የነቢዩ ትንቢት በእኛ እና በልጆቻችን ላይ መድረሱ አይቀርም። ስለዚህ በትሕትና ራሳችንን ዝቅ አድርገን ፈሪሐ እግዚአብሔርን ገንዘባችን አድርገን ለመኖር በቤቱ እስከ ፍጻሜያችን ድረስ መኖርን መምረጥ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው። ለዚህም የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

Tsige Yimer

56/ መዝሙረ ዳዊት 12: 1 አቤቱ፥ አድነኝ ደግ ሰው አልቆአልና፥ ከሰው ልጆችም መተማመን ጐድሎአልና።

ትንቢተ ሚክያስ 7: 2 ደግ ሰው ከምድር ጠፍቶአል፥ በሰውም መካከል ቅን የለም ሁሉ ደምን ለማፍሰስ ያደባሉ፥ ሰውም ሁሉ ወንድሙን በመረብ ለመያዝ ይከታተለዋል።

የዮሐንስ ወንጌል 7: 12 በሕዝብም መካከል ስለ እርሱ ብዙ ማንጐራጐር ነበረ፤ አንዳንዱም። ደግ ሰው ነው፤ ሌሎች ግን። አይደለም፥ ሕዝቡን ግን ያስታል ይሉ ነበር። [መዝ ፲፩፥፮—ዓመፅን የሚናገር በዓይኔ ፊት አይቀናም

ከእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ፤ ዓይኖቼ በምድር ምእመናን ላይ ናቸውና፤ በቀና መንገድ የሚሄድ እርሱ ያገለግለኛል።

ትዕቢትን የሚያደርግ በቤቴ መካከል አይኖርምና፤ ዓመፅን የሚናገር በዓይኔ ፊት አይቀናም። ማቴዎስ ወንጌል 12;- 36 እኔ እላችኋለሁ፥ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤37 ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ።

የዘመድኩን የዓለማው ደጋፊዎች

57/ "የሰማይ አምላክ የከናውንልናል እኛም ባርያዎቹ ተነስተን እንሰራለን"

ተሀድሶን/የእናት ጡት ነካሾችን/በመዋጋት ግንባር ቀደም የሆነው ወንድማችንን መምህር ዘመድኩንን የማግኘት እድሉን አግኝተን ነበር ።

በጉዳያችንም ላይ ስለተዘጉበት የ facebook Account እና ወደ ፊትም መስራት ስላሰበው

Website and Blog development በሐሳቡ ላይ

ተጨዋውተናል።

በመሆኑም የ IT ባለሙያ የሆኑ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች ስራውን በከፍተኛ ሁኔታ እየተወጡት እንደሆነም ነግሮናል።ሰሞኑንም Website እና blog ተደራሽ ይሆናል ማለት ነው።

እኛም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ከወንድማችን ከመምህር ዘመድኩን ዓላማዎች ጎን ከመቼውም ግዜ በበለጠ የምንቆምበት ግዜ አሁን ነው። # የቤተ ክርስትያናችን ጉዳይ ስለ ሚያገባን#

መረጃ ለምትፈልጉ የእጅ ስልኩም 0911608054 ነው።እውነትም ክፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል።

"የገሐነም ደጆች አይችሏትም"

like . Gojam Eshetu

እኛ የተዋህዶ ልጆች ሀገራችን በሠማይ ነው ማንም ምንምቢያወራ ከድንግል ማርያም እቅፍ የሚያወጣን የለም

Miko ZE Ethiopia

58/ የ ቆሙ መቃብሮች

በመ/ር ስምዓኮነ መላክ

መቃብር ሰዎች ሲሞቱ ወይም ነፍሳቸው ከሥጋቸው ሲለይ በክብር የሚያርፍበት ቦታ መቃብር ይባላል። መቃብር የሚለው ቃል የጎደጎደ ምድር ተብሎ ይተረጎማል። መዝ.14፥4፣ ኢሳ.22፥16 ሲያልንም መቃብር ሲል ይገኛል። መትሕተ ታሕቲት ናትና።

በማን ጊዜ እንደተጀመረ ባይታወቅም የሚቀበሩት በርስትነት በያዙት ቦታ ነበር ዘፍ.13። ያ ልማድ ሆኖልን ዛሬም በአዲስ ኪዳን የምንኖር ክርስቲያኖች እንደ አባቶቻችን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ እንቀበራለን። ስለምን ቢሉ ሥጋውን ደሙን የበላንበትና የጠጣንበት ብቸኛዋ ርስታችን በምድር ቤተ ክርስቲያናችን ናትና ነው።

የቀደመው ርስት በዋጋ ይገዛ ነበር የዛሬዋ የምእመናን ርስት ቤተ ክርስቲያን ዋጋዋ የክርስቶስ ደም ነውና ደሙ በነጠበበት ቦታ ብቻ ስትሠራ ትኖራለች የምእመናን መቃብር በጌታ ደም የተገዛ እንጂ በሰቅል በተመዘነ ወርቅ የተገዛ አይደለም። ይህም የጌታ ደም ከሁሉ በላይ የከበረ እንደሆነ የምእመናንም መቃብር የከበረ መሆኑን ያመለክታል።

ለዛሬው ግን መቃብርን ያነሣነው ከአቤል ሞት ጀምሮ እስከ ጌታ ዳግም ምፅአት የማያቋርጥ ታሪክ ያለውን ጀግና ባለ ታሪክ መቃብርን ታሪኩን ለትውልድ ልናስተዋውቅለት ሳይሆን መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለቆሙ መቃብሮች የተናገረውን ቃል ማስታወስ ስለሚገባ ነው።

መድኀኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ስብከት በጀመረ በመጨረሻው ዓመት በመቅደስ ተገኝቶ ለሕዝቡና ለደቀመዛሙርቱ ተናገረ፦ “ታላቅ ሽክም ማሰር ስለሚችሉት መሸከም ግን ስለማይወዱት ስለ ጻፎችና ፈሪሳውያን ነበር የተናገረው።

ለብዙዎች ብዙውን ኀጢአታቸውን በፍቅር የሸፈነው ጌታ ስለ ወንጀለኞች ሲጠየቅ ዝም የሚለው አምላክ ዮሐ.8፥11፣ ሉቃ.7፥47 በቤተ መቅደሱ አደባባይ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል የእነዚህን ታላላቅ የኦሪት አገልጋዮች በደል መዘርዘር ጀመረ። ተመክሮ ያልተመለሰን ሰው በአደባባይ

ሊወቅሱት ይገባልና ጌታ በቅዱስ ወንጌል እንደተናገረው “ቢሰማህ ብቻውን አድርገህ ብቻህን ሆነህ ምከረው ባይሰማህ ካንተ ጋር ሁለት ሆናችሁ ምከረው..... እነርሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት” ማቴ.18፥15-17 ብሎ በእግዚአብሔር ጉባኤ ላይም የማይገባ ነገርን አድርገዋልና መገሰጽ ስለሚገባቸው በታላቅ ቃል ገሰጻቸው 1 ቆሮ.5፥5 በመጽሐፍ ቃልህ እውነት ነው ተብሎ የተነገረለት መምህር ነውና ዮሐ.17፥17 እነርሱን ከውስጥ እስከ ውጭ ሊገልጹ በሚችሉ የተግሣፅ ቃላት ገሰፃቸው።

በዘመኑ የነበሩ መምህራን አባቶቻቸው በሠሩት ኀጢአት የተጸጸቱ ለመመሰል አባቶቻቸው የገደሏቸው የነቢያትን መቃብር በኖራ እየለሰኑ ይሠሩና ያሠሩ ነበርና ያንኑ የሠሩትን ልስን መቃብር እየተመለከተ “የተለሰነ መቃብር የምትመስሉ” ሲል ተናገራቸው ይህ መቃብር ቢከፍቱት ለአፍንጫ የሚከረፋ ለዐይንም የሚከፋ ነገር አይታጣበትም። ሥጋው ተልከስክሶ አጥንቱ ተከስክሶ፣ እዥ ፈሶ ሲታይ ከውጭ የተለሰነ ውበቱን ያጠፋዋል። አብረውት እንዳይኖሩ ያስገድዳል በዚህ ረጅም ዕድሜው እንደላዩ ሁሉ ውስጡ አምሮ አያውቅም።

ዘመኑን ሁሉ ሕይወት በሌላቸው ነገሮች የተሞላ ሆኖ ይኖራል እንጂ። ከዕለታት ባንዱ ስንኳን ንጹህ ነገር ክርስቶስን ቢያገኝ በሥጋ የሞተው በመንፈስ ግን ሕያው የሆነው ጌታ በትንሣኤ አሸንፎት ይዞ ማስቀረትም አይቻለው ብሎ ባዶውን ቀርቶ ይሄው እስከዛሬ ያለ ክርስቶስ ይኖራል። በእውነት ክርስቶስ በመቃብር መስሎ የተናገረበት ነገሩ ምን ይመስላችኋል? ለጊዜው የሚያመለክተው በዚያ ዘመን እስከ ክርስቶስ ወደ መቃብር

መውረድ ድረስ በሰው ልጆች ላይ ሙስና መቃብር በሥጋቸው ወደ ሲዖል መውረድ በነፍሳቸው የግድ የነበረባቸው መሆኑን ያመላክታል።

በዘመኑ ባለ ጊዜ ሆኖ ሞት ውጦ መቃብር ተረግጦ የማስቀረት ጎይል ነበረውና። ያንን የሚገልጽ ሲሆን ፍጻሜው ግን ከውጭ ለሰው መልካም መስለው ስለሚታዩት ከውስጥ ግን ለእግዚአብሔር የሚመች በጎ ተግባር የሌላቸው ሰዎች እንዲገሰጹበት የተጻፈ ነው።

ከውጭ ሲያዩአቸው ይጸልያሉ ይጾማሉ በጾምና በጸሎት ብዛት በገድልና በትሩፋት ጠውልገው ይታያሉ ስመ እግዚአብሔርን ጠርተው ይምላሉ ሐሰቱን እውነት ያስመስላሉ በልባቸው የሌላውን የእግዚአብሔር ቃል አንሥተው ሲናገሩ በቂሳርያ ከተመሰገነው ጴጥሮስ ይበልጣሉ ዝምነታን በማያውቀው አንደበታቸውም ደግመውና ደጋግመው ስሙን ሲጠሩ ከጳውሎስ በላይ ሰባኪ ይመስላሉ ከውስጣቸው ግን እንዲህ አይደሉም። አመጽንና ሽንገላን ተሞልተዋል። በክፉ ምኞታቸውና አስቀያሚ በሆነው መሻታቸው የገዛ ነፍሳቸውን ገለው የገዛ ሥጋቸውን መቃብር አድርገው ቀብረዋል።

በወይንና በአረቂ አልሰከሩም እንጂ በጎጢአት ሰክረው ወድቀዋል። ከመብልና ከመጠጥ እንጂ ክፉ ተግባራቸውን ከመተው የማይከለክሉ ይልቁንም በሞተ ሥራ የተሞሉ የቆሙ መቃብሮች ሆነዋል ስለዚህም መቃብር ውስጥ ያሉ ሙታንን ስንኳን የማይጠላ ጌታ ለተለሰኑ መቃብሮችም በቤተ መቅደሱ አደባባይ ቆሞ አሳምረው የለሰኑአቸው ልስን መቃብሮችን አሻግሮ እየተመለከተ ሁሉም ወደ መዳን የሚደርሱበትን ሕያው መልእክቱን አስተላለፉ።

ወንድሜ ሆይ! አንተስ እንዳምን ነህ? ከውስጥህስ ምን ይገኛል? እግዚአበሔር አንተን ክርስቲያን አድርጎ ሐዋርያት ከሰበሰቧት አንዲት ማኅበር አባል ሲያደርግህ ምን ዓይነት ዓላማ እንደነበረው ታውቃለህ? ጨለማውን ዓለም ካንተ በሚወጣው የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን ሊሞላው፣ ሕይወት አልጫ ለሆነችባቸው ማጣጫ ሊያደርግህ ማቴ.5፥12-13 በአሕዛብ መካከል ስሙን አሸክሞ ሊልክህ ሐዋ.9፥5 ዓላማ ስላለው ነው። የታመመውትንና በአጋንንት ተይዘው የሚሰቃዩትንም የሚፈውሳቸው ለምጻሞችን የሚያነጻቸው የረከሱትን የሚቀድሳቸው አንተን መሣሪያ አድርጎ እንደሆነ ታውቃለህ? አንተ ግን ለዚህ ዓላማ የተጠራህ መሆንህን የረሳህ ትመስላለህ። በአለባበስህና በከንፈርህ ብቻ እግዚአብሔርን ታመልካለህ ቀን ቆጥረህ ደማቅ በሆኑ የዓመትና የወር በዓላት ብቻ ለእግዚአብሔር ትዘምራለህ በሌላው ቀን ግን ትጠፋለህ ቃሉን ታውቃለህ እንደ ቃሉ መኖር ግን ተስኖሃል ከውጭ እንጂ ከውስጥ የሚታይ ነገር የሌለህ መጥፎ ሰው ሆነሃል። በክፉ መሻትህ እየወጋህ ሕያዊት ነፍስህን ገለህ የቆመ መቃብር ሆነሃታል።

የማይታይ የተሰወረ የማይገለጥ የተከደነ አለ ይመስልሀልን? ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመት ቆይታ በኋላ ተከድኖ ይኖር የነበረ መቃብር መገለጡን በጌታ ደም ድብቅ ምሥጢሩን ከረጅም ዓመታት በኋላ ማጣቱን እንዳትረሳ ማቴ.27፥57 አንተ ሆይ! ሳይነግሩት የሰውን ማንነቱን የሚያውቅ ጌታ አንተንስ ቢገልጥህ? ዮሐ.2፥25 ከላይ የተለሰነ ኖራህን ቢያነሳብህስ? የቆመው መቃብርነትህ በጌታ ቃል የሞተውን ሳይሆን ሕያው የሆነ አልዓዛርን የሚያስገኝ ይመስልሃል? ብታምን የልቡናህን ትንሣኤ ዛሬ ታየ

ዛሬም የተለሰነው መቃብር በር ላይ ቆሞ ይጣራል በውስጥህ ያሉት ሙታን አካሎችህ ዛሬ ድምጹን የሚሰሙበት ጊዜ ደርሷል እርሱም አሁን ነው ዮሐ.5፥25።

የሚያሳዝነው ነገር ተዘግቶ ተለስኖ መቀመጡ ነው እንጂ የተከፈተ መቃብርማ ለብዙዎች የሚያስገርም ምስጢር ተገኝቶበታል እኮ! ሉቃ.24፥12 መላእክቱ የከበቡት የጌታ ደቀ መዛሙርት የንበኙት ያ ቅዱስ መቃብር ባዶም ቢሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ትንሣኤውን የሰበከ እርሱ ነበር።

ወንድሜ ሆይ! የቆመ መቃብር ብትሆንም ለእግዚአብሔር ቃል የተከፈተ ልብ ካለህ እውነት እልሃለሁ ስላንተ ወዳንተ ወደመቃብሩ መላእክቱን ያዝልሀል ለደቀ መዛሙርቱ ሳይቀር የሚደንቅ ጥበብን ይገልጥብሃል ለጌታችን ቃል የተከፈተ ልብህ ዝቅ ብለው ቢያዩትስ የጌታ ልብስ ብቻ እንጂ ሌላ ምን ይገኝበታል። ከእውቀት፣ ከጥበብህ ከቅድስና የተለየሁ ባዶ ሰው ነኝ ብለህ ብታምን እንኳን እግዚአብሔር ባዶነትህን ለምስክርነት ይሻዋልና ከላይህ ላይ ያለ ልስንህን አስወግደው።

አለበለዚያ የክፉዎች አጋንንት ማደሪያ መሆንህን አትርሳው። ማቴ.8፥28 ከዚያ በፊት ግን አሁን ዕድል አለህ። እንደውጪ ሁሉ ውስጠኛውንም የመቃብር ክፍል ማጽዳት ትችላለህ። አንተ እኮ! ዕድለኛ ነህ። የአባትህ ድምጹ እስከመቃብር ድረስ ዘልቆ ይሰማል ቅዱስ የሆነው ደሙ በመቃብር ያሉትን ሳይቀር መቃብራቸውን ከፍቶ ይቀድሳል እንዳትረሳ! ይሄ ዕድል ላንተም ተሰጥቶሃል። ደግሞም አንድ ነገር አለ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባው ቃል ኪዳን አለ መቃብሩን ከፍቶ ለሞቱ አጥንቶች ሕይወትን ሰጥቶ

የሚያኖርበት ጊዜ አለ ይሄ ቃል ኪዳን ላንተም የተገባ ቃል ኪዳን ነውና አትፍራ ምን አልባትም ይሄ ቃል ኪዳን ላንተም የተገባ ተስፋ አትቁረጥ።

በዙሪያህ ሆነው ከመቃብሩ ደጃፍ ድንጋዩን ማን ያንከባልልናል የሚሉም ይኖራሉ ድንጋዩ ታላቅ ቢሆንም ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሔር መላኩን ልኮ አንተ ባልጠበቅከው ሰዓት ሊያነሣው እንደሚችል አትጠራጠር። መቃብር ብዙ ጎያላንን ይዞ ማስቀረቱ የተገለጠ ነው። እነ ዳዊት እነሶምሶን፣ ዮፍታሔ፣ ጌዴዎን ሌሎችም ጎያላን መቃብር ያድራሉ ደራሲዎቹ የደረሱላቸው ተራኪዎቹ የተረኩላቸው ዜመኞቹም ያዜሙላቸው ጀግኖች ሁሉም ከመቃብር አላመለጡም ምድራዊ ፍጥረት ሥጋዊ ደማዊ ሰውነት ሁሉም የመቃብር ምርኮኞች ሆነዋል።

አንተ ሆይ! ባንተም ውስጥ ስንት ጎያላን የእግዚአብሔር ቃላት ተቀብረው ቀርተዋል መሰለህ? እነ አባ ጳውሊ ከዓለም ወጥተው የኮበለሉባቸው እነ አባ እንጦንስ ሥርዓተ መላእክትን የተላመዱባቸው ይሄ ግዙፍ ዓለም የተከናወነባቸው እነዚያ ሰባሪ ቃላቶች አንተ ዘንድ ሲደርሱ ግን ሳይሠሩ ቀብረህ አስቀርተሃቸዋል።

እውነት እልሃለሁ አዲስ ሆነህ የምትሠራው በቅዱስ ቃሉ ነውና ቃሉን ጠብቅ ብታምንም ባትምንም በክፉት ብትሆን ሳትወድ በግድ “መቃብር ሆይ ይዞ ማስቀረትህ ወዴት አለ?” ሆሴ.13፥14፣ 1 ቆሮ 15፥55 ተብለህ መጣልህ አይቀርምና ይህ የፈጣሪህ ድምጽ ወዳንተ ባደረበት ቅጽበት ወዲህ በፈቃድህ ንስሓ ግባ ይሄ ጊዜ ለሌላ ለምንም የተመደበ አይደለም የንስሓ ብቻ ነው።

“እነሆ መቃብራችሁን እከፍታለሁ ከመቃብራችሁም አወጣችኋለሁ ወደ

እስራኤል ምድርም አገባችኋለሁ መቃብራችሁን በከፈትሁ ጊዜ ከመቃብራችሁም ባወጣኋችሁ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ ታውቃላችሁ" ሕዝ.37፥12-13።

Like · Gebremeskel Degwale

አሜን አምላከ ቅዱሳን ወደ ልቦናችን ይመልሰን።

Like · Semere Semere

ለጌታችን ቃል የተከፈተ ልብህ ዝቅ ብለው ቢያዩትስ የጌታ ልብስ ብቻ እንጂ ሌላ ምን ይገኝበታል።

59/ "<u>እግዚአብሔር በአንድም መንገድ በሌላም ይናገራል።" *ኢዮ.33፥14*</u>

ቀዳሚ ገጽ

የወቢይ ጾም ሳምንታት

ማኅበረ ቅዱሳን

ለሕጻናት

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

ክርስቲያናዊ ሕይወትና ሥነ ምግባር

ስብከት

ዜና

ትምህርተ ሃይማኖት

ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን

የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት

የቤተክርስቲያን ታሪክ

ኪነ- ጥበብ

ግእዝ ይማሩ

ያግኙን

ባሕረ ሐሳብ የዘመን መቁጠሪያ

ይህ ሶፍትዌር ከዚህ በፊት በ 2000

ዓ.ም. /እ.ኤ.አ. በ 2008 /

በተለቀቀው ሶፍትዌር ላይ አንዳንድ ማስተካከያዎች በማድረግ ማተም

/ፕሪንት ማድረግ/ እንዲቻል ተዘጋጅቶ

የቀረበ ነው። ወደ ኮምፒዩተርዎ

በመጫን ይጠቅሙ።

ሶፍትዌሩን እዚህ በመጫን ይጠቅሙ።

ሌሎች መካነ ድሮች

ድምፀ ተዋህዶ የማኅበረ ቅዱሳን ሬዲዮ

የማኅበረ ቅዱሳን የቴሌቪዥን መርሀ ግብር

ማኅበረ ቅዱሳን ህብር ሚዲያ መካነ ድር

ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ አዲስ አበባ

ማኅበረ ቅዱሳን አሜሪካ ማዕከል

ማኅበረ ቅዱሳን ድምጸ-ተዋህዶ(አሜሪካ)

ማኅበረ ቅዱሳን አውሮፓ ማዕከል

ማኅበረ ቅዱሳን አውሮፓ ማዕከል ፖልቶክ

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ መጽሐፍት 1

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ መጽሐፍ

የቀድሞው ድረ-ገጽ

ይህንን በመጫን የቀድሞውን ድረገጽ ይመልከቱ ፈልግ

“የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻው መቃጠሉን ስሰማ አልቅሻለሁ” /ወ/ሮ መስታወት ዓለሙ/

መስከረም 8 ቀን 2008 ዓ.ም

በእንዳለ ደምስስ

በማኅበረ ቅዱሳን የልማት ተቋማት አስተዳደር የንዋያተ ቅድሳት መማረቻ ክፍል በቅርቡ በደረሰበት የእሳት ቃጠሎ በርካታ የልብስ ስፌት ማሽኖችና አልባሳት በመውደማቸው ምእመናን እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ወ/ሮመስታወት Â ዓለሙ ይባላሉ። መስከረም 7 ቀን 2008 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከባለቤታቸው ጋር በመሆን አንድ የልብስ ስፌት ማሽን ይዘው ወደ ማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ይደርሳሉ። ማሽኑንም ለልማት ተቋማት አስተዳደር ዳይሬክተር ለአቶ ኃይሉ ፍስሐ ያስረክባሉ።

ከርክክቡ በኋላ ወ/ሮ መስታወት Â ዓለሙ ለምን ማሽኑን ለመስጠት እንደፈለጉ ጠየቅናቸው። የሚከተለውንም ምላሽ ሰጡን።

ማኅበረ ቅዱሳን ቤተ ክርስቲያንን በመደገፍ እየሰጠ ባለው አገልግሎት በጣም ደስተኛ ነኝ። በአገልግሎቱም መንፈሳዊ ሃሴት ይሰማኛል። የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻው ከነማሽኖቹ መቃጠሉን በሬድዮ ስሰማ በጣም አዝኛለሁ፤ አልቅሻለሁም። ማዘን፤ ማልቀስ ብቻ ውጤት ስለማይኖረው ልጇ ትጠቀምበት የነበረውን የልብስ ስፌት ማሽን ለመስጠት ወሰንኩ። በዚሁ

መሠረት ማኅበሩ እንዲጠቀምበት አበርክቻለሁ ብለዋል። ሌሎችም ማኅበሩ የሚሰጠውን አገልግሎት ለማጠናከር የድርሻቸውን እንዲወጡ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

የልማት ተቋማት ዳሬክተር አቶ ኃይሉ ፍስሐ ሥጦታውን ከተረከቡ በኋላ ወ/ሮ መስታወት

እና Â ባለቤታቸው Â የልብስ ስፌት ማሽኑን ለማኅበሩ አገልግሎት በማበርከታቸው መደሰታቸውን በመግለጽ ላበረከቱት ሥጦታም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

< ወደኋላ ወደፊት >

ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

60/የቱ ነው ትክክለኛ የእግዚአብሄር ቃል ††† መጽሐፍ ቅዱስ 81 ወይስ 66 ?††† ክፍል አንድ

††† መጽሐፍ ቅዱስ ማን ጻፈው? †††

መጽሐፍ ቅዱስ ባለቤቱ እግዚአብሔር ሲሆን ጸሐፊዎቹ ግን ከእርሱ የተላኩ ቅዱሳን ሰዎች ናቸው። ጸሐፊዎቹ ብዛታቸውም ከአርባ በላይ ሲሆን አንዳቸውም ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አልጻፉም። “በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ” 2 ጴጥ 1፡20

††† መጽሐፍ ቅዱስ አሁን በእጃችን ላይ እንዳለው በአንድ የተጠረዘ መጽሐፍ ነበር? †††

መጽሀፍ ቅዱስ በአንድ ወቅት በአንድ ጊዜ ተጠርዞ የተሰጠ ወይም ከሰማይ

የወረደ ሳይሆን የተለያዩ ክፍሎች በተለያዩ ጸሐፍት እና ዘመናት የተጻፉ ናቸው። በጥንት ዘመን መጸሀፍት በጥቅል ተጠቅልለው ይቀመጡ እንደነበር ብዙ ማስረጃዎች አሉ፡- ጌታችን መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ናዝሬት በሚገኘው ምኩራብ ያነበበው የነቢዩ ኢሳያስን ጥቅልል መጽሐፍ ነበረ፡-

“የነቢዩን የኢሳያስን መጽሀፍ ሰጡት መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ..... ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ። መጽሐፉንም ጠቅልሎ ለአገልጋዩ ሰጠውና ተቀመጠ።” ሉቃ 4፡17-20

ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው ቅዱሳት መጻህፍት ለየብቻቸው በአንድነት ሳይጠረዙ እንደነበሩ ነው።

††† ቅዱሳት መጻህፍት አሰባሰብ? †††

ቅዱሳት ሐዋርያት ስለ ስርዓተ ቤተክርስትያን የተለያዩ ቀኖናትን ደንግገዋል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ስለ ቅዱሳት መጻህፍት ነው። በ 325 እ.ኤ.አ በኒቂያ በተካሄደው ጉባኤ ላይ እውነተኖቹን

ቅዱሳት መጻህፍት ለመሰብሰብ በተወሰነው መሰረት ቅዱስ አትናቴዎስ በ 367 ዓ.ም በ 39 ኛው የትንሳኤ ምልዕክቱ ላይ የቅዱሳትን መጽሐፍትን እና አይነት በአብዛኛው አስታውቋል። ከዚያም በሎዶቅያ በተካሄደ ጉባኤ እና በ 393፣399 እና 419 እ.ኤ.አ በሰሜን አፍሪካ ትገኝ በነበረችው ቅርጣግና /ካርቴጅ/

በተካሄዱት ጉባኤዎች ቅዱሳት መጽሐፍትን ለይቶ ለማወቅ ጥረት ተደርጓል። የካርቴጁ ጉባኤ ከተካሄደ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍትን በአንድ ላይ መጠረዝ እንደተጀመረ ይነገራል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት መድብል/ጥራዝ/ ተብሎ መጠራት ተጀመረ::

†††

ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍት ብዛት ሰማንያ አንድ መሆኑን ትናገራለች። ዳሩ ግን በዓለም ላይ በብዛት ተሰራጭቶ የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ስልሳ ስድስት ነው።

- በስልሳ ስድስቱ ውስጥ የሌሉት መጻሕፍት:-

††† ከ ብ ሉ ይ (2 ኛ የቀኖና መጻሕፍት) †††

1.መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል

2.መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ

3.መጽሐፈ ጦቢት

4.መጽሐፈ ዮዲት

5.መጽሐፈ አስቴር

6.መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ

7.መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ

8.መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ

9. መጽሐፈ ሲራክ

10. ጸሎተ ምናሴ

11. ተረፈ ኤርሚያስ

12. ሶስና.

13. መጽሐፈ ባሮክ

14. መጽሐፈ ጦበብ

15. መዝሙረ ሰለስቱ ደቂቅ

16. ተረፈ ዳንኤል

17. መጽሐፈ ኩፋሌ

18. መጽሐፈ ሄኖክ

††† ከሐዲስ ኪዳን †††

1. ትዕዛዘ ሲኖዶስ

2. ግስው ሲኖዶስ

3. አብጥሎ ሲኖዶስ

4. ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ

5. መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ

6. መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ

7. ቀለሚንጦስ

8. ዲዲስቅሊያ (እነዚህ የሐዲስ ኪዳን መጻህፍት አሁን በእጃችን በሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተካተቱም። ይህም የሆነው እያንዳንዳቸው በጣም ትልቅ መጻሕፍት በመሆናቸው ለማካተት አስቸጋሪ በመሆኑ ነው። ግን ከ 81 መጻህፍት መድበን ነው የምንቆጥራቸው። ሁሉም መጻህፍት በቤተክርስትያኖች ቤተ-መጻህፍት ውስጥ ይገኛሉ እንዲሁም ገዝቶ ማንበብ ይቻላል።

ወስብሐት ለእግዚአብሄር

እንደ እግዚአብሄር ፍቃድ ክፍል ሁለት ይቀጥላል

ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

<u>61/ የቱ ነው ትክክለኛ የእግዚአብሄር ቃል ††† መጽሐፍ ቅዱስ 81</u>

ወይስ 66? ††† ክፍል ሁለት(፪)

††† መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ †††

ብሉይ ኪዳን በሐገራችን ቋንቋ በግዕዝ የተተረጎመው ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺህ ዓመት ቀደም ብሎ ሲሆን ይኸውም በንግሥተ ሳባ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ነው። ኢትዮጵያ ከዚህን ጊዜ ጀምሮ መጻሕፍትን ጠብቃ አቆይታለች። አባቶች ምንም አይነት ጦርነት ቢነሳ ህይወታቸውን በማስቀደምመጻሕፍትን ጠብቀው አቆይተውልናል።

ከምዕራባውያን በፊት ክርስትናን ሆነ የአይሁድ እምነትን የተቀበለችው ሀገራችን በምዕራባውያን የሌሉ መጻሐፍት መገኛ ብቸኛ ሀገር ናት። ለዚህም ነው በአይሁድ ዘንድ ሆነ በሮማውያን ዘንድ በነበረው ጦርነት የጠፉ መጻህፍት ኢትዮጵያ ውስጥ ግን የሚገኙት። ለዚህም መጽሐፈ ሄኖክ እና መጽሐፈ ኩፋሌ ምሳሌዎች ናቸው። የመጽሐፈ ሄኖክ ጥቅልል አሁን በቅርቡ በቁምራን ዋሻ ተገኝቷል። የተገኘው ጥቅልልም ሀገራችን ጠብቃ ካቆየችው መጽሐፈ ሄኖክ ጋር አንድ አይነት ሆኖ በመገኘቱምዕራባውያን ተርጉመው መጠቀም ጀምረዋል።

††† የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት †††

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁለት አይነት የቀኖና ክፍሎችን ያካትታል እነሱም ፕሮቶካኒካል እና ዲዩትሮካኖኒካል ይባላሉ።

ፕሮቶካኒካል ፦ እነዚህ መጻሕፍት የተሰበሰቡት በካህኑ እዝራ ሲሆን መጀመሪያ በቀኖና መጻሕፍትነት የተመዘገቡ ናቸው። 1ኛ. መቃብያን 2፡ 10 “ነህምያም የነገስትን መጻሕፍት የያዘ ቤተ መጻሕፍት አቋቁሞ ነበር“ እነዚህም መጻሕፍት በ ሶስት ይከፈላሉ እነሱም ቶራህ (አምስቱ ብሔረ

ኦሪት) ፣ ነበኢም (ቀደምት ነብያት እና ደኃርት ነብያት) እና ከተቢም (ታላላቅ የታሪክ መጽሐፍትና ታናናሽ የታሪክ መጽሐፍትን ያካትታል) ተብለው ይጠራሉ። እንዲሁም ዲዩትሮካኖኒካል የምንላቸው አይሁድ እንደ ቀኖና መጻሕፍት የማይቀበሉዋቸው ግን እንደ አዋልድ መጻህፍት የሚቀበሉዋቸው ናቸው።

በነገራችን ላይ-> አይሁዶች 24 የብሉይ ኪዳን መጻህፍትን ብቻ ሲቀበሉ (የመጽሐፋቸው አቆጣጠር ከእኛ አቆጣጠር ይለያል)-> ፕሮቴስታንቶች 39 የብሉይ ኪዳን እንዲሁም 27 የሐዲስ ኪዳን ይቀበላሉ።-> ካቶሊኮች 46 የብሉይ ኪዳን መጻህፍት እና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻህፍት ሲቀበሉ እኛ-> ኦርቶዶክስ ተዋህዶዎች ግን 46 የብሉይ ኪዳን እና 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንቀበላለን። (ከካቶሊኮች ጋር በብሉይ ኪዳን የምንቀበላቸው መጻሕፍት ላይ የአቆጣጠር እና የመጻሕፍት ልዩነት አለ።)እዚህ ላይ ከላይ በግልጽ እንደምንረዳው 81 የነበረው የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ብዛት ቀስ በቀስ በሰዎች እየተቀነሰ እንዲሁም በነበሩት ጦርነቶች መጻሐፍቱ እየጠፉ በመምጣታቸው፣ መጀመሪያ 73 እንዲሆን በመቀጠልም ማርቲን ሉተር ሲያምንበት ከነበረው የካቶሊክ እምነት ፣ከካቶሊክ መነኮሳት ጋር በነበረው የግል ጸብ እና የፖለቲካ ጸብ (የጀርመን ዜጋ ስለነበር የአይሁዶች ጥላቻ ስለነበረው) በነበረው ቅራኔ ምክንያት 7 መጻህፍትን በገዛ ፈቃዱ ቀንሶ ዛሬ በምዕራብውያን ዘንድ በስፋት የተስፋፋውን እና የእኛን ሐገር ጨምሮ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ሀይል የሌላቸውን ሀገራት የተቆጣጠረውን የ 66 መጻሐፍት ሊያስፋፉ ችሏል።

ወስብሐት ለእግዚአብሄር

እንደ እግዚአብሄር ፍቃድ ክፍል ሶስት ይቀጥላል

like . ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

የክፍል አንድን ትምህርት ያልተከታተላችሁ ይሄንን ሊንክ በመክፈት ማንበብ ይቻላል ----> https://m.facebook.com/story.php?story_fbid=171517593190515&id=100009968262042&refid=17&__ft__=top_level_post_id.171517593190515%3Atl_objid.171517593190515%3Athid.100009968262042%3A306061129499414%3A2%3A0%3A1446361199%3A2802468110348808566

ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

የቱ ነው ትክክለኛ የእግዚአብሄር ቃል

††† መጽሐፍ ቅዱስ 81 ወይስ 66 ?†††

ክፍል አንድ

††† መጽሐፍ ቅዱስ ማን ጻፈው? †††

መጽሐፍ ቅዱስ ባለቤቱ እግዚአብሔር ሲሆን ጸሐፊዎቹ ግን ከእርሱ የተላኩ ቅዱሳን ሰዎች ናቸው። ጸሐፊዎቹ ብዛታቸውም...

ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

62/ የቱ ነው ትክክለኛ የእግዚአብሄር ቃል ††† መጽሐፍ ቅዱስ 81 ወይስ 66? ††† ክፍል ሶስት(፫)

መናፍቃን 81 /ሰማንያ አሃዱ/ መጽሐፍ ቅዱስን የማይቀበሉባቸው ምክንያቶች እና እንዲቀበሉ የሚያስገድዳቸው ምክንያቶች እንዲሁም ከስልሳ ስድስቱ ውጭ ሌሎች ቅዱሳት መጽሐፍት የሉም እንዳይሉ ማስረጃዎች፡-ተቃዋሚዎች ከ66 ውጭ መጽሐፍ የለም ቢሉም ሐዋርያት ሆኑ ጌታ ከ81 መጻሐፍት እየጠቀሱ አስተምረዋል። ይህን እስቲ በማስረጃ እንመልከተው።

†††ማስረጃ 1. - ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር ይለናል ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ (ሉቃ.3፡3) - እንግዲህ ጌታችን አምላካችን መድሃኒታችንኢየሱስ ክርስቶስ ከ30 ዓመቱ በፊት የት ነበረ? ምን እየሰራ ነበረ? ብልን ስንጠይቅ መልሱን በ66 መጻሕፍት ውስጥ ሳይሆን በቤተክርስቲያናችን የትውፊት መጻህፍት ውስጥ እድገቱምን እንደሚመስል በዝርዝር ተጽፎ እናገኛለን።

†††ማስረጃ 2. - በማቴዎስ ወንጌል 27፡3-10 (በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደ ተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ÷ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሎች መልሶ÷ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ አለ። እነርሱ ግን። እኛስ ምን አግዶን? አንተው ተጠንቀቅ አሉ። ብሩንም በቤተመቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ። የካህናት አለቆችም ብሩን አንሥተው። የደም ዋጋ ነውና ወደ መባ ልንጨምረው አልተፈቀደም አሉ። ተማክረውም የሸክላ ሠሪውን መሬት ለእንግዶች መቃብር ገዙበት። ስለዚህ ያ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ የደም መሬት ተባለ። በዚያን ጊዜ በነቢዩ #

በኤርምያስ የተባለው።ከእስራኤል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን፥ የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ፥ ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡት። የሚል ተፈጸመ።) በዚያን ጊዜ የነቢዩ የኤርሚያስ ቃል ተፈጸመ ይለናል ይሁዳ... እንዲህ ያለው ‹‹የእስራኤል ልጆች የተስማሙበትን የክቡርን ዋጋ ሠላሳውን ብር ወሰዱ›› ይህንቃል የምናገኘው በስድሳ ስድስቱ ውስጥ ሳይሆን በተረፈ ኤርሚስ 7፥ 2-4 ባለው ላይ ነው። ቅዱስ ማቴዎስ ትንቢተ ኤርሚያስን ጠቅሶ ሲጽፍልን 'በነብዩ ኤርሚያስ የተባለው ብሎን ነው።' ምንተባለ ስንል ማቴዎስ ''የተባለውን'' እና ''ተፈጸመ'' ያለንን የምናገኘው መናፍቃኑ አንቀበለውም በሚሉት በ 81 መጽሐፍት ውስጥ ነው።

†††ማስረጃ 3. - ኦሪት ዘፍጥረት 1፡26 እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር። ‹‹እንፍጠር›› ሲል ከአንድ በላይ ብዛትን ሲያመለክት 2 ወይም 4 ወይም 10 ሳይሆኑ # ስላሴን /ሶስትነት/ ስለት መሆናቸውን የሚነግረን በሲራክ 2፤22 ሄኖክ 5፤38 ሄኖክ 6፤24 ሄኖክ 13፤14 እዝራ ስቱኤል 4፤56 እዝራ ስቱኤል 12፤48 ሲራክ 44፤10 በግልጽ ሥላሴ እያለ በማሳየት ነው። ክብር ለቅድስት ሥላሴ ይሁን!

†††ማስረጃ 4. በሉቃስ 14:13-14 “ነገር ግን ግብዣ ባደረግህ ጊዜ ድሆችንና ጕንድሾችን አንካሶችንም ዕውሮችንም ጥራ፤ የሚመልሱት ብድራት የላቸውምና ብፁዕ ትሆናለህ” የሚለውን ኃይለ ቃል ከጦቢት 4፡7፡ 10 የተገኘ ነው ‹‹ከገንዘብህም ምጽዋት ስጥ ምጽዋትም በመጸወትህ ጊዜ በገንዘብህ አትዘን፣ከድሃም ፊትህን አትመልስ፤ እግዚአብሔርም ገጸ

በረከቱን ካንተ አይመልስም።››

†††ማስረጃ 5. 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 4፡2 በጌታ በኢየሱስ የትኛውን ትእዛዝ እንደ ሰጠናችሁ ታውቃላችሁና። ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና፤ ከዝሙት እንድትርቁ፥ የሚለውን ኃይለ ቃል ቅዱስ ጳውሎስ ከጦቢት 4፡12 ጠቅሶ ነው ያስተማረው ነው።

†††ማስረጃ 6. በዮሐንስ ወንጌል 10፡22 በኢየሩሳሌምም የመቅደስ መታደስ በዓል ሆነ፤ ... ‹‹የመቅደስ መታደስ በዓል›› በሌሎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አናገኘውም ግን ቅዱስ ዮሐንስ ከመጽሐፈ መቃብያን 4 ላይ ጠቅሶ ተናገረ።

†††ማስረጃ 7. በ ሮሜ 13፡1 ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። የሚለው ኃይለ ቃል ከሲራክ 17፡14 የተወሰደ ነው።

†††ማስረጃ 8. አዳምና ሔዋን አቤልና ቃየልን ወለዱ። ቃየል ሚስቱን አወቀ ጸነሰችም ይላል ዘፍጥረት 4፡17 በ66ቱ መጽሐፍት ላይ ስለ አቤልና ቃየል መወለድ እንጂ ሌላ የሰው ዘር በምድር ላይ ስለመኖራቸው ምንም አያወራም። ታድያ ይህቺ የቃየል ሚስት ከየት መጣች? ስለስዋ ምንም አይናገርም በአለም ላይ የነበሩ ሰዎች አራት ብቻ እንደነበሩ ነበር የምናነበው። የዚህን መልስ የምናገኘው በኩፋሌ 5፡8-17 ላይ ነው።

†††ማስረጃ 9. - ይሁዳ በመልዕክቱ ‹‹የሄኖክን ትንቢት ከመጽሐፈ ሄኖክ ጠቅሶ›› ጽፎታል (ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ። እነሆ፥ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፥ በኃጢአተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭከና ነገር ሁሉ

ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከእእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል (ይሁዳ 1፡ 14-15) መጽሐፈ ሄኖክ ደግሞ በስልሳ ስድስቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። ሄኖክ ትንቢት ተናገረ ብሎ ከትንቢቱ ጠቅሱ ይሁዳ በመልዕክቱ ጽፎልናል ይህም ትንቢት በሄኖክ 1፡9 ላይ በግልጹ ተቀምጦ እናገኘዋለን። እንግዲህ ይሁዳ ሄኖክ ትንቢት መናገሩን እየነገረን ተቃዋሚዎች ሄኖክ ትንቢት አልተናገረም ይሉናል።እኛስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ የጻፈወን ይሁዳን እናምናለን። እሱ የተቀበለውን እንቀበላለን ጥበብ አይኮረጅም ::

ወስብሐት ለእግዚአብሄር

እንደ እግዚአብሄር ፍቃድ ክፍል አራት ይቀጥላል

Like . ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

የቱ ነው ትክክለኛ የእግዚአብሄር ቃል

††† መጽሐፍ ቅዱስ 81 ወይስ 66? †††

ክፍል ሁለት(፪)

††† መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ †††

ብሉይ ኪዳን በሐገራችን ቋንቋ በግዕዝ የተተረጎመው ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺህ ዓመት ቀደም ብሎ ሲሆን ይኸውም...

Like . Mesfin Adugna

እኛ የተዋህዶ ልጆች መጽሐፍ

ቅዱስ 81 ስለመሆኑ ጥርጥር

የለንም አባቶች ያቆዩልን እዉነተኛና ተፈላጊ ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ ስላላቸዉ እንጂ

ለገፅ ማብዣ ብለዉ አይደለም።

ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

63/ የቱ ነው ትክክለኛ የእግዚአብሄር ቃል ††† መጽሐፍ ቅዱስ 81 ወይስ 66 ? ††† ክፍል አራት(፬) የመጨረሻው ክፍል

††† መጽሐፍ ቅዱስ ትውፊታዊ የአምላክ ቃል †††

በመጀመሪያ እስኪ መጽሐፍ ቅዱስ ትውፊታዊ መረጃ መሆኑን እንተማመን። ትውፊት ማለት ቅብብል፣ ርክክብ ወይም ውርስ ማለት ነው። ይህ መንፈሳዊ ውርስ ከቀደሙት አበው ለእኛ በርክክብ ደርሶናል። አንዱ ከሌላው የተቀበለውን ለሌላው አሳልፎ በመስጠት እስከ ዘመናችን የደረሰ እውነታ ነው።ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት ያለ የነበረ ነው። እንደውም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚሐብሔር ቃል መሆኑን አምነን የተቀበልነው የቀደሙት አባቶቻችን የእግዚሐብሔር ቃል መሆኑንበትውፊት ስላስረዱን ነው።

ለምሳሌ፦-1-ዓለም ከተፈጠረ ሺህ 486 ዘምን መጽሐፈ ሄኖክ ተጻፈ 2-እስራሄል በግብጽ ሳሉ በፈርሆን ዘመን የኢዮብ መጽሐፍ ተጻፈ 3-3643 ዓ.ዓ. እስራሄል ከግብጽ ወጡ በዚህ ጊዜ ኦሪት ተጻፈ፣ ወዘተ. . . . . እንግዲህ ከ1486 ዘመን በፊት የተጻፈ ህግ አልነበረም፤ በዚያ ጊዜ የነበሩ አበው ይመሩ የነበሩት ሙሉ በሙሉ በትውፊት ወይም በህገ ልቡና ነበር ማለት ነው። ከስልሳ ስድስቱ (66) መጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ሌሎች ቅዱሳትመጻህፍትየለም የምትሉ ወይም ትውፊታዊ መረጃ አንቀበልም

ለምትሉ እስኪ የሚከተለውን ጥያቄ ላቅርብ

†††1- በኦሪት ዘፍጥረት አገላለጥ ቃየንም ሆነ አቤል ሁለቱም ለእግዚሐብሔር ከስራቸው ውጤት መስዋዕት አቅርዋል። ዳሩ ግን የተቀበለው የአቤልን መስዋዕት ብቻ ነው። የቃየንን መስዋዕት ያልተቀበለው ለምንድን ነው? መቼም ለአቤል አድልቶ ነው የሚል መልስ እንደማይሰጥ እርግጣኛ ነኝ ምክንያቱምእግዚሐብሔር ለሰው ፊት አያዳላም።

2- አቤል ከበጎቹ በኩራትና ከሰቡ እግዚሐብሔር መስዋእት አቅርቧል፤ ከበጎቹ መካከል በኩራትና ስቡን ማቅረብ እንደሚገባ እንዴት አወቀ? ምክንያቱም የጽሁፍ ህግና ትዕዛዝ በዘመኑ አልነበረም

3- ‹ቃየንም ሚስቱን አወቀ ጸነሰችም ሄኖህንምም ወለደች› ይላል። እግዚሐብሔርወንድና ሴት አድርጎ የፈጠረው አዳምንና ሄዋንን ብቻ ነው። አዳምና ሄዋን ደግሞ የወለዱአቸው አቤልና ቃየንን እንደሆነ በምዕራፍ 4 ተገልጽዋል ፤ታዲያ የቃየን ሚስት ማንነች? ከየትስ መጣች? ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትንጥያቄዎች ለመመለስ ከ66 መጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆኑትን ሌሎች ቅዱሳት መጻህፍትንና ትውፍታዊ መረጃ መሰረት ማድረግ ይገባል ያለበለዚያ ጥያቄዎቹ የማይፈቱ እንቆቅልሽ ሆነው መቅረታቸው ነው?

†††እስኪ ደግሞ ወደ ሐዲስ ኪዳን እንሂድ። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ቢያንስ ቢያንስ ለ20 ዓመታት ያህል ስለ ጌታ ይማሩ የነበሩት በቃል ነበር ምክያቱም ሐዲስ ኪዳን ገና በጽሁፍ አልተቀረጸም ነበርና በቅብብል ወይም በሰሚ ያገኙትንም እነርሱ ራሳቸው ከጌታ እደተቀበሉት አድርገው ያስተምሩ ነበር ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ጳውሎስ ነው (1 ቆሮ. 11፥23-

24)። ጳውሎስ ከሐዋርያት ቃል የተማረውን ለሌሎች ደግሞ አስተላለፈ። ስለዚህም ወንጌል የሚያሰኘው በጽሁፍ መስፈሩ ብቻ ሳይሆን የሕያው የእግዚሐብሔር ቃልና የህይወት መንገድ መሆኑ ነው። በጌታ ጊዜ ወንጌል ገና አልተጻፈም ነበር፣ “ለሐዋርያቱም ወደ ዓለም ሒዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ”(ማር.16፥1) ይህም ሲል የሰሙት ተማሩት እንጂ በጽሁፍ ቀርጾ የሰጣቸው ወንጌል አልነበረም። በተጨማሪም በማርቆስ ወንጌል ም.1፥21-22 ‹ወደ ቅፍራንሆም ገቡ ወዲያውም በሰንበት ወደ ምኩራብ ገብቶ አስተማረ እንደ ባለስልጣን ያስተምራቸው ነበር እንጂ እንደ ጸፎች አይደለምና በትምህርቱ ተገረሙ›። ይህ የክርስቶስንተቃዋሚዎች ራሱ ያስገረማቸው ትምህርት ምን አይነት ነበር ‹ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለእርሱ በመጻህፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጎመላቸው› ሉቃ 24-27 ከትንሳሄው በኋላ ለሁለቱ ደቀ መዝሙር ተረጎመላቸው የመጻህፍት ትርጓሜ በየትኛው ሀዲስ ኪዳን ላይ ይገኛል?

“በነቢያት ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ. . . ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ” ማቴ 2፥23 ይህን የተናገረው ነቢይ ማነው? በየትኛው የትንቢት መጽሐፍ ይገኛል? ማቴ 27፥9‹በዚያን ጊዜ በነቢዩ ኤርምያስ የተባለው ከእስራሄል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን የተገመተውን ዋጋ ሰላሳ ብር ያዙ ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሰሪ መሬት ሰጡት የሚል ተፈጸመ› ይህስ ከየት ተገኘ? በተጨማሪም ሉቃ 2፥25-32፣ 2ኛ ጢሞ 2፥ 8፣ ዕብ 12፥ 21 ፣ ራዕይ 2 ፥14፣ ዮሐ 20፥ 30 ፣ ዮሐ 21 ፥25፣ ይሁዳ 9 እንዲሁም ዮሐ 1 ፥48 ሌሎች ማሳያዎች ናቸው።

በአጠቃላይ እነዚህ መረጃዎች ከ66 ቱ መጻህፍት የማናገኛቸውና ነገር ግን ተዋህዶ እምነት በምትጠቀምበት ሰማንያ አህዱ ውስጥ ፍንትው ብለው የተጠቀሱ ናቸው። ታዲያ እነዚህን የመሳሰሉ ፍሬ ሃሳቦች ስለተቀመጡበት ነው ሰማንያ አሃዱን ከሌላው ጋር ይጋጫል የሚባለው?

ብርሃን ዓለም ጳውሎስ ‹እንግዲያስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ› ያለው (2 ተኛ ተሰሎንቄ 2 15)። በቃላችንምበመልእክታችንም የተማራችሁትን ‹ወግ› ያዙ ሲል ትውፊትን ማለቱ ነው።

ፊልጵ 4÷9 ‹ከህኔ የተማራችሁትና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም እና ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል›። የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ግልጽ ነው። በፊልጵስዮስ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ከእርሱ ከአንደበቱ የተማሩትንና በጽሁፍ የተቀበሉትንም የሰሙትንም ያዩትንም ሁሉ እንዲይዙ እንደያደርጉ እንጂ የተጻፈውን ብቻ እንዲይዙና እንዲጠብቅ አልነበረም። ዛሬም እኛ በትውፊት የደረሰንን ሁሉ ልንጠብቅ መንፈሳዊ ግዴታችን ነው ።

2 ኛ ጢሞ ‹የእግዚሐብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ስራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚሐብሔር መንፈስ ያለበትን መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል›። ምክሩም ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን ተዋህዶዋውያን እናምናለን። ስለዚህም በቤተክርስቲያናችን ያሉትን የእግዚሐብሔር መንፈስ ያለባቸውን ቅዱሳት መጻህፍትሁሉ ለክርስቲያናዊ ህይወታችን እንገለገልባቸዋለን።

--> በመጨረሻም ኦርቶዶክሳዊያን በቤታችን ያለን መጽሐፍ ቅዱስ:-81:

የኦርቶዶክስ 73: የካቶሊክ 66: የፕሮቴስታንት 24: የአይሁድመሆኑንና አለመሆኑን ለይተን ተረድተን የራሳችን የሆነውን ትክክለኛውን 81 አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስን እንጠቀም።

ወ ስ ብ ሐ ት ለ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር

ወ ለ ወ ላ ዲ ቱ ድ ን ግ ል

ወ ለ መ ስ ቀ ሉ ክ ቡ ር

የማርያም ባሪያ ኤፍራታ ኦርቶዶክስ with Sara Yemariyam Lij

ይትባረክ እግዚአብሄር አምላክ አበዊነ የጸረ ሐራጥቃ ይፋዊ የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ጉባኤ 2 እንድምታን በተከታታይ እናቀርባለን።

ማሳሰብያ ይህን ተከታታይ ፖስት share በማድረግ እንዲሁም ፖስት በማድረግ እንድታጋሩ ይሁን

ክፍል አንድ

By Daniel king

Melaku Gebremichael Hirphasa

☞ ካልተረዳቹት comment ም ሆነ ላይክ ባታረጉት ይመረጣል ።

✔.....✔.....✔

<u>64/ ይህን ውብ "መጽሐፈ ጨዋታ፣ ወንጌላዊ"የተሰኘ ፁፍ ሳታነቡት አትለፉ !</u> የቀደምት አበው ስራ ነው ። ደስ ከተሰኛቹበት ለሌሎችም

አጋሩዓቸው share አርጉት ። ካልተረዳቹት comment ም ሆነ ላ
ይክ ባታረጉት ይመረጣል ።
==========
እግዚአብሔርም፥ በደብረ ሲና፥ በእጁ አስር ቃል ዘራ፤
ዛሬ የሚያጭደውም በታጣ ጊዜ፥ አንድ ልጁን ቢልከው፥
እንግዳ ነውና በዳዊት ቤት አደረ። ይህንም አዝመራ፥
ዓመት ሙሉ ብቻውን አጭዶ በጨረሰ ጊዜ፦ "አባቴ!፥
አባቴ! አመስግነኝ" አለ፤ ምነው፥ ከእረኛ ቤት ተወለደ፥
ብለን አምተነው አልነበር?
አሁንስ እርሱራሱ እረኝነቱን ገለጠው። ለካ፥ "የበጎች እረኛ
እኔ ነኝ" እያለ ከሰማይ ድረስ ተሰዶ የመጣ፥ በጎችን
ሊጠብቅ ነውን?
ከሰማይ ድረስ መጥቶ በግ መጠበቅ ካልቀረለትስ፥
ይህችን ታናሽ መንጋ መጠበቁ ለምንድን ነው?
ከምድር ዳር እስከ ምድር ዳር ድረስ ያለውን መንጋ፥ አንድ
አድርጎ ጠብቆ ደመወዙን በምስጋና አውጥተን
አንሰጠውምን?
እርሱስ ቢሆን፥ የተሰበረውን ጠግኖ፥ የደከመውን አሳርፎ፥
ተኩላ እንዳይነጥቃቸውም ጠብቆ፤ ከበጎቹስ መልከ
መልካሙን እየመረጠ አይወስድምን?
ደግሞም እኮ፥ አንድ በግ ባገኘ ጊዜ፥ ነጥቆ ወደ ጉድጓድ
እንደሚገባ፥ ቀበሮውንስ ቢሆን ያውቀው የለምን?

ያችም በግ ከእረኛዋ ፈቃድ ወጥታ ከተገኘች መዳን
የላትም። ምነው እርሱ ባዘዛት ብትገባ ኖሮ? ደጁ የእርሱ
አይደለምን?።
አዳምና ሔዋንን የሐጢዓት ብርድ ቢያንቀጠቅጣቸው፣
ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ለበሰ፤ በበረትም ወድቆ፣ ወገኖቹ
የላም እረኞች አዩት፤ ለላም እረኞችም የምሥራች
ነገራቸው፤ ለካ፣ እረኛ፣ እረኛ! ነው።
❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊
ኢየሱስ ክርስቶስ፦ "ኑ፣ ያባቴ ብሩካን፣ ዓለም ሳይፈጠር
የተዘጋጀላችሁን ውረሱ" ይላል፤
ከቶ ዓለም ሳይፈጠር ምን ኖሮታል? እርሱ ጥበቡ
አይታወቅ?
እንደገናም፣ "ለቀበሮዎች ጉድጓድ አላቸው፥ ለሰማይ
ወፎችም ማረፊያ ዛፍ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን
የሚያስጠጋበት የለውም" አለ። ለካ፣ ሰማይና ምድር
ቢጠበው ነው፣ ከሰው ውስጥ መጥቶ ያደረ? እንደ ባሪያም
የመሰለ?
"እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ!" አለን፤ ከእንደገናም፣
"መብራት አብርቶ በእንቅብ ውስጥ የሚያኖር የለም"
ይላል።
ዓለምን ያህል እንቅብ ደፍቶብን የለምን? ታዲያ እኛ
በወዴት እናብራ? ጳውሎስስ በእድሜው ልክ አበራ።

❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊

አንበሳ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ዱር ገባ፤ ምን እንስሳ ይሰብር ይሆን ከዲያቢሎስ በቀር?

እነዚያ ወራቱ መላእክትስ፥ እንስሶች ናቸው፤ ከጀርባቸው ላይ አንድ ፍም መጥቶ ከሰው ላይ ሲወድቅ አለመናገራቸው፥ ከቶ ምን ሆነው ነው? ከእነርሱስ ገብርኤል ይሻላል፥ ተሸቀዳድሞ መጥቶ ለቆንጆዪቱ የነገረልን።

የሰማይ እሳት ከሰው ላይ ወድቆ አለማቃጠሉስ ከቶ ምን ይሉታል?

ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር፤ የእግዚአብሔር ልጅስ፦ "ገንዘባችሁን እየሰበሰባችሁ ወደ ሰማይ ላኩ፤ ከዚያ ይቆያችኋልና" ይለናል። ለካ፥ የእርሱ ገንዘብ አልበቃው ቢል ነው ወደኛ ልጁን የላከ፥ ቀስ ብሎም ገንዘባችንን በብልሃት እንዲያከማች ኖሯልና! ከእንግዲህስ አወቅንበት፥ ገንዘባችንንማ አናባክንም፤ ከሰማይስ እኛ ምን አለን? ገንዘባችንንስ ወደዛ አሸክመን ከምንልክ፥ አንካሶችን፣ እውሮችን፣ ችግረኞች ወንድሞቻችንን ይዘን፥ እዚሁ እንክት እያደረግን እንበላዋለን፤ እንጠጣዋለንም፤ በገዛ ገንዘባችን ከቶ ምን ይመጣብን ብላችሁ?

አላመጣችሁም ብሎ የሚያደርገውን ደግሞ እስቲ እናየዋለን? ከዚህ ቀደም፥ አባቶቻችንን አታሎ ያወጣው

ገንዘብ ይበቃዋል።

ዳግመኛም፥ "ባለጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ፥
ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሄድ ይሻላል" ይላል። አሁን ማን
ይሙት፥ ከእርሱ የበለጠ ባለጠጋ አለን? እርሱስ
በመንግሥተ ሰማይ ይኖር የለምን? ይህንን እያመካኘ
የሰው ገንዘብ አሻግሮ ማየቱስ ምንድን ነው?
ከዚህ ቀደም አስሩን ቃል ተናግሮ፥ ተናግሮ፥ ከወንጌል
አደረሰን፤ በመጣ ጊዜም፦ "ለነገ አታስቡ፥ ምን እንበላለን
ብላችሁም አትጨነቁ፥ ሀብትም አታከማቹ" እያለ
ገንዘባችንን ሊያስበላብን አይደለምን?
ወዲያው ደግሞ፦ "ተርቤ አላበላችሁኝም፥ ተጠምቼ
አላጠጣችሁኝም፥ ታርዤ አላለበሳችሁኝም፥ ታምሜ
አላያችሁኝም፥ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝም" አለን፤
ይህን ያህል ስድስት ቃል ምን ያናግረዋል? ወዲህ ደግሞ
ለነገ አታስቡ ይላል።
ከእኛ ወገን፥ የተራበ፥ የተጠማ፥ የታረዘ፥ የታመመ የለም
መስሎት ይሆንን? እርሱስ ቢሆን ከሰማይ ድረስ ተሰድዶ
መጥቶ፥ አሁን እኛን፦ "ተርቤያለሁ፥ ተጠምቻለሁ፥
ታርዣለሁ" የሚለን ለምንድን ነው? ሰማይን ያህል ሰፊ
አገር ይዞ፥ አባቱ ከዚያው አያበላውምን? አያጠጣውምን?
አያለብሰውምን?፤ ልጁስ ሲለምን ነውር አይፈራምን?
ኧረ እኛስ ለሰማይ ንጉሥ ልጅ፥ አናበላም፥ አናጠጣም፥

አናለብስም፤ ከዚሁ ካሉት ከድሆች ወንድሞቻችን ጋራ ገንዘባችንን ተካፍለን እንበላለን፥ እንጠጣለን፥ እንለብሳለን እንጂ።

እንደዚህ ያለ ዘወትር ንዝንዝ ምንድን ነው? በወንጌል ገንዘባችንን ሊወርስ የጦም አዳር እያለ ሊካፈለን አስቧል መሰለኝ?

❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊

እግዚአብሔር ለካ ፈሪ ነው፥ እኛ ብንበድለው ልጁን ልኮ፥ ቀስ ብለህ ተዛምደህ ና!፥ ብሎ በልጁ ታረቀን፤ አሁን ምን ያደርጉኝ መስሎት ነው? ለካ፥ በየቤቱ ፍርሀት አይታጣም፤ እኛ ስለበደልነው የምንክሰውን እርሱ ካሰን። ከእንግዲህ ወዲህ ሥጋችን ከኾነ አይቀር፥ በሰበብ ባስባብ ብለን ርስቱን እንካፈለዋለን፤ ጥቂት ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ እንደሚሉት፥ እንኳን ልጁን ልኮ ተዛመደን።

ኧረ፥ የክርስቶስስ ነገር እጅግ አስቸገረ፥ ልጅ ስለሆነ ይሆን? አንድ ጊዜ፥ "ተርቤ አላበላችሁኝም" ይላል፤ አንድ ጊዜ አምስት እንጀራ ለአምስት ሺህ ሰው አብልቶ፥ አትርፎ ያስነሳል። ከእንደገናም፥ "ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም" ይላል፤ ወዲያው ደግሞ የጋኖቹን ውኃ፥ ወደ ወይን ጠጅ ቀይሮ ሕዝቡን ያጠጣል።

መጽሐፍ አንዳንድ ጊዜስ አያውቅም ልበል? "ሰው ቢሞት ደስ አይበልህ" ይላል፤ አሁን በኔ ሞት ይዣችኋለሁ፥

ክርስቶስ ባይሞት ኖሮ፥ ለኔ መንግሥትን ማን ሊሰጠኝ
ኖሯል? የእርሱ ሞት እኔን ጠቀመኝ፥ እሰይ!፤ እሰይ! እንኳን
የሞተልኝ! እልል!፤ እልል!፤ እንግዲህማ ሥጋውንስ
ብበላው÷ ደሙንም ብጠጣው ምነው? እኔን የመሰላችሁ
ሁሉ ደስ ይበላችሁ።

❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊

ዳዊት ይሁዳን፦ "አገሩ ምድረ በዳ ትሁን" እያለ ምን
ያራግመዋል? እርሱ ካልበላሁለት ብሎ ነውን? መቼም
እንደ ይሁዳ ያለ መልካም ነጋዴ የለም፤ የዘላለሙን
ምግብ በሠላሳ ብር ሸጠልን።
እግዚአብሔር፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ÷ ከሙሴ
ጀምሮ እስከ ዮሐንስ ድረስ ጮኸ!÷ ጮኸ!፥ የሚሰማውም
ታጣ፤ ቃሉም ደግሞ ታሰረ፥ እንግዲህ በምኑ ይንገራችሁ?

❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊ ❊

አብ እሳት÷ ወልድ እሳት÷ መንፈስ ቅዱስ እሳት፤ ስሙ
ሦስት ቢሆን፥ ኪሩቤል ይጨነቁ እንጂ እኔ ምን እዳዬ፤
መቼውንም አንድ እሳት ነው፤ በሥጋዬ ጠቅልዬ
ተሸክሜዋለሁ።
ኪሩቤልማ በስም እንስሶች ናቸው እንጂ ጥቂት እንኳ ሥጋ
የላቸውም፤ ይህን የማይጠፋ እሳት ኧረ እንዴት ይችሉታል?
ሙሴ አስር ቃል ተናግሮ ሰውን ሁሉ አስፈጀ፤ ምነው
ባልተናገረ ኖሮ የማይችለውን ነገር? አሁን ሙሴ ባጠፋ

የክርስቶስን ሥጋ፣ ጥሬውን ይበሉታል? አይሁዶች ግን
ምን ነክቷቸው ይሆን እንዲህ ያደረጉት? ፊት ከሙሴ ጋር
ነበረ ብለው ይሆን?
ለነገሩማ፣ "አብርሃም ሳይወለድ በፊት፣ እኔ አለሁ"
ካላቸው፣ ከሙሴም ጋር አብሮ መኖሩስ መች ይቀራል
ብላችሁ ነው።
እግዚአብሔር፣ ሰው ባጠፋ ባስሩ ቃል አመካኝቶ አንድ
ልጁን ቢያስገድለው አሁን ምን ተጠቀመ? "አዳምም
ከእኛ እንዳንዱ ኾነ!" ያለውን ቃል እፈጽም ብሎ ነውን?

65/ ወይን መጠጣት ይፈቀዳልን! መጠጥ መጠጣት ኃጢአት ነውን ወይን መጠጣት ለምንድነው?

ብዙ ሰዎች ወደ መናፍቅነት ወደ ልዩ ልዩ ኃጢአት ልባቸው
ወደ ፈለገው የሚሄደው መጽሐፍ ቅዱስን እንዳለ ጥሬ ንባብ
በመውሰድ ለተለያዩ ተግባሮች ሲያውሏቸው ይታያሉ።
አንዳንዶች በራሳቸው ጥፋት ያልበደላቸውን ሲሰድቡ ምክንያት
ሲያረጉ ይታያሉ ነገር ግን እነዚህ እና ሌሎቹም ችግሮች ተራ
ግለሰቦች የሚፈጥሩአቸው ችግሮች እንጂ የቤተክርስቲያኒቱ
የቀኖና ችግሮች አይደሉም ሊሆኑም አይችሉም ሃይማኖት
ሌላ ግለሰብ (ነጻ ፈቃድን የሚፈጽም) ሌላ ሀይማኖቱ
የሚፈቅደውን ሳያውቁ ሳይተገብሩ ነበርኩበት ማለት አላዋቂ
ሳሚነት ነው።

የመጀመሪያው "ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል ዘይትም ፊትን ያበራል እህልም ጉልበትን ያጠነክራል።" /መዝ.103፥15/ ከዚህ ጥቅስ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስም ብዙ ስፍራ የወይን ጠጅን ሲያነሳ ይገኛል። /መዝ.4፥7 መክ.10፥19/

ወይን አስቀድሞ በነቢያት ኋላም በጌታችን እና በሐዋርያት ትምህርት ውስጥ በምሳሌነት ከመቅረቡም በላይ የሚሰጠውን ጥቅም (መዝ.103፥15)፣ እንዴት መጠቀም እንዳለብን (1 ጢሞ.5፥23) ተጠቅሶ እናገኛለን። በተለይም ከእስራኤላውያን ጋር ሰፊ ግንኙነት ነበረው። እነርሱም በሦስት ዋና ዋና ነገሮች ይጠቀሙበት ነበር።

1፦ ብርድን ለማራቅ (የሰውነታቸው ሙቀት ለመጠበቅ)

2፦ ለንግድ (በመሸጥ ገቢ ለማግኘት)

3፦ ለቤተ እግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረቢያ ናቸው።

ዛሬም ሰዎች ወይንን ለተለያዩ ነገሮች የሚጠቀሙበት ሲሆን ከእነዚህም መሀከል አንዱ ለመጠጥ ነው። ቅድስት ቤተክርስቲያን ወይን ይጠጣ አይጠጣ ለሚለው ሀሳብ የምትሰጠውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ እንሆ፦

ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል። የሚለው ነፍስ በኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔርን ፀጋ ስላጣች ደሃ ሆና ነበር።

ወይን_የተባለው_ደመ_ክር ስቶስ የነፍስን ኃዘኗን ያስረሳታል መከራዋን ያዘነጋታል ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ያድናታል

መንፈሳዊ ደስታን ይሰጣታል ማለት ነው። እህል የሰውን
ሓይል ያጸናል ማለቱ ለጊዜው ሰው ያለምግብ ያለመጠጥ
ጉልበት አያገኝም ቢባልም ዋናው ግን የእግዚአብሔር ቃልና
የእግዚአብሔር ወልድ ሥጋው ነው። የክርስቶስ ስጋ መቀበል
የነፍስ ኃይል ያጸናል። በሃይማኖት በገድል በትሩፋት ያጸናል
ማለት ነው ሥጋዊ ምግብና መጠጥ ቢፈቀድም አብዝቶ
ከተጠቀሙ ይጎዳል። መጠጥ አብዝተው ቢጠጡት ያሰክራል።
(ኃጢአትም ይሆናል) እህልም ቢበዛ ቁንጣን ያመጣል
ፈትወት ይቀሰቅሳል ከእግዚአብሔር ጸጋ ይለያል። በመጽሐፍ
ቅዱስ ውስጥ ከምናገኛቸው አበው መሀከል መስፍኑ ሶምሶን፣
ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ የወይን ጠጅ፣ የሚያሰክርም መጠጥ
ከአፋቸው ፈጽመው እንደማያቀርቡ (እንደማይቀምሱ)
ተመዝግቦልን እናገኛለን። (ሳሙ.13÷1-5, ሉቃ.1÷15)።
ዛሬም ባህታውያን ወይን እንደማይጠጡ ይተወቃል።
ከምዕመናም ወገን ይህንን አብነት አድርገው መላ
ዘመናቸውን ከውኃ በስተቀር ሌላ መጠጥ የማይጠጡ አሉ።
ይህ በጎ ምግባር ነው ነገር ግን ወይን የማይጠጡት ወይን
መጠጣት ኃጢአት ነው በሚል ሀሳብ ወይም ሥርዓት ባለው
መንገድ የሚጠጡትን በመንቀፍ ሊሆን አይገባም። ለምሳሌ፦
ሰዎች ምንኩስናን ሲመርጡ ጋብቻን አቃለው እንደ ርኩስ
ቆጥረው ሊሆን አይገባም።
ሌላው በመጽሐፍ ምሳሌ ላይ 31÷6-7 እንዲህ ይላል።

"ላዘኑ ሰዎች ወይን ስጧቸው ሀዘንን ይዘነጓት ዘንድ መከራንም ከእንግዲህ ወዲህ እንዳያስቡ ወይን ይጠጡ" ያዘኑ የተባሉት ኃጢአት በመስራታቸው ተጸጽተው ለመምህረ ንስሐቸው እንባቸውን እያፈሰሱ እያዘኑ በደላቸውን ለሚናገሩ ሰዎች ነው። ንስሐቸውን ከጨረሱ በኋላ ካህናት ለእነርሱ ደስ የሚያሰኛቸውን ሀዘናቸውን መከራቸውን የሚያስረሳቸውን አይን የተባለ ደግሞ የክርስቶስን ሥጋና ደሙን ስጧቸው ሀዘንን ይዘነጓት ዘንድ መከራንም ከእንግዲህ ወዲህ እንዳያስቡ ማለት ነው። የእዚህ ዓለም ወይን ጠጅ ጊዜያዊ ደስታን ይሰጣል። ኋላ ግን ደዌ ይሆናል። ሰው በሲዖል ከሚያገኘው በኃጢአት ከሚመጣበት ፍዳ ሀዘን ለመዳን በንስሐ ወደ ሥጋወደሙ በመቅረብ ፍጹም ተድላ ደስታ የሚያገኝ መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

ወይን መጠጣት ኃጢአት ነው እንዳንል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዶኪማስ ሠርግ ቤት ውኃውን ወደ ወይን ከመለወጡም በላይ ወይን ጠጥቷል ስለዚህ ነገር "ማንም ያስገደደው ሳይኖር በፈቃዱ ጠጣ" በማለት በሃ.አበው ላይ ገልጾልናል። በግብጽ ገዳማት ያሉ መነኮሳትም ወይንን መጠጣት ኃጢአት አለመሆኑን ለማስረዳት በዓመት አንድ ቀን ወይንን ይጠጣሉ። ቅዱስ ዳዊትም "ወይን የሰውን ልቡና ያስደስታል" /መዝ.103÷15/ ሲለን ልጁ ጠቢቡ ሰለሞንም "ነፍሱ ለመረረውም የወይን ጠጅ ስጡት ይጠጣ ድህነቱንም

ይርሳ፤ ጉስቁልናውንም ከእንግዲህ አያስብ።" /
ምሳ.31፥7-8/ ብሏል። ቅዱስ ጳውሎስም ለደቀመዝሙሩ
ለጢሞቴዎስ "ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን
ጠጅ ጠጣ እንጂ ወደ ፊት ውኃ ብቻ
አትጠጣ።" /1 ጢሞ.5፥23/ ብሎታል። ከላይ በተገለጸው
ወይን አለመጠጣት የተሻለ ሲሆን ይህን መጠበቅ ያለተቻለው
ግን ለኃጢአት በማያደርሰው መጠን ቢጠጣ አይከለከልም።
ይህ ሲባል ግን ሰው አልሰከርኩም ብሎ ብዙ መጠጣት
አይፈቀድለትም። ሰው አብዝቶ ከመጠጣቱ የተነሳ በተለያዩ
ኃጢአቶች ይማረካል ጠቢቡ ሰለሞንም "ዋይታ ለማነው?
ጎዘን ለማን ነው? ጠብ ለማን ነው? ጩኸት ለማን ነው? ያለ
ምክንያት መቁሰል ለማን ነው? የዓይን ቅላት ለማን ነው?
የወይን ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን? የተደባለቀ
የወይንን ጠጅ ይፈተኑ ዘንድ ለሚከተሉ አይደለምን? ወደ
ወይን ጠጅ አትመልከት በቀላ ጊዜ መልኩን በብርሌ
ባንጸባረቀ ጊዜ፥ እየጣፈጠም በገባም ጊዜ። በኋላ እንደ እባብ
ይነድፋል፥ እንደ እፉኝትም መርዙን ያፈስሳል። ዓይኖችህ
ጋለሞታዎችን ያያሉ፥ ልብህም ጠማማ ነገርን ይናገራል።
በባህር ውስጥ እንደ ተኛ ትሆናለህ። በደቀልም ላይ እንደ
ተኛ። መቱኝ፥ ያውም አልተሰማኝም ጎሰሙኝ፥
አላወቅሁምም። መቼ እነሳለሁ? ደግሞ ጨምሬ እሻታለሁ
ትላለህ።" /ምሳ.23፥29-35/ እንዲል ሰው አብዝቶ በጠጣ

ጊዜ አእምሮውን ያጣል ስለዚህ ከላይ እንዳየነው የመጽሐፍ
ቅዱስ ጥቅሶች ስለ ወይን ጠጅ ቢናገሩም ምስጢራቸው
ሥጋወደሙን የሚመለከት እንደሆነ ግልጽ ይመስለኛል።
አስተዋይ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉትን ሐይለ ቃል
ፍቻቸውን ማስረጃዎች ብቻ በመመልከት መጽሐፉ መጠጥ
መጠጣትን ያይደለ ስካርን እንደሚያወግዝ ልብ ሊል ይገባል።
"ስካር የስጋ ሥራ ነው" /ገላ.5፥19/ ስለ ስካር ቅዱስ ዮሐንስ
አፈወርቅ እንደተናገረው ልብስን የሚያስጥል <<የፈቃድ
እብደት>> ነው /ዘፍ.9፥21/ ስካር በማወቅ የሚደረግ ጥፋት
በመሆኑ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅጣት ያመጣል። የስካር
መዘዝ በምድር ብቻ አይወሰንም ንስሐ ካልገቡና ካልታረሙ
"ሰካራሞች የእግዚአብሔርን መንግሥት
አይወርሱም።" /1 ቆሮ.6፥10/ ከዚህ በላይ የስካር ጉዳት
ከየት ይመጣል። ወዴ ለሰካራሞች ወዮታ ይገባል። /
ኢሳ.28፥1-8 ፣ ምሳ.23፥29 ፣ ኢዮ.1፥5/
አብዝቶ መጠጣት ሱሰኛ ይልደርጋል ሱስ ደግሞ ኃጢአት
ነው። /ዮሐ.8፥34/ "ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባርያ
ነው" ይላል በመጠጥ ሱስ የተሸነፈ የስካር ባርያ ነው።
በክርስቶስ ደም ነጻ የወጣ ክርስቲያን ግን እንኳን ለመጠጥ
ለምንም ነገር ቢሆን ተገዥ መሆን የለበትም። ሰው በሁለት
ጌታ መገዛት አለመቻሉ ግልጽ ነው /ማቴ.6፥24/ ለመጠጥ
የሚገዛ ሰው ለእግዚአብሔር ሊገዛ እንዴት ይችላል ማለትም

ለመጾም፣ ለመጸለይ፣ ለመስገድ፣ ለመመጽወት፣ መንፈሳዊ
በዓላትን ለማክበር ወደ ቤተ ክርስቲያን መሔድ የመሳሰሉትን
ማከናወን እንዴት ይችላል? የመጠጥ ሱስ ፈተና ነውና
በደስታና በመከፋት ሰዓት ወደ መጠጥ አትይ ተጠንቅቄ
አደርገዋለው አትበል። ስካር በራሱ ኃጢአት ነውና። ሰው
እየኝ አላየኝ እያልክም ተደብቀህ አትጠጣ ሰው ባያይህ
እግዚአብሔር ያይኃልና!።
በመጨረሻም ስለ መጠጥ በምታስብበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ
"እንግዲህ እንዲህ የምትሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ
ወይም ማናቸውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉ ለእግዚአብሔር
ክብር አድርጉ" በማለት የተንልገረውን ቃል አስብና
መመሪያህ አድርገው ከሱስም ነጻ ትሆናለህ ሰዎችም
የሚነግሩህን መልካም ምክር ስማ ጠጣ ጠጣ ከሚሉህ ሰዎች
መጠጥ ይቅርብህ የሚሉህን አክብር! ክርስቲያኖች ሁላችን
ይዘለዓለም መጠጥ የዘለዓለም ምግብ የሚሆን ሥጋወደሙ
በመቀበል በንስሐ ነፍሳችንን እናድሳት ሕይወታችንን
እንጠብቅ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን። ቃሉን
በልቦናችን ያሳድርብን ትእዛዙን ጠብቀን መንግሥቱን
ለመውረስ ያብቃን አሜን!
ወሥብሐት ለእግዚአብሔር!!!

ይድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ

66/ "የግእዝን ያህል ጥንታዊ ቋንቋ የለም።" አለኝ በውቄ ከዝምታ መልስ።

"ለምሳሌ ሰው የሚለውን ቃል ውሰጂ፤ በግዕዝ ሰው ሰብዕ ይባላል። ሰብዕ ማለት ሰባት፣ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ መፈጠሩን ለማጠየቅ የተሰጠው ስያሜ ነው።"

"እና?!"

"በዚህ ውስጥ ምንም ምስጢር አይታይሽም?"

"ኧኧ..." አልኩት አንገቴን እየሰበቅሁ፣ እንዲቀጥል ፈልጌያለሁ።

"ዐዬሽ አባቶቻችን በቋንቋ ከመግባባታቸው በፊት መቁጠር ጀምረዋል፤ በቋንቋ ከመግባባታቸው በፊት መፈላሰፍ ጀምረዋል። ልብ በይ ከሥነ ጽሑፍ በፊት አይደለም፤ ከቋንቋ በፊት ነው። አይገርምም?!"

"ቁጥርና ፍልስፍና ከቋንቋ ቀድመዋል? እንዴት ሊሆን ይችላል? ለመቁጠርና ለመፈላሰፍ መጀመሪያ ሐሳብን በቋንቋ መወከል ያስፈልጋል።" አልኩት።

"ምናልባት ስያሜው የተሰጠን በሌላ አካል ነው። እንደዛ ከሆነ ስያሜውን የሰጠን አካል ሰው አይደለም። ምናልባት ፈጣሪ...? ወይ ደግሞ የሆኑ 'ኤሊያንስ' ሊሆኑ ይችላሉ። ኧረ... ሌላ ምሳሌ

ልስጥሽ፤ ገብርኤል በሁሉም ቋንቋዎች ገብርኤል ነው።
እግዚአብሔር ሰው ሆነ፣ ሰውም እግዚአብሔር ሆነ ማለት ነው።
በጥሬ ትርጉሙ ስንሄድ ገብረ–ኤል ሠራ፣ሆነ፣አደረገ–እግዚአ
ብሔር ማለት ነው። እግዚአብሔር ፍጡር ሆነ፣ እግዚአብሔር
ተአምር ሠራ የሚል ጥልቅ ፍልስፍናዊ ትርጉም ይሰጠናል።"
"ግን ለምንድነው ይህን የምታወራልኝ? ዙረህ ዙረህ ግእዝ
የመላእክት ቋንቋ ነው ልትለኝ ነው አይደል?!"
"አይደለም! እሱን አንቺ ’ራስሽ የምትወስኝው ጉዳይ ነው። የኔ
ነጥብ ከፍጥረተ አዳም ቀድመን የቋንቋ ባለቤት የነበርን፣
የተፈላሰፍንና የሠለጠንን ሰዎች፣ አሁን ላይ የብዙ ቋንቋዎች፣
ታሪኮችና ሥልጣኔዎች ጎብር መሆን ሲገባን፣ ያ ታላቅነታችን
ስንፍናችንን አጋልጦ በሰው ፊት እንዳያስነውረን በግእዝ ውስጥ
ደብቀነዋል። ደብቀነውም ዐይናችን በጨው አጥበን የኛ ያልሆነን
እንቀላውጣለን። በዚህ ምድር ስንኖር ለዚህች ዓለም ምን
አበረከትን ብለን ብናስብ፣ መልሱ ምንም ነው። ምንም ደግሞ
ይጨንቃል። ኢትዮጵያውያን ከዚህ ምድር ቢጠፉ የዓለም ሕዝብ
ምን ይጎድልበታል ብለሽ አስበሽ ታውቂያለሽ?" ጸጥ ብዬ
አዳምጠዋለሁ። እሱ ቀጠለ እቴ፣
"ቡናና ወርቅ እንዳትይኝ። ምክንያቱም እሱን የሚለቅም እየሸለለ
መምጣቱ አይቀርም። አትሌቶቻችን እንዳትይ ኢትዮጵያውያን
ስለማይሳተፉ ውድድሩ አይቀርም፣ መዝናናቱ አይቀርም። እና
ምን ልልሽ ፈልጌ መሰለሽ... እኔ ሀገር አይደለሁም፤ እኔ አንድ

ግለሰብ ነኝ። እንደ ግለሰብ ግን እኔ ስጠፋ ከዚህች ምድር አንድ ነገር የማጎድል እንድሆን እፈልጋለሁ።" ጸጥ አለ። ከዚህ በላይ እንዲያወራም አልፈለግሁም። መልእክቱ ደርሶኛል፤ በዚህ ሰዓት ላንሰላስለው ግን አልፈቀድሁም።

... ከነጻነት ዲያሪ የተወሰደ።

Daniel King and
56 others .

67/ ከነብዩ ዮናስ ምን እንማር??? ክፍል ሁለት

ዮናስ እግዚአብሔር ያዘዘውን ከመፈጸም ይልቅ ከፊቱ መሸሸን መረጠ ለእግዚአብሔር አልታዘዘምና በመንገዱ ላይ ፈተና ገጠመው፦

(((እግዚአብሔርም በባሕሩ ላይ ታላቅ ነፋስን አመጣ፥ በባሕርም ላይ ታላቅ ማዕበል ሆነ፥ መርከቢቱም ልትሰበር ቀረበች። ዮና. 1፡4)))

ዛሬም ለእግዚአብሔር አልታዘዝም ያልን ብዙ ነን፤ ህጉን የናቅን፤ መንገዱን የሳትን፤ ከጽድቅ የራቅን፤ በኃጢያት የተጨማለቅን እጅግ በርካቶች አለን። ስለኛ አመጸኝነትም ዓላማችን በከባድ መከራ ላይ ነች፤ ሀገራችንም ማዕበሉ እጅግ ከብዶባታል፤ ሁላችንን የረሀብ ማዕበል፤ የበሽታ ማዕበል፤ የትራፊክ አደጋ ማዕበል፤ የዘረኝነት ማዕበል፤ የሽብር ማዕበል..... እያናወጠን ነው።

ወደ ዮናስ እንመለስ ቁጥር 5 ላይ ደግሞ እንዲህ ይለናል፦

(((መርከበኞቹም ፈሩ፥ እያንዳንዱም ወደ አምላኩ ጮኸ፤ መርከቢቱም እንድትቀልልላቸው በውስጥዋ የነበረውን ዕቃ ወደ ባሕር ጣሉት፤ ዮናስ ግን ወደ መርከቡ ውስጠኛው ክፍል ወርዶ ነበር፥ በከባድ እንቅልፍም ተኝቶ ነበር።)))

ስለእኛ ክፋት የእግዚአብሔር ቁጣ በነደደ ጊዜ ብዙዎች በመከራ ይወድቃሉ እኛ ግን በሰላም እናንቀላፋለን፤ ለእኛ ችግር ብዙዎች መፍትሄ ለመፈለግ ይደክማሉ እኛ ግን ተኝተናል።

ዮናስ ከእንቅልፉ በቀሰቀሱት ጊዜ ያደረገውን ሁሉ ነገራቸው፤ ለእግዚአብሔር አልታዘዝ ብሎ እየኮበለለ እንደሆነና ይህ ሁሉ መከራ በሱ ምክንያት እንደሆነባቸው አመነ፡-

(((ይህ ታላቅ ማዕበል በእኔ ምክንያት እንዳገኛችሁ አውቃለሁና አንሥታችሁ ወደ ባሕር ጣሉኝ፥ ባሕሩም ጸጥ ይልላችኋል አላቸው። ዮና. 1፡12)))

ዮናስ ማዕበሉ የመጣው በእኔ ምክንያት ነው አለ።

ወደ ራሳችን እንመልከት

እስቲ እናስተውል ለሚፈጠሩት ችግሮች፤ እየደረሰብን ላለው መከራ ሁሉ ጣታችንን ሌሎች ላይ መጠቆማችን ይብቃ እኛም ከነብዩ ዮናስ እንማርና ራሳችንን እንመልከት፡-

ሀገራችን በረከት የራቃት፤ የዝናብ ዕጥረት የገጠማት፤ የረሀብ አለንጋ የሚገርፋት በእኛ ምክንያት ነው እንበል፤

በሽታው የበረታብን ስለእኛ ኃጢያት ነው እንበል፤

የትራፊክ አደጋው አስከፊነት በእኛ አለመታዘዝ የመጣ ነው እንበል፤

ዘረኝነት የተንሰራፋብን እርስ በርስ የሚያጫርሰን የእኛ ክፋት ነው እንበል፤ መከራው የከበደብን ስለኛ በደል ነው እንበል፤

እየሆነብን ያለው ሁሉ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ባለማክበራችን ቁጣው እየነደደብን ነው እንበል

ቃሉም ስለ መታዘዝ እንዲህ ነው የሚለው፡-

(((እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ፥ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እንቢ ብትሉ ግን ብታምፁም፥ ሰይፍ ይበላችኋል፤ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና። ኢሳ. 1፡19-20)))

ወደራሳችን ከተመለከትን፤ ችግራችን ምን እንደሆነ እናውቃለን፤ ድክመታችንን ከተረዳን መፍትሄውንም ከራሳችን ጀምረን መፈለግ እንጀምራለንና ችግሩን ለመፍታት ቀላል ይሆንልናል።

ወደራሳችን በመመልከት ካለንበት የኃጢያትና የክፋት መንገድ እንድንወጣ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!!!

ገኒ የማሪያም ልጅ

☞አንብበው ካልጨረሱት አይጀምሩት!!! ከጨረሱት ለጓደኛወ ያካፍሉት!!

ስለ አዳምና ሄዋን ጥያቄ ከነ መልሱ

68/ 1/ እግዚአብሔር አዳምን ከፍጥረታት መጨረሻ ለምን ፈጠረው?

2/ እግዚአብሔር ሌሎችን ፍጥረታት አስጎንብሶ ሲፈጥራቸው አዳምን አቅንቶ ለምን ፈጠረው?

3/ እግዚአብሔር አዳምን ለሚቆም ፣የሚተኛ አድርጎ ለምን ፈጠረው?

4/ እግዚአብሔር ለአዳም ስንት ሀብታትን ሰጠው? ምንምን ናቸው?

5/ እግዚአብሔር ሄዋንን ከአዳም ከጎኑ አጥንት ለምን ፈጠራት ? ከግንባር ወይም ከ እግር ለምን አልፈጠራትም?

6/ በገነት ውስጥ ስንት አይነት ዛፎች ነበሩ?

7/አዳምና ሄዋን የእግዚአብሔርን ህግ በማክበር በገነት ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ቆዩ?

8/ አዳምና ሄዋንን በእባቤቱ ላይ አድሮ ያሳታቸው ሰይጣን ስም ማን ይባላል?

9/አዳምና ሄዋን ስንት ልጆች ነበራቸው ?

10/ አዳም በተፈጠረ በስንት አመቱ አረፈ?

አዳም ማለት ከመሬት የተፈጠረ ያማረ መልከ መልካም ማለት ሲሆን የተፈጠረው ከአራት ባህርያተ ስጋ ማለትም ከነፋስ፣ከእሳት ፣ከውሀ፣ከመሬት እንድሁም ከሶስቱ ባህርያተ ነፍስ ማለትም ከልብ ፣ከቃል፣ከእስትፋስ

የስነ ፍጥረት መካተቻ በሆነች በእለተ አርብ በ 3 ስዓተከሀቱም ምድር ሚያዝያ 4 ቀን በምድር መካከል በምትገኘው <ኤልዳ> በተባለች ስፍራ

የ 30 አመት ጎልማሳ ሁኖ በእግዚአብሔር አርአያነት መልክ ተፈጠረ።

ኦሪት ዘፍጥረት 1፣27 ፣ኩፋሌ 5፣6

መልስ ፡-

1/አዳም ከፍጥረታት መጨረሻ ለምን ተፈጠረ?

☞መጨረሻ የተፈጠረበት ምክንያት እግዚአብሔር አምላካችን "በጎ አምላክ" ስለሆነ በጎ አባት ለልጁ አብሮት ከብት ያረባለታል ፣ጥማጅ ያጠምድለታል፣ የኑሮ ጓደኛ ያመጣለታል አስቀድሞየሚበላው፣የሚጠጣው፣የሚገዛውና የሚነዳውን ፈጥሮለት በመጨረሻም በሁሉ ላይ ሊያሰለጥነው አዳምን ፈጠረው።

2/ ሌሎችን ፍጥረታት አስጎንብሶ ሲፈጥራቸው አዳምን ለምን አቅንቶ ፈጠረው?

☞ እሱ ገዥ እናተ ተገዥ ናችሁ ሲል ነወ፣እንድሁም እናተ ፈርሳችሁ በሰብሳላችሁ ትቀራላችሁ እሱ ግን" ትንሳኤ ሙታን " አለው ሲል አቅንቶ ፈጠረው።

3/ አዳምን የሚቆም የሚተኛ አድርጎ ለምን ፈጠረው?

☞ መቆሙ- ሰማያዊ ፣

☞መቀመጡ- ምድራዊ ነህ ሲለው ነው፣

☞የሚተኛ ፣ የሚነሳ አድርጎ መፍጠሩ ደግሞ ☞መተኛቱ- ሞቱን

☞መነሳቱ - ትንሳኤውን ሲነግረው ነው።

4/ እግዚአብሔር አምላክ ለአዳም ስንት ሀብታት ሰጠው? ምን ምን?

☞ሰባት ሀብታትን የሰጠው ሲሆን እነሱም፡-

❶ሀብተ መንግስት (የማስተዳደር ሀብት

❷ ሀብተ ክህነት (የመቀደስ፣የመባረክ፣መስዋዕት የማቅረብ

❸ ሀብተ ትንቢት (የመጣውን የመናገር

❹ ሀብተ መዋኢ (የማሸነፍ

❺ ሀብተ ሀይል (የጥንካሬ

❻ ሀብተ ፈውስ (የመዳን ፣የመፈወስ

❼ ሀብተ ዝምሬ (የመዝሙር

5/ ሄዋን ከአዳም ከጎኑ አጥንት ወስዶ ለምን ተሰራች?ከግንባር ወይም ከእግር ለምን አልሰራትም?

☞ አዳም ለእንሰሳት፣ለሰማይ ወፎች ና ለምድር አራዊቶች ሁሉ ተባእትና እንስት ሁነው ሲመጡ ስም ያወጣላቸው ነበር።ነገር ግን ለአዳም እንደ ራሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር ።

"እግዚአብሔርም " ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት ልፍጥርለት አለ ።ኦዘፍ 2፣18

ከዚያም በአዳም ላይ እንቅልፍ አመጣበትና ፈፅሞ ሳይተኛ ፣ፈፅሞ ሳይነቃ ከጎኑ አጥንት አንስት አንስቶ ያችን ስጋ አልብሶ የ15 አመት ቆንጆ አድርጎ ፈጠራት ፣ኦዘፍ 2፣18

አዳምም ስሟንም "ሄዋን" አላት ፣ሄዋን ማለት "ህያው" ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም" የህያዋን ሁሉ እናት "ማለት ነው።

ፈፅሞ ሳይተኛ ፣ፈፅሞ ሳይነቃ ሄዋንን መፍጠሩ

☞ፈፅሞ ተኝቶ ቢሆን ኑሮ ምትሀት መስሎት ከየት መጣች ብሎ ይፈራታል

☞ፈፅሞ ነቅቶ ቢሆን ኑሮ ከአካሉ አጥንት ሲነሳለት ያመው ነበርና ይጠላት ነበር ።

☞ከፍ አድርጎ ከግባር ዝቅ አድርጎ ከእግር ያልሰራት ግባርና እግር በልብስ አይሸፈንም ጎኑ ግን በልብስ ይሸፈናልና ተሰውራ ወይም ተሸፍና መኖር ይገባታል ሲል ነው።

በሌላ በኩል ግንባር የባለቤት እግር፣ የቤተሰብ ምሳሌ ነው ፡እሷም ከባለቤቷ በስተቃኞ ከቤተሰብ በላይ ሁና ትኑር ሲል ነው ። 1ኛ ቆሮ 12፣19-22

እንድህ አድርጎ አዳምና ሄዋንን እስከ 40 ቀን ድረስ በተፈጠሩበት በማዕለ ምድር በቀራንዮ አስናበታቸው

ጌታችን አምላካችንና መድሀኒታችን እየሱስ ክርስቶስ የሚሰቀልበት ቦታ ነውና ከዛም በ40ኛው ቀን አዳምን ብርሃን አልብሰው ፣ብርሀን አጎናፀፈው፣የብርሀን ዘውድ አቀናጅተው በብርሃን ሰረገላ አስቀምጠው ወደ ገነት አስገቡት።

ሄዋንንም በ80 ቀኗ እንደ አዳም ባለ ክብር ወደ ገነት አስገቧት ።ኩፋሌ ፈ 4፣12-15

አዳምና ሄዋን ከእግዚአብሔር የባህሪ ደግነት የተነሳ እርሱን ለማመስገንና ክብሩን ለመውረስ ተፈጠሩ። ኩፋሌ 4 ፣3-5

እግዚአብሔር ለአዳም ረዳት የፈጠረለት ስለ ሶስት ነገሮች ሲል ነው።

❶ዘርን ለማብዛት

❷ ከዝሙት እንድፀዳና

❸ረዳት እንድትሆነው ነው

6/ በገነት ውስጥ 3 አይነት ዛፎች ነበሩ

❶ ዕፀ መብል -እንድበሉት የተፈቀደላቸው ምግብ ነው

❷ዕፀ በለስ-እንዳይበሉ የታዘዙት ነው

❸ዕፀ ህይወት - እንደ <እግዚአብሔር > ፈቃድ የሚመገቡት የዘለዓለም ህይወት የሚሰጥ ምግብ ነው።

ህግን ጠብቀው በገነት ውስጥ 1000 አመት ከኖሩ ብኃላ እፀ ህይወት በልተው ከገነት ወደ ሰማያዊ እየሩሳሌም (መንግስተ ሰማይ) እንድገቡ ለበለጠ ክብርና ፀጋ ሽልማት እንድሎናቸው ነበር። ነገር ግን ያለ ጊዜው ሳቱ እንጅ

'እፀ በለስ ' እንዳይበሉ የታዘዙበት ህግ አዳም ፈጣሪ እንዳለው ፣ለፈጣሪው ያለውን ፍቅር የሚገልፅበትና ተገዥነቱን የሚያሳይበት ነው።

7/ አዳምና ሄዋን የእግዚአብሔርን ህግ በማክበር በገነት ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ቆዩ?

☞አዳምና ሄዋን ይህን ህግ በማክበር በገነት ውስጥ ለ 70 አመት ከ 2 ወር ከ 17 ቀን ኖሩ።

8/ አዳምና ሄዋንን በእባብ ላይ አድሮ ያሳታቸው ሰይጣን ስም ማን ይባላል ?

☞አዳም በሳጥናኤል ተተክቶ መቶኛ ሁኖ ከመላእክት ጋር ተቆጥሮ ነበር ሰይጣንም በእባብ አድሮ አሳቻቸው ጽድቃቸውም ተገፈፈ አዳምና ሄዋንን በእባብ ላይ አድሮ ያሳታቸው ሰይጣን ስም ' ጋርድኤል ይባላል።

በመሆኑም አትብሉ የተባሉትን እፀ በለስ ህጉን አፈረሱ ከገነት ተባረሩ ፡ ኦዘፍ 3፣1 ኦዘፍ 3 ፣22-24

9/ አዳምና ሄዋን ስንት ልጆች ነበራቸው?

☞ ከገነት ከተባረሩ ብኃላ በደብረ ቅድስት ይኖሩ ነበር፣

አዳምና ሄዋን በሰሩት ሀጢያት በመፀፀታቸውና በንሰሀ በመመለሳቸው

"እግዚአብሔር" መሀሪ ነውና 5 ቀን ተኩል ወይም 5500 ዘመን ሲፈፀም ሰው ሁኖ በመወለድ እንደሚያድናቸው ቃል ኪዳን ገባላቻው ።።
ኦዘፍ 3፣15-22
አዳም ግን የራሱን ደም በስንደ ለውሶ ሲሰዋ ጌታችን በአንተ ደም አይደለም አለም የሚድነው በእኔ ነው ብሎ ተስፋ ሰጠው።።
አዳምና ሄዋንም በምድር ላይ ዘርን ተክተዋል ገብርኤል ፣ሚካኤል ፣ሩፋኤል ወርቅ ,እጣን,ከርቤ አምጥተው ለአዳም ሲሰጡት ወርቁን ማጫ ይሁንሽ ብሎ ሰጣት ከዛም አዳምና ሄዋን በ 30 ሩካቤ 60 ልጆችን ወልደዋል
10/ አዳም በተፈጠረ በስንት አመቱ አረፈ?
☞ አዳም በተፈጠረ በ930 አመቱ አረፉ ፡አዳም ለሄዋን የሰጣት ወርቅ ለሴት ሰጠችው ሴትም ለኖህ አስተላለፈው እጣኑንም ኖህ አፅመ አዳም እያጠነ ድኖበታል ።።
በአዳም ስም በሀገራችን የተሰሩ ቤተክርስቲያኖች ብዛታቸው 5 ናቸው
በአዳም ስም የተቀረፀው ታቦት ከሶሪያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ያመጣው ፃድቅ አባት 'መልከአ እግዚአብሔር ' ይባላል።።እንድከበር ያደረገው ቅዱስና ሊቁ ያሬድ ማህሌት ነው።።
----------ምንጭ----------
መፅሀፈ ኩፋሌ
ኦሪት ዘፍጥረት
ዜና አዳም
ገድለ አዳም

ዜና አበው

ቅዱሳን ታሪክ

ለአባ ህርያቆብ ፣ለቅዱስ ኤፍሬም ፣ለቅዱስ ያሬድ፣ለአባ ጊወርጊስ ዘጋስጫ የተገለፀች እመቤታችን እኛንም በበረከትና በረድኤት ተጎብኘን ከልጇ ከወዳጇ ከመድሀኒታችን ከእየሱስ ክርስቶስ ጋር ታማልደን አሜን

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለ ወላድቱ ድንግል

ወለ መስቀሉ ክብር

አሜን

Jimma Maekel Abalat Guday

69/ ‹እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ› ዘዳ 30፥19

በዲ/ን ሄኖክ ኃይሌ

አምላካችን እግዚአብሔር በሥልጣኑ ገደብ የሌለበት ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ነው። ከሥልጣኑ ማምለጥ የሚችልም የለም፤ ሁሉ በእርሱ መግቦት፣ ጥበቃና እይታ ሥር ነው። በምድር ላይ ያሉ ባለሥልጣናት ሥልጣናቸው በድንበር፤ በጊዜ፤ በሕግ የተገደበ ነው። እንዲህም ሆኖ በቦታና በጊዜ የተገደበ ሥልጣናቸውን ያለገደብ ለመጠቀም ይሞክራሉ።

ሥልጣናቸውና ኃይላቸው የፈቀደላቸውን ያህል ጎብረተሰቡን እንደ ሰም አቅልጠው፤ እንደገል ቀጥቅጠው በግርፋት፣ በቅጣት፣ እየተጠቀሙ ልክ ሊያስገቡት ያም ባይሆን ሊያዳክሙት መሞከራቸው የምድራዊ ገዢዎች ጠባይ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስና በታሪክ የምንረዳው ሀቅ ነው። እግዚአብሔር ግን ገደብ የሌለው ሥልጣኑን በራሱ መግቦት ቸርነት፣ ምሕረት ገድቦ ሁሉን የሚያኖር አምላክ ነው።

የሰው ልጅን ታሪክ ስንመረምርም ይህን እውነት መረዳት እንችላለን። አዳም የእግዚአብሔርን ሥልጣን (አምላክነትን) ሽቶ በዲያብሎስ ምክር ሕገ እግዚአብሔርን በጣሰ ጊዜ እግዚአብሔር ‹ሥልጣኔን ልትጋፋ አሰብህን? ብሎ በአዳም የፈረደበትን ፍርድ በራሱ ላይ አድርጎ ለመቀበል የፈጠረውን ሥጋ ተዋሕዶ በመከራው፣ በሞቱ አድኖታል። ይህም እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በግድ ሳይሆን በነፃነት የሚገዛ አምላክ መሆኑን ያስረዳል። ከአዳምም በኋላ የሰው ልጆች እርሱን ከማምለክ ወደኋላ ሲሉና ለፍቅር አገዛዙ ሊመለስ የማይገባ ያለመታዘዝና የአመጽ አጸፋን ሲመልሱ የነጻነት እርምጃውን አልተወም። ሰውን ሁሉ እርሱን ወደ ማምለክና ለእርሱ ብቻ መገዛት የሚችልበት ችሎታ ሲኖረው ‹እሳትና ውኃን አቀረብኩልህ ወደ ወደድኸው እጅህን ስደድ› የሚል የነፃነት ጥሪን ከማቅረብ በቀር ምንም አላደረገም። ዛሬም ድረስ “እግዚአብሔር የለም” እስከማለት፤ በእርሱ ላይ እስከማፌዝና እስከመዘበት የሚደርሱ ብዙዎችን እየተመለከተ ዝም ማለቱ ማንም ሰው በፍላጎቱ ብቻ እርሱን እንዲመርጥ ስለሚፈልግ ነው። ‹ወደ እኔ ኑ! ወደ እኔ ቅረቡ› እያለ መጣራቱን ወደንና መርጠን በፈቃደኝነት ወደ እርሱ እንድንሄድ፤ ነፃነታችን ላለመንፈግ እንጂ

እኛን ወደ እርሱ ማቅረብ ተስኖት የሚያደርገው የልምምጥ ጥሪ አይደለም። ይህን ሁኔታም አሁን ከምንረዳው በላይ በእግዚአብሔር ፊት በሞት እጅ ተይዘን በምንቀርብበት ጊዜ በይበልጥ የምንረዳው ነው።

አንባብያን ሆይ! እግዚአብሔር አባታችን አዳምን በገነት ሳለ ዕፀ በለስን እንዳይበላ መከልከሉ ከሞላ ዛፍና ፍሬ አንዲት ዕፅ ተበልታ እርሱ የሚጎድልበት ሆኖ ነው? ወይስ ዲያቢሎስ ለሔዋን እንደነገራት አምላክ እንዳይሆን ነው? እንዲህ እንዳንል ደግሞ አዳም ዕፅዋን ሲበላ እንኳን አምላክነት ሊጨመርለት የነበረው ፀጋ ተገፍፎ ዕርቃኑን ቀርቶአል። ታዲያ ለእግዚአብሔር አንዲት ቅጠል ምን ልትረባው ነው አትብላ ብሎ የከለከለው? በንባብና በትምህርት ከምንደርስባቸው በርካታ ምክንያቶች በተጨማሪ የአዳም ነጻ ፈቃድ እንዲታወቅ ነው።

እግዚአብሔር ለአዳም ያለውን ፍቅር በመፍጠር፤ ሁሉን በመስጠት ከገለጠ አዳም ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅርስ በምን መለካት ይቻላል? አዳም ለእግዚአብሔር ሊሰጠው የሚችለው እግዚአብሔር ከሰጠው ነገር ሌላ አዲስ ነገር ምን አለ? ምንም የለም! አዳም ለአምላኩ ያለውን ፍቅር የሚገልጠው በምንም ቁስ አይደለም የመታዘዝና ያለመታዘዝ ነጻ ፈቃዱን ለእግዚአብሔር በመስጠት (በመታዘዝ) ብቻ ነበር። ዕፀ በለስም የዚህ ነጻ ፈቃድ መመዘኛ ነበረች። አዳም ግን ነጻ ፈቃዱን ለእግዚአብሔር ሊሰጥ አልፈቀደም። በነጻነት ከሚገዛው ፈጣሪ ይልቅ ረግጦ የሚገዛውን የዲያብሎስን አገዛዝ መረጠ።

አንዳንዶች ‹ፈጣሪ የሰው ልጅ ኃጢአተኛ እንደሚሆን እያወቀ፤ እያየ ለምን ኃጢአት እንዳይሠራ አላደረገውም? ይላሉ። ይሁንና እግዚአብሔር የሰውን

ልጅ ነጻ ፈቃድ የማይነካ የነጻነት ገዢ ነው። ደግሞም ሰው በበጎው መንገድ ብቻ እንዲሔድ ቢያስገድደው ኖሮ ‹ነጻነቴን ተነፈግሁ› ባለ ነበር። እንኳን ዕድሜያችንን ሙሉ በመንፈሳዊው አኗኗር ለመኖር በዕለተ ሰንበት በቤተ ክርስቲያን መጥተን ሥርዓተ ቅዳሴ እስከሚጠናቀቅ ለመታገስ ፈቃደኛ ያልሆንን ብዙዎች ነን።

ወደ ሲኦል ወይንም ወደ ገነት መግባታችን የነጻነት አገዛዙ አካል ነው። አንዳንዴ ‹እግዚአብሔር እንዴት ሰው ወደ ሲኦል እንዲገባ ያደርጋል? ለምን ይጨክናል?› ብለን ባላወቅነው ልንፈርድ እንችላለን። እግዚአብሔር በምድር ሳለን ‹ይህን ብትፈጽሙና ብታደርጉ ገነትን ትወርሳላችሁ፤ ይህንን ብታደርጉ ደግሞ ሲኦል ትገባላችሁ ብሎ ሁለት አማራጮችን ሰጥቶናል። የምንመርጠው መንገድ የምንወርሰው ርስት ምን እንደሆነ ይወስነዋል። እግዚአብሔር ሁሉም ሰው ቢድን (ወደ ገነት ቢገባ) የሚወድ አምላክ መሆኑን ራሱ በቃሉ ተናግሯል። ይሁንና በምድር ሳሉ ሲኦል ለመግባት የሚያበቃቸውን መንገድ የመረጡ ሰዎችን ግን ከምርጫቸው ለይቶ ወደ ገነት መውሰድን የነጻነት አገዛዙ አይፈቅድም። ስለዚህም ማንንም ማስገደድ የማይወድ አምላክ የሰው ልጅ በተሰጠው ነጻ ፈቃድ በምድር ሳለ የመረጠውን ርስት እንዲወርስ ያደርገዋል።

የዚህ ጽሑፍ መሪ ጥቅስ የሆነው ቃልም ከላይ ለጠቀስነው ሀሳብ ምሳሌ የሚሆን የነጻነት ጥሪ ነው። ‹በፊታችሁ ሕይወትና ሞትን፤ በረከትና መርገምን እንዳስቀመጥኩ እኔ ዛሬ ሰማይና ምድርን ባንተ ላይ አስመሰክራለሁ። እንግዲህ ‹አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ› ዘዳ 30፥19

እግዚአብሔር ሕይወት የተባለች ሃይማኖትንና ምግባርን በእርስዋ ከሚገኘው በረከት ጋር፤ ሞት የተባለች ኃጢአትንና ርኩሰትን በእርስዋ ከሚመጣው መርገም ጋር በፊታችን አስቀምጧል። የምንወደውን የምንመርጥበት ነጻ ፈቃድ አለንና።

የዚህ ምርጫ ታዛቢዎች ሰማይና ምድር ናቸው። ሰማይና ምድር ደግሞ በየትኛውም ዘዴ የማይታለሉና ንቁ ታዛቢዎች ናቸው። ወደ ሞት መንገድ እየሄድን የመረጥነው ሕይወትን ነው ብሎ ማታለል አይቻልም፤ ሰማይና ምድር ይመለከታሉና። ኃጢአትን አብዝተን እየፈጸምን በመላ ሰውነታችን ርኩሰትን እየመረጥን የመረጥነው ሕይወት ነው ብንል ከሰማይና ከምድር ዕይታ ውጪ የሰራነው ኃጢአት ስለሌለ እግዚአብሔር እነርሱን ምስክር ያደርግብናል። ብሎም በምድር በሰው ልጆች በሰማይ በመላእክት ያስመሰክርብናል። መላእክቱም ጠባቂዎቻችን ፤ የሰው ልጆችም አብረውን የሚኖሩ ናቸውና ሥራችንና ምርጫችን ምን እንደሆነ ለመታዘብ አይቸገሩም። እግዚአብሔር ታዛቢዎች አቁሞ ምረጡ ሲለን ምንም ነጻ ፈቃዳችንን ባይነካም፤ ብንሰማውም ባንሰማውን እንደ አባትነቱ የቱን ብንመርጥ እንደሚሻለን ይመክረናል ‹እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ› በማለት።

ሕይወትን ምረጡ ሲል ወደ ሞት የምትወስደውን የኃጢአት መንገድ ትታችሁ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት የምትወስደውን የሃይማኖትና የጽድቅን መንገድ ተከተሉ ማለት ነው። ከእግዚአብሔር ቤት መራቅና ዓለማዊ ተድላ ደስታን ብቻ ማሳደድ ሕይወትን አለመፈለግ ነው። ወደዚህች ቅድስት ስፍራ የሚመጣ ሁሉ ሕይወት የሆነ አምላክን ከእርሱም የሚገኘውን መንፈሳዊ

ስጦታ ሁሉ ያገኛል። እግዚአብሔር ሕይወትን ምረጡ ማለቱ በሌላው ምርጫችን የሚደርስብንን ክፉ ነገር ሁሉ እንዳናይ በማሰብ ነው።

ውድ አንባብያን! ቀጣዩን አንቀፅ ከማንበባችን በፊት እስቲ ቆም ብለን ‹ባለፈው የሕይወት ዘመናችን መርጠን የነበረው መንገድ የሕይወት ነው? ወይስ የሞት?› በማለት ራሳችንን እንጠይቅ የብዙዎቻችን ሕሊና የሚነግረን ምርጫችን የጥፋት መንገድ እንደነበረ ነው። ከነፍሳችን ይልቅ ለሥጋችን፤ ከሕይወታችን ይልቅ ለሞታችን፤ከልማታችን ይልቅ ለጥፋታችን ስንደክም መኖራችን ነው። ሌላው ቀርቶ የደጋግ ቅዱሳን አባቶች መፍለቂያ የሃይማኖትና የምግባር መነኻሪያ በነበረችው ቅድስት ሀገራችን ያለአንዳች እፍረትና ፍርሃት ተከፍሎ የሚያልቅ፤ የማይመስል የኃጢአት ዕዳ ሲከማች እንደዋዛ መታየቱ ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ‹ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች› ቢል የብዙ ኢትዮጵያውያን እጅ ግን ወደ ሌላ አቅጣጫ መዘርጋቱን የሚያመለክት ነው። ለመንፈሳዊ አገልግሎትና ለሥራ ዳተኛ የሆነ ሁሉ ለዝሙትና ለዳንኪራ ያለስስት ገንዘቡን፣ ጊዜውንና ጉልበቱን ሲሰጥ በመንፈሳዊ ዓይን ለሚመለከተው ሰው እጅግ የሚያሳዝን ነበር።

ክርስቲያኖች፣ በዚህ ዲያብሎስና የዓለም ጠባይ ሰውን ሁሉ ከሃይማኖትና ከምግባር ለማውጣት፤ የተቀደሰ ኢትዮጵያዊ ባሕሉን፤ ማንነቱንና ሥርዓቱን ለማጥፋት ታጥቀው በተነሱበት ጊዜ ‹ሕይወት ምረጡ› የሚለው አዋጅ እጅግ ተገቢ አይደለም ትላላችሁ? ስለዚህ ነው ፈጣሪ እያንዳንዱ ክርስቲያን ‹ወደ ሌላው ሰው በደል መጠቆምና ማመካኘት ትተህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ› በሚለው ቃል ራስን

ለመመርመር ወደ ቤተ ክርስቲያን መቅረብ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ሕይወትን የሚመርጡ ሁሉ የሚገቡባት በር ናት። ምንም እንኳን በቤተ ክርስቲያን ስላሉ ሰዎች መጥፎ ወሬን ቢሰሙ እንኳን እንደ ተራ እንቅፋት ቆጥረው በጽናት መቀጠል ለክርስቲያኖች ይገባቸዋል። ያለፉት የኃጢአትና የርኩሰት ዓመታት በንስሐ በማጠብ ወደ ሥጋ ወደሙ መቅረብ ፤ ሕይወትን መምረጥ ፤ብሎም በሕይወት መኖር ነው።

የእግዚአብሔርን ጥሪ ተቀብሎ ይህንን የሕይወትና የሞት ምርጫ ለመምረጥ ልዩ መሥፈርት የለውም ክርስቲያንነት ብቻ በቂ ነው። ከዚህ ቀደም መንፈሳዊውን መንገድ መርጠን መኖር ጀምረን በድክመታችን ያቋረጥነው ሰዎችም አሁን ዳግመኛ ሕይወትን መርጠን በሕይወት ከመኖር አንከለከልም። አውራጣታችንን ይዞ ቀለም እየቀባ ‹እናንተ ከዚህ በፊት መርጣችኋል ድጋሚ መምረጥ አትችሉም!..›የሚል ከልካይ በቤተ ክርስቲያን የለም። ዲያብሎስ ግን «ጠፍቼ ጠፍቼ እመለሳለሁ?» እንድንል ወደ ኋላ ሊስበን ይሞክራልና ሕይወትን በመምረጥ የክርስቶስን መንገድ በመያዝ እናሳፍረው።

የእግዚአብሔር ሁሉን የመቀበል፣ ይቅር የማለት ባህርይ የእኛን ድኅነት ከመሻቱ ነውና የተዘረጋልንን የምሕረት እጅ ቸል ብንል እንቀጣለን። ነገሩም እንዲህ ያለውን መዳን ቸል ብንል የሚብስ ቅጣት የሚገጥመን አይመስላችሁም? እንዳለው ነው። እርሱ ይቅር ማለት ሳይታክተውና እኛ ይቅር መባልና ይቅር በለኝ ማለትን ልንጠላ አይገባንም።

እግዚአብሔር መጪውን ጊዜ የንስሐ፤ የስምምነት፣ የፍቅርና መደማመጥ የሞላበት የአገልግሎትና የመንፈሳዊነት ዘመን ያድርግልን! አሜን!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ሀገሬ ከልቤ እወድሻለው

70/ # ጥያቄ አንዳንድ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ሰዎች ከአንድ በላይ ሚስት ለምን አገቡ? እንዲህ በማድረጋቸውስ እግዚአብሔር ፈቅዶላቸዋል ማለት ይቻላልን?

ምላሽ፡- በብሉይ ኪዳን ከአንዲት ሚስተ በላይ አግብተዋል ከሚባሉት እነ አብርሃም፣ ያዕቆብ፣ ዳዊት እና ሰሎሞን ተጠቃሾች ናቸው። ከአንድ በላይ አግብተዋል ማለት ግን እግዚአብሔር ፈቅዶላቸዋል በሥራቸውም ተደስቷል ማለት አይደለም። እያንዳንዳቸውን እያሳጠርን መመልከት እንችላለን፡- 1. አብርሃም፡- አብርሃም የደረሰባትና እስማኤልንም የወለደላት አጋር ሚስቱ ሳትሆን ገረዱ የነበረች ናት። ከእርሷ እንዲወልድ የተደረገው እንኳ ሚስቱ ሣራ ልጅ ስላልነበራት አስገድዳው እንጂ እርሱ ራሱ ሊደርስባት ፈልጎ አልያም ደግሞ እግዚአብሔር ይህን እንዲያደርግ ስለፈቀደለት አልነበረም። አብርሃም ይህን ያደረገው ዝሙት ለመፈጸም ወይም ሌላ ሚስት ለመጨመር ብሎ ሳይሆን የሚስቱን ቃል ሰምቶ ነው /ዘፍ.16፡3/። ሊቃውንት ሣራ አብርሃምን ለምን እንዳስገደደችው ሲያመሰጥሩት፡-

እግዚአብሔር “ከጕልበትህ የሚወጣ ልጅ እንጂ ከአንተ ጋር ያለው ባርያ አይወርስህም” የሚል ቃል ገብቶለት ስለነበረ /ዘፍ.15፡4/ እርሷ ደግሞ ልጅ ስላልነበራትና እግዚአብሔር የገባውን ኪዳን ያስቀረ ስለመሰላት በሰውኛ ጥበብ ልጅ እንዲወልድ ማድረጓ ነበር ይላሉ።

አብርሃም በመጨረሻ ያገባት ሚስት ኬጡራ ትባላለች /ዘፍ.25፡1/። ነገር ግን ኬጡራን ያገባት ሣራ እያለች ሳይሆን ከሞተች በኋላ ነበር። ይህ ደግሞ በመሐመዳውያን ዘንድ የምናየው ዓይነት አይደለም። 2. ያዕቆብ፡- በዘፍጥረት መጽሐፍ ያዕቆብ ራሔልንና ሊያን እንዳገባ እናነባለን። ነገር ግን ያዕቆብ ሊያን ያገባት በአጐቱ በላባ አታላይነት እንጂ እርሱ ስለፈለገ ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ስለፈቀደለት አልነበረም /ዘፍ.29፡25/። 3. ዳዊት፡- መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ሚዛን ስለሆነ ዳዊት በቅድስና በተመላለሰባቸው ጊዜያት ከአንበሳ አፍ በጐችን ማስጣሉ፣ በአንዲት ጠጠር ሕዝበ እስራኤልንና እግዚአብሔርን የወቀሰ ጐልያድን መግደሉ፣ ሳውልን በይቅርታ ማሸነፉ፣ ሲሞት እንኳን “እሰይ እንኳን ሞተ” ሳይሆን ማልቀሱንና ማዘኑን፣ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ዛሬ በተለይ ለኢትዮጵያውያን ልዩ ምግብ የሆነውን መዝሙር መዘመሩ ቢጽፍልንም ከዚያ በኋላ ያደረገውን ኃጢአትም አያስቀርብንም። እናም ዳዊት ወደ ንግሥና ከወጣ በኋላ የሰውነት ድካም ታይቶበታል። ከአንድ ኃጢአት ወደ ሌላ ኃጢአት ሲሸጋገርም እንመለከታለን።

ቅዱስ ኤፍሬም፡- “ስንፍና ሕሊናንና አስተሳሰብን ያደነዝዛል፤ የማይወዱትንም ኃጢአት እንዲያደርጉ በርን ይከፍታል” እንዳለው ዳዊት በዚያን ጊዜ ከአሞናውያን ጋር በነበረው ጦርነት ሠራዊቱን አዝምቶ

መጸለይ ሲገባው እርሱ በስንፈና አልጋ ተኝቶ ነበር። መተኛቱም ሳያንሰው ከእንቅልፉ ሲነቃ በሰገነቱ ሲመላለስ አንዲት መልከመልካም ሴትን ቢመለከት በዝሙት ጾር ተነድፏል። መነደፍ ብቻም ሳይሆን ደረሰባት። እናም አረገዘች። በኋላም ይህን ኃጢአቱ ለመሸፈን ብሎ ባሏን ጠርቶ ከእርሷ ጋር እንዲተኛና ከባሏ እንደጸነሰች ማስመሰል ፈልጎ ነበር። ኦርዮ ግን ወደ ሚስቱ ወደ ቤርሳቤህ አልሄደም። ለኦርዮ ወደ ቤቱ ሂዶ ከሚስቱም ጋር መተኛት ማለት እግዚአብሔርን (ታቦተ ጽዮንን)፣ ሕዝቡን (እስራኤልን)፣ ነገደ ይሁዳን፣ አለቃው ኢዮአብን እና በጦር ሜዳ ያሉትን ጓደኞቹን ሁሉ እንደ መሳደብ ነበረ።

ዳግመኛ በመላ ፍትወቱ እንዲነሣሣበት ፈልጎ ቢያሰክረውም ኦርዮ በጌታው ምንጣፍ ከባሮቹ ጋር ተኛ እንጂ ወደ ሚስቱ አልሄደም። ከዚህ በኋላ ዳዊት ያሰበው ሁሉ እንዳልተፈጸመለት ባየ ጊዜ ኦርዮን ማስገደል መርጧል። እናም አስገደለው። መጽሐፍ ዳዊት ያደረገው ሁሉ ማለትም ከቤርሳቤህ ጋር መድረሱ፣ ይባስ ብሎም አንዱን ባሏ ኦርዮን ማስገደሉ “በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሆነ” ይላል /2 ሳሙ.11፡27/። ምንም እንኳን ዳዊት መንፈሳዊ ልምምዶችን የተለማመደ፣ ሕግ አዋቂ፣ በሕዝብ ላይ የሚፈርድ ንጉሥ፣ የእግዚአብሔርም ነብይ ቢሆንም ከዚህ ኃጢአቱ ሊመለስ ባለመቻሉ ሌላ ነብይ አስፈልጎታል። ስለዚህም ነብዩ ናታን በጥበብ ገስጾታል። ከዚህ ሁሉ በኋላ ዳዊት ያለ ምንም ማመካኘት ኦርዮን ወይም ቤርሳቤህን ሳይሆን “እግዚአብሔርን በድያለሁ” በማለት ንስሐ ገብቷል /2 ነገ.12፡13/። እንዲህ በማድረጉም “እግዚአብሔር... ኃጢአትህን አርቆልሃል” ተባለ። ስለዚህ ዳዊት በግልጽ ቋንቋ አመነዘረ እንጂ ሌላ ሴት አገባ አይባልም፡

ለዚህም ነው ሊቃውንት “የዳዊት ቅድስና ከንስሐ እንጂ ካለመበደል የተገኘ አይደለም” የሚሉት። 4. ልጁ ሰሎሞንም ቢሆን ብዙ ሚስቶችን ቢያገባም መጽሐፍ ቅዱስ “እንዲህ በማድረጉ እግዚአብሔርን አሳዘነው” እንጂ “አስደሰተው” ብሎ አልመዘገበልንም። እንዲያውም እንዲህ በማድረጉ ዕድሜው አጥሯል፤ መንግሥቱ ለሁለት ተከፍሏል። ይህን ታሪክ በ1ነገ.11 ሙሉውን ማንበብ ይቻላል። በአጠቃላይ ከአንዲት በላይ ሚስት ማግባት ከሕገ እግዚአብሔርና ከስነ ተፈጥሮ አንጻር ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም ከሕገ እግዚአብሔር አንጻር ስናየው አንድ ወንድና አንዲት ሴት አድርጐ ፈጠራቸው ብቻ ሳይሆን አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ጋር ብቻ መተባበር እንዳለባቸውም ትዕዛዝ ሰጥቷል። ይህ ፈቃዱም ትዕዛዙም ባይሆን ኖሮ ወይም ደግሞ አንዱ ወንድ ከአንዲት ሚስት በላይ ማግባት ተፈቅዶለት ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለአንድ አዳም ብዙ ሴቶችን በፈጠረለት ነበር። ወይም በግልባጩ አንዲት ሴት ከአንድ ወንድ በላይ ማግባት ተፈቅዶላት ቢሆን ኖሮ ብዙ ወንዶችን ፈጥሮ ከአንዲቷ ሴት ጋር ባጣመራቸው ነበር። ነገር ግን እንዲህ አላደረገም። ስለዚህ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ይህን ሕገ እግዚአብሔር የሚጻረር ነው።

ከሕገ ተፈጥሮ አንጻር ስናየው ደግሞ ባልና ሚስት አንድ አካል ናቸው። የአንድ አዳም አካል የአንዲት ሔዋን አካል ነው። ይህ የአንድ አዳም አንድ አካል ከአንድ በላይ ሚስት አገባ ማለት ግን ከአንድ በላይ ሆነ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ፈጽሞ ሕገ ተፈጥሮን የሚጻረር ነው። ስለዚህ ከአንዲት በላይ ሚስት ማግባት በመሐመድ የተሰበከ የሰይጣን ትምህርት እንጂ እግዚአብሔር ከመጀመርያው ያዘዘው ትእዛዝ ወይም በተፈጥሮ የሰጠው

አይደለም። እግዚአብሔር በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን እንድናገባ የፈቀደልን አንዲት ሚስትን ብቻ ነው። ክርስቶስ አንድ ነው፤ ሙሽራይቱ ቤተ ክርስቲያንም አንዲት ብቻ ናት። በክርስቶስ የተመሰለው ባልም ልትኖሮው የሚገባት አንዲት ሚስት ብቻ ናት /ኤፌ.5፡23/።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!!

Éñátyé Hulyém Éwédsháléw and 12 others.

71/ የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድን ነው?

=========>>>Share

"እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው። ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል?

የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው?

አሉት።ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። ማንምእንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ።ብዙዎች። እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤

ብዙዎችንም ያስታሉ።ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን

ግድ ነውና ተጠበቁ፥ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው።

ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፥ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፤ እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው

ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፥ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ እርስ በርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፤ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።

እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።

ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው

ይመጣል።

እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሸሹ፥

በሰገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ፥በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላውአይመለስ።በዚያችም ወራት ለርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው።

ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ፤በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ

ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና።እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነምነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች

ያጥራሉ።በዚያን ጊዜ ማንም። እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም።

ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት

ይነግሉና፥

ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።እነሆ፥ አስቀድሜ ነገርኋችሁ።እንግዲህ። እነሆ፥ በበረሀ ነው ቢሉአችሁ፥ አትውጡ፤

እነሆ፥ በእልፍኝ ነው ቢሉአችሁ፥ አትመኑ፤

መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፤በድን ወዳለበት በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ።ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥

ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ።

ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደ

ቀረበ እወቁ።እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም።

ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም።

ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀርየሰማይ መላእክትም

ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም።የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ

ይሆናልና።በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም

እንደ ነበሩ፥የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ

ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች

አንዲቱም ትቀራለች።ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ

ንቁ።ያን ግን እወቁ፤ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ ቤቱም ሊቈፈር ባልተወም

ነበር።ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅበማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና።

እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ ሰዎች ላይ የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው?

ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው፤

እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል።ያ ክፉ ባሪያ ግን። ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ

በልቡ ቢያስብ፥ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፥

የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥ከሁለትም
ይሰነጥቀዋል፥ እድሉንም ከግብዞች ጋር
ያደርግበታል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።"
ማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24!